# አሰብ የማን ናት?

## (የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ)

በያዕቆብ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

2003 ዓ.ም. አዲስ አበባ

© መጽሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ደረሲው ፈቃድ መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

**መታሰቢያነቱ**

ለዴሞክራሲ፣ ለፍትሕና ለአንድነት ሲታገሉ ለወደቁ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያት ነው።

ከመጽሐፉ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ሰበጉ አድራጐት ድርጅት/ድርጅቶች ይውላል።

**ማስታወሻ**

ምዕራፍ 13 ላይ የሚገኙ መጣጥፎች የኢትዮ-ኤርትራ የድምበር ውዝግብ ለድምበር ኮሚሽኑ ከመቅረቡ በፊት የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዲከበር ለኢሕአዲግ ከተሰጡ ማሳሰቢያዎች በጣም ጥቂቶቹ ናቸው።

በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረቡት ደግም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ ስለሚያስፈልግ ለእነዚህ ሰዎች መጠነኛ ግንዛቤ እንዲሰጥ የተዘጋጀ ነው።

**ምስጋና**

ይህንን መጽሐፍ በማረምና በማስተካካል ለረዱኝ ለታዋቂው ደራሲ ለአቶ ማህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም፤ ለአዝማች ይርጋ ገብሬንና ለታናሽ ወንድሜ ደነቀ ኃይለ ማርያም ምስጋዬን አቀርባለሁ።

ለአስተያየትም e_mail yacobhm@Gmail.Com
ስልክ 0922115987

## ማውጫ


መግቢያ..........1

ምዕራፍ 1

1. የባህር በር ለአገር የሚያስገኘው ጥቅምና አለመኖሩ ደግሞ የሚያስከትለው ጉዳት..........11

1.1. በኢኮኖሚው ዘርፍ..........11

1.2. በዲፕሎማሲው በኩል..........20

1.3. ከጠላት መከላከልን በተመለከተ..........21

ምዕራፍ 2

2. የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት በታሪክና የባህር በር ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች..........27

2.1. የኢትዮጵያ የባህር በር ይዞታ በታሪክ..........27

2.2. የኢትዮጵያ የባህር በሮችን ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች..........32

2.2.1. የአጼ ቴዎድሮስ ትግል..........32

2.2.2 የአጼ ዮሐንስ ትግል..........33

2.2.3. የአጼ ምኒልክ ትግል..........37

2.2.4. ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ በኂላም አፄ ኃይል ሥላሴ ያደረጉት ትግል..........41

2.2.5. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት (ደርግ) ጥረት....44

2.2.6. የባህር በር ለማዘጋት ሕወሓት/ኢህአዲግ/ ያደረገው ጥረት....48

ምዕራፍ 3

3. ሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ የነበሩት አራቱ አገራት፣ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ፣ ጣልያን ኢትዮጵያና ኤርትራን አስመልክቶ የደረሱባቸው ውሳኔዎች..........65

## ምዕራፍ 4

4. የኤርትራ በጦር ኃይል መገንጠል ኢ-ሕጋዊነትና በኢትዮጵያ የተሰጣት ዕውቅ ....................80

## ምዕራፍ 5

5. የአልጀርስ ስምምነት ኢ-ፍትሐዊነት ሲገመገም....................92
5.1. ተዋዋዩቹ....................93
5.2. የተዋዋዮች አቅም አለመመጣጠንና ኢትዮጵያ በውሉ ለሰጠችው ምንም አለማግኘቷ....................94
5.3. ኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛቷዋን እንድታስርክብ ተገድዳ የፋረመቻቸው ውሎች....................95
5.4. የውሎቹ ጉድለቶችና ውድቅ መሆናቸው....................98
5.5. የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለል መሠረት እንዲሆኑ የአሜሪካ መንግሥት የተጫወተው ሚና ....................101
5.6. ፍትሀና ዕርት ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት እንዳይሆን የተደረገ ገደብ....................103
5.7. የውሉ አፈፃፃምና የኢትዮጵያ የተዛባው አካሄድ.......105

## ምዕራፍ 6

6. በአልጀርስ ስምምነት መሠረት የተቋቋመው የድምበር ኮሚሽን አመሠራረትና ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ሲገመገም....................107
6.1. የየአገራቱ ተወካዮች ማንነት....................108
6.2. የድርድሩ የጊዜ ሰሌዳ ....................110
6.3. የድርድሩ ቀጣናና የአደራዳሪው ማንነት....................112
6.4. የድንበር ኮሚሽኑ ዳኞች ማንነት ....................114
6.5. ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወይስ የግልግል መድረክ 116
6.6. የክርክር ፍሬ ነገሮች....................118

## ምዕራፍ 7

7. በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ኢትዮጵያን የወከለው ቡድን ለኤርትራ ያስረከባቸው የኢትዮጵያ መብቶች....................124.
7.1. በምስራቅ በኩል .................... .......124
7.2. ከአሰብ በስተ ምዕራብ ያለው ቡሬ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን ሊሆን እንዴት ቻለ ?....................127
7.3. ምዕራብ ትግራይ....................128
7.4. የደብር ቢዘን ገዳም....................130
7.5. የህግ አመራረጥ....................131
7.6. ሁለት ወደ አይሆንም ....................132
7.7. "በያዝከው እርጋ" (UTI POSSIDETIS JURIS)............133
7.8. የድምበር ኮሚሽኑ መሬታቸውን ወደ ኤርትራ ያካለለባቸው ኢትዮጵያውያን የዜግነት መብት ....................137
7.9. ከጦርነቱን በፊትም ሆነ በኋላ አሰብን ማስመለስ የሚያስችሉ የነበሩ ሁኔታዎች....................139
7.10. ኢትዮጵያ ሸንፈትን ከድል መንጋጋ አወጣች" (ፕሮፌሰር ክላፋም) ....................143

## ምዕራፍ 8

8. የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኢትዮጵያ መሰረዝ ይገባታል......145
8.1. የተኩስ አቁም ስምምነት መጣስ....................145
8.2. ምሰሶ ወይንም ችካል በወሰኑ ላይ ስለመትከል.......145
8.3. አንዳንድ የሰላም አስከባሪ ኃይል አባላት ከኤርትራ መባረር....................149
8.4. የሰላም ቀጣናው በኤርትራ ጦር መወረር....................153

## ምዕራፍ 9

9. የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን አስመልክቶ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሲቪክ ማህበራትና የሕዝባዊ ድርጅቶች አቋምና ያደረጉአቸው ትግሎች....................155
9.1. የፖለቲካ ፓርቲዎች....................155
9.2. የሲቪክና፣ የኃይማኖት ተቋማት በውጭ አገር ያደረጉአቸው ትግሎች....................165

## ምዕራፍ 10

10. አሰብ - የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ....................170
10.1. አሰብናታሪካ....................170
10.2. የአሰብ እድገት....................174
10.3. ጁቡቲ፡ አሰብን አትተካም....................176
10.4. ኢትዮጵያ የባህር በር (አሰብ) እንዳይኖራት የሚጠነሰሰው ሤራ....................177
10.5. አሰብ ፣ሰላምና ልማት፣ የቀይ ባህር አፋሮች ኢትዮጵያዊነት ....................179

## ምዕራፍ 11

11. በአግባቡ የተስተናገደ የካሜሩንና የናይጀርያ የድንበር ውዝግብ...184

## ምዕራፍ 12

12. የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ መደምደሚያና አንዳንድ
12.1. የመፍትሔ ጥቆማዎች .................... 190

## ምዕራፍ 13

13. አባሪዎችና የተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች አስተያየቶች ..........201

## መግቢያ

ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች በአገር ውስጥ ብቅ ያሉ አምባገነን መሪዎች የጫኑባቸው በደሎች ሰው ሠራሽም ሆኑ ተፈጥሮ የወለደቻቸው ችግሮች በትዕግስት ያስተናገዱ ሲሆን፣ኢትዮጵያውያን በትዕግስት የማይመለከቱት ነገር ቢኖር የድንበር መደፈርን ነው ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢዎች ገመድ ወጥረው ወርድዋንና ርዝማኔዋን ለኩተው አጎራባቾቿ እነማን እንደሚሆኑ ወስነው የቀረጹአት አገር አይደለችም። የጥንቱን ታሪክ እናቆየውና አፄ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስና አጼ ምኒልክ እንደሩሲያዊው ታላቁ ጴጥሮስ፣ እንደጣሊያኑ ጋሪባልዲ፣እንደ ጀርመኑ ቢዝማርክና ሌሎችም የዓለም ነገሥታት፣ እነዚህ የኢትዮጵያ ነገሥታትም የጎረቤት ህዝቦችን በጦር ኃይል በግዛታቸው በመጠቅለል በታልቅ ተጋድሎና መስዋዕትነት ዛሬ የምናውቃቸውን የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ድምብሮችን መሠረቱ። እነዚህ ወሰኖች በኢትዮጵያ ህዝብ አጥንት የተገነቡ በደሙ የተለሰኑ ቅዱስ መሬቶች በመሆናቸው እንደ ድንበር መደፈር ኢትዮጵያውያንን የሚቀሰቅስ ነገር የለም ማለት ይቻላል። የአገር ድንበር ተደፈረ ሲባል ሕዝቡ አገሩን ለመታደግ "እመልህን በጉያህ ስንቅህን በአህያህ" ብሎ ጠመንጃውን በትከሻው አንግቶ ክተት ብሎ ወደ ጦር ግንባር መትመም የቆየ ልምዱ ነው። ያም ሆኖ ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት በህዝቡ ላይ በፈረቃ የፈፀሙበትን በደል ችላ ብሎ አገሬ ይበልጥብኛል በማለት የሕይወት መስዋዕትነት ከፍሎ አንዳንድ ድሎችን ቢጐናጸፍም፣ በተጐናፀፋቸው ድሎች እርካብ እረግጦ ወደ ዴምክራሲ ፍትሕና ብልጽግና ሊሸጋገር አልቻለም።

ቅርብ ጊዜ ኤርትራ ያልተካለለውን የአስተዳደር ወሰን በመጣስ ወደ ትግራይ ዘልቃ የኢትዮጵያን ግዛቶችን በያዘች ጊዜ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ የነበረው የተለያዩ ቅሬታዎትን ከስሌት ሳያስገባ ልዩነቱን ወደ ጐን አድርጎ በብዙ መስዋዕትነት ጠላትን ወደ መጣበት መመለስ ቢችልም በፖለቲካ አመራር ድክመት፣ምናልባትም ከዚያም በዘለለ, ምክንያት የባህር በር መብቱን ሊያስከብር ካለመቻሉም ባለይ፣ ለዚያ ሁሉ ሕዝቡ

የተከፈለው ወርቃ ዴሞክራሲን አቅጭጮ የሕዝቡ ተባተፎ አመንምኖ ሥልጣን በአንድ ፓርቲ አምባ ገነንነት ሥር ማጠቃለል ነበር።

ኤርትራ በ1983 ዓ.ም በጦር ኃይል ከኢትዮጵያ ከተገነጠለች በኋላ የኢትዮጵያ ወደ ውጭ መተላለፊያና መግቢያ የባህር በር መዘጋትን ያህል ኢትዮጵያውያንን ያስቆጣና ያሳዘነ ብሔራዊ ጉዳይ በአገሪቱ ከቶም ተከስቶ አያውቅም ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም። የኢትዮጵያ የባህር በር መቀርቀር አባቶቻችንና እናቶቻችን ምስጋና ይግባቸውና በድል ከተወጡአቸው ከአድዋም ይሁን ከማይጨው የጣልያን ወረራዎች በላይ የከፋ በደል ተደርጎ በብዙ ወቾ ዘንድ ይቆጠራል። ይህንኑ አስተሳሰብ በማንጸባረቅ ዶ/ር አክሎግ ቢራራ"ከሁሉም የከፋና ተቀባይነት ከሌላቸው የኢሕአዴግ ፖሊሲ የኢትዮጵያን የባህር በር አሰብን ለኤርትራ መንግሥት ማስረከቡን"[1]ነው ሲሉ ጽፈዋል።

ኤርትራ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ እ.አ.አ በግንቦት 1998 ዓ.ም ወረራ ከፍታ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ወረራውን ለመቀልበስ በሚዋደቅበት ሰዓት የኢትዮጵያ ምሁራን፣ በእንግሊዝና በፈረንሳይ መሃከል የተደረገው የአንድ መቶ ዓመት ጦርነት እንኳን በድርድር እንደተቋጨ ሁሉ በዚህ በወንድማማቾችና በእህትማማቾች መሃከል የተከሰተው ትርጉም የለሽና አላስፈላጊ ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት እንደሚደመደም ቢገመትም እንደማንኛውም ጦርነት ወቅቱን ጠብቆ በድርድር እንደሚጠናቀቅ አስገንዝበው ነበር። በማያያዝም በድርድሩ ወቅት የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዳይጨናገፍና አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባርን (ኢሕአዴግን) በብዙ ተማፅነዋል። በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊያት ጦርነቱ ሳይቋጭ ገና ከጠዋቱ ለድርድሩ ጠቃሚ ግብአት ይሆናሉ ብለው ያመኑባቸውን የክርክር ነጥቦች በተለያዩ ጋዜጦችና ጥናታዊ ጽሁፎች በአገርና

[1] Aklog Birara, Ph.D Endemic Poverty that Globalization Can't Tackle But Ethiopians Can. Signature Printing (2010), p. 76.



ኢትዮጵያ ጉዳይ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ጦርነቱ እየጋመ እያለ በኢዴፓ አሰባሳቢነት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ፊርማ ለተባበሩት መንግሥታት ማቅረብና በኒውዮርክ በተባበሩት መንግሥታት ደጃፍ፤ "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር አይዘጋም"፤ "አሰብ የኢትዮጵያ እንጡራ ሃብትና የተፈጥሮ የባህር በር ነች"፤"የአፋር ህዝብ አይከፋፈልም" የሚሉ መፈክሮችን በማንገብ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግን ጨምሮ፣ በሙያቸው የተካኑ ዓለም አቀፍ ደረጃ በትምህርታቸውና በሙያ ብቃታቸው የታወቁ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ኢሕአዴግን አሳምኖ በድርድሩ ወቅት ለኢትዮጵያ የባህር በር እንዲሟገቱ ያልፈነቀሉት ድንጋይ፤ የልማሱት ስር የለም ማለት ይቻላል። (ለአብነት ያህል ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተፃፈ ግልፅ ደብዳቤ ገፅ 213 ላይ መመልከት ይቻላል)። ከእነዚህ አገር ወዳድ ምሁራን ውስጥ ፕሮፌሰር ንጉሤ አየለ፣ አቶ በላይ አባይ፣ አቶ ዘርኡ ከሃሸን፣ ፕሮፌሰር ተከላ ወርቀ ሐጎስ፣ ሜጀር ጄኔራል አበበ ተክለሃይማኖት ካህሣይ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው፣ አቶ አሥራት አብርሃም፣ አቶ ስዩ አብርሃ፣ አቶ ሞገስ ሰለሞን፣ ፕሮፌሰር መብራህቱ በጋዬና አቶ ገብሩ አሥራት ጥቂቶቹ ናቸው።

እነዚህ ምሁራን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የሚያስችሉ በዋቢነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የታሪክ፣ የሕግ፣ የፖለቲካ መረጃዎች በግል ጋዜጦችና በሌሎችም መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለኢሕአዴግ አቅርበው ነበር። የቀይ ባህር አፋር ህዝብ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት የአሰብ ባለቤትነትም ጭምር በታሪክ አስረግጠው ለኢሕአዴግ ብዙ መረጃዎችን አቅርበው ነበር።

የአሰብ ኢትዮጵያዊነት ወይንም አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮና ሕጋዊ የባህር በር መሆንዋን የማይቀበለውና ኤርትራን

ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘሩት ግለሰቦች በአንድ ወይንም በሌላ ወቅት በጽሁፍ ወይንም በቃል አሰብ የኢትዮጵያ የባህር በር መሆንዋ የተከራከሩና የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከፈነዳ ማግስት ጀምረው በጦርነቱ ወቅትና ከዚያም በኋላ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዲያረጋግጥ በብዙ የወተወቱ ምሁራን ናቸው

ከኢትዮጵያ "ቅኝ ግዛት ቀንበር" ነፃ ለማውጣት የተዋደቀው ሕዝብ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች ወደ ኢትዮጵያ መታጠፍ ይገባታል ለሚሉ ኢትዮጵያውያን ኢሕአዴግ መልስ የመስፋፋት አባዜ የተጠናውተችው ናቸው በማለት ያወግዛቸዋል። በኢሕአዴግ በሻቢያ መሃከል የተደረገው ጦርነቱ በተደመደመ ማግስት ኢትዮጵያና ጣሊያን ከመቶ ዓመታት በፊት በተፈራረሙአቸው በቅኝ ግዛት ውሎችና በሌሎች ወደፊት በሚብራሩ ሕግጋት መሠረት የኤርትራ አገራዊነትን ለማረጋገጥና የኢትዮጵያን የባህር በር ለማዘጋት ኢሕአዲግ በሶምሶማ ሩጫ ለድርድር ወደ አልጀርስ አቀና። አልጀርስ ከደረሰም በኋላ ኢሕአደግ በአጼ ምኒልክ ላይ በግድ በተጫኑ በኋላም ጣልያን እራሷ፤ ኢትዮጵያና የተባበሩት መንግሥታት በሰረዙአቸው የኢትዮጵያን የባህር በር በሚዘጉ የቅኝ ግዛት ውሎች መሠረት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከኤርትራ ጋር ለመካለል ኢሕአደግ ተስማማ፡

የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት መብትን አስመልክቶ በኢትዮጵያውያን በኩል ሁለት አቋማት ይንጸባረቃሉ። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምናልባትም ከዘጠና ከመቶው በላይ አሰብ በታሪክ በህግና በሕዝብ አሰፋፈር የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ነች፤ ሲሆን በዲፕሎማሲያዊ ትግል ካልሆነም አስፈላጊ በሆነ መንገድ ሁሉ ከኤርትራ ማስለቀቅ አለብን ሲል፤ ሌላው በጣም አናሳው ደግሞ አሰብ የኤርትራ አካል ነች፤ ወደ ኢትዮጵያ ለማጠፍ ሕጋዊም ሆነ ታሪካዊ ምክንያት የለም በማለት ይከራከራሉ። እነዚህ ወደብ "አስረካቢዎች" አሰብ ለኢትዮጵያ ትገባለች ባዮችን የአሰብ ኤርትራዊነትን የሚክዱ፤ የደርግና የፊውዳል ሥርዓት ርዝራዦችና አቀንቃኞች፤ የወደብ አባዜ የተጠናወታቸው፤ የሰውን አገር ለመቀማት የሚቋምጡ፤ ሰላምን የማይወዱ፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦችን በጦርነት ለመማገድ የሚፈልጉ፤ ጦርነት ናፋቂዎች፤ ለጥያቄአቸው ምንም ህጋዊም ሆነ ታሪካዊ መሠረት ሊያቀርቡ የማይችሉ ተስፋፊዎች ናቸው በማለት ያወግዙአቸዋል። ሆኖም ግን ዛሬ ይህንን አቋም የሚያራመዱ ከሕወሓትም ውስጥ ቁጥራቸው እጅግ እየተመናመነ ሄዶአል። ምናልባትም ከአቶ መለስና ዜናዊ፤ ከጥቂት የሕወሓት



አባላትና ከአገሪቱ ፕሬዝዳንት ከአቶ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ* በስተቀር ዛሬ የአሰብን ኢትዮጵያዊነት የሚክድ የለም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አቋማቸውን ቀይረው አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንድትታጠፍ ከሚከራከሩት ከከፍተኛ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ውስጥ የኢትዮጵያ የቀድሞው የአየር ኃይል አዛዥ ሜጀር ጄኔራል አበበ ተክለሃይማኖት ካሕሣይ እንደሚከተለው ፅፈዋል።

*እ.ኤ.አ እስከ 1994 ዓ.ም የማእከላዊ ኮሚቴ አባልና ከፍተኛ የመከላከያ አዛዦች አንዱ እንደመሆኔ መጠን በጊዜው [የኤርትራ ነፃነትና የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ] አስመልክቶ የመንግስት አቋም አውቅ ነበር። የባህር በር ጥያቄ የሚያነሱ [ኢትዮጵያውያን] ሕገ መንግሥቱን በተለይም የብሔር ብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን [እስከ መገንጠል] የሚደነግገው አንቀፅ 39 የማይቀበሉ የፊውዳል ሥርዓትና የወታደራዊው አገዛዝ የሚናፍቁ የኤርትራ ነፃነትን የማይቀበሉ ጦርነት ናፋቂዎች አድርጌ እቆጥራቸው ነበር።*

*አሰብ ወደብ ውስጥ ብቻ የነበረው የኢትዮጵያ ሃብት ዝርፊያ [2]የባህር በር ጥያቄ እንዳነሳ ቀስቃሰኝ። ለምን [ሕዋሃት/ኢሕአደግ] ይህንን አቋም እንደወሰደ ታሪክ እስኪያጣራ ምስጢር ሆኖ ይቆያል። ሆኖም ለኔ ምክንያቱ ድንቁርናና አጉል ትዕቢት ነው[3]።*

---

* በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል የተደረገው ጦርነት ተጠናቅቆ ህዝቡ ስለ አሰብ ጉዳይ የሞቀ ውይይት በሚያደርግበት በአንድ ወቅት ክቡር ፕሬዝዳንቱ፡ አሰብ የኤርትራ ሉዓላዊ ግዛት መሆንዋን በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በተገለጸው ዘገባ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ከዚያም በኋላ፤ይህንን አቋማችውን ለመለወጣቸው ምንም ማስረጃ የለም።

[2] "ከአሰብ ወደብ ብቻ ከኢትዮጵያ የተዘረፈው ንብረት ከአምስት መቶ ሚሊዮን ብር አያንስም። ይህም የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ንብረት አይጨምርም። ባለቤቶቹ የባንክ ባለዕዳ ሆነዋል"። ብዙነህ እሸቱ ከፍጥጫው በስተጀርባ (ጥናታዊ ፅሁፍ)፤አዲስ አበባ፤የካቲት 12 ቀን 1997.ዓ.ም ገፅ 90

[3] Abebe T. Kahsay "Ethiopia's Sovereign Right of Access to the Sea Under International Law". A Thesis, University of Georgia, Athens, Geogia (2007) (unpublished).

የቀድሞው ከፍተኛ የኢሕአደግ ባለሥልጣንና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃ ተመሳሳይ አቋም በማንፀባረቅ የኢሕአደግን ስህተት ሲገልጹ "ጦርነቱ አይቀሬ ከሆነ የራሳችን [የሕወሓት] እምነትና ጠባብ አመለካከት ብቻ ሳይሆን ከታሪክና ከአገራችን ጥቅም አኳያ የአገራችንን ምሁራኖች አማክረን የባህር በር የምታገኝበት መንገድ ቀይሰን ያንን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲፈፀም ማድረግ ይገባ ነበር። ሊረሳ የማይቻለው በወቅቱ የሠራነው ስህተት ይሄ ነው። ይህ ደግሞ ያመጣው የራሳችን ግትርነት ነው። እኔ ብቻ ነኝ ትክክል ብሎ ሙጭጭ ማለት ራስን መፈተሽና የሌሎች ሃሳብ ለማድመጥ አለመሞከር የኖረ የድርጅቱ ችግር ነው"[4] ሲሉ አቶ ስዬ ጸጸታቸውን ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች የኢሕአደግ አባላት በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት እንደ ብዙዎቻችን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊያት ከቁጭት አልፎ እንደሚበግኑ አያጠራጥርም። በተመሳሳይ መልኩ ከፍተኛ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አመራር አባላት የነበሩ ግለሰቦች፤ የአሰብ በኤርትራ መያዝ በአገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን በመገንዘብ በነበራቸው አቋም መጸጸታቸውና የኢትዮጵያን የባህር በር መብት ለማስከበር እንደሚታገሉ በአደባባይ ቃል ገብተዋል። አንዳንዶቹ ሁኔታው በፈቀደ ሁሉ እየታገሉም ነው። በምሳሌነትም አቶ ገብሩ አስራት የቀድሞው የሕወሓት ከፍተኛ ባለስልጣና የትግራይ አስተዳዳሪ የነበሩ በአሁኑ ወቅት የትግራይ ለዴሞክራሲና ሉዓላዊነት ፓርቲ (ዓረና) ኘሬዝዳንትና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መድረክ (መድረክ) ሊቀመንበር፤ እንዲሁም ሕወሓት ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸውና አሁንም የመድረክ የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ስዬ አብርሃ፤ የዓረና የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ አሥራት አብርሃምና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

የዚህ ጽሁፍ ዋናው ዓላማ ታሪክን፣ ዓለም አቀፍ ሕግን፤ የቀይ ባህር አፋሮች አንድነትና መብትን ከግንዛቤ አግብቶ፤ የአሰብ ወደብ ሕጋዊ ባለቤት ኤርትራ ወይስ ኢትዮጵያ ነች ለሚለው

---

[4]ሪፖርተር እሁድ የካቲት 07 ቀን (2003)ዓ.ም.



ጥያቄ ለሚያነሱ ምላሽ ለመስጠት መሞከር ሲሆን ለዛሬም ሆነ ለነገው ትውልዶች አንዳንድ ግብአት ለመስጠትና የአሰብ ጉዳይ እንደ አሁኑ በኢትዮጵያውያን አእምሮ እየተንቀለቀለ እንዲኖርና ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ ከዋነኛ ብሄራዊ አጀንዳነት እንዳይወርድ ለማድረግ ነው።

የጽሁፉ ተጨማሪ ዓለም የኢትዮ-ኤርትራ የድምበር ኮሚሽን በዘሄግ ኔዘርላንድስ እ.አ.አ ኤፕሪል 13 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መገምገም አይደለም። የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በዚህ ጽሁፍ የተጠቀሰው፤ ውሳኔው ለኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ያደረገው አስተዋጽኦ በሚመለከት ብቻ ነው። ጠቅላላው የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ግምገም የአካባቢው ጂኦግረፊ፤ ታሪክና የሕዝብ አሰፋፈር ጠንቅቆ በሚያውቅ ሰው እንዲሚደረግና ስህተቶች ወይንም አድሎዎች ካሉ እንደሚያወጣቸው ተስፋ ይደረጋል። በዚህ አንጻር አቶ በላይ አባይ <u>የኢትዮጵያ መንግሥት ብሄራዊ ግዛቶችን ለኤርትራ ሰጠ</u> <u>(The Ethiopian Regime Cedes National Territories to Eritrea</u>,1991) በሚለው መጽሐፋቸው ያደረጉት ጥረት የሚመሰገን ነው።

ዶ/ር አክሎግ ቢራራ እንደሚሉትም "አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆንዋ የሚደርስባት ጉዳት ጠንቅቆ ያውቅ እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ እንደ አብዛኛው አገራዊ ጉዳይ ይህንንም ገዢው ፓርቲ አዳፍኖት ተቀምጦአል"[5]። ስለሆነም ገዢው ፓርቲም ስህተቱን ተገንዝቦ እርማት ለማድረግ ወይንም ወደፊትም የሚያደርገው የዲፕሎማሲያዊም ሆነ ሌላ ጥረት ስለሌለ ለባለጉዳዩ ለኢትጵያ ሕዝብና ለመጪው ትውልድም በተቻለ አቅም ግንዛቤ ማስጨበጥ የጽሑፉ ሌላው ዓላማ ነው።

ፅሁፉ በመጀመሪያ የአንድ አገር የወደብ ባለቤት መሆን የሚያመጣው ጥቅም ወደብ አልባ መሆን ደግሞ የሚያስከትለው ጉዳት ከኢኮኖሚው ልማት፤ የአገሩ ሰላምና ደህንነት ከማረጋገጥና ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ዘንድ ከሚ[illegible]ት

---

5 Aklog Birara, PhD. supra note 1, p.77.

ተዳማጭነት አኳያ ምን ያህል ጫና እንደሚጥል ለመዘርዘር ይሞክራል። ቀጥሎም ኢትዮጵያ በታሪክ የነበራት የባህር በር ባለቤትነት በአጭሩ በመገምገም የኢትዮጵያ ጠላቶች አቶማን ቱርኮች፤ ግብፆችና ጣሊያኖች የሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛቶች በመቆጣጠራቸው ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር አካባቢ መገለልዋን በአጭሩ ያትታል። በመቀጠልም የኢትዮጵያ የባህር በር ለማስመለስ ከሕወሓት/ኢሕአደግ በስተቀር በየጊዜው በአገሪቱ የተፈራረቁ መንግሥታት ምን ያህል እንደኳተኑ ይዳስሳል። በማስከተልም የኢትዮጵያን የባህር በር መብትን አስመልክቶ የዓለሙ ሕብረተሰብና የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ቲደምድሞ የኤርትራን የወደፊት እጣ ፈንታ በወሰኑበት ጊዜ የወሰዱት አቋም ምን ይመስል ነበር የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይሞክራል።

ጽሁፉ እ.አ.አ በታህሣሥ 2000 ዓ.ም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በአልጀርስ ለተፈረመው የወሰን መካለል ስምምነት መሠረት የሆኑት ጣሊያን በግድ በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የ1900፣1902፣ እና 1908 ውሎች (treaties) በሕግ ፊትውድቅነት ይተነትናል። ቀጥሎም ጣሊያን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተሸነፈች በኋላ የቀድሞው የጣሊያን ቅኝ ግዛቶች የነበሩት አገራት መጻኢ ዕድል እንዲወስኑ የተሰየሙት አራት ኃያላን አገራት አሜሪካ እንግሊዝ፣ፈረንሳይ፤የሶቭየት፤ኅብረትና የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በዋናነት የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ከኢትዮጵያ ጋር አዲስ አሳሪ ውል በመዋዋል ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀልና ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን መወሰኑ ጽሁፉ ይተነትናል።

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስር በፌዴሬሽን እንድትተሳሰር በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ድል አድራጊ አራቱ ኃያላን አገራትን በመጠከል የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ጣልያንና ኢትዮጵያ የተፈራረሙት ውል ተጥሶ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት ያበቃው የአልጀርስ ስምምነትና የድምበር ከሚሽኑ ውሳኔ ሲሆን የስምምነቱና



የውሳኔው ኢ-ሕጋዊነት እንመረምራለን። ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌዴሬሽን ሲተሳሰሩ ቀጥሎም ፌዴሬሽኑ በኤርትራ ፖርላማ ውሳኔ ፈርሶ ውህደት ሲፈጥሩ የኤትዮጵያ የባህር በር መብት መረጋገጡን አመላክተን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል የኢትዮጵያ ሉዓላዊት የባህር በር አሰብን ይዛ መሄድዋ ሕገ ወጥ ድርጊት መሆኑን እንፈትሻለን።

ጹሁፉ አሰበን ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል የነበሩ እድሎች በኢሕዴግ ድክመት እንዳመለጡ ከዘረዘረ በኋላ የኢትዮጵያ የባህር በር [አሰብን] ማስመለስ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ግዴታ እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አቅሙ የሚፈቅደውንና ሊያደርግ የሚችለውን እንዲያደርግ ይማጸናል። በመጨረሻም የአሰብ ጉዳይ የሁለት ወንድማማቾችና፤ እህትማማቾች፤ ሕዝቦች ሰላምና መልካም ጉርብትናን በሚያጉለበትና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ እንዲፈታ አንዳንድ አማራጭ ሃሳቦችን ጠቁመን ጽሑፉን በዚሁ እንዘጋዋለን፡፡

# ምዕራፍ 1

## 1. የባህር በር ለአንድ አገር የሚያስገኘው ጥቅምና አለመኖሩ ደግሞ የሚያስከትለው ጉዳት

### 1.1. በኢኮኖሚው ዘርፍ

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንደዘገቡትና የኢትዮጵያ መንግሥትም እንዳረጋገጠው ከ አራት ሚሊዮን በላይ አረሃብተኞች የሚገኙባት አገር ስትሆን ሥራ አጥነት፣ የአካባቢ ውድመት፣ ጣራ የነካ የኑሮ ውድነትና ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ግሽበት በሰፊው ተንሰራፍቶውባት ከመጨረሻ ድሀ ከሚባሉት አገራት ተርታ ትሰለፋለች። ኢትዮጵያ እነዚህን ችግሮችን ሁሉ ታቅፋ ኢሕአደግ በ1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሥልጣን ከመያዙ በፊት አስር ሳንቲም መክፈል ቀርቶ እንዲያውም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ለነበረው የወደብ አገልግሎት ዛሬ አገሪቱ በቀን ከሦስት ሚልዮን ዶላር በላይ ለጅቡቲ ትከፍላለች። ይህ ለወደብ የሚከፈለው በጣም ከፍተኛ ገንዘብ ውሃ እንደበላው የሚቆጠር ነው። ምክንያቱም በለውጡ ኢትዮጵያ የምታገኘው ዕቃም ሆነ ገንዘብ ወይንም ሌላ ጥቅም የለምና። ይህም ማለት ድህነትን ለመቅረፍ ሊረዱ ይችሉ የነበሩ በየዓመቱ ሃያና ሰላሳ ፋብሪካዎች ሊገነባ የሚችል ወይንም ጠጠር ስራ ለሆነ መሠረተ ልማት ግንባታ ሊውል ይችል የነበረ ገንዘብ በሕወሓት መሪዎች የዲፕሎማሲና በሌሎች ሌሎችም ያልታወቁ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ይህንን ሁሉ ገንዘብ ለጅቡቲ ትገብራለች።

የኢትዮጵያ የወጪና የገቢ ንግድ የሚካሄደው አብዛኛው በባህር ላይ ሲሆን ኢትዮጵያ የኬንያ፣የሱዳን፣የጅቡቲ፣አንዳንዴም የሶማሊያ ወደቦች ትጠቀማለች። ሆኖም ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከውና ከውጭ የምታስገባው ጠቅላላ ንግድ 90% በዱባይ

የወደብ ባለሥልጣን በሚተዳደረው በጅቡቲ በኩል ነው[6]:: እ.ኤ.አ በ3 ሜይ 2009 በአፍሪቃ ፕሬስ ኤጀንሲ እንደተዘገበውና እንዲሁም የኢትዮጵያ የመገናኛ ሚኒስቴር እንደገለጸው ኢትዮጵያ በአንድ ወደብ ላይ ብቻ በመንጠልጠልዋ የንግዱን እድገት አቅጭጮታል:: እንዲሁም ለጅቡቲ ወደብ በኢትዮጵያ በኩል የሚከፈለው ታሪፍ በየጊዜው እየጨመረ በአንድ ወቅት በአንድ ጊዜ 25% ጭማሪ ታሪፍ መቆለልዋ የሚታወስ ነው[7]::

የአሰብ ወደብ በአካባቢው ካሉ ኢትዮጵያ ልትጠቀምባቸው ከምትችል ወደቦች በሙሉ ለመሃል አገሩ የቀረበች ነች:: የኬንያው ሞምባሳ ወደብ ለሰሜኑ ኢትዮጵያ ከሺህ ስምንት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ የሚርቅ ሲሆን በኬንያና በኢትዮጵያ መሃከል ያለው የመኪና መንገድም የተበላሸና ለከባድ የጭነት መኪኖች አዳጋችም ነው::

[6] Getachew Begashaw, Ph.D ``Port of Assab as a Factor for Economic Development and Regional Conflict`` http//ethiomedia.Com. Accessed on January 8, 2010.

* በሆነ ምክንያት ጅቡቲ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያገናኛት መንገድ ቢዘጋና ወደቡ ለጥቂት ቀናት እንኳን ለኢትዮጵያ ዝግ ቢሆን የሚያስከትለው ጉዳት ሲታሰብ ያስደነግጣል::. በኢትዮጵያ በኤርትር ጦርነት ጊዜ እንዲህ ዓይነት አደጋ እንደከሰት ኢሕአደግ በጅቡቲ ወደብ አካባቢ 4000 የሚጠጋ የኢትዮጵያ ጦር አሰፍር እንደነበር ይነገራል::

[7] Id.



ሠንጠረዥ 1

በአዲስ አበባና በአካባቢዋ የሉት ወደቦች መሃከል ያለው እርቀት በኪሎ ሜትር

| | | |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ | ሞምባሳ | 1804 |
| አዲስ አበባ | ፓርት ሱዳን | 1696 |
| አዲስ አበባ | ሞቃዲሾ | 1520 |
| አዲስ አበባ | በርበራ | 943 |
| አዲስ አበባ | ጅቡቲ | 910 |
| አዲስ አበባ | አሰብ | 624 |

ምንጭ [8]

በዚህ ሰሌዳ መሠረት ዕቃ ጭነው ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ወይንም ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ የሚሄዱ መኪኖች አሰብ ደርሰው ከሚመጡ መኪኖች ወደ አንድ ቀን የሚጠጋ ተጨማሪ ጉዞ አለባቸው ማለት ነው:: ለዚህ ጉዞ የነዳጅ ወጪ፤ሹፌሮች የሚያጠፉት ጊዜና በመኪናዎቹ ላይ የሚደርሰው ብልሽት እንዲሁም ለወደብ የሚከፈለው ታሪፍ በሙሉ ቢተመን በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ክስረት እንደሚያስከትል ማንም አይስተውም::

እንደ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆኑ አገሮች ከዋና ዋና የገበያ ማዕከሎች የተገለሉና ከገበያ ማዕከሉ የራቁ ሲሆኑ ወደብ አልባነት

[8] Id.

ለኢኮኖሚ እድገታቸው ከፍተኛ ማነቆ ሆኖባቸዋል። ቻውድሪና ኤርዳነቢልግ የተባሉ ምሁራን ባደረጉት ጥናት መሠረት አንድ ወደብ አልባና ወደብ ያለው በሌላ በሁሉም ነገር ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት አገሮች ብንወስድ ወደብ አልባው አገር በኢኮኖሚ እድገቱ በ1% ወደብ ካለው አገር ወደ ኋላ ይቀራል። ይህም ማለት ወደብ ያለው አገር በ24 ዓመት ውስጥ ኢኮኖሚው በእጥፍ ሲያድግ ወደብ አልባው አገር ኢኮኖሚው በእጥፍ እንዲያድግ 36 ዓመታት እንደሚፈጅበት እነዚህ ምሁራን ያረጋግጣሉ[9]። በሌላ ጥናት እንደተረጋገጠው ደግሞ ወደብ አልባ በመሆን ብቻ የአንድ አገር የውጭ ንግድ መጠን ከ33% እስከ 43% ሊቀንስ ይችላል። ዶ/ር አክሎግ ቢራራ በቅርብ ጊዜ ከሰሃራ በታች በሚገኙ አገራት የተደረገ ጥናት ሲጠቅሱ ከሰሃራ በታች የሚገኙ ወደብ አልባ አገራት የውስጥ ለውስጥና ወደ ወደቡ የሚያሸጋግረው የትራንስፖርትና ተያያዥ ወጪዎች ወደብ ካላቸው አገራት በአራትና በአምስት እጅ እንደሚበልጥ ይገልጻሉ። ይህም ከዕቃው ሽያጭ የሚገኘው አብዛኛውን ገንዘብ ይወስደዋል ማለት ነው። ይህም ማለት ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶች ዋጋቸው ስለማነር በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ አይችሉም። እንዲሁም ወደ አገር የሚገቡሽቀጦች ዋጋቸው በጣም ከፍ ይላል። ይህም በመሆኑ ገዥው ፓርቲ የአሰብ ወደብ ለኤርትራ በማስረከቡ የአገሪቱ ደህንነትና እድገቷ በከፋ ሁኔታ ላይ ጥሎአል ማለት ነው[10]።

በ2008 ዓ.ም በዓለም 44 ወደብ አልባ አገሮች ሲኖሩ ከእነዚህ ውስጥ ሠላሳ አንዶቹ ድሃ ሲሆኑ አሥራ ሦስት ደግሞ የድሃ ድሃ የሚባሉ ናቸው። አሥራ ሦስቱም የድሀ ድሀ አገሮች አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ኢትዮጵያም ከእነዚሁ አሥራ ሦስቱ ድሃ አገሮች ተርታ ትሰለፋለች። እነዚህ ወደብ አልባ ድሃ አገሮች ወደ ውጭ የሚልኳቸው ምርቶቻቸው በአብዛኛው በአንድና በሁለት ሰብሎች ወይንም በአንድ በሁለት በእንዱስትሪ

9 Chowdhury A.K and Erdnebileg Sondagdory. Geography against Development:
A Case for Landlocked Countries, United Nations, (2008) p. 77

10 Aklog Birara, Ph.D. supra note 1 p.78



ውጤቶች ወይንም ጥሬ እቃ የተወሰኑ ናቸው። ስለሆነም ከድህነት የመላቀቅ እድላቸው በጣም የመነመነ መሆኑ ሊቃውንት ይናገራሉ። የኢኮኖሚ ልማት ሊቅ ፖል ኮልየር (Paul Collier) "የመጨረሻዎቹ ድሃ ቢሊዮኖች (The Bottom Billion) በሚለው መጽሃፋቸው ቀጥሎ ያለውን አስፍረዋል። "ድሃ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ወደብ አልባ አገሮች ከአራቱ የልማት ማነቆዎች በአንዱ [በወደብ አልባነት] ተጠፍረው የተያዙ ናቸው። የባህር በር ካለህ ገበያህ መላው ዓለም ነው። የባህር በር ከሌለህ ደግሞ ገበያህ የጎረቤት አገር ብቻ ነው"[11]። ስለሆነም አገራት ወደብ አልባ ላለመሆን ጥረት ያደርጋሉ። ኮልዬር በተጨምሪ ወደብ አልባ አገሮች የጎረቤቶቻቸው እስረኞች ናቸው[12] ብለዋል።

እንዲሁም ጀፍሪ ሳክስ (Jeffrey Sachs) የተባሉ የኢኮኖሚ ልማት ሊቅ የባህር በር የሌለው አገር ከሚገጥሙት ዋነኛ የኢኮኖሚ ችግሮች ወደብ አልባ መሆን ገልፀዋል። በመቀጠልም የባህር ጠረፍ ለኢኮኖሚ ልማት የላቀ ሚና ይጫወታል ማለት ማጋነን አይደለም፤ የባህር በር አለመኖር ደግሞ በጠቅላላው ለአንድ አገር የኢኮኖሚ ልማት ወደ ኋላ መቅረት ዋነኛ ምክንያት መሆኑን ጀፍሪ ሳክስ ይገልፃሉ[13]።

በተጨማሪም ኪሾር ኡፕሬቲ (Kishor Uprety) የተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ኮሚሽንን (United Nations Commission on Trade and Development) በመጥቀስ የባህር በር አለመኖር ለኢኮኖሚ እድገትና ለልማት ዋነኛ እንቅፋት መሆኑን ያረጋግጣል ብለዋል[14]።

11 Path Cother, The Bottom Billion. Why the Poorest Countries are Felling and what Can Be Done About it Oxford University Press, (2007) p.54-63

12 Id

13 Faye. M. Macarthur, J.Sachs, J Snow. T. " The Challenges Facing Land Locked Developing Countries," Journal of Human Development.(1) (2004)

14 Kishor Uprety "Right of Access to the Sea of Land Locked States Retrospect and Prospect for Development". Journal of

ይህንኑ በማረጋገጥ፣ "የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የመጨረሻ ድሀ አገሮች ተወካይ" ሚስትር ቻይክ ሲዲ ዲያራ በአዲስ አበበ በተደረገ ሰብሰባ ተገኝተው ወደብ አልባ አገሮች ለእድገት የሚያስፈልግ እርዳታ ቢጨመርላቸውም፣ ዕዳ ቢሰረዝላቸውም፣ በዓለም ገበያ ለመሳተፍ ሁኔታው ቢመቻችላቸውም፣ በዓለም ኢኮኖሚ ያላቸው ድርሻ የበይ ተመልካች ሆነው እንደቀሩና መሠረታዊ ለውጥ ማስመዝገብ እንዳልቻሉ ገለጡ[15]።

የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በታቃራኒው የባህር በር ለአንድ አገር እድገት ምንም የሚጫወተው ሚና እንደሌለ በመግለጽ የሚከተለውን ብለዋል።

"…..አሁን የአሰብንም የምጽዋንም ወደብ አንጠቀምም። እነዚህ ወደቦች ባለመጠቀማችን ምንድን ነው የቀረብን ነገር የለም። ልማት ቢሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ልማት፣ፈጣን ልማት የተመዘገበው በአለፉት አራት ዓመታት ነው። ስለዚህ ወደብ ለላመኖሩ እረሃብ አያመጣም፣ በጐረቤት አገር ወደብ በመጠቀም መሥራት ይቻላል። ያለ ነገር ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ያለወደብ ቀረች ብለን የምንቆጭበትና የምናዝንበት ምክንያት የለም። ወደብ አለመኖር አይጐዳንም፣ ሊጐዳንም አይችልም። ወደብ በነበረን ጊዜ ኢትዮጵያ ድሀ ነበረች። አሁን ወደብ የለንም። እድገት ግን እያስመዘገብን ነው። ስለዚህ ለማደግ ወደብ አስፈላጊ አይደለም"[16] በማለት የወደብ ጠቃሚነት አጣጥለዋል።

ከላይ የተጠቀሰው የአቶ መለስ አባባል በባህር በር መዘጋት የሚበግኑና የሚበሳጩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያንን አያጽናናም፣ ምክንያቱም ሀቁ ከላይ የጠቀስናቸው በጣም የታወቁ የኢኮኖሚ ልማት ሊቃውንት ከሚሉት ፍጹም የተለየ ብቻ ሳይሆን ተቃራኒም ነው።

---

International Legal Studies, 21(1995)

[15] ስባይ ሚድይ ሰኔ 11 ቀን 2000ዓ.ም.

[16] አሥረት አብርሃም ከአገር በስተጃርባ፣ሕዋሀትና ሻቢያ የትርያ ፈረበና የባሰፉሩስ ተልክ 2ኛ ዕትም ሕዳር 2003 ገጽ 156



ለአንድ አገር ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ዋነኞቹ ግብአቶች አንዱ ከውጭ ወደ አገር የሚገባውና በሥራ ላይ የሚውለው ገንዘብ (foreign investment) ነው። አንድ የውጭ ኢንቬስተር በሌላ አገር ገንዘቡን ሥራ ላይ ከማዋሉ (ኢንቬስት ከማድረጉ) በፊት የሚጠይቃቸው አያሌ ጥያቄዎችና የሚያደርጋቸው ምርምሮች አሉ። ከእነዚህም ጥያቄዎቹ ከዋነኞቹ አንዱ የሚያመርተው ምርት እንዴት አድርጎ ወደ ዓለም ገበያ ማዝለቅ እንደሚችል ሲሆን ለዚህም አስተማማኝ የሆነ በቅርብ የሚገኝ ብዙ ወጪ የማያስወጣው መገናኛ መኖርና አለመኖር ነው።

ወደብ አልባው አገር የሚያመርተው ዕቃ ግዙፍ ዓይነት ከሆነ በየብስ ትራንስፖርት ወደ ባህር ተሸጋግሮ ከዚያም ወደ ዓለም ገበያ ለማዝለቅ ወጪው ቀላል አይሆንም። ስለዚህ አንድ ኢንቬስተር በአንድ አገር ውስጥ መዋለ ንዋዩን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ይኸ አገር የባህር በር ባለቤት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ወሳኝነት ያለው ጥያቄ ይጠይቃል።

አገሩ የባህር በር ከሌለው በባህር በሩና ዕቃው ከተመረተበት አካባቢ ያለው እርቀት ከረዘመ ለወደብ ግልጋሎት የሚከፍለው ገንዘብ ከፍተኛ ከሆነ በወደቡና ዕቃው በተመረተበት መሃከል ያለው መንገድ ጥራት ከጐደለው ኢንቬስተሩ ገንዘቡ ሥራ ለይ የሚያውልበት የተሸለ አማራጭ ይፈልጋል ።

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪም ሆነ የእርሻ ውጤቶች የሚመረቱት ከወደቡ በራቀ አካባቢ በአብዛኛው በመሃሉና በምዕራቡ የአገሪቱ ክፍል ስለሆነ እነዚህን ምርቶች ወደ ወደቡ ለማዝለቅ ብዙ ወጪ ይጠይቃል። ስለሆነም ክባድ ዕቃ ለማምረት ለሚፈልግ ኢንቬስተር ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ምርጫ አትሆንም። በእርግጠኝነት ለልማት ጠቃሚ የሆነውና ለብዙ ዜጎች የሥራ እድል የሚከፍተው ቴክኖሎጂ ወደ አገር የሚያስገባው የኢንቨስትመንት መስክ የከባድ ዕቃ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ወይንም ፋብሪካ ነው። በኢትዮጵያ ሁሉም ነገሮች ተስተካክለው ቢገኙ እንኳን ወደብ አልባ በመሆንዋ ብቻ እንደዚህ ካሉ ኢንቬስትመንቶች የመቋደስ ዕድሏ በጣም ይቀንሳል።

ቀይ ባህር ወደ አፍሪቃ፤ ባብኤል መንደብ፤ሜዲቲሪንያንና ሕንድ ውቅያኖስ የሚያሸጋግር ከፍተኛ ትራፊክ የሚያስተናግድ መስመር ነው። ወደ እነዚህ አካባቢ የሚጓዙ መርከቦች አሰብ ላይ በሚቆሙበት ጊዜ ከፍተኛ ገቢ ያስገባሉ። ቀደም ሲል ከዚህ ዘርፍ ኢትዮጵያ ትሰበስበው የነበረ ገቢ ከአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ ጋር ወደ ኤርትራ መንግሥት ካዝና ይገባል ማለት ነው። እንዲሁም የወደብ ግልጋሎት ብዙ ሠራተኛ የሚይዝ ሲሆን ከአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ ጋር የብዙ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድልም ተዘግቶ እነዚህ ሠራተኞች ለብዙ ጊዜ አዲስ አበባ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ሰፍረው በችግር ይንገለቱ እንደነበር ይታወቃል።

አሰብ ከፍተኛ የቱሪስት መስብህ ስትሆን ባህሩም በአሳ ሃብት የበለፀገ መሆኑ ተረጋግጧል። ወደ 1960ዎቹ መባቻም በአሰብ አካባቢ ከከርሰ ባህር የፈነዳው የተፈጥሮ ጋዝ አሰብ የነበሩ መሃንዲሶች መዝጋት ተስኖአቸው ፍንዳታውን ለመዝጋት መሳሪያዎችና ኢንጂነሮች ከሊቢያ ነበር የመጡት ። ስለነዳጅ እውቀት ያላቸው ሰዎች የተፈጥሮ ጋዝ ፈንድቶ መውጣት ከተፈጥሮ ጋዝ ሌላ በተጨማሪ በአካባቢው ነዳጅ (ቤንዚን) መኖሩ ዓይነተኛ ማስረጃ መሆኑ ያረጋግጣሉ። በተጨማሪም በቀይ ባህር ልዩ ልዩ እንደ ማንጋኒዝ የመሳሰሉት ማዕድናት መኖራቸው በተለያዩ ጊዜያት ተጠቁሞአል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ኢትዮጵያን ለከፍተኛ ኪሣራ የሚዳርጉ ሁኔታዎች እያሉ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ እ.አ.አ. በ2000 ዓ.ም "አሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንመልስ ማለት ከኢትዮጵያ መንግሥት እምነትና መርህ ውጭ ነው። አሰብ የምንታገልለት ጉዳይ አይደለም፡ ሌሎች አማራጭ ወደቦች አሉን። አሰብ በመሄዱ ምንም አላጣንም። ስለዚህም ነው አሁንም በድርድር [በአልጀርስ] ወቅት አሰብን ያላነሳነው"[17] ብለው ነበር። ሁኔታው እርሳቸው እንደሚሉት ሳይሆን የአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ በኢኮኖሚው ላይ ያስከተለው ጉዳት በአሃዝ አስልቶ

[17]መለስ ዜናዊ እ.አ.አ በጁን 20 ቀን 2000ዓ.ም ከአሜሪካን ድምፅ ራድዮ ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ



መናገር ይቻላል። በአጭሩ ሌላ ሌላው ሳይዘረዘር ከላይ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ በዓመት ለወደብ አገልግሎት በቀን ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደምትከሰክስ የአደባባይ ምስጢር ነው።

በአገር ደረጃ ከላይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ፤ ወደብ አልባነት ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የቀን ተቀን ኑሮ ጋር ቁርኝት አለው። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ለተከሰተው በየቀኑ ወደ ሰማየ ሰማያት የሚመጥቀው የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት የስቃይ ኑሮ ያደረገው የእቃዎች የዋጋ መናር እጅግ ውድ የሆነው የወደብ አገልግሎትና ቀረጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በዚህ በአስጨናቂ ጊዜ ኢትዮጵያ የራስዋ ወደብ ቢኖራት ኖሮ ለሰው ሕይወት አስፈለጊ የሆኑትን ምግብን የመሳሰሉ ሸቀጣ ሸቀጦች ከቀረጥ ነፃ ወይንም አነስተኛ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ቢገቡ ለተከሰተው የኑሮ ውድነት ማስተንፈሻ በሆነ ነበር።

በዓለም የበለጸጉ ጥቂት ወደብ አልባ አገሮች እንዳሉ ሲታወቅ በእነዚህ አገሮች አካባቢ የሚገኙ ሰፋፊ ገበያና የዳበረ ኢኮኖሚ በመጠቀም የወደብ አገልግሎት አለመኖር የሚያስከትለው ጉዳት መቀነስ ችለዋል። እነዚህ አገራት የደረጁ የመገናኛ አውታሮችና መጓጓዣዎች በመጠቀም ያለ ብዙ ችግር ወደ ወደብ ይዘልቃሉ። ለምሳሌ ያህል ኦስትርያ ሉክሳምቡርግ እና ስዊዘርላድ ወደብ አልባ ቢሆኑም ወደብ አልባነቱ እጅግም አልጉዳቸውም። ድሀ በሆኑ አገሮች ግን ወደብ አልባነት የአንድን አገር ንግድ ከላይ እንደተጠቀሰው ከ33% እስከ 43% ስለሚቀንሰው ይህንን በመረዳት የተባበሩት መንግሥታት እነዚህ ወደብ አልባ አገሮች ወደ ውጭ የሚልኩዋቸውና ከውጭ የሚያስገቡአቸው ዕቃዎች በቀላሉና በተቀላጠፈ መልኩ እንዲከናወኑ በተባበሩት መንግሥታት በውሳኔ ቁ. 1028 (x1) በ2002 እና 2003 ዓ.ም. የወደብ ባለቤት የሆኑ አገሮችን ጠይቋል[18]።

[18] United Nations Resolutions, No. 1028 (x1) 2002 and 2003

## 1.2 በዲፕሎማሲው በኩል

ኢትዮጵያ ከ90 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት እና በሕዝብ ብዛት በአፍሪቃ ሁለተኛዋ አገር ስትሆን፣ የአፍሪቃ ሕብረት ዋና ጽህፈት ቤት፣ የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንና ሌሎችም ዓለምአቀፍ ድርጅቶች አዲስ አበባን ቤታቸው አድርገዋል። ከእነዚህ አንጻር ሲታይ ኢትዮጵያ በዓለምም ሆነ በአፍሪቃ የተባ የዲፕሎማሲ ሚና ልታደርግ የምትችልና የምትደመጥ አገር መሆን ይገባት ነበር። አሁን ግን እንደሚታየው በዲፕሎማሲው ድክመት ምክንያት ብቸኛ መውጪያና መግቢያ የባህር በርዋ ከመዘጋት በተጨማሪ ሉዓላዊነቷ ለአደጋ ሊጋለጥ በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። የአለም 70% የንግድ ዕቃዎች ከሚተላለፉበት እጅግ ስትራተጂክ ከሆነው ክቀይ ባህር አካባቢ በመገለልዋ በአካባቢው ተሰሚነትና ክብር ከባህር በሮቿ ጋር ሄደዋል። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው አሜሪካኖችና ምዕራባውያን ሽብርተኞችን ለመዋጋት ኃይላቸውን ያደራጁት ጅቡቲ ውስጥ ሲሆን ጅቡቲ ለዚህ ግልጋሎትዋ ብዙ ጥቅማ ጥቅሞችን ታገኛለች ። ዛሬ ጅቡቲ ሲያሰኛት በኢትዮጵያ ላይ ከምትቀልለው ከፍተኛ የወደብ አገልግሎት ክፍያና ሌሎችም በርካታ ክፍያዎች ከአሜሪካና ከምዕራባውያን በምታገኘው ገቢ በታሪክዋ ታይቶ የማይታወቅ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ላይ እንደላች ይነገራል ከዚህ ቀደም እንደነበረው ሳይሆን ዛሬ ጅቡቲ የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ ከኢትዮጵያ መግዛቱን ቀንሳ ከተለያዩ የአረብ አገሮች ጋር የነበራትን የንግድ ግንኙነት ስለአጠናከረች ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ሊኖራት የሚችል ሚና እምብዛም ነው።

አረቦችም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ብቸኛ የቀይ ባህር ተቀናቃኛቸው የነበረችው ኢትዮጵያን ከባህሩ አካባቢ አግልለው ቀይ ባህርን የአረብ ሃይቅ (Arab Lake) ለማድረግ ሲታገሉለት የነበረው ዓላማቸውን አሳክተው ዛሬ በአብዛኛው ቀይ ባህር "የአረብ ሃይቅ" ሆናለች።

ስለሆነም በቀይ ባህር በተለይ በአሰብ የኑክሌር መሣሪያ ቢጠመድበትና የጠላት ጦር ቢሰፍርበት፣ ለኢትዮጵያ ለህልውናዋ



ሥጋት የሚፈጥር ሁኔታ ቢጠነሰስባት ይህንን ለመከላከል ኢትዮጵያ ልታደርገው የምትችል ምንም ነገር አይኖርም።

## 1.3 ከጠላት መከላከልን በተመለከተ

ኢትዮጵያ በድንበር ዘለል ወንዞችዋ፣ በታሪካዊና በጂኦ-ፖለቲካዊ ምክንያቶች በአንዳንድ በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በጠላትነት የተፈረጀች አገር ለመሆንዋ ጥርጥር የለውም። ከዚህ ቀደም እንዳልተኙላት ሁሉ አሁንም ወደፊትም እንደማይተኙላት በገቢር አረጋግጠዋል። በዓለም ሁኔታዎች ከፍተኛ ዕውቀትና ተሞክሮ ያላቸው አቶ በላይ አባይ የኤርትራ የአረብ ሊግ ታዛቢ አባል መሆን አረቦች በቀይ ባር ያላቸውን የበላይነት እምብዛም እንዳማይቀንሰው አሳሰበው፣ አቶ አባይና አቶ ዘሩዕ እንደሚከተለው አስጠንቅቀዋል። "ኢትዮጵያ የባህር በር ኖሮአት ካልተቋቋመቻቸው በስተቅር የታሪክ ጠላቶችዋ በባህር በር በኩል ገብተው ነው የሚያንቋት። እንደ ጥንቱ ግብጽ በአባይ ላይ ባላት ጥቅም ምክንያት ኢትዮጵያ አባይን ለልማትዋ እንዳታውል ግብጽ ኢትዮጵያን ማተራመስዋን ትቀጥላለች"[19]።

"ኤርትራና ሶማሊያ ቀይ ባህርንና ሕንድ ውቅያኖስን ሲቆጣጠሩ ኢትዮጵያን ለማነቅ እድሉ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ አገልግሎቶችና ሸቀጥ ታስገባበት የነበረው ወደብም ኢትዮጵያን ለመሰለል ተግባር ይውላል"[20]። የእነዚህ ሰዎች አባባል ከዚህ በፊት በገቢር እንደታየው በኢትዮጵያ ጥናት የታወቁ ፕሮፌሰር ሃሮልድ ማርከስ (Harold Marcus) ታሪክን በማጣቀስ የሚከተለውን አስገንዝበዋል።

*ኢትዮጵያና ፈረንሳይ በ1908 ዓ.ም. ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ስለተገነባው ባቡር ስምምነት ባደረጉበት ወቅት በአንቀጽ 11*

---

[19] See Belai Abbai and Zeru Kihishen, "Meles" Assab Policy Threatens,Ethiopia's.National.Security," http://www.ethiopians.com/belai_and_zeru.htm,(July15,2000), Accessed on January 12, 2011.

[20] Ibid.

*በጦርነት ጊዜ ሁሉ ባሩሩ በኢትዮጵያ ግልጋሎት ስር ይውላል የሚለውን በመጣስ እ.አ.አ.በ1935/1936 ዓ.ም. ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ በጅቡቲ በኩል ለማስገባት ስትሞክር ፈረንሳይ ውሉን በመጣስ አሻፈረኝ ብላ ከለከለች። ይህ መሣሪያ የማስገባት ክልከላ ለኢትዮጵያ በጦርነቱ መሸነፍ ከዋነኞቹ ምክንያቶች አንዱ ነበር። ኢትዮጵያ ወደ ባህር የሚያዘልቀውን ባቡር ብትጠቀምም ወደብ አልባ ከመሆን አልዳነችም። ኢትዮጵያ ከባህሩ አካባቢ የሚያገሉዋት የቅኝ ገዢዎች ውል ባትቀበላቸውም ካለወደቦችዋ በጐረቤት አገራት ቅኝ ገዢዎች ጫና ስር መውደቅዋ አልቀረም። ጣልያኖች በጦርነቱ ወቅት በኢትዮጵያ ወታደር ላይ ከነሰነሱት በዓለም ሕግ ከተከለከለው የመርዝ ጢስ ውጭ ኢትዮጵያን በጦርነቱ ለሽንፈት የዳረጋት ቀጥተኛና ወቅታዊ ዋነኛ ምክንያት የምድር ባቡር በፈረንሳይ የፖለቲካ ጫና መውደቁ ነው። ይህም ማለት በአጭሩ ለኢትዮጵያ በጦርነቱ መሸነፍ ዋነኛው ምክንያት ወደብ አልባ መሆንዋ ነው[21]።*

እንግዲህ ኢትዮጵያ ለጠላት ጥቃት የተጋለጠች እንደመሆንዋ መጠን መከላከያ ኃይልዋን ማጠናከር ይገባታል ማለት ነው። ለዚህም የመከላከያ ኃይልና መሣሪያ መኖሩ የግድ ይላል። ተፈላጊው መሣሪይ ማለፍ ያለበት በሌላ አገር ወደብ አድርጐ በመሆኑ እንቅስቃሴው እክል ሊገጥመው ይችላል። የዓለም አቀፍ ሕግ እንደሚደነግገው አንድ ወደብ አልባ አገር ሰላማዊ ዕቃዎችን በሌላው አገር ወደብ የማስተላለፈ መብት አለው። ይህ የሚሆነው ግን ባለወደቡ አገር የሚጠይቃቸው ሥርዓቶችንና ክፍያዎችን ፈጽሞ ሲገኝ ነው። ባለወደቡ አገር በወደቡ ላይ ሉዓላዊ መብት ስላለው የፈለገውን ቅድመ ሁኔታዎችን ከማስቀመጥ የሚያግደው ነገር የለም። ለምሳሌ አንዱ አገር የጦር መሣሪያ በወደቡ አድርጎ ወደ አገሩ ለማሻገር ቢፈልግ ይህ ከጠላት ለመከላከለ ከሚያስፈልግህ በላይ ነው በማለት ማስተላለፍ ሊክለክለው ስለሚችል የወደብ አልባው አገር ሉዓላዊነቱ ዘወትር በቋፍ ላይ ነው ማለት ይቻላል።

[21] See, Marcus Harold, <u>Ethiopia, Great Britain and the United States</u>, 1941-1974, University of California Press, (1983), p.238.



የባህር በር ከኢኮኖሚው ጠቀሜታ ይልቅ የአገርን ነፃነትና ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር የሚኖረው ሚና የላቀ ነው። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ወደብ ሸቀጥ ማስተላለፊያ መሆኑና እራሱም ሸቀጥ ስለሆነ እንደማንኛውም ሸቀጥ ዋጋ አወዳድሮ ከረከሰበት ሄዶ መግዛት እንደሚቻል ተናግረው ነበር። ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ካሉት በተቃራኒው ወደብ ከሸቀጥነቱ አልፎ የሕልውና ጥያቄ መሆኑ ብዙዎቹ ይቀበሉታል። ሳሙኤል ፒዬአት ሜንፊ (Samuel Pyeatt Menfee) ስለኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የሚቀጥለውን ብለዋል። "ከአፍሪቃ ቀንድ በሕዝብ ብዛት አንደኛ፣ በአህጉሪቱ ደግሞ ሦስተኛ [በአሁኑ ወቅት ሁለተኛ] የሆነችው አገር ወደብ አልባ በመሆንዋ ደህንነትዋ በቋፍ ላይ ተንጠልጥሎአል[22]። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የባህር በር የአገርን ነፃነትና ደህንነትን በማረጋገጠ በኩል ያለው ወሳኝነት ሳይገነዘቡት ቀርተው ሳይሆን ሸቀጥ ማስተላለፊያ ነው ያሉት ኤርትራ የአሰብን ወዳብ በመከልከልዋ ምክንያት የሚበግነውን ሕዝብን ለማዘናጋት ይመሳሳል።

በባህር በኩል አድርጎ የሚመጣን ወራሪ ኃይል ለመመከትና እዚያው ባህሩ ውስጥ ማስቀረት ከመሬት ውጊያ በጣም የቀለለ ለመሆኑ የጦር ስልት አዋቂዎች ይናገራሉ። ወደብ አልባ አገርን ለመውረር በወደብ በኩል ገብቶ ወደ ተወራሪው አገር ለመዝለቅ በየብስ አድርጎ ከመሄድ በባህሩ በኩል መግባት የቀለለ መሆኑ እነዚሁ የጦር ስልት አዋቂዎች ይናገራሉ[23]። ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ጠላቶችዋ በቀይ ባህር በሚገኙ የባህር በሮች በኩል አድርገው ገብተው የአገሪቱን የሰሜን ክፍል ይዘው ነው ወደ መሃል አገር የዘለቁት። የእንግሊዙ ጄኔራል ናፕዬር አጼ

[22] Samuel Pyeatt Menefee, "The Oar of Odysseus; Landlocked and Geographically Disadvantaged States in Historical Perspective", 1992, 23 <u>Cal.W.Int'l L.J.</u>1 Cited in Abebe T. Kahsay supra note 3

[23] ብርጋድዬር ጄኔራል ተሰፋዬ ሃብት ማርያም፣ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወደር የሌለው ጀግና፣ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም ከዚሁ ፀሐፊ ጋር ባደረጉት ውይይት የገለፁት

ቴዎድሮስን ለመውጋት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዚሁ በቀይ ባህር ወደብ በኩል በዘይላ አድርጎ ነው።

አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ የቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት ባለ ሥልጣን፤ ከኤርትራ ጋር የተደረገውን ጦርነትን አስመልክቶ በጦርነቱ ወቅት በሰጡት ቃለ ምልልስ በቅርብ ጊዜ የሆነውን በመገምገም.... "ወደ ኤርትራ የሚጫነው የጦር መሣርያ ኢትዮጵያን ለመውጋት መሆኑን ገልጸው የራሳችን የባህር በር ቢኖረን ኑሮ ጠላት የኢትዮጵያ መሬት ሳይረግጥ መሣሪያውን መቆጣጠር ይቻል እንደነበር አሁን ግን ዘመሬታችን ድረስ እስኪደርስ እጃችንን አጣምረን እያየን በመሆኑ ቅሬታቸውን ገልጸዋል[24]።

ከታሪክ መረር ተሞክሮዎች በመነሳት ነበር ኢትዮጵያ በምጽዋ ጠንካራ የባህር ኃይል ገንብታ የአያሌ የጦር መርከቦች ባለቤት በመሆን የኢትዮጵያ የጦር መርከቦች ቀይ ባህርን እያሰሱ እስከ ሜዲቴራንያንና ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ይዘልቁ የነበረው። እንደዛሬ ኢትዮጵያዊነት በዘር በማይመነዘርበት ዘመን የመጀመርያ የጦር መርከብ ስሙ "ዘርዓይ ደረስ" ይባል እንደነበር መዛግብት ያስረዳሉ።[25] ዛሬ ሁኔታው በሙሉ የተገላቢጦሽ ሆኖ አሰብ የነበረው የባህር ኃይሉ ቅርንጫፍ ጣቢያ (base) በኤርትውያን እጅ ወድቆ እንደጥንቱ አሰብ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ዋነኛ መግቢያ በር ልትሆን እንደምትችል መገመት አያዳግትም።

በሻቢያና በደርግ መካከል የነበረው ጦርነት ተደምድሞ አሰብ የነበረው የባህር ኃይሉ ማዕከል ተዘግቶ የኢትዮጵያ የባህር ኃይል ተበታትኖ ወደ የመን ይሸሹ ከነበሩት የባህር ኃይሉ አባላት አንዱ እንዲህ ሲል አንጐራጐረ ይባላል።

---

[24] ኃይለ ሚካኤል ገብርአናንያ ሪፖርተር እሁድ የካቲት 7ቀን 2002

[25] ኢትዮጵያ የባህር ጠረፍና ባህር ኃይል፤ (አዲስ አበባ) ፤ (2000 ዓ.ም)፤ገጽ 494.



*የባህር ኃይላችን መልሀቅ የጣለበት፤*
*የጠቅል አሽከሮች በፓሪስ በኒውዮርክ የተሟገቱለት፤*
*የአሉላ ፈረሶች ውሀ የጠጡበት፤*
*የኢትዮጵያ ወጣቶች ዋና የዋኙበት፤*
*የት አለ ባህሩ በደም የማልንበት? **

ከዚህ በታች በዝርዝር እንደተገለጸው የኑክሌር መሣርያ ለመታጠቀ መንፈቅ የሚቀራት የኤርትራና የግብጽ ወዳጅ ኢራን በአሰብ አካባቢ ጦርዋን አስፍራለች የሚለው ዘገባ በአንድ ወቅት በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ተደምጦአል።

ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር በጠላትነት እስከ ተፋጠጠች ድረስ አሰብ የጠላት መርከብ ማረፊያ ሆና የጦር አይሮፕላኖች ከመርከቦች ወይንም ከወደቡ እየመጠቁ ተነስተው መሃል ኢትዮጵያን ለማጥቃት ይችላሉ። ወይንም ጠላት ጦሩን አሰብ ላይ አስፍሮ ወደ ኢትዮጵያ ለመዝለቅ አመቺ የሆነ በኢትዮጵያ ድሀ ገበሬ ሃብት የተገነባ ጥሩ መንገድ አለለት።

- ለማጠቃለል አንድ አገር የወደብ ባለቤት መሆንና አለመሆን ለአገሩ ድክመትና ጥንካሬ ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለው ፕሮፌሰር ሺመት ሲሻኝ፡ የራሳችን ታሪክ በመጥቀስ ቁልጭ አድርገው እንደሚከተለው፡ አስቀምጠውታል።

*ኢትዮጵያ በታራኳ ያለፈቻቸው መነሳትና መውደቅ ከባህር ጋር ከነበራት ቅርበትና ርቀት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግኙነት አለው። የባህር በሮቿ በእጇ በነበሩበት ዘመን የጐለበተችና የበለፀገች ኢትዮጵያን መመሥረት ተችሎአል። በአንፃሩ የባህር በሯን በተነጠቀችባቸው ዘመኖች ኢኮኖሚዋ የከሰሰ ባሕሏ የደበዘዘ ፓለቲካዊ የተናጋ ኢትዮጵያን በተደጋገሚ አይተናል። በኢትዮጵያ እጅግ ፈንፃባራቂ የነበርው የአክሱም ሥልጣኔ እንዲያ መግነኑ በሌላ አጋጣሚ ባልሆን አክሱም፤በቀይ ባህር*

---

* በአቶ እሥራት አብርሃም ከአገር በስተጀርባ ህዳር 2003 ገጽ 9 ላይ በተለየ መልኩ ቀርቧል።

*ጠረፍ ላይ በገነባችው የበላይነት ምክንያት ነበር። አዱሊስን ዋና በር በማድረግ በወቅቱ በነበረው ዓለማቀፋዊ ንግድ በማንባር ቀደምትነት በመሳተፏ አክሱም እስካሁን የሚያስደንቀው ብሩህ ሥልጣኔ መገንባት ቻለች*[26]::

ለአሁኑ የኢትዮጵያ ትውልድ የሚቀርበው ግልጽ ጥያቄ ኢትዮጵያ ወዳብ አልባ ሆና ኢኮኖሚዋ የኮሰሰ በህዷ የደበዘዘ ፓለቲካዋ የተናጋ ሆኖ ትቀጥላለች ወይስ የባህር በር ኖሮአት ጥንት በአንድ ወቅት እንደነበርችው የጉለበተችና የበለጸገች ትሆናለች፤ መልሱ አሰቸኳይ ነው። ምክንያቱም በኮሰሰችና በደበዘዘች ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ የለምና።

[26] ሹመት ሲሻኝ፤ ፕሮፌሰር፤ <u>ጦቢያ መጽሔት</u>፤ጥር 6 ቀን 1993 ዓ.ም ገጽ20.



# ምዕራፍ 2

## 2. የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት በታሪክና የባህር በር ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች

### 2.1. የኢትዮጵያ የባህር በር ይዞታ በታሪክ

ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንደነበረች በመጀመሪያ የታወቀው ከ100 እስከ 150 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተጻፈ በሚገመተው <u>በፔሪፕለስ ኦቭ ዘ ኤሪትሪያን ሲ (PERIPLUS OF THE ERYTHREAN SEA)</u> በተሰኘው መጽሐፍ ነው። ይህም መጽሐፍ የአክሱም መጠነ ሰፊ ንግድ በዋነኛው የባህር በርዋ በአዱሊስ በኩል ይተላለፍ እንደነበረ አትቶአል[27]።ቀጥሎም ኮስሞስ (Cosmos) የተባለ ሰው በጻፈው የ<u>ክርሲቲያን ፎቶግራፊ (Christian Photography)</u> በሚለው መጽሐፍ አዱሊስን መጎብኘቱና በጊዜው የነበረው ንጉሠ ነገሥት አጼ ካሌብ እንደነበረ አጼ ካሌብም እጅግ የዳበረ የባህር ኃይል እንደነበረውና ቀይ ባህርንም ተሻግሮ የመንንና ደቡብ አረቢያን ይቆጣጠር እንደነበር ጽፎአል[28]።

የአክሱም መዳከምና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ሥልጣን ላይ መውጣት ኢትዮጵያን የባህር በር አላሳጣትም ነበር። ነገሥታቱ በቀጥታም ይሁን ወይንም በጥገኞቻቸው (Vassals) አማካይነት የቀይ ባህር ወደቦችን ይቆጣጠሩ ወይንም ይገለገሉ ስለነበር

[27] W.H Schoff ed. <u>The Periplus of the Erythrean Sea</u>,1912 p.4, cited in Moges Solomon "<u>Outlet to the Sea and Ethiopia's claim over the port of Assab</u>," Thesis, Addis Ababa University Faculty of Law, (May 2003) (Unpublished)

[28] Ibid

አክሱም ሙሉ በሙሉ ከቀይ ባህር የተገለለችበት ጊዜያት ጥቂት ነበር ማለት ይቻላል።

የባህር በርን በቀጥታ በቁጥጥር ስር በማዋል ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ያደረጓት አጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-1468) ሰሜን ትግራይና ደጋውን ኤርትራ በመቆጣጠር የግብጽ ጥገኞች ይፋቶችን ድል አድርገው ቀይ ባህርን ሊቆጣጠሩ በቻሉበት ወቅት ነበር[29]።

ከዚያም በኋላ ቱርኮች ምጽዋን ከመያዛቸው ቀደም ብሎ ጥንታዊት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ዳርቻ ላይና ታቹ የባህር በሮች እንደነበሩአት የታሪክ ጸሐፍት ያረጋግጣሉ። እነዚህ ወደቦችም አዱሊስ፣ ገምበዛን፣ ዘይላና ምጽዋ ይባሉ ነበር። የዘይላ ወደብም ዋነኛው የይፋቶች ሡልጣን መኖርያ እንደነበርና ሡልጣኖች ደግሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት ጥገኛ በመሆናቸው ኢትዮጵያ በተዘዋዋሪ የባህር በር የዙላ ባለቤት እንደነበረች ተዘግቦአል[30]። በዚህ ወቅት ማዕከላዊ መንግሥት በመዳከም ላይ ሆኖ ዘመነ መሳፍንት እያቆጠቆጠ በነበረበት ጊዜ ነበር።

ለመጀመሪያ ጊዜ ቱርኮች በ1557 ዓ.ም. ምጽዋን ከጥቂት ጊዜ በኋላም የባህረ ነጋሽ ግዛት ዋና ከተማ ደባርዋን መያዝ ችለው ነበር። ሆኖም በቱርኮች አማካይነት ግብጾች ምጽዋንና አርኪኮን በመቆጣጠራቸው ቱርኮች ምጽዋን ግዛታችን ነው በማለት ይዞታቸውን አጸኑ። ቱርክ ምጽዋ የያዘችው ሦስት ኃያላን መንግስታት እንግሊዝ፤ ፈረንሳይና ጣልያን አፍሪቃ ለመቀራመት ትግል በሚያደርጉበት ጊዜ፤ፈረንሳይ ከምዕራብ አፍሪቃ እስከ ምስራቅ ቀይ ባህር ኩታ ገጠም የሆነ ቅኝ ግዛት ለመያዝ ስትጥር፤እንግሊዝ ደግሞ በበኩሏ ከሰሜን አፍሪቃ ከግብጽ ወይንም ከሱዳን እስከ ደቡብ አፍሪቃ ኩታ ገጠም ግዛት ለማድረግ በምትንቀሳቀስበት ጊዜ ነበር። እንግሊዝ ከፈረንሳይ ጋር በነበራት ፉክክር ኢጣልያን የራስዋን መሣሪያና ደጋፊ ለማድረግ አቅዳ ከአሰብ እስከ ምጽዋ ያለውን የባህር በር ጠረፍ ጣሊያን እንድትይዝ ሁለቱ አገሮች ተስማሙ። በዚህ ጊዜ ጣሊያን ኃያሏ ታላቋ ብሪታንያ ከጉኗ ከማሰለፍም በላይ ከብሪታንያ ድጋፍና

---

[29] Ibid

[30] ኢትዮጵያ ጠረፍዋና የባህር ኃይል፣ ዝኒ ከማሁ 25 ገጽ 45



እርዳታ ስላልተለያት ያለምንም መከላከያ ትገኝ ወደ ነበረች ምጽዋ በኮ/ሌ ሳሌታ የሚመራው 802 የጣልያን ጦር አዝምታ ፌብርዋሪ 1885 ዓ.ም ያለምንም ደም መፍሰስ ምጽዋን በቁጥጥርዋ ስር አደረገች። ሩባቲኖ ኩባንያ አሰብን በገንዘብ ከገዛው ከ10 ዓመታት በኋላ ነበር ጣልያኖች ምጽዋን በቁጥጥራቸው ስር ያደረጉት[31]። በምጽዋና በአካባቢዋ ይዞታቸውን ከአጠናከሩ በኋላ ጣልያኖች ግዛታቸው በአዋጅ "የአሰብ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት" የሚል ስያሜ ቀርቶ "በቀይ ባህር የኢጣልያ የቅኝ ግዛቶች" የሚል አዲስ ሥያሜ ከሰጡአቸው በኋላ ሁለቱንም የአሰብና የምጽዋ ግዛቶቻቸው በማጠቃለል በ1890 ዓ.ም "ኤርትራ" የሚል ስም ሰጥተው ቅኝ ግዛት መሠረቱ። ምጽዋ ለ300 ዓመታት በቱርኮች እጅ በነበረችበትም ጊዜም ይሁን፤ ከቱርኮችም በኋላ ግብጾች ተረክበዋት በሚያስተዳድሩበት ጊዜያት ሁሉ የኢትዮጵያ ነገሥታት በምጽዋ ወደብ ላይ አለከልካይ በወደቡ ይጠቀሙ ነበር[32]።

በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ማዕከለዊ መንግሥት ከመዳከሙ ቀደም ብሎ በአጼ ፋሲል ሞትና (1667) በአጼ በካፍ መንገሥ መሃከል ለ65 ዓመታት የኢትዮጵያ የባህር ጠረፍ ይዞታ እየተዳከመ ቢሄድም በአጼ በካፋ (1721-1730) ፤በአጼ ኢያሱ II (1730-55) ፤በአጼ ኢዮአስ (1755-69) ዘመነ መንግሥታት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፍ የተጠናከረ ይዞታ እንደነበራት ታሪክ ይገልጻል[33]።

የኢትዮጵያና የባህር በር ጥያቄ ኤርትራ ምን ያህል የኢትዮጵያ አካል ነበርች ከሚለው ጋር የተያያዘ ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራ የታሪክ ትስስር ወርዱ፤ስፋቱና ጥልቀቱ ብዙ ሰዎችን ያከራከረ ጉዳይ ሲሆን የተከራካሪዎቹ አቋም በአብዛኛው በፖለቲካ አቋማቸው ላይ የሚያጠነጥን ነው ለማለት ይቻላል።

አንዱ ጽንፈኛው ወገን ዛሬ በምናውቃት መልኳ ኤርትራ ምንም ሳይቀነስላት እንዲያውም ከዚህም በላይ ተጨምሮ የኢትዮጵያ አካል ነበረች ሲሉ ይከራከራሉ። ሌላው ጽንፈኛ ወገን

---

[31] ተወልደ ትኩእ ዶ/ር ፤የኢትዮጵያ አንድነትና ኢጣልያ፣ አዲስ አበባ (ሚያዝያ 1990 ዓ.ም) ገጽ 158

[32] ዝኒ ከማሁ

[33] ተወልደ ትኩእ ዶ/ር ፤ዝኒ ከማሁ 31, ገጽ159

ደግሞ ኤርትራ በዛሬው ቅርጽዋ ዝንተ ዓለም በነፃነት ከኖረችዋ ከኢትዮጵያ ጋር ከጉርብትና ውጭ ሌላ ምንም ዓይነት ግንኙነት ያልነበራት እራስዋን ችላ የቆመች አገር ነበረች በማለት ይከራከራሉ።

ሐቁ ግን ከእነዚህ አቋሞች ከሁለቱም ሳይሆን ኤርትራዊው ምሁር ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድሃኔ የሁለቱም ጽንፈኞች አቋም በማጣጣል ኤርትራ ቢያንስ ከ4ኛው እስከ 8ኛው ምዕተ ዓመታት በራስዋ የቆመች የተለየች የፖለቲካ ተቋም እንዳልነበረች ሲገልጹ በአንጻሩ ደግሞ ዛሬ የምናውቃት ኤርትራ በሙሉ የኢትዮጵያ አካል ነበረች የሚለውም እንደማያስኬድ ያስረዳሉ። በመቀጠልም ፕሮፌሰሩ ከ4ኛው እስከ 8ኛው ምዕተ ዓመታት ደጋው ኤርትራ የአክሱም ነገሥታትና ሥልጣን መዐከል እንደነበረች የዛሬይቱ ኢትዮጵያም ከአክሱም ተያይዛ የወረደች ስመሆንዋ ይቀበላሉ[34]።

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፖንክረስትም በታሪክ የምትታወቀው ኢትዮጵያ ከቀይ ባህርና ከኤደን ገልፍ ጋር ትዋሰን እንደነበር ሲያረጋግጡ ይህም ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንዳነበረች አንድ ሌላ ማስረጃ ነው[35]። አንድ የአፋር ተወላጅ የታሪክ ጸሐፊ ስለ አፋር ሕዝብ ታሪክ ሲጽፉ በ16ኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ዙሪያ የበላይነቱን ይዛ እንደነበርና ሰፊም ይዞታ እንደነበራት የአንድ በአረብኛ የተጻፈ ካርታ ያረጋግጣል ብለዋል። ጸሐፊው ካርታውን ሲጠቅሱ

"......ካርታ ቁ.3/4(ለ) በአረብኛ የተጻፈ ካርታ ነው። በዚህ ካርታ ላይ Ethiopia (ኢትዮጵያ) ተብሎ የተሰየመው ግዛት በቀይ ባህር ዙርያ ያሉትን የቤጃ ሕዝቦች ምድር፤ የ[illegible]ብና የበለው ሕዝቦችን ምድር እንዲሁም በአፋር ግዛት ከዳህላክ[illegible]ሴቶች እስከ ዘይላ ድረስ ያለውና ከዚያም ያለው የሱማሌን ግዛት ያጠቃልላል ሲሉ ጽፈዋል[36]። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ኮንቲሮሲኒና

[34] Tesfatsion Medhane, Professor, Eritrea Dynamics of a National Question, B.R. Gruner Amsterdam (1986) p.6-7.

[35] Richard Pankhurst, Professor "Images of Ethiopa over the Centuries, Capital, Sunday October 31, 2010 p.38.

[36] ሸህ ጁማለዲን ኢብራሂም ኸሊል ኡሽሚና በልጃቸው ሃሺም ጃማለዲን ኢብራሂም ኡሽሚ (ዶ/ር) (የተጻፈ) የአፍር/ ደናኪል ታሪክና መረጃ አርኪ ምንጫ፤ አዲስ አባባ 2000 ዓ.ም ገጽ 89.



ታዲያ የተሠኙ ጣልያናዊያንን ካመረር የተባለ ፈረንሳዊ ፀሐፊ እና ሌሎችም የውጭ አገር ፃህፍትንና አገር ጎብኚዎችን በዋቢነት ለመጥቀስ የጥንታዊት ኢትዮጵያ፣ የምሥራቅ ወሰን ቀይ ባህር እንደነበረ ማረጋገጣቸውን አሰምረውበትል። ፕሮፌሰር መስፍን ወደ አገር ምንጮች በመመለስ በምሳሌነት የአፄ አምደ ፅዮን (1312-1392)፤ የአፄ ገላውዲዋስ (1532-1551)፤ የአፄ ሠርፀ ድንግል (1555-1587) እና ሌሎችም ዜና መዋዕሎችን በማመላከት የኢትዮጵያ፤ የምሥራቁ ወሰን ቀይ ባህር እንደነበር ይልፀዋል [37]

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከአክሱም ጀምሮ ሳያቋረጥ አንዱ ሥርወ - መንግሥት ከሌላው እየተወራረሰ የወረደች ማህበረሰብና አገር እንደሆነችና የባህር በሮችም እንደነበሩአት ቀደም ሲል ሲክድ የነበረው ሕወሓት አንኳን ዛሬ በዚህ ጉዳይ ከመላው ሕዝብ ጋር ሰልፉን አሣምሮ ይገኛል። አሁንም ሕወሓት በድፍረት ወጥቶ ጥንት እንደነበረው የኢትዮጵያ የባህር በር መከበር አለበት ለማለት ግን ወኔው የገደበው ይመስላል።

ኢትዮጵያ የሰሜን ግዛቶችዋና የባህር ጠረፎቿ በ1885 ዓ.ም በቱርኮች በግብጾች፤ በጣልያኖችና በፈረንሳዮች ሤራ ከተያዙባት ጊዜ ጀምሮ የባህር በሮችዋን ለማስመለስ በየጊዜው የተፈራረቁ ነገሥታት የዓለምን ሕብረተሰብ ከመማጠንና ሁለገብ ትግል ከማድረግ የቦዘኑበት ጊዜ የለም።

ከኢሕዴግ መንግሥት በስተቀር ከአጼ ቴዎድሮስ ጀምሮ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ፣ ንግሥተ- ነገሥታት ዘውዲቱና፣ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሁሉም የባህር በር ማስመለስ ከውጭ ግንኙነቶቻቸው ፖሊስ ግዙፉና ቀዳሚውን ቦታ አስይዘውት ነበር ማለት ይቻላል። የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግም በሻቢያና በኢህአዴግ በጦርነቱ ሊሸነፍና ኤርትራም ልትገነጠል እንደምትችል ከተረዳ በኋላ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንዳትሆን የበኩሉን ጥረት አድርጓል።

[37] መስፍን ወልደ ማርያም ፕሮፌሰር ፤የክህደት ቀልቅለት አዲስ አበባ (2003) ዓ.ም 28-32 ያለውን ማየት ይቻላል

## 2.2. የኢትዮጵያ የባህር በሮችን ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች

### 2.2.1. የአጼ ቴዎድሮስ ትግል

አጼ ቴዎድሮስ እ.አ.አ. በ1855 ዓ.ም. በጥቅምት 20, ጉጃም ሳሉ ለንግሥት ቪክቶርያ በጻፉት ደብዳቤ ጥንት የኢትዮጵያ ነገሥታት ባህረ ነጋሽ እያሉ ተጠሪዎቻቸውን ይሾሙበት የነበረውን የቀይ ባህር አካባቢና ወደቦቹን የያዙት ቱርኮችን ለማስለቀቅ ጽኑ ፍላጐት እንዳላቸው ለንግሥቲቱ አስታውቃው ነበር። ይህንኑ በመግለጽ "....ቱርኮች የአባቶቼን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነው። ቱርኮች በባህር ላይ ሆነው መልእክተኛዬን አላሳልፍም ብለው ችግር ፈጥረውብኛል"[38]የሚል ነበር ደብደቤው።

በተጨማሪም አጼ ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ቆንስል ኘላውደንና እረዳቱ ካሜሩንን ተቀብለው ባነጋገሩበት ጊዜ ምኞታቸው ከእንግሊዝ ንግሥት እርዳት ጋር የቱርክና የግብጽ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ጠረፎች ለመንቀልና የጥንት ኢትዮጵያን የባህር በር ለማስመለስ ማሰባቸውን ለእንግሊዞቹ ገልጻውላቸው ነበር[39]።

ሆኖም አጼ ቴዎድሮስ ቱርኮችንና ወኪሎቻቸው የነበሩት ግብጾችን አባርረው የኢትዮጵያን የባህር በር መብት ለማስመለስና ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድረግ የወጠኑት ዓላማ ግቡ ሳይመታ ሞት ቀደማቸው።

[38] ተክለጻዲቅ መኩርያ፣ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት አ.አ.አ (1981 ዓ.ም) ገጽ 301.
[39] ዝኒ ከማሁ.



### 2.2.2. የአጼ ዮሐንስ ትግል

አጼ ዮሐንስ አራተኛው ሥልጣን ላይ ሲወጡ ኢትዮጵያ በቱርኮች፣ በግብጾች፣ በጣልያኖችና በእንግሊዞች ሤራ ከአክሱም ነገሥታት ጊዜ ጀምሮ የነበሩአት የባህር በሮችዋ ተነጥቃ ሙሉ በሙሉ ወደብ አልባ የነበረችበት ጊዜ ነበር።

ይህ ወደብ አልባ መሆን አጅግ ካሳሰባቸውና የችግሩ ጥልቀት ከገባቸው የኢትዮጵያ መሪዎች አጼ ዮሐንስ ግንባር ቀደሙ ሳይሆኑ አይቀሩም። የባህር በር ለአንዲት አገር ሉዓላዊነት መከበርና ለኢኮኖሚ ዕድገት ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለውና የባህር በር አለመኖር የአገር ሉዓላዊነትን ለከፍተኛ አደጋ ሊዳርግና ኤኮኖሚውንም ምን ያህል ሊያቀጭጭ እንደሚችል አጼ ዮሐንስ በቅጡ የተረዱ ለመሆኑ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶርያ በተለያዩ ጊዜያት የጻፉአዋቸው ደብዳቤዎችና የአደረጉአቸው የዲኘሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች ዋቢ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከነዚህም ከመጀመሪያዎቹ እንቅስቃሴአቸው አንዱ ከአክሱም ከተማ ሰኔ 10 ቀን 1872 ዓ.ም ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶርያ አጼ ዮሐንስ ምጽዋን እንዲይዙ እንዲረዱአቸው የጻፉት ደብዳቤ ነበር።

> *"..........የምጽዋን በር እኔን ደስ ይበለው ብለው እንደከፈቱልኝ ኢያሱስ ክርስቶስ የማያልፈውን የመንግሥተ ሰማይን በር ከፍቶ ደስ ያሰኝልኝ። በመንግሥትዎ ውስጥ ያሉት መማክርትዎ እኔን ደስ ሊያሰኙ ይህን አስበው ስለመከሩ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማይ ደስ ያሰኛቸው። እኔንም ከእርስዎ ጋር በምክርዎ አንድ ሆኜ ከፈቃድዎ ለማዋል ያብቃኝ። ጥንቱንም በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመንግስት የበቃሁት እርስዎ በሰጡኝ መድፍና ነፍጥና ባሩድ ነው። አሁን ደግሞ ይልቁንም ይበልጥ ፈጽመው ደስ አሰኙኝ። ከዚህ በፊትም እናት ለልጅዋ እንድትጨነቅ ለኔ መንግሥት ሲጨነቁ ይኖራሉ ። ነገር ግን በቅርብ ቀን ቀርቶ ነው እንጂ እንኳን እርስዎ የአውሮፓ ነገሥታት መላው ያውቃሉ።*

*የምጽዋ በር የአባቶቼ የነገሥታት ኢትዮጵያውያን ነው አሁንም እንዝብል በር ቤተ መንግሥት አይቀርምና በእርስዎ ወኪልነት እርዳታ የምጽዋን በር እንድይዘ ያድርጉልኝ ብዬ አለምናለሁ የቀረው ነገር ሁሉ ሲወሰን የዚህ ነገር አልተወሰነልኝም*፡፡*(ሰርዝ የተጨመረ) ደግሞ ሬር አድሚራስ ሰር ውሌም ሂዊት ሹምዎ የምጽዋን ቀረጥ እኩሌታውን የያዙ አለኝ እሺ አትምልኝና ልያዝ ብለው ማህተምስ ንግሥትን ሳልጠይቅ አላትምም ብሎኝ መጥቷል*[40]፡፡

ቀደም ሲልም አጼ ዮሐንስ፣መቀሌ ላይ ሆነው ጥቅምት 27 ቀን 1870 ዓ.ም ለፈረንሳይ ፕሬዝዳንት በጽፉት ደብዳቤ ጐርዳን ፓሻ የተባለ ሰው ተልኮባቸው ከቱርኮች ጋር እንዲያስታርቃቸው ቢጠየቁ ከቱርኮች ጋር ሊታረቁ የሚችሉት ቱርኮች የያዙትን የኢትዮጵያን መሬት በሙሉ ለቅቀው ሲወጡና ድንበር ሲካለሉ ብቻ መሆኑን አስታወቁ፡፡

አጼ ዮሐንስ ዋና ዓላማቸው ምጽዋንና አካባቢውን ይዘውባቸው የነበሩትን ቱርኮችንና ወኪሎቻቸው ግብጾችን ከአካባቢው ማባረር እንደነበር ሆኖ የሂዊት (Hiwot Treaty) ስምምነት የተባለው ውል "..... ከታተመበት ቀን ጀምሮ በምጥዋ ወደ ሐበሻ የሚገባ ከሐበሻ የሚወጣ ዕቃ ሁሉ የጦር መሣሪያ ነፍጥና መድፍ ጥይትም ቢሆን በእንግሊዝ ውክልና በነፃ እንዲወጣና እንዲገባ"[41] በመፍቀዱና ቦጐስ የተባለው ግዛታቸው የዛሬው ሐማሴን ስለተመለሰላቸው ለጊዜውም ቢሆን አጼ ዮሐንስ ውሉን ተቀብለው ፈረሙ፡፡ በመጀመሪያ እንግሊዞች ወደቡ ለኢትዮጵያ እንዲመለስ በመሠረተ ሃሳቡ ቢስማሙም የግብጽን መንግሥት ሳያስቀየም ሲሉ ኢትዮጵያ ወደቡን በነጻ እንድትጠቀም አሳሰቡ፡፡ የሂዊት ውል በሚደነግገው መሠረትም የግብጽ ጦር ካርቱም ውስጥ ተከብቦ ለእልቂት ሲዳረግ ሲል እንግሊዞች አጼ ዮሐንስ እንዲያስለቅቁአቸውና በለውጡም ምጽዋን ከቱርኮችና ከግብጾች አስለቅቀው እንደሚሰጡአቸው ቃል ገብተውላቸው ነበር፡፡ ሆኖም

[40] ታደሰ ገድሌ ከአሰደናቂዎቹ የነገሥታትና የመሳፍንት ደብዳቤዎች ፤ (ከዲፕሎማሲና ከወዳጅነት አንጻር) አዲስ አበባ (2002 ዓ.ም) ገጽ 61.

[41] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ዝኒ ከማሁ 38 ገጽ 270.



ራስ አሉላ ደርቡሾቹን ወግተው ግብጾችን ካስለቀቁ በኋላ እንግሊዝች እራሳቸው "በታሪክ ጥቂት ተወዳዳሪ ብቻ የሚገኝለት" ያሉትን ክህደት በመፈጸም ምጽዋን ለጣልያን ሰጡባቸው፡፡ ፈረንሳዮችም በበኩላቸው እምነታቸው ሙሉ በሙሉ በጅቡቲ ላይ ስለጣሉና ጅቡቲንም ለማሳደግ ስለፈለጉ ኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይኖራት ከእንግሊዞች ጋር አሴርውባት ነበር[42]፡፡

በዚህ ጊዜ ቁርኝን ተከታ የነበረችው ግብጽ በደረሰባት የኢኮኖሚ ውድቀት ምክንያት ተዳክማ በእንግሊዞች ጫና ስር ስለነበረች እንግሊዞች ከዲሽ ተውፊቅን በመጫን ምጽዋ ወይንም ዙላ ለኢትዮጵያ መመለስ በቻሉ ነበር፡፡ ሆኖም የሂዊት ውል ዓላማው ምጽዋና አካባቢው ለጣልያኖች አሳልፎ ለመስጠት የተጠነሰሰና ኢትዮጵያን ከአካባቢው ለማግለል የታቀደ ሴራ ስለነበር እንግሊዞች ውሉን ለመጣስ አላመነቱም[43]፡፡

ጣሊያኖች በእንግሊዞች ፈቃድ ምጽዋን ሲይዙ እንግሊዞች እንዳላዩ በመሆን ፊታቸውን አዞሩ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው እንደ ዶክተር ተወልደ አባባል ጣልያን "ተዝናንታ ነበር የገባችው"[44]፡፡ ጣልያን እንግሊዝን ከጐኗ አሰልፋ አስፈላጊውን ድጋፍ በእንግሊዝ እየተሰጣት ያለ ምንም መከላከያ በግብጽ እጅ ትገኝ የነበረችው ምጽዋ- በኮሎኔል ሳሌታ የሚመራው 802 ወታደሮችን የያዘ የጣልያን ጦር አዝምታ እ.አ.አ. ፌብርዋሪ 1885 ዓ.ም ያለ ምንም ደም መፋሰስ ምጽዋን በቁጥጥርዋ ሥር አደረገች[45]፡፡

ጣልያኖች በዚህ ዓይነት አለአንዳች ተቃውሞ ሰተት ብለው ገብተው ምጽዋን መያዝ የቻሉት፣ራስ አሉላ ጦራቸውን ይዘው የሂዊት ውል በሚደነግገው መሠረት የውል ግዴታቸውን ለመፈጸም ከላይ እንደተገለጸው በደርቡሾች ተከበው የነበሩ

[42] ተፈራ ኃይለ ሥላሴ (አምባሳደር) ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ 1970-1996፤ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ አዲስ አበባ፤ (1999 ዓ.ም) ገጽ 106.

[43] Shumet Sishagne, Professor. Unionists and Separatists; The Vagaries of Ethiopia Eritrean Relations 1940-1991. Hollywood, CA. 90078, 1982.

[44] ተወልደ ትኩእ ዶ/ር ዝኒ ከማሁ 31 ገጽ 42

[45] ዝኒ ከማሁ ገጽ159

ግብጾችን ለማስለቀቅ ሱዳን ሄደው በቦታው ባለመገኘታቸው ነበር[46]::

አጼ ዮሐንስ ከአክሱም ከተማ ለንግሥት ቪክቶርያ በሰኔ 10 ቀን 1870ዓ.ም ደብዳቤ ከጻፉ ከሁለት ወራት በኋላ እንግሊዞች ምጽዋን ለጣልያን በመስጠታቸው ከደብረ ታቦር ሆነው ለንግሥቲቱ እንደገና በጻፉት ደብዳቤ ባስተላለፉት መልክት "ቱርኮች ሲለቁ የምጽዋን በር እይዛለሁ ስል ጣልያን መጥቶ ምጽዋንና ሌላውን አገሬን ያዘብኝ..... አሁንም ምጽዋ ይሰጠኝ:: ቀድሞም የአባቶቼ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታት እንደሆነ ያውቃሉ:: የተለቀቀበት ጊዜም ቅርብ እንደሆነ አይጠፋዎትም"[47] ብለዋል:: ለደብዳቤያቸው ምንም መልስ ባለማግኘታቸው በእንግሊዞች ክህደት የተበሳጩት አጼ ዮሐንስ አሁንም ጣልያን መሬታቸውን እንዲለቅ በማሳሰብ ለንግሥቲቱ እንደገና ቁጣ አዘል ደብዳቤ ጻፉ:: "ለጥንት ለልጅ ልጅ ሊሆን የታረቅነው አሁን ዓመት ሳይሆነው ሦስቱም [የሂዌት] ውል ፈርሶ እንደሆነ እኔ ግድ የለኝም:: መልካም ነገር ከማድረግ በቀር! አሁንም የጣልያን ጦር መምጣቱ በእናንተ ፈቃድ ነው"[48] ሲሉ እንግሊዞችን ወቅሰዋል::

በዚህን ጊዜ ጣልያኖች ምጽዋ ይገባናል የሚለው ጥያቄአችውን እንዲተዉ እንግሊዞች ኢትዮጵያና ጣልያንን ለማግባባት ወይንም ኢትዮጵያን ለማታለል ራስ አሉላ ምጽዋንና አካባቢውን ሰሐጢን ጨምሮ ለጣልያን እንዲለቅቁ ባሳሰቡ ጊዜ ራስ አሉላም "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድምበር ቀይ ባህር ነው:: ይህንን ለቅቄ ወዴት እሄዳለሁኝ" በማለት ጽኑ አቋም ወሰዱ[49]::

በእንግሊዞች አታላይነት ምጽዋና አካባቢዋ በጣልያኖ[illegible] እጅ መውደቅና የአገራቸውን ወደብ አልባ መሆን አጼ ዮሐንስን እጅግ ያሳዘነ ጉዳይ ነበር:: አንዳንዴ ንግሥቲቱን በመለመን ሌላ ጊዜ አካባቢውን በቱርኮች ስም ይቆጣጠሩ የነበሩ ግብጾችንም በመውጋትና ድል በማድረግ ምጽዋ እንዲመለስላቸው የእንግሊዝ

---

[46] S.Rubenson, King of Kings Tewodros of Ethiopia, London (1966), p. 25.
[47] ታደሰ ገድሌ ደጋዬ ዝኒ. ከማሁ 40 ገጽ 58
[48] ዝኒ. ከማሁ
[49] አሥራት አብርሃ ዝኒ. ከማሁ 16 ገጽ16



እርዳታ ለመጠየቅ ንጉሠ ነገሥቱ ለእንግሊዝ ንግሥት አምስት ጊዜያት ያህል ደብዳቤ ጽፈዋል:: እንግሊዞች የኢትዮጵያ ነፃ አገር ሆና መቆም በፍጹም የማይፈልጉት ነገር ስለነበር በአጼ ዮሐንስ ላይ በፈጸሙአቸው ደባዎች ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆነች::

አጼ ዮሐንስ በአካባቢው ልዕለ ኃይል የነበረችውን እንግሊዝን በመፍራት ተቆጥበው ነው እንጂ ራስ አሉላ ቱርኮችንና ግብጾችን ከኢትዮጵያ ምድር ማባረር ባላቃታቸውም ነበር:: ምክንያቱም ራስ አሉላ ግብጾችን በተደጋጋሚ በጦር ሜዳ ድል በማድረግ ከአካባቢው ሊያስወጡአቸው ይችሉ እንደነበረ አስመስክረዋል::

አጼ ዮሐንስና የሐማሴኑ ገዢ ራስ አሉላ ለአገራቸው ነፃነትና ለባህር በር ባላቸው ቁርጠኝነትና ቀነአኒነት አጼ ዮሐንስ መተማ ላይ ባይሰዉና ጊዜ ቢያገኙ ኖሮ ምጽዋንና ቢያንስ ደጋውን ኤርትራና አሰብንም ከጣልያኖች መንጋጋ ፈልቅቀው ማውጣት ባልገደዳቸውም ነበር::

አጼ ዮሐንስ "ያለ ባህር በር ቤተ መንግሥት አይቀናም" ሲሉ ያለ ባህር በር የአንድ አገር ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል መግለጻቸው መሆኑ መረዳት ይቻላል:: የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች የባህር በር አሰብ ከዕቃ ማስተላለፊያነት ውጪ የሚፈይደው ነገር የለም ሲሉ ከመቶ አምሳ አመታት በፊት ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ያህል ግንዛቤ የላቸውም ማለት ነው፤ ወይስ "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም" ሆኖ ሃቁን ለማሽመድመድ ነው::

### 2.2.3. የአጼ ምኒልክ ትግል

አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያን ግዛት ለማስፋፋት ከተያያዙት ትግል በተጨማሪ በሰሜኑ እንግሊዞች በምሥራቅ ጣሊያኖች፤ ፈረንሳዮችና እንግሊዞች፤በምዕራብ እንግሊዞች፤ በደቡብ አሁንም እንግሊዞች ከብበዋቸው ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛታቸው ውስጥ ለመጠቅለል በተናጠልና በቡድን አስጨንቀው የያዛቸው ወቅት ነበር:: ስለሆነም ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት የማድረጉ ጉዳይ ከአገር ነጻነትና ሉዐላዊነት ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚታገሉለት ግብ ነበር ማለት ይቻላል:: ያም ቢሆን አጼ ምኒልክ በምሥራቅ

በኩል ወደ ባህር የሚያሻግር ወደብ በመሻት ለጣልያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ በ1876 ዓ.ም. በጻፉት ደብዳቤ "የዘይላን በር ነገር በሚቻልዎ ነገር ሁሉ ተጣጥረው በእኔ እጅ ቢሆን እንኳን በሐረርጌ፣ በአሩሲ በከንባታ በጅማና በከፋ ያለው ንግድ ሁሉ በዘይላ አድርገው ነበር፤ ስለዚህ ጠንቅቀው ቢያስለቅቁልኝ እወዳለሁ። ይህም ማለቴ ለእርስዎ እንዳይቸግርዎ ባውቀው የኢትዮጵያ ልጆች በንጉሥ ኡምቤርቶ ብርታት የዘይላ በር እጃችን ተመልሶ ገባ እያሉ እንዲሉ ስምዎ በነገሥታት ታሪካችን ይተከላል"[50]።

አጼ ምኒልክ ለጻፉት ደብዳቤ ምላሽ ከለማግኘታቸውም ሌላ ንጉሥ ዑምቤርቶም ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ምንም ያደረጉት ዕርዳታ አልነበረም። አጼ ምኒልክ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛታቸው ውስጥ ለማስገባት ይቋምጡ ከነበሩበት ጠላቶቻቸው ለመከላከል መሣሪያ የሚያስገቡት ከምጽዋ ይልቅ ለሸዋ ቅርብ በሆነው በአሰብ በኩል ነበር።

አጼ ዮሐንስ በተሰዉበት በዚያው ዓመት አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው መላው አገሪቱን ማስተዳደር ሲጀምሩ የግዛታቸው መጠንና የኢትዮጵያ ወሰን የትና የት እንደሚያካልል ለዓለም መንግሥታት ለማስታወቅ ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብደቤ ገልጸው ነበር። በምሥራቁ በኩል የኢትዮጵያን ወሰን ሲዘረዝሩ "ከሣምቦሳ አንስቶ የአሰልን ባህር ጨምሮ የጥንት ዜጋችን የምሣመድ ሃንፋሬን ግዛት ሙሉ ይዞ በባህር ዳር እየሄደ አረፋሊ ይደርሳል"[51] ሲሉ አስታውቀው ነበር።

አጼ ምኒልክ በዚሁ ለንግሥት ቪክቶርያ በጻፉት ደብዳቤ "....የጥንቱ ዜጋችን የመሃመድ ሃንፍሬን ግዛት" ~~ሲሉ የአፋርን~~ ምድር ያስተዳድሩ የነበሩት የሱልጣን ሃንፋሬን የዛሬው የቢትወደድ አሊ ሚራህ አባትን ሲጠቅሱ ነው። ሱልጣን አሊሚራህ ደግሞ እንደዛሬው የኢትዮጵያና የኤርትራ አፋር የሚባል ክፍፍል ስላልነበር ዋና ቀያቸው አውሳ ሆኖ የሁሉም

---

[50] ታደሰ ገድሌ ጸጋዬ ገጽ ዝኒ ከማሁ 40 ገጽ 71.

[51] ተክለ ጻዲቀ መኩሪያ ዝኒ ከማሁ 38. ገጽ 301



አፋሮች መሪ ነበሩ። አጼ ምኒልክ ይህንን የጠቀሱት ግዛት የአሰብን ወደብ እንደሚጨምር ግልጽ ነው።

ቀድመዋቸው ከነበሩት ነገሥታት ሁሉ አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ማድረግ ጉዳይ አሳልተው የያዙት ቢመስልም ዘወትር ያሳስባቸው እንደነበር ጸሐፍት ይገልጻሉ። አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን በያዙበት ጊዜ አውሮፓውያን አፍሪቃን እየተቀራመቱ በነበረበት ጊዜ ሆኖ ኢትዮጵያንም የቅኝ ግዛት ቀንበር ለማሸከም በብዙ የሚጥሩበት ወቅት ስለነበር አጼ ምኒልክ ለባህር በር ለመታገል ፋታ አላገኙም ነበር።

አጼ ምኒልክ ዋነኛው ይጠቀሙበት የነበረው የባህር በር ፈረንሳዮች ቀደም ሲል ይዘውት የነበረው አቦክ፣የዛሬይቱ ጅቡቲ ሲሆን አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድረግ ዲፕሎማሲያዊ ትግላቸውን በመቀጠል በጃንዋሪ 29, 1897 ዓ.ም. ራስ መኩንን ከፈረንሳይ ሱማሌ ተወካይ ኤም ላጋርድ ጋር የተፈራረሙት ውል በተደራደሩበት ወቅት አጼ ምኒልክ ጅቡቲ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወደብ መሆኑ የሚያረጋግጥ አንቀጽ እንዲያካትት ለራስ መኩንን ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር[52]። ይህ አጼ ምኒልክ በውሉ እንዲካተት ያዘዙት አንቀጽ በሙሉ ተካትቶ እንደነበረ ወይንም እንዳልነበረ መረጃ የለም።

አጼ ምኒልክ የአሰብም ሆነ የጅቡቲ ያባህር በሮች ለኢትዮጵያ የሚያመጡት የኢኮኖሚ ጥቅምና የደህንነት ዋስትና እየተረዱ እነዚህን የባህር በሮች ለማግኘት ለምን ጥረት አላደረጉም የሚለው ጥያቄ ብዙዎችን ያከራከረ ጉዳይ ነው።

---

[52] R.K.Pankhurst "Ethiopia and The Red Sea and The Gulf of Aden Ports in the Nineteenth Century Ethiopia The Observer, vol.8 no.1 (1964) p. 73.

ይልቁንም አጼ ምኒልክ እ.አ.አ በ1896 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ጣልያንን ድል ከአደርጉ በኂላ ወደ ሰሜን አለመግፋታቸውና ቢያንስ ከደጋው ኤርትራ ጣልያንን አባርረው ጥንት የኢትዮጵያ አካል እንደነበረ የማያጠራጥረው አካባቢ እንኳን አለመያዛቸው በአንዳንዶቹ ዘንድ እንደ ብልህ ውሳኔ ሲቆጠር በሌሎች ደግሞ እንደ ክህደትም ተቆጥሮባቸዋል[53]*።

ከላይ እንደተገለጸው አውሮፖውያን አፍሪቃን በቅኝ ግዛትነት የሚቀራመቱበት ወቅት ነበርና ብቸኛዋ ነፃ አፍሪቃዊ አገር ኢትዮጵያንም ለመዋጥ ምክንያት የሚፈልጉበት ሁኔታ ላይ ነበሩ።አንዳንድ የታሪክ ፀሐፊዎች ግምት አፄ ምኒልክ ጣልያንን እ.አ.አ. በ1896 ዓ.ም አድዋ ላይ ድል ቢያደርጉትም ወዳ ኤርትራ የማስወጣት አቅም ግን አልነበራቸውም፤ በሌሎች ዓይን ደግሞ ንጉሡ ወዳ ሰሜን ሊዘልቁ እንደማይችሉ ከመገንዘባቸውም በላይ አድርገውት ቢሆን ኖሮ ተጠናክሮ ይጠብቃቸው የነበረውን የጣሊያንን ጦር ሊቋቋሙት አይችሉም ነበር። [54] ከምጽዋም ሆነ ከአፋር ሰላጤ ጣልያኖችን ለማስወጣት ቢሞክሩ ኖሮ አሥመራ ውስጥ ተጠናክሮ ለተቀመጠው የጣልያን ጦር ሰለባ ሆነው ሌላውንም የኢትዮጵያ ክፍሎች አደጋ ላይ በጣሉ ነበር። ቡተጨማሪም እንግሊዝ፣ ጣልያንና ፈረንሳይ ምኒልክን የ1908

[53] See Tecola W.Hagos Professor http://www.tecolahagos.com/part4.html

*ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ለዚህ ወቀሳ መልስ ሲሰጡ የሚከተለውን ጽፋዋል። "ዶ/ር ተውልደ ትኩእ አፄ ሚኒልክን ከጣልያኖች ጋር አባሪና ከሃዲ አድርገው መወቀሳቸው ብዙ ሁናቴዎችን ካለመገንዘብ የመነጨ ይመስለኛል። ከብዙ የኢትዮጵያ ሰሜት ያለችው የኤርትራ ተወላጆች ጭምር የሚሰማ ወቀሳ ነው።.........አጼ ምኒልክ ከኢጣልያ ጦር ጋር የተዋጉበት ዘመንና የኢትዮጵያ ሁኔታ አብዛኛው የኢትዮጵያ ጦር ከመሃል አገር ከሺህ ኪሎ ሜትር በላይ ነበር የሚመጣው ። የራሱን ስንቅ እየያዘና በራሱ መሣርያ የ[illegible] መሆኑን፤ ትግራይም ሆነ ኤርትራ ይህንን ሠራዊት ለመመገብ [illegible]ለመቻላቸውና የኤርትራም ሰዎች ምንም ንቅናቄ አለማድረጋቸው መታሰብ አለበት። እንዲህ ያለ አጋጣሚ በሌሎች አገሮችም ላይ በሃያኛው ምዕተ ዓመትም የደረሰ ነው"። ሲሉ ገልጸዋል። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ዝኒ ከማሁ 37 ገጽ 48 የግርጌ ማስታወሻ 13.

[54] Haggai Erlich, Ethiopia and Eritea During the Scramble for Africa. London (1982), p 193.



ዓ.ም. ውል ጭነውባቸው ስለነበር በዚህ አስጨናቂ ሁኔታ እያሉ ጣሊያኖችን ከምጽዋም ይሁን ከአሰብ አባርረው ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ሊያደርጉ አልቻሉም[55]።

## 2.2.4. ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ በኂላም አፄ ኃይል ሥላሴ ያደረጉት ትግል

ኢትዮጵያን በተጨባጭ የባህር በር ባለቤት ለማድረግ በንግሥት ዘውዲቱና በልዑል ራስ ተፈሪ በኂላም በግርማዊ ቀደማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ እንደነበር በታሪክ ተዘግቦአል።

እ.ኤ.አ. በ1924 ዓ.ም ልዑል ራስ ተፈሪ አውሮፖን በጉበኙበት ወቅት ኢትዮጵያ በጅቡቲ በኩል የባህር በር እንዲኖራት ፈረንሳዮችን ጠይቀው አልተሳካለቸውም። እንዲሁም ሮማ ዘልቀው ይህንኑ የባህር በር ጥያቄ ቆይቶ ደመኛ ጠላታቸው ለሆነው ለሙሶሎኒ አቅርበው ኢትዮጵያ በአሰብ ለዘጠና ዘጠኝ ዓመታት በነፃ እንድትጠቀም ጣልያኖች ሲፈቅዱ በለውጡ ደግሞ ኢትዮጵያ ከጣልያኖች ውጭ ከማንም ጋር እንዳትገበያይ ገደብ ያስቀምጥ ስለነበር በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት አላገኘም። ራስ ተፈሪ እንግሊዞችንም ከመጠየቅ ባይቦዝኑም እንግሊዞች ግን ለጥያቄአቸው መልስ ሳይሰጡ ቀሩ[56]።

አሁንም ባለመታከት የንግሥት ዘወዲቱ መንግሥት በጣልያኖች እጅ የነበረውን አሰብን የኢትዮጵያ ወደ ባህር መግቢያና መውጫ በር ለማድረግ በማሰብ ለጣልያኖች የንግሥቲቱ መንግሥት ጥያቄ አቅርቦ በሁለቱ መንግሥታት መሃከል ድርድር ተካሂዶ ከድርድሩ በኂላ ኢትዮጵያን ወደ ቀይ ባህር የሚያዘልቅና አሰብንም ለመጠቀም የሚያስችል ከቀረጥ ነጻ የሆነ መተላለፊያ (corridor) እንዲኖራት እ.አ.አ. በአገስት 1928

[55] Teggai Mebrahtu, http://ethiopia first.com/news2002 mar.rule_of_law_and_justice_Lasting_place.html

[56] ኢትዮጵያ ጠረፍዋን የባህር ኃይል ፤ ዝኒ ከማሁ 25 ገጽ 65.

ዓ.ም. ጣልያንና ኢትዮጵያ ውል ተፈራረሙ። ሆኖም ጣልያኖች የውል ግዴታቸውን በመሻር ከቀረጥ ነፃ ይሆናል የተባለው መተላለፊያ ሳይፈቀድ ቀረ[57]።

አፄ ኃይለ ሥላሴ በማናቸውም ዓይነት በጭሰኝነት እንኳን ቢሆን ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት ከጣልያን መሪ ጋር ተነጋግረው በኮንሴስዮን ሊሰጣቸው ታስቦ የነበረው ከጥቂት ሺህ ካሬሜትር የማይበልጥ እንደነበረ ይነገራል። ያም ሆኖ ይህንን ትንሽ የወደብ መሬትንም ሊያገኙ አልቻሉም[58]።

በእነዚህ አፍሪቃን በቅኝ ግዛትነት ጠቅልለው የያዙ አውሮፓውያን (ጣልያን፣ እንግሊዝና፣ ፈረንሳይ) ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር በማግለል የባህር በር እንዳይኖራት ውስጣዊ ስምምነት አድርገው ስለነበር እስከ 1952 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆና ቀጠለች።

ጣልያኖች በአፍሪቃ ቅርምት ሊቢያና ሶማሊያ የደረሳቸው ሲሆን ሰፊዋና ለሟን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት ይዞ ሃብቷን ለመበጥበጥ ለኑሮ ምቹና ነፋሻ በሆኑ አካባቢዎች ጣለያኖችን ለማስፈር ሲደክሙ ከቅኝ ግዛት አጋሮቻቸው ጋር ሲያሤሩ ብዙ ቆይተዋል። ስለሆነም እ.አ.አ. በ1933 ዓ.ም. ጦርነት ከፍተው ማይጨው ላይ ኢትዮጵያ ድል ሆና ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በከፊልም ቢሆን በፋሽስት ጣልያኖች ሥር ማቃሰች።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በቃል ኪዳን አገራት አሸናፊነት ከተደመደመ በኋላ፣ የኢትዮጵያ አርበኞችና እንግሊዝ ጣልያንን ከኢትዮጵያ አባረሩ። አፄ ኃይለ ሥላሴ እንግሊዞች ወደ ሥልጣናቸው እንደሚመልሷቸው ከተረዱ በኋላ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀልና ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድረግ ወዲያውኑ ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ዘመቻ ጀመሩ[59]።

በዚህም መሠረት አሜሪካኖች ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስና አገሪቱ የባህር በር እንዲኖራት እንዲደግፉ እ.አ.አ በ1943 ዓ.ም. አፄ ኃይለ ሥላሴ የውጭ ጉዳይ ምክትል

[57] Tseggai Mebrahtu, supra note 55.
[58] Ibid.
[59] Shumet Sishagne, Professor, supra note 43, P.98.



ሚኒስትራቸውን አቶ ይልማ ደሬሳን ወደ ዋሺንግተን ዲሲ ልከው አሜሪካኖችም ሃሳቡን ሲደግፉት እንደሚችሉ ለአቶ ይልማ አረጋገጡላቸው[60]።

አፄ ኃይለ ሥላሴ በፌብርዋሪ 13 1945 ዓ.ም. ከያልታ (Yalta) ስብሰባ መልስ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሩዝቬልትን (Roosevelt) ባነጋገሩበት ወቅት ቀደም ሲል በጦርነቱ ጊዜ ጅቡቲ ደርሶ የነበረውን መከላከያ መሣሪያ ወደ አገር እንዳይገባ በፈረንሳይ መከልከሉ የተሰማቸውን ቅሬታ በምሬት ገልጸው የባቡር ግልጋሎት ቢኖርም ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በመሬት የታጠረች በመሆንዋ በፋሽስቶች በጦርነቱ ለመሸነፍዋ ዋናው ምክንያት ይኸው ወደብ አልባ መሆንዋ ነበር ሲሉ ገለፁ። አፄ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያ ወደብ እንዲኖራት የአሜሪካን ዕርዳታ ጠይቀው ይኸም ሊፈጸም የሚቻለው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትዋሃድ መሆኑን ለሚስተር ሩዝቬልት አስረዱ።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን የወደብ ባለቤት ለማድረግ የማያወላውል አቋምና ፅኑ እምነት ስለነበራቸው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ከመተሳሰርዋ አምስት ዓመት ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ በ1947 ዓ.ም "አዱሊስ፣ ባህረ ነጋሽና ወልወል" ብላ የሰየመቻቸውን ሦስት መርከቦች ገዝታ ቀይ ባህር ላይ አሰማርታቸው ነበር[61]።

አፄ ኃይለ ሥላሴ በአፍሪካና በሌሎችም አካባቢዎች መልካም ስምና ይልቁንም ትልቁ የአዓም አቀፍ የሕግና የዲፕሎማሲ ምሁር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ኃብተወልድና ሌሎችም ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ትግል ኤርትራ በ1952 ዓ.ም. በኤርትራ ሕዝብ ተወካዮች ፍላጐትና በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቀለች። ለዘመናት ትግል ሲደረግለት የኖረው የባህር በር ጥያቄም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ዕውን ሆኖ ኢትዮጵያ የሁለት ወደብ ማለት የምጽዋና የአሰብ ባለቤት ሆነች። በሂደትም ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ የኢትዮጵያ ሙሉ አካል ስትሆን የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ለአንዴና ለሁሌም ዘላቂ መፍትሔ ያገኘ መሰለ። ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ

[60] Ibid.
[61] Ibid

ከኢትዮጵያ ጋር ሙሉ በሙሉ ስትዋሃድ ሁሉቱም ወደቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት ሆኑ።

ሆኖም የፌዴሬሽኑ መፍረስ የኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ አስነስቶ ሻቢያ፣ ጀብሃ እና በኋላም ሕወሓት ኤርትራን ቅኝ ገገር ከሚልዋት ከኢትዮጵያ ነጻ ለማውጣት የትጥቅ ትግል ጀመሩ[62]።

### *2.2.5. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት (ደርግ) ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንዳትሆን ያደረገው ጥረት*

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሳቸው መጠነ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ጥፋቶች እንዳሉ ሆኖ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት ላይ ፅኑ አቋም እንደነበረው ጠላቶቹ እንኳን አሌ ሊሉት ያልቻሉ እውነታ ነው። ምናልባትም ይህ በሉዓላዊነት ላይ ያለው ግትር አቋሙ ለውድቀቱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አስተዋጽዖ አድርጎአል ማለት ይቻላል። ማለትም ደርግ የኤርትራን መገንጠል ተቀብሎ አገሪቱን ወደብ አልባ ቢያደርግ ኖሮ በሥልጣን ሊቆይ ይችል ነበር ወይ የሚለው ጥያቄ ሊያከራክር ይችላል።

ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ገና ከመነሻው በ1967 ዓ.ም አሰብን ከኤርትራ ለመለየትና "የአፋር ነፃነት ንቅናቄ"ን (Afar Liberation Movement) ከሻቢያ ጋር ለማጋጨት በማሰብ ንቅናቄውን ኃበዞ በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መሪነት ውይይት ይካሄድ ነበር። በውይይቱም ይኸው ንቅናቄ ለኤርትራ ነፃነት ከሚዋጉ ኃይሎች ለመለየት በደርግ በኩል ብዙ ጥረት ተደርጐ ነበር።

ደርግ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ከኤርትራ ከማንኛውም ክፍል በላይ አሰብን አጥብቆ ይዞ ትኩረቱ ያሳረፈበት እንደነበር ይታወቃል። ኢትዮጵያ በሶማልያ ጦርነት ተጠምዳ [illegible]ነበር ሻቢያ

62 See Tekeste Negash. Professor ,Brothers at War Making sense of Eritrean-Ethiopan War (Eastern African Studies),(April 1,2001)



በአብዛኛው የኤርትራ ግዛቶች መንቀሳቀስ ችሎ በነበረበት ጊዜ እንኳን አሰብ ቁጥሩ ከፍተኛ በሆነ የኢትዮጵያ ጦር ጥበቃ ስር ስለነበረች ሻቢያ አንድም ጊዜ አሰብ ለመዘለቅ ባለመቻሉ በአካባቢው ሰላም ሰፍኖ ነበር[63]።

የቀይ ኮከብ ዘመቻ ታውጆ ደርግ ከተሸነፈ በኋላ ምናልባትም ሻቢያንና ሕወሓት ሊቋቋማቸው የማይቻለው ኃይሎች መሆናቸውን ደርግ እራሱ እየተረዳ መጣ። የኤርትራ መገንጠልም ዕውን ሊሆን እንደሚችል ስለተገነዘበ የኢትዮጵያን የባህር በር ከመዘጋት የሚያድን የመሰለው አማራጭ የኢትዮጵያና የኤርትራንም ጨምሮ የውስጥ ድንበሮችን የሚያሸጋሽግ ቀመር ቀየሰ[64]። በማያያዝም ኤርትራ ተገንጥላ ብትሄድም አሰብን በኢትዮጵያ እጅ ለማቆየት እንዲቻል ዝግጅት ሲያደርግ ቆየ።

ደርግ በቀየሰው ቀመር መሠረት አሰብን ራስ ገዝ አድርጎ ሙሉ በሙሉ ከኤርትራ መለየት ነበር። ራስ ገዝ አሰብ በቋንቋ፣ በባህል፣ በዘር፣ በጂኦግራፊም ሆነ በሕዝብ ሥነ ልቦና ከኤርትራ ጋር ምንም የሚያገናኛት ነገር አለመኖሩን በእፅንኦት ከአስቀመጠ በኋላ ነበር በአዋጅ ቁጥር 16/1980 አሰብን ራስ ገዝ አስተዳደር አድርጐ ያወጀው። የዚህም መሠረታዊ ዓላማው ኤርትራ ብትገነጠልም እንኳን አሰብን ለይቶ ወደ ኢትዮጵያ ማስቀረትና የኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይዘጋ መከላከል ይቻላል ከሚል ግምት ተነስቶ ነበር።

ደርግ አሰብንና ሌሎችንም ራስ ገዝ ያደረገበትን ምክንያት ሲያስቀምጥ የሰጣቸው ምክንያቶች በኢኮኖሚ ራሳቸውን መቻላቸው፣ በአውራጃው የብሔር ጥያቄ መኖር፣ የጂኦግራፊ አቀማመጥ፣ ለአስተዳደር አመቺነት፣ የሕዝቡ አንድ ጎሳ

63 John Markakis, Resource and Conflict in the Horn of Africa. Thousand Oaks, Ca. Sage publications, (1998),p.188.

64 Andargachew Tiruneh, The Ethiopian Revolution 1974-1987 A Transformation From an Aristocratic to a Totalitarian Autocracy. Press Syndicate of the University of Cambridge, Cambridge (1993), p 283.

መሆን፣ፖለቲካዊ እሳቤዎች፣የአገር ደህንነትን ከግንዛቤ በማስገባት እንደነበረ ገለጸ።

ደርግ እነዚህ ሁኔታዎችን ለራስ ገዝነት እንደ መሥፈርት ቢያስቀምጣቸውም ዋነኛው ዓላማው ግን አሰብን በሁሉም መልኩ ከኤርትራ ለይቶ ኤርትራ ብትገነጠልም አሰብን በመያዝ የኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይዘጋ ለማረጋገጥ እንደነበር መገመት ይቻላል። ምክንያቱም እንደ አሰብ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች የብሔር ጥያቄ የሚንፀባርቅባቸው የአንድ የኢኮኖሚ ነፀብራቅ ወዘተ. የሆኑ ሌሎች ክልሎች ወይንም አውራጃዎች በሙሉ እንደ አሰብ ራስ ገዝ አልተባሉም። ድሬደዋና ኤርትራም ራስ ገዝ የተባሉበት ዋናው ምክንያት እንዲያውም ራስ ገዝ የሚል ቀመር የተቀረፀው አሰብን ከኤርትራ ለመለየትና ኤርትራ ከኢትዮጵያ ብትገነጠል አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማስቀረት ይቻል ይሆናል ከሚል እሳቤ መሆኑ ግልፅ ነበር።

ሆኖም እንደሚታወቀው ሁሉ ሻቢያ በጦርነቱ ደርግን አሸንፎ ኤርትራን በተቈጣጠረ ጊዜ አሰብም ከኤርትራ ጋር ከዚህ በታች እንደተገለጸው ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ጠቀለለ። በኢሕአዴግ ቡራኬም አሰብን የኤርትራ አካል በማድረግ ኢትዮጵያ ለአርባ ዓመታት የተጠቀመችባቸውን የባህር በሮች ተነጥቃ ከዚህ በታች ያለው ሰሌዳ እንደሚያስረዳው በዓለም በሕዝብ ቁጥር ትልቋ ወደብ አልባ አገር ሆነች። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ድንበርና በባህሩ መሃከል ያለው 60 ኪሎ ሜትር በዓለም በአንድ አገርና በባህሩ ያለው እርቀት በጣም አጭሩ ለመሆን በቃ።



| ሰሌዳ 2 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አገር | የህዝብ ቁጥር | ተ.ቁ | አገር | የህዝብ ቁጥር |
| 1 | አፍጋኒስታን | 29,802,000 | 23 | ማሶዶኒያ | 506,928 |
| 2 | አንዶራ | 7,638 | 24 | ማላዊ | 15,263,417 |
| 3 | አርመንያ | 3,082,000 | 25 | ማሊ | 13,010,209 |
| 4 | ኦስትሪያ | 8,217,280 | 26 | ሞልዶቫ | 3,603,506 |
| 5 | አዘርባይጃን | 8,781,000 | 27 | ሞንጎልያ | 2,670,966 |
| 6 | ቤላሩስ | 9,049,000 | 28 | ኔፓል | 29,330,505 |
| 7 | ቡታን | 691,141 | 29 | ኒዠር | 15,263,417 |
| 8 | ቦሊቪያ | 9,362,860 | 30 | ፓራጓይ | 6,348,917 |
| 9 | ቦትስዋና | 1,949,780 | 31 | ሩዋንዳ | 9,997,614 |
| 10 | ቡርኪና ፋሶ | 15,756,927 | 32 | ሳንማሪኖ | 30,000 |
| 11 | ብሩንዲ | 8,303,330 | 33 | ሰርቢያ | 7,344,847 |
| 12 | ሴንትራል አፍሪካ ሪፑብሊክ | 4,000,004 | 34 | ስሎቫኪያ | 5,400,000 |
| 13 | ቻድ | 11,206,152 | 35 | ስዋዚላንድ | 1,184,936 |
| 14 | ቼክሪፐብሊክ | 10,500,000 | 36 | ታጂኪስታን | 6,250,000 |
| 15 | ኢትዮጵያ | 82,824,732 | 37 | ኡጋንዳ | 32,709,865 |
| 16 | ሃንጋሪ | 10,000,000 | 38 | ኡዝቤኪስን | 27,767,100 |
| 17 | ካዛኪስታን | 25,000,000 | 39 | ቫቲካን ሲቲ | 826 |
| 18 | ኪርጊስተን | 5,138,000 | 40 | ዌስት ባንክ | 2,514845 |
| 19 | ላኦስ | 6,800,000 | 41 | ዛምቢያ | 12,935,368 |
| 20 | ሌሴቶ | 3,066,919 | 42 | ዚምባብዌ | 12,891,000 |
| 21 | ሊተንሽንይን | 34,247 | 43 | ቱርክሜኒስታን | 4,254,000 |
| 22 | ሉክሱምበግ | 500,000 | 44 | ዌስት ባንክ | 2,514,843 |

*Source: Compiled from the Internet on February 20, 2011*

በአንዳንድ ሰዎች ስሌት ኢትዮጵያ ከ90 ሚልዮን ሕዝብ በላይ ሲኖራት በዚህ ሰሌዳ መሠረት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 82,824,732 ነው ተብሎአል። እንደ አውሮጳውያን አቈጣጠር በ2015 የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከመቶ አሥራ አምስት ሚልዮን በላይ እንደሚሆን ይጠበቃል። በሕዝብ ብዛት ከኢትዮጵያ ቀጥሎ ያለው ወደብ አልባ አገር ኡጋንዳ ሲሆን የሕዝቡ ቁጥር የኢትዮጵያ አንድ ሦስተኛው ያህል (32,709,865) ነው። ቀጥሎም ሦስተኛዋ አገር ኔፖል ስትሆን እርስዋም 29,330,505 ሕዝብ ያላት ሲሆን ቫቲካን ሲቲ፣ ሉክስምቡርግ አንዶራና ሊሽተንታይን የአዲስ አበባን አንድ አምስተኛ አያህሉም።

## 2.2.6. የኢትዮጵያን የባህር በር ለማዘጋት ሕወሓት/ኢህአዲግ/ ያደረገው ጥረት

የሕወሓት መሪዎች ኤርትራን አስገንጥሎ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ እንድትሆን የሰረጸባቸው ምኞት ገና በተማሪነታቸው "ማህበረ ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ" የተባለው የተማሪዎች ማህበር ከአቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ነበር። ወደ ሕወሓትነት ከተለወጡም በኋላ ይህንን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ የኤርትራ ጥያቄ የብሔረሰቦች እኩልነት የማረጋገጥ ጥያቄ ሳይሆን የመገንጠልና ነፃ የመውጣት የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው በማለት የትግላቸውን አንኳር መሠረት ጣሉ። ይህንን ኢትዮጵያ የባህር በር የሚያሳጣ ኤርትራን ማስገንጠልና ደርግን ከሥልጣን ማባረር ዋነኞቹ ዓላማዎቻቸው ሆነው መሪዎቹ ይህንኑ በሕወሓት አባላትና በህዝቡ እንዲሰርጽ ቅስቀሳ ጀመሩ። ከሕወሓት ቀዳሚ መሪዎች አንዱ አቶ መለስ ዜናዊ በ1979 ዓ.ም ኤርትራን አስመልክቶ በጻፉት መፅሐፍ "…. ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ማለት ትክክለኛና ሳይንሳዊም ነው"[65] ሲሉ ፅፈዋል። በተጨማሪም "…ኢምፔርያሊስቶች የዛሬይቱን አፍሪቃ እንደ ቅርጫ ሥጋ

[65] መለስ ዜናዊ የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት? (ግምገማ)፣ (1979 ዓ.ም), ገጽ 20.



ይከፋፈሉት የነበረበት ወቅት ስለነበር የማንኛውም አፍሪቃ አገር አንድ ወጥ ሆኖ መፈጠር የራሱ የታሪክ ምዕራፍ የመጀመር ታሪኩንም ከዚሁ ይጀምራል። አንድ አገር ሆኖ መፈጠርም በዚሁ ወቅት ይጀምራል"[66]። "ኢትዮጵያ የ3000 ዓመት ዕድሜ ያለው ጠንካራ ታሪክ የላትም። በአንድ በማእከላይ መንግስት በመተዳደር በሃገር ደረጃ መቆም ከጀመረች ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ወዲህ የ100 ዓመት ዕድሜ አይሞላትም"[67] በማለት፣መጽሐፋቸው የኤርትራ ትግል እንዲያሸንፍ በመመኘት ይደመድማል። በዚህ አባባል የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መቼም ቢሆን የጥንቷ የአክሱም ወራሽ ሆና አታውቅም። የአክሱም ወደቦችም ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት አልነበራቸውም። ጥንታዊት ኢትዮጵያ የባህር በር ኖሮአት ስለማታውቅ ዛሬ የባህር በር ባይኖራት ምን ያስገርማል ለማለት የተሰነዘረ ይመስላል።

አቶ መለስ በኢትዮጵያ ውስጥ በኤርትራ ጥያቄ ላይ የጠራና ሳይንሳዊ አቋም ያሏቸው ዴሞክራቲክ ኃይሎች እንደነበሩ ይነግሩንና ሕወሓትም ከእነዚሁ ውስጥ መገኘቱን ገልጸው ሕወሓት ለዚህ ዓላማ ለብዙ ጊዜ መታገሉን ያስረዳሉ። አከታትለውም ይህ ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ የጫነችው የቅኝ ግዛት ቀንበር መደምሰስ እንደዋነኛ ዓላማው አድርጎ የተነሳው ሻቢያ የሚያደርገው ትግል መደገፍ እንዳለበት አቶ መለስ ያሳስባሉ። ሕወሓት የትግራይ ሕዝብን ለማሳሳት እንደሞከረ አቶ መለስ ሲገልጹ "ሕወሓት የትግራይ ህዝብ በኤርትራ ሕዝብ የመገንጠል ጥያቄ ላይ ትክክለኛ የድጋፍ አቋም እንዲይዝ አድርጓል " ይላሉ። ዘለዓለም በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ የተሰነዘሩ ጥቃቶችን በመመከት የወራሪዎች ቀዳሚ ገፈት ቀማሽ የሆነው የትግራይ ሕዝብ የኤርትራን መገንጠልን ደግፎ አገሩን ወደብ አልባ የማድረግ የሕወሓት ስብከት ተቀብሎ ነበር ብሎ ጠላቱም ቢሆን አያማውም። በሕወሓት መሪነት ግን ኤርትራን ከኢትዮጵያ "ቅኝ ተገዥነት" ነጻ ለማውጣት በኮሎኔል አምሳሉ ገብረዝጊ አባባል "የትግራይ ልጆች በማይመለከታቸው ጉዳይ ወደ

[66] ዝኒ ከማሁ ገፅ 6.
[67] ዝኒ ከማሁ.

ኤርትራ መሬት ሄደው ጸረ ኢትዮጵያ ለሆነው ለሻቢያ ወታደራዊ ድጋፍ በመስጠት ቆስለዋል፤ ሕይወታቸውንም አጥተዋል"[68]።

አንዳንድ የሕወሓት መሪዎች ኢትዮጵያ የአክሱም ወራሽ አይደለችም የሚለው አቋማቸው እስከ ዛሬም ይዘው እንደቀጠሉበት ነው። "ኢትዮጵያ የአክሱም ወራሽ አይደለችም፤ እንደ አገር ከተቋቋመች ከመቶ ዓመት አይበልጥም፤ ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት ተይዛለች" እየተባለ በሕወሓት መሪዎች የተለፈፉ ኃላፊነት የጎደላቸው አባባሎች ከሃያ ዓመታት በፊት የተባሉ ከመሆኑም በላይ በጊዜው ከዕውቀት ማነስና ከዕድሜ ለጋነት የመነጩ ይሆናሉ ተብሎ ሊታለፉ ይቻል ነበር። ሆኖም ግን እነዚህ ሰዎች አቋማቸውን ስለ መቀየራቸውና በአባባሎቻቸው ስለ መጸጸታቸው ምንም ያሳዩት ወይንም ያሉት ነገር ካለመኖሩም በላይ በተለይ ኤርትራ የኢትዮጵያ "ቅኝ ግዛት" ነበረች የሚለው አቋማቸውን ዛሬም እንደገፉበት ነው።

ይህንኑ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 እና በአልጀርስ ስምምነት በማያጠራጥር መልኩ አረጋግጠዋል። አንቀጽ 39 የመጀመሪያው ክፍል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ማንኛውም ብሔረሰብ አንዳንድ ፎርማሊቲዎችን እስካሟላ ድረስ ውሃ ቀጠነ ብሎ መገንጠል እንደሚችል በግልጽ ይደነግጋል። እንዲህ ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ወይንም ምክንያት አልባ መገንጠል የዓለም አቀፍ ሕግ የሚፈቅደው ተገንጣዩ የሌላው አገር ቅኝ ግዛት ከነበረ ነው[69]። ሕወሓት/ኢሕአዴግም የኤርትራን መገንጠል የደገፈው ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ከሚል እምነት ተነስቶ ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ካለ ደግሞ ነፃነትን ወይንም መገንጠልን ከመደገፍ ሌላ አማራጭ አልነበረውም፤ ምክንያቱም ቅኝ ግዛት የሆኑ አገሮች ነፃ የመውጣት ያልተገደበ መብት ስላላቸው የተቀረው የዓለም አቀፍ

---

[68] አምሳሉ ገብረዝጊ (ኮሎኔል) የኤርትራ መዘዝ አዲስ አበባ ፤ጥር 11 ቀን (2002 ዓ.ም) ፤ገጽ 52

[69] Macolm N. Shaw, International Law. 6th edition, Cambridge, university press, (2008) p. 257.



ሕብረተሰብ ድጋፉን እንዲለግሳቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስለሚያሳስብ ነው።

እንዲሁም በአልጀርስ ስምምነት አንቀጽ 41 ኢትዮጵያና ኤርትራ ለወሰናቸው መካለል የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የካይሮው የመሪዎች ጉባዔ እ.አ.አ በ1964 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኢሕአዴግ መሠረት ሲያደርገው ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ከሚል እምነት ተነስተው ነው፤ ምክንያቱም ይህ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ አግባብነት የሚኖረው ከቅኝ ግዛት ነጻ ለሚወጡ አገሮች ብቻ ነው። ይህም ውሳኔ ቅኝ ግዛት የነበሩ የአፍሪቃ አገራት ነፃ ሲወጡ በቅኝ ግዛት ጊዜ የነበረው ወሰን መከበር አለበት የሚል ሲሆን ሕወሓት ይህንኑ ተቀብሎ ኤርትራ የኢትዮጵያ "ቅኝ ግዛት" በነበረችበት ጊዜ የነበራትን ድንበር እንዲከበርላት ተስማማ።

እነዚህን የቅኝ ግዛት መርሆዎችውን በመከተል ሻቢያና ሕወሓት ፖሊሲዎቻቸውን ቀርፀው በመታገላቸው ቅኝ ግዛት ይሏት የነበረችው ኤርትር ዛሬ ነፃ ወጥታለች። ለመሆኑ የሕወሓትና አንዳንድ የሌሎች የእትዮጵያ ብሔርና ብሔረሰቦች መሪዎች አገሮች ቅኝ ግዛት ናቸው ሲሉ ቅኝ ግዛት ምን ማለት እንደሆነ፣ የቅኝ ገዢዎቹ ዓላማና ፍላጐት ምን እንደሆነ፤ እነዚህ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ይንፃባረቁ እንደሆነ በቅጡ ተገንዝበውታልን የሚል ጥያቄ ያስነሣል።

ቅኝ ግዛት በመሠረቱ ከ15ኛው እስከ 20ኛው በነበረው ክፍለ ዘመን አውሮፓውያን ወደ ሌሎች አህጉራት ተሻግረው በአገሬው ሕዝብ ላይ የጫኑት የአገዛዝና የብዝበዛ ሥርዓት ነበር። ዓላማቸው ትርፍ ፍለጋ በቅኝ ግዛቱ ተገዢው ሕብረተሰብ ኪሳራ ለመበልፀግና፤ የሃይማኖት ወይንም የፖለቲካ እምነት ለማስፋፋት ነበር። ቅኝ ግዛት በአገሬው ተወላጆችና በወራሪ መጤዎች መሃከል የጌታና የሎሌ ግንኙነት ይመሠረታል። ቅኝ ገዢዎች በዋና ከተሞቻቸው ተቀምጠው የቅኝ ግዛቱ አገርና ሕዝብ የእለት ተእለት ኑሮውና መጻኢ እድሉን ይወስናሉ። ቅኝ ገዢዎች የተገዢዎችን ባህል በማንቋሸሽ ስብእናቸውን በማሳነስ የበታችነት ስሜት እንዲሰርጽባቸው አድርገዋቸዋል። ቅኝ ገዢዎች እነዚህን ሕዝቦች ለመግዛት የተፈጠሩ ናቸው የሚለውን እምነት

በተገዢዎች ላይ በማሳደር በንብረትና በህይወታቸው ወሳኝ ሆነው ኖረዋል[70]።

ቀደም ሲል የሕወሓት መሪዎች የማርክሲስት ሌኒኒስት እምነት አክራሪ ተከታዮች (የአልቤንያው ዓይነት) ስለነበሩ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በዚህ በማርክሲስት መነፅር ያዩት ነበር። በማርክሲስት ሌኒኒስቶች አስተሳሰብ የቅኝ ግዛት ዋናው ዓላማ ተገዢውን ሕዝብ መበዝበዝ ነው። የቅኝ ግዛት ሥርዓት የተቀነባበረ ብዝበዛ እያካሄደ ለቅኝ ገዢዎች ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ በጣም በእርካሽ ዋጋ ወይንም በነፃ ማቅረብ ሲሆን፣ ምርቱንም በተገዢው ሕብረተብ ላይ መገልበጥና እንዲሁም የቅኝ ተገዢው መሬቱን ነጥቆ ለቅኝ ገዢዎች ማከፋፈል ነው።

በእነዚህ የቅኝ ግዛት መስፈርቶች ሲለካ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት የቅኝ ገዥና ተገዥ ነበረ የሚያስብል አንድም ምክንያት የለም። ኢትዮጵያ ለየትኞቹ ፋብሪካዎቿ ነበር ኤርትራን የምትበዘብዘው? በወቅቱ እንዲያውም የጥሬ እቃው ትራፊክ የሚያመዝነው ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ ሲሆን በጊዜው ኤርትራ ውስጥ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት በቁጥር ይበልጡ ስለነበር የፋብሪካ ምርቶች ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ይጓዙ ነበር።

በኢትዮጵያውያንና በኤርትራውያን መሃከል የነበረው ግንኙነት የጌታና የሎሌ ሳይሆን የመከባበርና የመፈቃቀር፣ የወንድማማችነትና የእህትማማችነት እንደነበር አንዳንድ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ በተባረሩ ጊዜ በግልጽ ታይቶአል። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ኤርትራውያን ጎረቤቶቻቸውንና ወዳጆቻችውን ወደ ኤርትራ እንዳይላኩ ደበቀው መከላከል ሲያቅታቸው ደግሞ በእምባ እየተራጩ የሸኙባቸው ሁኔታዎች ታይተዋል።,

የትኛውስ የኤርትራ ለም መሬት ነው ኢትዮጵያውያን ከኤርትራውያን ነጥቀው የሰፈሩበት። ይልቁንስ ኤርትራውያን በተለይ በአፄ ኃይለ ሥላሴ የአስተዳደር ዘመን በኢትዮጵያ

[70] Colonialism, http://en.wikipedia/wiki/colonialism.com. Accessed on 22 January 2011.



በከፍተኛ የሥልጣን እርከን በመገኘት በተጨማሪም በነበራቸው የሥራ ትጋትና ተሞክሮ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው ሃብት አፍርተው ከብረውና ከብደው ያለ እንዳች ስጋት ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን በፍቅር ይኖሩ እንደነበር የትናንት ሐቅ ነው። ስለዚህ የኢትጵያ አካል የነበረችው ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ማለት "ትንሽ ዕውቀት አደገኛ ነው" Little Knowledge is Dangerous ከሚለው የእንግሊዘኛ ብሂል የመነጨ ይመስላል።

ዛሬ ኢትዮጵያ የባህር በር አያስፈልጋትም በጐረቤት አገራት ወደቦች እንጠቀማለን የሚሉ የሕወሓት መሪዎች በአንድ በኩል ኤርትራን ለማስገንጠል ሲጥሩ በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመሪያ ታላቋ ትግራይን ፈጥረው የትግራይ ሪፐብሊክን አቋቁመው የቀይ ባህረ ሰላጤን ከታላቋ ትግራይ ጋር ለመቀላቀል ወጥነው እንደነበር ፕሮፌሰር ተኮላ ወርቅ ሃጎስ ያስገነዝቡናል[71]።

ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነችና እንደማንኛውም ቅኝ ግዛት ነፃ መውጣት አለባት፤ ለዚህም የተራማጆች ድጋፍ የግድ ይላል የሚለው የጨቅላ አስተሳሰብ ከሕወሓትም ውጭ ሌሎችም ተስፈንጣሪ ማርክሲስት ሌኒኒስት እርዮተ ዓለም ይከተሉ የነበሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያንም የሚያራምዱት አቋም ነበር። እነዚህ ጥራዝ ነጠቆች ቅኝ ግዛት ምን እንደሆነ፣ቅኝ ገዥውና ተገዢው ምን ዓይነት የኢኮኖሚ፤የፖለቲካና የሶሻል ግንኙነት እንዳላቸው ተንትነው ተረድተው ሳይሆን፤ በጊዜው ተራማጅ መስሎ ለመታየት የኤርትራንና የሌሎች ጎሳዎች መገንጠልን መቀበልና ማጠንጠን ያስፈልግ ስለነበረ ነው።

ከዚህም አልፎ በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ማንኛውም ኤርትራዊ ነገር መወደስ ሲገባው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ደግሞ መንኳሰስ ነበረበት፤ በኢትዮጵያዊነት የሚያኮራ ምንም ነገር አልነበረም። ጸረ ኮሎኒያሊስት ድሉች እንኳን ፊውዳሎችን

[71] Tecola W. Hagos, Professor, "Prime Minister Meles Speaks at the National Press Club in Washington DC" http://ethioembassy.org.UK. Accessed on Febrary 2011.

በሥልጣን ለማቆየት ካልሆነ በቀር ለሰፊው ህዝብ የሰጡት ጥቅም የለም በማለት ሲያንኳስሱ ተደምጠዋል። እንዲያውም ጉዳቱ አመዝኖአል ሲሉ የሚከራከሩም አልጠፉም። በእነዚህ ሰዎች እይታ ኤርትራውያን ለ60 ዓመታት በጣልያን ስለተገዙ እንደሰለጠኑ ሲቆጥሩአቸው ኢትዮጵያውያንን ግን ትናንት ከዛፍ የወረዱ አድርገው የሚያዩ ነበሩ።

እነዚሁ ተስፈንጣሪ ግራ ዘመም እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን በበታችነት ስሜት (Inferiority complex) ተለክፈው ስለነበር ኤርትራውያን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ይበልጥ በተፈጥሮ ብልህ (Intelligent) ናቸው ከማለት እንኳን አይመለሱም ነበር።

ከኢትዮጵያውያን ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶችም አንዳንዶቹ ኤርትራውያን ለሰብአዊና ለፖለቲካዊ መብቶቻቸው ሲታገሉ ሊደገፉ ይገባል ከማለት ሌላ ከሕወሓት በስተቀር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ቡድን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች፣ ተገንጥላ ነጻ ትውጣ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ይለያዩ ፣ የኢትዮጵያ የባህር በር ይዞታ ያስ የለም።

በጊዜው ዋነኞቹ ተራማጅ ይባሉ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እና የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) በኤርትራ መገንጠል ተመሳሳይ አቋም ያራምዱ ነበር። ኢሕአፓ በኢትዮጵያ በሙሉ በኤርትራም ጭምር በደርግ ይደረግ የነበረውን ጨካኝና መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በፅኑ ተቃውሞአል። በዚህም ትግል ወጣት የኢሕአፓ አባላትና መሪዎች ከባድ መስዋዕትነት እንደ ከፈሉ የትናንት ትዝታ ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነችና ነፃ ትውጣ፣ የባህር በሮቿ ይዞታ የሚል አቋም ኢሕአፓ እንዲቀበል ሻቢያ ከፍተኛ ጫና ቢያደርግበትም ኢሕአፓ ይህን አቋም ለማራመድ እስከ መጨረሻው ፈቃደኛ አልሆነም። በዚህም ምክንያት ኢሕአፓ ከሻቢያና ከሕወሓት ጋር ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ገብቶ በዚህም አቋሙ በሻቢያ በሚደገፈው ሕወሓት ግፊት አሲምባን ለቅቆ እንዲወጣ ተገድዶአል። መኢሶንም በጊዜው የደርግ ፖሊሲ ተጋሪ ወ[illegible]ተያሽ ስለነበር



ኤርትራ ተገንጥላ አገሪቱን ወደብ አልባ ማድረግን በጽኑ ይቃወም ነበር።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ገና ከጅምሩ በ1983 ዓ.ም አዲስ አበባ ለመግባትና ሥልጣን ለመጨበጥ በሚያኮበኩብበት ወቅት በሻቢያ፣ በኢሕአዴግ፣ በደርግና በኦሮሞ ነፃ አውጪ ግምባር (ኦነግ) መሃከል በአሜሪካ አደራዳሪነት ለንደን ስብሰባ ተቀምጠው በነበረ ጊዜ ኢሕአዴግ ከኦነግ ጋር ሥልጣን ተጋርቶ አዲስ አበባ ገብቶ በትረ ሥልጣኑን እንዲጨብጥ፣ ኤርትራም ነፃ እንድትወጣ ሲወሰን በድርድሩ ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወት የነበረው አደራዳሪው አሜሪካዊው ባለስልጣን ኸርማን ኮኸን (Herman Cohen) የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ጉዳይ አንስቶ እንደነበር ይነገራል።

በዚህ ጊዜ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ቡድን መሪ አቶ መለስ ዜናዊ አደራዳሪው ያነሳው ጥያቄ ለድርድሩ ምንም አግባብነት እንደሌለው በመግለጽ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ጥያቄ በዚህ ተቋጭቶ በፕሮፌሰር በጋዬ መብራሕቱ አባባል "በአንድ ሰው የዓይን ጥቅሻ ኢትዮጵያ በ60 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቀይ ባህረ ሰላጤ (Red sea littoral) ሙሉ በሙሉ ተገለለች።

የሕወሓት መሪዎች የአልጀርስ ስምምነት ድርድር ከመጀመሩ ቀደም ብሎ የሕወሓትን ፖሊሲ በማንፀባረቅ በተደጋጋሚ በተለያዩ ሚዲያዎች አሰብ የኤርትራ አካል ነች፣ ወሰን መካለሉም አጼ ምኒልክ ከጣልያኖች ጋር በፈረሙአቸው ውሎች መሠረት እንደሚሆን አስታውቀው ነበር። ይህም በአቶ በላይ አባይና በአቶ ዘርዑ ክሕሸን አይታ ገና በድርድሩ ወቅት ኢትዮጵያ አሰብ ይገባኛል የሚል ጥያቄ እንደማታነሳ በድርድሩ ተሳታፊ ለነበሩት ለኤርትራ መንግሥት፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ ለአውሮፓ ሕብረትና ለዩናይትድ ስቴትስ ለማስታወቅ ነበር። እነዚህ የድርድሩ ተሳታፊዎች

ቢያነሱት እንኳን በኢሕአዴግ በኩል ተቀባይነት እንደማይኖረው ለማስታወቅና በቅድሚያ ጥያቄው በእንጭጩ ለማስቀረት ነበር[72]።

ሕወሓት የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን ማስከበርና አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ሃሳብ ጭራሹኑ እንደሌለው የሚያመላክት የኢሕአዴግ የአሁንም ይሁን የወደፊት ፖሊሲው አቶ መለስ ዜናዊ ከአስመሪኖ ድረ ገፅ ባለቤት ከአቶ ተስፋ ልደት መሐረነ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ቁልጭ አድርገው አስቀምጠውታል።

አቶ መለስ እንዳሉት "ይህ አሰብን እንይዛለን፥ እንወርራለን የሚል አካሄድ ከዚያው ከዘውዳዊ ትምክሕተኛ አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው። ሁለተኛ ደግሞ ይህ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ሰዎች ከዘመነ ግሎባላይዜሽን ጋር አብረው ሊሄዱ ያልቻሉ ከድንጋይ ዘመን አስተሳሰብ ያልተላቀቁ ናቸው።....አሰብን ካልያዝን እያሉ ይፎክራሉ። ተግባራዊ ለማድረግ በአሰብ ላይ ወረራ እስካልተፈፀመ ድረስ እርምጃ ልንወስድባቸው አንችልም"[73] ብለው ነበር። ከዚህ በተቃረኒ አቶ መለሰ ዜናዊ በአንድ ወቅት ከሲ.አይ.ኤው ፓል ሄንዝ ጋር ባደረጉት ምሥጢራዊ ውይይት "ትግራይ የባህር በር እንዲኖራት እንፋልጋለን:: ይህ ደግሞ የሚሆነው በኤርትራ በኩል ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ሆነችም አልሆነችም ወደብ ያስፋልገናል"[74] ብለው ነበር:: ትግራይ የኢትዮጵያ አካል እንደመሆንዋ መጠን ወደብ ብታገኝ ጥቅሙ ለመላው ኢትዮጵያ ስለነበር ትግራይ ወደብ ቢኖራት ኢትዮጵያውያን እሰይ ባሉ ነበር። ይህ ትግራይ ወደብ ያስፈልጋታል የሚለው የአቶ መለስ አቋም መቼና ለምን እንደተቀየረ አይታወቅም።

ይኽ ሁሉ የአቶ መለስ ማስፈራራትና ስድብ ለምን እንዳስፈለገ ግልፅ አይደለም። ምክንያቱም የወደፊቱ ባይታወቅም እስካሁን

---

[72]Belai.Abbal.and.ZeruKehishen,http://Ethiopians.com/belai_and_zeruml July 15, 2000. Accessed May 22, 2010

[73] See WWW.Ethiomedia.com accessed on December 12, 2010

[74] "የመለስና የ ሲ፡አይ፤ኤው አባል ምስጢራዊ ውይይት" [illegible]ራምባ ታይምስ ቅዳሜ ሰኔ 4,2003.



በፅሁፍም ይሁን በቃል አንድም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ታንክ አሽከርክሮ ሳንጃ ወድሮ አሰብ ዘልቆ በጦር ኃይል አሰብን ይያዝ ያለበት ጊዜ የለም።

ይህም ማለት ግን የአሰብ ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ ብቻ ይስተናገድ የሚለው አቋም ለወዳፊት ሊሸረሸር አይችልም ማለት አይደለም። እንዲያውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሉዓላዊ ግዛታችን አሰብን አስፈላጊ በሆነ በማንኛውም መንገድ ሁሉ ማስመለስ ይገባል የሚሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እየተበራከተ ሄዷል።

ከላይ በተጠቀሰው በአቶ መለስ አባባል ኢሕአዴግ የኤርትራ አካል አድርጎ በሚቆጥረው በአሰብ ላይ ጥቃት ቢደርስ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ወጣቶችን በማሰለፍ ኤርትራን እንደሚታደጉ አቶ መለስ ግልጽ አድርገውታል። እነዚህ አባባሎችን በማጠናከር አቶ ስብሐት ነጋም ለድምፅ ወያኔ ሬድዮ በሰጡት ቃለ ምልልስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ አሁንም ቢሆን የኤርትራ ሉዓላዊነት የሚፈታተን ኃይል ከመጣ ሕወሓት/ ኢሕአዴግ ከኤርትራ ሕዝብ ጎን እንደሚቆም አረጋግጠዋል። ይህ የአቶ ስብሃት ነጋ አባባል እንዴት እንደሚያዩት አቶ መለስ ተጠይቀው ሲመልሱ "ከድርጅታችን መግለጫዎች አብሮ የሚሄድ ይመስለኛል" ብለው ነበር።

ሌላው የኢሕአዲግ የአሰብ ፖሊሲ ጠቋሚ የሚሆነው የመንግስት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር አቶ በረከት ስምዖን ለእንግሊዝ ብሮድካስቲንግ ኮርፓሬሽን ባልደረባ ለሚስተር ሮቢን ኋይት ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ነው።

ሚስተር ሮቢን ኋይት አሰብን አስመልክቶ አቶ በርከትን ለጠየቋቸው ጥያቄዎች እንደሚከተለው መልሰውልታል፦

*እኛ የአሰብን ወደብ አንፈልገውም። መንግሥታችን አቋሙን በግልጽ ነው ያስቀመጠው፤ በአልርስ ስምምነቱ ላይ የትኞቹ አካባቢዎች የእኛ እንደሚሆኑ በትክክል አስቀምጠናል። በዚህ ወቅት የአሰብ ወደብ ከጥያቄአችን ውስጥ አልተካተተም።*
*ጥቂት ኢትዮጵያውያን የአሰብን ወደብ የኢትዮጵያ ግዛት አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን ሲብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝቦች*

*አሰብን አይጠይቁም። ምክንያቱም የአሰብ ወደብ የኤርትራ ሉዓላዊ ግዛት መሆኑን ስለሚያውቁ ነው። አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ነች ይላሉ። ጅቡቲም ቢሆን እንደዚሁ ተመሳሳይ ጠቀሜታ አለው። የቅኝ ግዛት ውሎች አሰብን የኢትዮጵያ አካል አድርገው ባለማካለላቸው የይገባኛል ጥያቄ ለማንሳት የምንሔድበት ምክንያት አይኖርም*[75]።

አቶ በረከት እንደሚሉት ጥቂት ኢትዮጵያውያን አይደሉም አሰብ የኢትዮጵያ ግዛት ነች የሚሉ። ሁልቄ መሣፍርት ከሲቅ እስከ ደቂቅ ከገብሬው እስከ ምሁሩ በጠቅላላው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው አሰብ የኢትዮጵያ ነች የሚለው። በቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ሳይወሰኑ እንደልባቸው በአዲስ አበባና በተቀረው የአገሪቱ ከተሞችና በገጠሩም ተዘዋውረው በማየትና በመስማት ከአቶ በረከት ይበልጥ አሰብን በተመለከተ የህዝቡ ስሜትና እምነት ሊያውቁና ሊገመግሙ የሚችሉት አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረ አናንያ ከሕዝቡ የሚከተለውን አድምጠዋል። "ይሄ የባህር በር ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀብሎታል ብሎ ዝም ማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም ሕዝቡ በየሆቴሉና በየካፌው የሚናገረው ስለዚህ ጉዳይ ነው። በፖለቲካ ስብሰባ የሚናገረው ይሄንኑ ነው"[76] በማለት የታዘቡትን ገልጸዋል።

በደርግ፣ በሕወሓትና በሻቢያ መሃከል የተደረጉ ፍልሚያዎችን አስመልክቶ የፓለቲካና የጦርነት ትንታኔ በማድረግ ጥልቅ ምርምር የደረጉት ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ የሚከተለውን ጽፈዋል። "...ሕወሓት ትግራይ ውስጥ ደርግን ባያሸንፍ ኖሮ የኤርትራ ነፃነት ለዛላለም ባይሆንም ላልተወሰነ ጊዜ ሊዘገይ ይችል ነበር" ብለዋለል። ይህም ማለት ሕወሓት ሻቢያን በጦርነቱ ባይረዳ ኖሮ ኤርትራ ከኢትዮጵያ በጦር ኃይል የመገንጠልና የባህር በር መዘጋት እጅግ ቢያንስ አጠራጣሪ በሆነ ነበር።[77]የሕወሓት ሻቢያን

[75] BBC interview with Mr.Robin White circa 2001

[76] ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ ሪፖርተር ፤እሁድ የካቲት 7 ቀን 2002 ዓ.ም.

[77] Gebru Tareke , Professor, The Ethiopian Revolution War in the Horn of Africa, Yale University Press, New Haven & London, (2009), p321.



መርዳት ቀደም ሲል በሻቢያና በደርግ መሃከል ተደጋግም የተሞከረው የሰላም ድርድር እንዲቀር አስተዋጽኦ አድርጎአል*።

የባህር በር አስረካቢዎች አቋም ለማጠቃለል ያህል፤ ኢሕአዴግ አሰብን ለኤርትራ ለማስረከብ የነበረው ጉጉት ጥቅምት 11 ቀን 1995 ዓ.ም በወጣው የኢሕአዴግ ልሣን የሆነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ የጻፋውን በመገመገም ኢትዮጵ የተባለው ሳምንታዊ መጽሔት የሚከተለውን ጽፎአል "......ኢትዮጵያ አወዛጋቢነት በሌላቸው ቦታዎች ማለትም በመላው ምሥራቃዊ ወሰን ....ድንበሩ በአስቸኳይ እንዲካለል የኢሕአደግ መንግሥት የሚያደርገው ግፊት ታዛቢዎችን አስገርሞአል። የአሰብ ወደብ የኤርትራ ግዛት ሆኖ እንዲቀጥል ተጨማሪ ማረጋገጫ እንዲሰጥ ከኤርትራ በላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያደርገው ግፊትና አቶ መለስ ቀይ ባህር ሲነሳባቸው የሚበሳጩበት ምክንያት ከማስገረምና ከማሳዘንም አልፎ ይበልጥ አሳሳቢ ሆኖአል"[78]

የሕወሓት መሪዎች የኢትዮጵያን ዋባህር በር አዘግተዋል ሲባል የሁሉም የሕወሓት አመራሮችን አያጠቃልልም። ጥቂትም ቢሆኑ በጊዜው ድምጻቸው ባይሰማም የኢትዮጵያ የባህር በር አልባ መሆንዋ የሚቈረቈራቸው አንዳንድ የሕወሓት የአመረር አባላት እንደነበሩ አቶ አሰግድ ገብረ ሥላሴ የሕወሓት መሥራች አባልና የዓረና ትግራይ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ከአውራምባ ታይምስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ገልጸዋል። በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው "ኢሕአዴግ በታሪኩ ዴሞክራሲያዊ ሆኖ አያውቅም። የተለየ ሃሳብ የሚያቀርቡ ወገኖችም ጠላት አድርጎ ስለሚያያቸው ባለው አቅም ሁሉ ለመታገል ወደ ኋላ አይልም" ካሉ በኋላ ኢሕአዴግ [የኤርትራን መንግሥት] ለማስወገድ በቅርቡ የአቋም ለውጥ አድርጎአል ወይ ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ "ዋናው ነገር ይኸ የኤርትራ መንግሥትን የማስወገድ ነገር እስከ የት ድረስ ይሄዳል? ያለ አግባብ ያጣናቸውን መብቶቻችን ያረጋግጥልናል ወይ? የባህር በር ባለቤትነታችንስ ያረጋግጥልናል ወይ? የሚሉት መመለስ

* ፕሮፌሰር ገብሩ በሻቢያና በኢትዮጵያ መንግሥት መሃከል አውሮፓ ውስጥ ብዙ ውይይቶች ተደርገው እንደነበር ይጠቅሳሉ።

[78] ኢትዮጵ፤ ጥቅምት 18 ቀን 1996 ዓ.ም

አለባቸው" ሲሉ እነዚህ እስካልተፈጸሙ ድረስ ግን የኤርትራ መንግሥት መወገድ ፍሬ ከርስኪ መሆኑን ገልጸዋል። ስለ አንዳንድ የሕወሓት መሪዎች ለኤርትራ ያላቸው ተቊርቋሪነትና ስለአሰብ ኢትዮጵያዊነት ሲገልጹ አቶ አስገድ የሚከተለውን ብለዋል።

*ይህ ታላቅ ነጥብ ነው ። ይኸ ሸንጥን ጎትሮ [ለኤርትራ] ጥብቅና መቆም በትግሉ ወቅትም ነበር ። ያን ጊዜ የአሰብ ጉዳይ ሲነሳ እንኳን ልዩነታችን የሁለት አገር ዜጐች የሆንን ያህል እስከ መመዛገብ ያደረሰን ነበር። በምንም አግባብ አሰብ የኤርትራ እንዳልሆነች ይታወቃል። እነዚህ የሕወሓት አመራሮች ግን ይህንን ሃሳብ የምናነሳውን ትምክህተኞች ይሉን ነበር። ነገሩ በቅስቀሳ ብቻ ያቆመ አልነበረም። ለምሳሌ ሸብሃት ነጋ በኤርትራ ነፃነት ላይ የሚቃወም ካለ ከምንጠላው ሻቢያ ጉን ተሰልፈን እንዋጋለን ብሎ ነበር። ምን ማለት ነው እስከዚህ ድረስ ወሰን ያለፈ ተቊርቋሪነት?*[79] ሲሉም ጠይቀዋል

እንደሚታወቀው ሕወሓት ከጥንስሱ ጀምሮ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች፣ ከነወደቦችዋ ነጻ መውጣት አለባት እያለ ለዚህም የደም ዋጋ የከፈለ ድርጅት መሆኑ ከዚህ በላይ ተገልያአል። በጣም የሚገርመውና ግር የሚለው ግን፣ በቅርብ ጊዜ ከሕወሓት ጋር በመቀላቀል ኢሕአዴግን የፈጠሩ ድርጅቶች መሪዎች አሰብን አስመልክቶ የሕወሓትን አቋም ሲያስተጋቡ መስማት ነው። እነዚህ ሰዎች አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች፣ኢትዮጵያ በአሰብ ላይ ምንም መብት የላትም ከሚል እውቀትና እምነት ተነስተው ወይንም በሌላ ሌላ ምክንያት ይሁን ይህንን ለህሊናቸው እንተወዋለን። የእነዚህ ከሕወሓት ጋር ተቀላቅለው ኢሕአዴግን የፈጠሩ መሪ ተብዮች አቋም ምን እንደሚመስል በአሁኑ ወቅት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ከጥቂት ወራት በፊት የመንግስት ተጠሪ በነበሩበት ጊዜ <u>ለሪፖርተር ጋዜጣ</u> የተናገሩትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። አቶ ኃይለ ማርያም ሲናገሩ "ኢትዮጵያ የባህር በር ቢኖራት አንጠላም። ተቃዋሚዎች

[79] <u>አውራምባ ታይምስ፤</u> ቅዳሜ ሚያዝያ 15/2003 ዓ.ም.



ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እናደርጋታለን የሚሉት የህዝብን ስሜት ለመግዛት እንጂ በተግባር የወደብ ባለቤት ለማድረግ አይደለም"[79] ብለዋል ። ተቃዋሚዎች በዚህ አቋማቸው ያላቸውን ማስረጃ አሰባስበው ወደ ሕግ ቢያመሩ መንግሥት ድጋፍ ስለመስጠቱ ሲጠየቁ "ኢሕአዲግ የሚሰጠው አንዳችም ድጋፍ የለም። በጉዳዩ ቢያምንበት ኖሮ ራሱ ኢሕአዲግ ይሄድበት ነበር"[80] ብለዋል።

የአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ መልሶች ብዙ ሐቆችን የያዙ ናቸው። በመጀመሪያ ተቃዋሚ ኃይሎች ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት እናደርጋታለን የሚሉት የህዝብን ስሜት ለመግዛት መሆኑን ሲገልፁ የባህር በር ባለቤትነት በሕዝብ ስሜት ትልቅ ቦታ እንዳለውና የህዝቡንም ስሜት ሲገዛ እንደሚችል ይቀበላሉ ማለት ነው። በመቀጠልም የአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ገለጻ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት ሊያስደርጋት የሚችል ማስረጃ ወይንም መከራከሪያ ነጥብ የለም ሳይሆን "ኢሕአዲግ ስለማያምንበት" መሆኑን ይገልጻሉ። እዚህ ላይ እውነቱን ነው የተናገሩት። ኢሕአዲግ አሰብ የኢትዮጵያ የባህር በር መሆንዋ በታሪክና በሕግ የተደገፉ ምክንያቶች እንዳሉ ጠፍቶት ሳይሆን ስለማያምንበት ወይንም በሌላ ሌላ ምክንያት ነው። እነዚሁ ከሕወሓት ጋር ተቀላቅለው ኢሕአዴግን የፈጠሩ አንዳንድ አዳዲስ መጤዎች የሚያስተጋቡት አቋም በጣልያን ጊዜ የተገጠመ ስሞታን ያስታውሰናል። አንድ ገንዘብ የሚሰጠውና ጠላቶቹን የሚያጠቃለት አርኮ የተባለ ጣልያንን ተማምኖ ጎረቤቶቹን ይበድል የነበረ ኢትዮጵያዊ ነበር። በዚህ ኢትዮጵያዊ በደል የደረሰበት ሌላው ኢትዮጵያዊ እንዲህ ሲል እሮሮውን አሰማ።

[79] ሪፖርተር ፣የካቲት 24ቀን 2002 ዓ.ም.
[80] ዝኒ ከማሁ.

*አርኮም (Arco) ይሄድና ሶልዲም ያልቅና፤*

*ያስተዛዝበናል ይቺ ቀን ታልፍና፤*

ከጊዜ በኋላ ጣልያኑ አርኮም አገሩ ገባ፤ ሶልዲውም ጠፋ፤ግፈኛው ኢትዮጵያዊውም በሕብረተሰቡ ዘንድ ትዝብት አተረፈ። አንዳንድ የቀድሞ የሕዋሓት መሪዎች፥ ዛሬም በአባልነት ያሉት ቢሆኑም በፓርቲያቸው የተሳሳተ አቋም ኢትዮጵያ አገራቸውን ወደብ አልባ ማድረጋቸው እንደ ውስጥ እግር እሳት ይለበልባቸዋል። አሁንም ለይስሙላም ቢሆን አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች በሚለው አቋማቸው የፀኑት እንኳን አንዴ ከተሳሳትኩ አይመልሰኝ ሆኖባቸው ነው እንጂ የስሕተታቸውን ግዙፍነት ይረዱታል። የኢትዮጵያ የባህር በር ማዘጋት ለኤርትራ ነፃነት ደማቸውን ያፈሰሱለት የሕወሓት የቀድሞ መሪዎች እንኳን የማይደግፉበት ጉዳይ እነዚህ ትናንት ከሕዋሃት ጋር ኢሕአዴግን የተቀላቀሉ አዳዲሶቹ አሰብ የኤርትራ አካል ነች እያሉ የሕዋሓትን አቋም ሲያስተጋቡ መስማት ግርም ይላል።

የኢትዮጵያ ብቸኛዋ የባህር በር ለሌላ አገር ማስረከብ ከፍተኛ ብሄራዊ ጥፋት መሆኑ እንኳን የበቁና የነቁ የሕዋሃት መሪዎች ቀርቶ ቅንጣት ያህል የአገር ፍቅር ያለው የገጠሩ ገበሬ ሊስተው አይችልም።

በዚህ ጉዳይ እንኳን ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵየ በጎ የሚያስቡ ሁሉ ያዝናሉ* ምናልባት ይህንን በመረዳት ይሆናል ሕወሓት የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን በሌላ ኃይል ሊያሳክከው የፈለገው። ሕወሓት ከደሙ ንፁህ ነኝ ለማለት ይመስላል አቶ መለስ በአንድ ወቅት "አሰብ የኢትዮጵያ ወደብ ሆና የማገልገልዋ ጉዳይ

---

* ሶልዲ በጣልያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ይሠራበት የነበረ የጣልያን ገንዘብ ነበር።
* የኢትዮጵያና የኤርትራ ውዝግብ ለአልጀርስ ድምበር ኮሚሽን በቀረበ ጊዜ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ኢትዮጵያ ብትጠይቅ ኖሮ ሁለት የአውሮጳ አምባሳደሮች አገራቸው የኢትዮጵያን ጥያቄ ይደግፉ እንደነበር ለዚህ ጸሐፊ አረጋግጠውለታል።



እንዲያበቃ ያደረገው የ30 ዓመት ትግል ነው። የ30 ዓመቱ ትግል ለአሰብ ጉዳይ መልስ ሰጥቶአል"[61] ሲሉ የተናገሩት።

ኢሕአዲግ የአልጀርስን ስምምነት በመቀበል፤ የሽግግር መንግሥት ኤርትራን ከነወደቦችዋ፡ እውቅና እንድታገኝ አደረገ። በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ጊዜ የአሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ባለመከራከር፤ የአፋር ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብት በመቃወም፤ የአሰብ እራስ ገዝ ከኤርትራ ጋር ደባልቆ እውቅና ሰጠ። በእነዚህና በመሰል ምክንያቶች ሁሉ ሕወሓት አሰብን ለኤርትራ መርቆ መስጠቱና ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ማድረጉን ሊክድ አይችልም። ኃላፊነቱም ከጫንቃው አይወርድም።

ኢትዮጵያ የባህር በርዋ አሰብ እስካልተመለሰላት ድረስ ኢሕአዴግ ከየትኛውም በጉም ይሁን መጥፎ ሥራዎቹ የባህር በር ማዘጋቱ ከሁሉም በላይ ጉልቶ ይወጣል። አሰብ ለኢትዮጵያ እስካልተመለሰ ድረስ ዘመናት እልፈው ዘመናት ሲተኩ በጊዜው ኢሕአዴግ ማን ነበር ሲባል መልሱ መንገዶችን፤ ትምህርት ቤቶችን ወይንም ሐኪም ቤቶችን ያነጸው አይሆንም ። መልሱ የኢትዮጵያን የባህር በር ያዘጋው መንግሥት ነው የሚሆነው።

---

[61] መለስ ዜናው ፣ገጽ፣ ከማሁ

## ምዕራፍ ፫

## 3. በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ የነበሩት አራቱ አገራት፣ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ፣ ጣልያንና ኢትዮጵያ ኤርትራን አስመልክቶ የደረሱባቸው ውሳኔዎች

አሰብ የኤርትራ አካል ሳትሆን ጣልያን ከኤርትራ ጋር ደባልቆ እስከ ፌዴሬሽኑ ስለገዛት በጣም ጥቂት ኢትዮጵያውያን አሰብና ኤርትራን መለየትና አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋን መቀበል ይቸግራቸዋል። የዚህ ምዕራፍ ዓላማ አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋን በተጨባጭ ሕጐች፣ ማስረጃዎችና በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎች ላይ በመመርኰዝ ለማስረዳት ነው። በታሪክ፣ አሰብ ማለት ጠቅላላው የአፋር አውራጃ የኢትዮጵያ አካል እንደነበርች አጼ ምኒልክ ግዛታቸውን ለዓለም ያስታወቁበት ደብደቤና ሌሉችም መረጃዎችም እያሉ አሰብ አለ ኢትያጵያ መንግሥት እውቀት ለጣልያን ኩባንያ እንደተሸጠችና ቆይቶም በጣልያን መንግሥት መጠቃለሏ ከላይ ተገልጾአል።

ከዚህ በታች ደግሞ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አሰብ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የኤርትራ ባለ አደራ በነበሩት በአራቱ ኃያላን አገራት፣ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔና በኤርትራ ፖርላማ ውሳኔ እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰች እንተነትናለን።

ጣልያን በጦርነቱ በተሸነፈች ማግሥት በአፍሪቃ የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ የተረከቡት አራቱ ኃያላን አገራት (ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካና የሶቭየት ሕብረት) የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሮች፣ የጣልያን ተወካይ፣ በጊዜው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በግፍ የገደላቸው ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ እ.እ.አ በ10 ፌብርዋሪ , 1947 ዓ.ም የሰላም

ስምምነት በፓሪስ ከተማ ፈርመው ነበር። በዚህም ውል መሠረት ጣልያን በአፍሪቃ ቅኝ ግዛቶችዋ የነበራትን ማንኛውም መብትና በቅኝ ገዢነትዋ ጊዜ የተፈራረመቻቸው ውሎችንም ጨምሮ ተሰረዙ።

የአራቱ ኃያላን አገራት ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ለእነዚሁ አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የቀድሞዋ የጣልያን ቅኝ ግዛት መጻኢ እድል ምን መሆን እንዳለበት የውሳኔ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ታዘዙ። በዚሁ መሠረት የፈረንሳይ ተወካይ በአቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ በዙላ ገልፍና በፈረንሳይ ሶማሌላንድ ያለው የባህር ዳርቻ(አሰብን ማለት ነው) ከሙሉ ሉዐላዊነት ጋር ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ ሲያሳስብ የአሜሪካ ተወካይ ደግሞ የደንከልን ጠረፍ፤አክለጉዛይና፤ሠራኤን፤ወደ ኢትዮጵያ እንዲጠቃለሉ፤እንግሊ በበኩልዋ የደንከል እረጅም የባህር ጠረፍ አሰብን ጨምሮ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለልና የአፋር ሕዝብ አንድነት እንዲጠበቅ ሃሳብ አቀረቡ[83]። እዚህ ላይ እንገዲህ የኤርትራ ጉዳይ ባለቤቶች የነበሩት አራቱ ኃያላን አገራት የኤርትራ የወደፊት እጣ ምንም ይሁን ምን የኢትዮጵያን የባህር በር መብት አረጋግጠዋል[84]።

የእነዚህም የአራቱ ኃያላን አገራት አቋም የዓለም አቀፍ ሕግ አካል ሆነ። ይህ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ዕውቅና እንዳለ ሆኖ አራቱ ኃያላን አገራት የኤርትራን የወደፊት ዕጣ ፈንታን አስመልክቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጡ የኤርትራ ጉዳይ ወደ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ እንዲመራ ተስማሙ።

በዚህም መሠረት የተባበሩት መንግሥት ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያው ኮሚቴ (First Committee) እ.ኤ.አ. በ13 ሜይ 1949 ዓ.ም. በ34 የድጋፍ በ16 የተቃውሞና በ 7 ድምጸ ተአቅቦ የምዕራቡ ኤርትራ ከሱዳን ጋር እንዲቀላቀል የተቀረው ኤርትራ

[83] Report of the United Nations Commission For Eritrea, General Assembly, Official Records: Fifth Session Supplement No. 8 (A/1285).

[84] Belai Abbai, The Ethiopian Regime Cedes National Territories. Washington D.C (2001).



በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ የሚለው የኮሚቴው አሳብ በጠቅላላው ጉባዔ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ስላልተደገፈ የውሳኔው ሃሳብ ውድቅ ሆኖ፤ ለኤርትራ ጉዳይ የመፍትሔ ሃሳብ እንዲሹ በጠቅላላው ጉባዔ የውሳኔ ቁጥር 289 A (IV) በርማ፤ ጓታማላ፤ ኖርዌይ፤ ፓኪስታንና ደቡብ አፍሪቃን የያዘ አንድ ኮሚሽን ተቋቋመ። ይህም ኮሚሽን በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተለውን ቀጥሎ ያለው መመርያ ተሰጠው።

1. የኤርትራ ሕዝብ የተለያዩ የኃይማኖቶችና የሕዝባዊ ማህበራትና የጎሣ አባላትንም ፍላጎት ተገንዝቦ እንደሁም የኤርትራ ሕዝብ ራሱን ለማስተዳደር ያለውን አቅም አገናዝቦ፤
2. የምሥራቅ አፍሪቃን ሰላምና ደህንነት ከስሌት ውስጥ አስገብቶ፤
3. ኢትዮጵያ በጂኦግራፊ፤ በታሪክ፤ በዘር፤ በኢኮኖሚ ተመስርታ የምታነሳው በተለይም የኢትዮጵያ ተገቢና ሕጋዊ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ አዎንታዊ መልስ እንዲያገኝ፤ ኮሚሽኑ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የውሳኔ ሐሳብ እንዲያቀርብ ታዘዘ።

ለሥራዉ ክንውን እንዲረዳ የተለያዩ ኮሚቴዎች ተቋቁመው የተባበሩት መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ እ.አ.አ በጀንዋሪ 10 ቀን 1950 በአሥመራ ተተከለ። ኮሚሽኑ አርባ ሕዝባዊና ሰላሳ ምሥጢራዊ፤ በጠቅላላው ሰባ ስብሰባዎችን አካሄደ። ኮሚሽኑ እ.አ.አ ከፌብርዋሪ 29 ቀን 1950 ዓ.ም እስከ ማርች መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ በኤርትራ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ፤ ማናቸውም የሕዝብ ተወካዮች አሳባቸውን ለኮሚሽኑ እንዲያቀርቡ ተጋበዙ።

ኮሚሽኑ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወኪሎችን፤ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የሙስሊሙ ምዕመናን ተወካዮችን፤ የንግዱ ማህበረሰብን መሪዎችን ተቀብሎ አነጋገረ። የኤርትራ የተለያዩ ክፍሎችና ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ሃሳቦችን አሰባሰበ። እ.አ.አ በኤፕሪል 10 ቀን 1950 ዓ.ም የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአቶ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ንግግሮችን ካዳመጠ በኋላ ኮሚሽኑ ግብጽንና ጣልያንን ጎብኝቶ ሪፖርቱን አዘጋጀ።

በዚህ መሠረት የበርማው፣የኖርይና የደቡብ አፍሪቃ ተወካዮች የኤርትራን አጠቃላይ ሁኔታ አጥንተው የውሳኔ ሃሳብ አቀረቡ። በዚሁ የውሳኔ ሃሳባቸው "ኤርትራ በጣም ጥቂት የተፈጥሮ ሃብት እንዳላት፣ በአጭር ጊዜ እይታ ኢኮኖሚዋ በጣም ደካማና በአብዛኛው በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ የተንጠለጠለ (dependent) እንደሆነ አመለከቱ። የፖለቲካውን ሁኔታ ሲመረምሩ በጊዜው ከነበሩት ፓርቲዎች ሁሉ የአንድነት ፓርቲ (Unionist Party) ትልቁ መሆኑንና ይህ ፓርቲ ከደጋፊው ሙስሊም ፓርቲ ጭምር ከኢትዮጵያ ጋር ውህደት እንደሚፈልጉ ገለጹ። ስለሆነም አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል እንደሚፈልግ ይኸው ቡድን አረጋግጠናል አለ[85]።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትም መላው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ፍላጐቱ የጸና ቢሆንም የኤርትራ ምዕራቡ ጠቅላይ ግዛቶች ከዚህ የተለየ ፍላጎት ካላቸው ይህንኑ በመቀበል ለምዕራቡ ክፍል የሚሰጠው ልዩ መፍትሔ እንደሚያከብር ለኮሚሽኑ አረጋገጠ። የፈረንሳይ መንግሥት ተወካይ አስተያየታቸውን ሲሰጡ ለኤርትራ መፍትሔ የኢትዮጵያና የጣልያን ትብብር አስፈላጊ መሆኑን ከገለጹ በኋላ ጣልያን ደግሞ ከዚህ ቀደም እንደጠየቀችው አሁንም ኤርትራን በአደራ እንድታስተዳድር የምትጠይቀውን ለቅቃ በኤርትራ ለሚገኙ ጣልያኖችና ልጆቻቸው ጥበቃ ብቻ እንዲደረግላቸው አስገነዘበች። እንግሊዝም ቀደም ሲል ሲያራምደው የነበረው የቀይ ባህር አውራጃ ምጽዋንም ጨምሮ አከለጉዛይ፣ ሠራዬና፣ ሃማሴን ወደ ኢትዮጵያ ተጠቃልለው በኤርትራ ለሚኖሩ ጣልያኖች ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸው አሳሰበ። በመቀጠልም ቡድኑ ኤርትራ ለብቻዋ እንደ አገር ሆና ብትቆም የምሥራቅ አፍሪቃ ሰላምና ደህንነት አደገኛ ሁኔታዎች ውስጥ ይወድቃል ሲል ገለጸ። ስለሆነም የአብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ያንጸባርቃል በሚል ኖርዌይ ኤርትራ ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ አቋም ስትይዝ፣ በርማና ደቡብ አፍሪቃ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር

[85] Report of the United Nations Commission For Eritrea, General Assembly Official Records, supra note 83.



በፌዴሬሽን እንድትተሳሰር የሚል አቋም ለጠቅላላው ጉባዔ አቀረቡ[86]።

ሌሎቹ ሁለቱ የኮሚሽኑ አባላት ጉዋታማላና ፖኪስታን ኤርትራ ለአሥር ዓመታት በተባበሩት መንግሥታት ከተዳደረች በኋላ ነፃነትዋን እንድትጐናጸፍ የሚል የውሳኔ ሃሳብ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ አቀረቡ። ይህ አምስት አባላት የያዘው ኮሚሽን በተሰጠው መመርያ መሠረት ስምምነት ስላልደረሰ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁጥር 390 (V) ኤርትራ በኢትዮጵያ ዘውድ ስር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀለ ተወሰነ። በኢትዮጵያና በኤርትራ በ1952 ዓ.ም ፌዴሬሽን ተመሠረተ። ፌዴሬሽኑ በሆይሆይታ ሳይሆን በጥንቃቄና በትዕግሥት የተከናወነ ለመሆኑ ግልጽ ነው። ስለሆነም የፌዴሬሽኑ መመሥረት ሕጋዊ አልነበረም ብሎ የሚያከራክር ምንም ነገር አልነበረም።

ይኸ ሁሉ የኃያላን አገራትም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ አካሄድ ሃቅና ሕግን የተከተለ አይደለም። ምክንያቱም በ1900 ዓ.ም "ውል" ኢትዮጵያና ጣልያን በተስማሙት መሠረት ጣልያን በማንኛውም ምክንያት ኤርትራን ብትለቅ ኤርትራ ወደ ሌላ መንግሥትም ሆነ ተቋም ሳትዛወር በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ እንድትታጠፍ ተደንግጎ ነበር። ስለሆነም ኤርትራ ወደ አራቱ ኃያላን አገራት ብሎም ወደ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ መመራት አይገባትም ነበር። ከመጀመሪያውኑ ኤርትራን ከጣልያን የተረከቡት አራቱ ኃያላን አገራት የኤርትራ የወደፊት እድል ምን መሆን ይገባዋል ከማለት ይልቅ ኤርትራን በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ይገባቸው ነበር። ይህም መሆን ይገባው የነበረው የቅኝ ግዛት ውል ስለሚደነግግ ብቻ ሳይሆን ከመነሻው ኤርትራ የጥንታዊ ኢትዮትጵያ አካልም ስለነበረችም ጭምር ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር አንቀጽ 10 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በቻርተሩ በተጠቀሱ በማንኛውም ጉዳዮች ላይ ተነጋግሮ ለአባላቱ ወይንም ለጸጥታው ምክር ቤት

[86] Ibid

ወይንም ለሁሉቱም የውሳኔ ሐሳብ ሊሰጥ ይችላል ይላል[87]። የተባበሩት መንግሥታት የኤርትራን ጉዳይ በአጀንዳነት ይዞ የተወያየው ይህንኑ ሥልጣኑን ተገን በማድረግ ነው ማለት ይቻላል።

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በውሳኔ ቁጥር 390 (V) የሰጣቸው የውሳኔ ሃሳቦች በኢትዮጵያ፣ በጣልያን፣ የኤርትራን ጉዳይ በተረከቡት በአራቱ ኃያላን አገራት ላይ አሳሪነት አለው ወይ የሚለው ጠሳኝነት ያለው ጥያቄ ነው። የዚህ ጥያቄ መልስና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕግጋት የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን ስለሚያረጋግጡ በዝርዝር ይታያሉ።

በመሠረቱ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች አንዳንድ ሁኔታዎችን ካላሟሉ በስተቀር አሳሪ ሊሆኑ አይችሉም[88]። ሆኖም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተባበሩት መንግሥታትም ጭምር የተስማሙባቸውና የተቀበሉአቸው የውሳኔ ሳቦች አሳሪ ሊሆኑ ይችላሉ። የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት "በሬፓሬሽን" ጉዳይ እንዳተተው እነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የፈጠሩአቸው አገራት የሚሰጥዋቸው ሥልጣን ይኖራቸዋል። ይህ ሥልጣናቸው ከተቋቋሙባቸው መመሥረቻ ጽሁፎች ወይንም ከድርጅቶቹ ባህርያት ሊመነጩ ይችላሉ[89]። እነዚህ ጉዳያቸውን ወደ ጠቅላላ ጉባዔ የሚያቀርቡ አገራትም ሆኑ ድርጅቶች ጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጠው ውሳኔ አሳሪ እንዲሆን ተስማምተው ነው። የእነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሥልጣንን አስመልክቶ "በሬፓሬሽን" ጉዳይ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሚከተለውን ብሎአል። "በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት አንድ ድርጅት በግልጽ ባያስቀምጠውም የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስችል ሥልጣን ይኖረዋል" በማለት ወስኖአል።

ስለሆነም የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የኤርትራ ጉዳይ ከአራቱ ኃያላን አገራት ተረክቦ ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔ ይህ ነው ብሎ ያቀረበው የፌዴሬሽን ውሳኔ ከሥልጣኑ በላይ ነበር ማለት አይቻልም። ስለሆነም ኤርትራ በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር

[87] U.N.Charter Article 10

[88] Malcolm Shaw. supra note 69 p. 1212.

[89] Ibid



እንድትተሣሰር የተሰጠ ውሳኔ ተዋዋዮቹ፤ ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ፣ ጣልያን፣ አራቱ ኃያላን አገራትን የሚያስር ውሳኔ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ያሳለፋቸው የውሳኔ ቁጥር 390 (V) አራቱን ኃያላን አገራትን ወክሉ በተባበሩት መንግሥታት፤ በጣልያንና በኢትዮጵያ መሃከል የተፈረሙ ውሎች (Treaties) ናቸው። የዋናውን ውል የውሳኔ ቁጥር 390 (V) ይዘትን ለመድገም ያህል እንደሚከተለው ይነበባል። "የኤርትራ ሕዝብ የተለያዩ ኃይማኖቶች ምዕመናንና የጐሣ አባላትን ፍላጐት አገናዝቦ ፤ እንዲሁም የኤርትራ ሕዝብ እራሱን ለማስተዳደር ያለው አቅም ፈትሾ፤ የምሥራቅ አፍሪቃን ሰላምና ደህንነት ከስሌት አስገብቶ፣ የኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር በጆኦግራፊ፣ በኢኮኖሚ፣ በዘር ያላትን ትስስር ተገንዝቦ፤ <u>በተለይም የኢትዮጵያ ተገቢና ሕጋዊ የባህር በር ጥያቄ አምንታዊ ምላሽ እንዲያገኝ</u> (ሰርዝ የተጨመረ) ጠቅላላው ጉባዔው ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽኑን ቀላቀለ። በዚህም መሠረት የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር የነበረው የአንድነት ፍላጐት ተካትቶአል። ኤርትራ እራስዋን የማስተዳደር አቅም እንደሌላትና በረሰዋ ብትቆም ለአፍሪቃ ሰላምና ደህንነትን ስጋት መሆንዋን አረጋግጦአል። ከሁሉም በላይ (ውሉ "በተለይ" ይለዋል) የኢትዮጵያ የባህር በር መብት በምጽዋና በአሰብ አማካይነት ተረጋግጦአል። በውሳኔው ተዋዋዮቹ ፌዴሬሽኑ ለመመሥረት አመዛኙና ዋናው ምክንያታቸው የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ነው ቢባል ከእውነትነት የራቀ አይደለም። እንደዚሁም ጀኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት ካህሣይም አራቱን ኃያላን አገራት ወክሉ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ያሳለፈው የውሳኔ ሃሳብ ጣልያንና ኢትዮጵያ የተስማሙባቸው ውሎች አድርገው ይቆጥሩታል[90]። በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የፌዴሬሽን ሥርዓት የመሠረቱት የውሳኔ ሃሳቦች የተባበሩት መንግሥታትም ሆነ ኢትዮጵያ ወይንም ኤርትራ ሊጥሱአቸው የማይችሉ የሕግ ሰብእና የተላበሱ ውሎች ወይንም በተዋዋዮቹ የሕግ የተመሠረቱ ሕጎች ናቸው።

[90] Abebe T. Hamare Kabsay sup e.cote 3.

ይህ ጣልያን የሰላሙን ውል ፊርማ በኤርትራ ላይ የነበራትን መብት ስትለቅቅ አራቱ ኃያላን አገራት የጣልያን መብቶች ወራሾች ሆነው እነርሱንም ወክሉ የተባበሩት መንግሥታት ከኢትዮጵያ ጋር የተፈራረሙት የፌዴሬሽን የዘወትር ዓይነት ውል ባይሆንም አንድ ውል ሊኖረው የሚገባውን ሁሉ ያካትታል። በውሉም መሠረት የተባበሩት መንግሥቷት ጠቅላላ ጉባዔ ወኪል ኮሚሽነር በመመደብ ኢትዮጵያና ኤርትራ ተደራድረው የሚቀበሉት የፌዴራል ሕግ ተዘጋጅቶ፤ ይህም የፌዴራል አስተዳደር ሕግ በ1952 ዓ.ም ጸድቆ በሥራ ላይ ዋለ። እነዚህ ውሎች ከ1947 ዓ.ም ከተፈረመው የሰላሙ ውል ቃልና መንፈስ የመነጩ ስለሆነ እንደ ሰላሙ ውል በተዋዋዮቹ መሃከል ማለትም በአራቱም ኃያላን መንግሥታት እነዚህኑ በወከለው በተባበሩት መንግሥታት በጣልያንና በኢትዮጵያ መሃከል አሳሪ መሆናቸውን አቶ ሞገስ ሰለሞንም ይስማማሉ[91]። ፌዴሬሽኑ የ1947 ዓ.ም የሰላሙ ውል የደነገገውን በሥራ ላይ አዋለ እንጂ የሰላሙን ውል ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎችን የሚያፈርሱ ወይንም የሚቃረኑ ግዴታዎችን በተዋዋዮቹ ላይ አልጫነም።

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ አሳሪ ሆኖ አባላቱ ለውሳኔው ተገዢ ሲሆኑ ይህ የመጀመሪያው አይደለም። ከሊግ ኦቭ በዓለም ብዙ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ተከናውነዋል። ኔሽን ጊዜ ጀምሮ ሁለት አገራት የሊጉ ካውንስል የውሳኔ ሃሳቦች ተቀብለው አሳሪ ግዴታዎች ያደረጉባቸው አያሌ ጊዜአት አሉ። በእንዲህ ዓይነት ውሳኔዎች ድንበር የተካለሉ አገሮች ድንበራቸው የመጨረሻ ሆነዋል ሲሉ አቶ ሞገስ ሰለሞን በጽሁፋቸው አስረድተዋል[92]። የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕጋዊ ግንኙነት የተመሠረተው አሁንም ሕጉ የሚያውቀው ግንኙነት በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ 390 (V) የተደነገገው ቀጥሎም እ.አ.አ በ1962 ዓ.ም የኤርትራ ፓርላማ ሁለቱን አገራት

---

91 Moges Solomon. "Outlet to the Sea and Ethiopia's claim over the Port of Assab". Thesis, Faculty of Law, Addis Ababa University. (Unpublished (May 2000).

92 Ibid



ያዋሃደበት ውሳኔ ነው። የኤርትራ መገንጠል ይህንን ሕጋዊ ሐቅ ሊሽረው አይችልም።

ምናልባትም ካሴሴ (Cassese) እንዳለው የተባበሩት መንግሥታት አባል አገራት የተለያዩ የፖለቲካ ስትራተጂና ጥቅሞች ከዕውነተኛው የኤርትራ ሕዝብ ስሜት በላይ ሆኖ የነጻነት ጥያቄውን አደብዝዞት ሊሆን ይችላል[93]።ሆኖም አረረም መረረም ይህ የፌዴሬሽን ትስስር አሌ ሊባል ውይንም በተዋዋዮቹ ወይንም መሃከል አሳሪ አልነበርም ለማለት አይቻልም።

የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን መተሳሰር በተነሳ ቁጥር ኤርትራውያን በፌዴሬሽን ውይይት ወቅት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዝነኛው ሚስተር ጆን ፎስተር ያሉትን ይጠቅሳሉ።የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያሉትን በየአጋጣሚው ኤርትራውያን የሚጠቅሱት ከዚህ በታች የተጻፈውን ነው ። "ከፍትሕ አንጻር ስናየው የኤርትራ ሕዝብ ነጻነቱን መጐናጸፍ ይገባው ነበር። አሜሪካ በቀይ ባህር ሰላጤ ላይ ያላት ስትራቴጂክ ጥቅሞችና የዓለም ሰላምን ከግንዛቤ ስናስገባ ኤርትራ ከደጋፊአችን ከኢትዮጵያ ጋር መተሳሰር አለባት"[94]ብለው ነበር። ይህ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአሁኑ አባባል ቀደም ሲል የደንከል የባህር ጠረፍ (አሰብ) ወደ ኢትዮጵያ መካለል አለበት ከሚለው ጋር የሚጣረስ አይደለም። ኤርትራ በጊዜው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔም ሆነ በአራቱ ኃያላን አገራት ውሳኔ ሙሉ ነፃነትዋን ብትጐናጸፍ ኖሮ ቢያንስ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ያካልሉ እንደነበር ምንም አያጠራጥርም። ይህንን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ የኤርትራ ነፃነትን ይደግፉ የነበሩት እንደ ፓኪስታን ያሉ አገራት እንኳን የሚቀበሉት ጉዳይ እንደነበረ ምንም ሊካድ አይቻልም። በተባበሩት መንግሥታት

---

93 Antonio, Cassese "Self Determination of Peoples: A Legal Reappraisal," University Press,1955 p.222 cited in Moges Solomon, supra note 89.

94 Quoted in a speech by Eritrean Ambassador at the 275th meeting (Ministerial level) of the African Union. Peace and Security Council, Addis Ababa, 26th April 2011.

ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችም ሆነ በጠቅላላው ጉባዔ በተደረጉ ውይይቶች አንድም ጊዜ አንድም አገር ኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን አለባት ያለበት ጊዜ የለም። ዛሬም ቢሆን ከሻቢያን ከሕወሓት/ኢሕአዴግ በስተቀር ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ትሁን ሲል የተደመጠ አገርም ሆነ መሪ የለም።

ይህንኑ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቀደም ሲል በ1947 ዓ.ም በአራቱ ኃያላን አገራት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ የኤርትራ ምሥራቃዊ ክፍል ምጽዋንም ጨምሮ ወደ ኢትዮጵያ መታጠፍ አለበት ብለው ነበር። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በንግግራቸው ኤርትራ ነፃ መሆን ይገባት ነበር ሲሉ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ተጠብቆ ለመሆኑ ግልጽ ነበር።

የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ የተኬደው ወደ የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖች፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች፣ የሠራተኛ ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት ወዘተ ሲሆን ከእነዚህ ቡድኖች አንዱም ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንተሳሰር ያለ የለም። የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በራሱ ተነሻሽነት በባለጉዳዮቹ ማለት በአራቱ ኃያላን አገራትና በኢትዮጵያ ላይ የጫነው ነገር ነው። ምናልባት እነዚህ ሕዝባዊ ቡድኖች ፌዴሬሽኑን ቢቃወሙም በጊዜው የሚያመጡት ለውጥ አይኖርም ነበር።

ፌዴሬሽኑ በኢትዮጵያም ጉሮሮ የተሸናቆረ እንጂ ኢትዮጵያ ወድዳ የተቀበለችው ነገር አልነበረም። የኢትዮጵያን ተቃውሞ በመግለጽ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ ቀጥሎ ያለውን ብለው ነበር።

*"ለብዙ ምዕተ ዓመታት ነጻና ሉዐላዊ ሆና የኖረች አገር አንድ ሃያኛ ከማታህልና ነፃ ሆና ከማታውቅ አገር ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቅላ ሉዓላዊነቷ ጠፍቶ ከምድረ ገጽ ልትደመሰስ ፈቃደኛ አትሆንም። ኢትዮጵያ ዓለማቀፋዊ ልዕልናዋ ታሪኳና ሕልውናዋ እስካልተጠበቀ ፌዴሬሽን የሚባል ነገር አይኖርም። የኤርትራ ችግርም አይፈታም። ኢጣልያን ያቀረበችው የከሰረ የነጻነት ፎርሙላ ሥራ ላይ ከዋለ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትዋን አደጋ ላይ እንደወደቀ ትቆጥረዋለች። ጣልያን በተባበሩት መንግሥታት ምንም የአስተዳዳሪነት አደራ ሳይሰጣት ተሽቀዳድማ ሶማሌላንድ መግባትዋ እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ በድጋሚ ከኤርትራ በኩል ለሚሰነዘርባት ጥቃት አጸፋውን ለመመለስ የማታደርገው ነገር አይኖርም*[95] በማለት ቁርጠኝነታቸውን ገለጹ።



ስለሆነም የኢትዮጵያ መንግሥት ለውህደቱ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ሁለት ስስተኛ ድምጽ እንደማያገኝ ስለተረዳ ፌዴሬሽኑን የግድ ተቀበለ።

ኢትዮጵያ ፌደሬሽኑን ያለ ውዴታዋ ብትቀበልም እንዲፈርስ ወዲያውኑ ጥረት ማድረግ ጀመረች። ፕሮፌሰር ጆን ስፔንሰር፣ አሜሪካዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የሕግ አማካሪ እንዳሉት ከሆነ የተባበሩት መንግሥታት ጊዜያዊ ኮሚቴ ስለፌዴሬሽኑ ውይይት በሚያደርግበት ወቅት ፌዴሬሽኑ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያና የኤርትራ ፓርላመንት ሰርዘውት ውህደት ቢፈጥሩ ፌዴሬሽኑ እንዳይፈርስ የተባበሩት መንግሥታት ጣልቃ እንደማይገባ የኮሚቴው አባላት ለሚስተር ስፔንሰር እንደአረጋገጡላቸው ገልጸው ነበር[96]።

አሜሪካ ቃኘው ሻለቃ ቴሌኮሙኒኬሽን ጣቢያ ከአሥመራ ትንሽ ወጣ ብሎ ባለው አካባቢ እቋቁማ ስለነበር የፌደሬሽኑ መፍረስ እምብዛም አላስከፋትም ነበር። እንዲያውም የኢትዮጵያ መንግሥት ፌደሬሽኑ በተመሠረተ በሁለተኛው ዓመቱ ሲያፈርሰው ይፈልግ እንደነበረ ኢትዮጵያ ለእነዚህ መንግሥታት አስታውቃ ነበር ይላሉ ጆን ስፔንሰር[97]። ለማንኛውም የኢትዮጵያ መንግሥት ፌዴሬሽኑን በቀዘቀ!! ስሜት ሲቀበለው ለንጉሡ "ውህደት" ወይም "ፌዴሬሽን" ምንም ልዩነት እንደሌላቸው ተናግረው ነበር[98]።

በተቃራኒው ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው በጊዜው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ፌዴሬሽኑ ይፍረስ ከተባለ በኤርትራ ሕዝበ-ውሳኔ (Refurendum) መሠረት መሆን እንደሚገባው አስገንዝበው

---

[95] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) <u>የኤርትራ ጉዳይ 1941-1963</u> ዓ.ም አዲስ አበባ ገጽ 416.

[96] John Spencer, <u>Ethiopia at Bay: A Personal Account of Haile Selassie</u> (1984) p 211.

97 Ibid

[98] Shumet Sishagne, Professer supra note p.43 P.175-176

ነበር። ፌዴሬሽኑ በመንግሥት ውሳኔ ይፍረስ ከተባለ ቆይቶ ችግር እንደሚፈጠር አሳስበው ነበር። ለማንኛውም ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ ለ 10 ዓመታት በሞትም በሕይወትም መካከል ሲያጣጥር የነበረው ፌዴሬሽን እ.አ.አ ረቡዕ ሕዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም በከፍተኛ ስነ ሥርዓት በኤርትራ ፓርላማ ውሳኔ ግብአተ መሬቱ ተፈጸመ[99]።

ከዚያም ኤርትራ ውስጥ ምንም ዓይነት ነጻ የፓለቲካ እንቅስቃሴ ለመደምሰስ ከነበራቸው የንጉሡ ጉጉት ኮተቃዋሚ ፖርቲዎች ጀምሮ የውህደቱ ደጋፊዎችንም ጭምር አጠፉአቸው[100]። በዚህም ድርጊታቸው ዋነኛው የኢትዮ-ኤርትራ ውህደት አቀንቃኝ የነበረው "የአንድነት ፓርቲን" ሲዘጉ የውህደቱ ዋነኛ አንቀሳቃሽ የነበረውን ኃይል ናዱትዞ "የኤርትራ መንግሥት" የሚለው ቃል "የኤርትራ አስተዳደር" በሚለው ተቀየሮ ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕጐች በኤርትራ ላይ ተጭነው በኤርትራ ፖርላማ ውሳኔ በሙሉ ድምጽ የኤርትራ ፖርላማ ራሱን አፍርሶ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች አንዷ ሆነች[101]።

ጆን ስፔንሰር የኤርትራ ፖርላማ ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ውህደት እንዲመሠረት ፍላጐቱ መሆኑን ቢያውቁም አንዳንድ ኃያላን መንግሥታት ይቃወማሉ በማለት በእርሳቸው በኩል የፌዴሬሽኑ መፍረስ መቃወማቸውን ገልጸዋል[102]።

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ በኤርትራ ፖርላማ የተሰጠው ድምጽ ነፃ አልነበረም አባላቱ ተገድደው ነው፤ የሚል ስሞታ ከኤርትራውያን ብዙ ጊዜ ተደምጦአል። ሆኖም የትኞቹ የፖርላማ አባላት ፖርላማውን እንዲያፈርሱ ተገድደው ድምጽ ሰጡ፤በምን መልኩ ነው የተገደዱት ለሚለው ሁሉ እስከ ዛሬ ታአማኒ የሆነ ማስረጃ አልቀረበም። ምናልባትም ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ፍላጎት የነበራቸው የፓርላማ አባላት እንደማንኛውም አማራጭ ሃሳብ ወይንም የሚደግፉትን አቋም ተቀባይነት እንዲያገኝ ቅስቀሳ

[99] ዘውዴ ረታ (አምባሰደር) ዝኒ ከማሁ ገጽ 502

[100] Shumet Sishagne, Professor, supra note p. 43, p.176

[101] ትዕዛዝ ቁ.27/1962 ነጋሪት ጋዜጣ 20ኛው ዓመት ቁ 27 አዲስ አበባ

[102] John Spencer, supra note 96, p.303



አድርገው ከሆነ ይህ በሕግ የተፈቀደና የትም የሚደረግ ነው። ሕጉ የማያውቀው ግን የኤርትራ ፖርላማ በዚያው በኤርትራ ፖርላማ አባላት ሙሉ ድምጽ ያለ አንዳች ተቃውሞ መፍረሱ ነው። እዚህ ላይ ምናልባት አንድ የሕግ ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል።

የኤርትራ ፓርላማ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ ኤርትራን ከኢትዮጲያ ጋር ለመቀላቀል ሥልጣን ነበረው ወይ የሚለው ነው። የፌዴሬሽኑ ሁኔታ በሙሉ የሚገዛው በፌዴራል ሕግ (Federal Act) ሲሆን በዚህ ሕግ ስለፌዴሬሽኑ መፍረስ የሚያትተው ነገር የለም።

እስከ ዛሬ ድረስ ስለ ኤርትራ በተደረሱ ጽሁፎች የኤርትራ ፓርላማ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ሥልጣን አልነበረውም የሚል ክርክር ተሰምቶ አያውቅም። በእርግጥም ውህደቱ በሕዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ እንዳአሳሰቡት በሕዝብ ውሳኔ ቢደረግ በተሻለ ነበር። ጸሐፊ ትዕዛዝ ስለዲኘሎማሲ የጠለቀ ዕውቀት የነበራቸው ሰው ስለነበሩ የተባበሩት መንግሥታት የመሠረተው ፌዴሬሽን በኤርትራ ፓርላማ ቢፈርስ በተባበሩት መንግሥታትና በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ያስወቅሳል ከሚል ተነስተው ነው እንጂ ጸሐፊ ትዕዛዝ ውህደቱ ከመሠረተ ሃሳቡ ሳይወዱትና ሳይፈልጉት ቀርተው አይደለም። ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሃድና ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ያደረጉት ትልቅ ትግል በደርግ ታስረው በነበረ ጊዜ ለመርማሪ ኮሚሽን እራሳቸው ከጻፉት ማስታወሻ መረዳት ይቻላል[103]።

ፌዴሬሽኑ የፈረሰው በኢትዮጵያ መንግሥት አስገዳጅነትና ጫና ነበር የሚሉ ብዙዎች ሲሆኑ በአንጻሩ ደግሞ በጊዜው እጅግ የተከበሩ ለኤርትራ ነፃነት ወይንም ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ ከፍተኛ ትግል ያደረጉ ግለሰቦች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም። ከእነዚህም በዋናነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዱ የሕግ

[103] ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ የአክሊሉ ማስታወሻ፣ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓ.ም. (ለመርማሪ ኮሚሽን ያቀረቡት ማስታወሻ፣)፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ (2002 ዓ.ም.)

አስፈጻሚው ክፍል የበላይ የነበሩት ደጃዝማች ተድላ ባሁሩ ናቸው። እርሳቸውም "...... ያገሬ የመረብ ምላሽ ሕዝብ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ከማደር ይልቅ ፍጹም የሆነ ውሕደት እንዲደረግ በ.መርጥ ለደስታዩ ወሰን አልሰጠውም"[104] ብለው ነበር።

ደጃዝማች ተድላ ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ አቋማቸውን ቀይረው በኤርትራ የነጻነት ትግል ተሠማሩ። ልጃቸው አቶ ሕሩይ ተድላ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ከተመረቁ በኋላ የኤርትራን ትግል ተቀላቅለው ከጀብሃ መሪዎች አንዱ ሆነው ነበር። ኤርትራ ነፃ ከወጣች በኋላ ግን ከአቶ ከኢሣያስ ዋነኛ ተቃዋሚዎች አንዱ ሆነው የአቶ ኢሣያስ ተቃዋሚዎችን በማስተባበር ላይ ይገኛሉ። ለዚህም ጥረታቸው ከኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን በተለያዩ ጊዜአት አዲስ አበባን ጎብኝተዋል።

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስና ሙሉ ውሕደት እንዲደረግ ከማንም በላይ የጎከሙት ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል ከዚህ በታች የተመለከተውን ተናግረዋል።

*"........የፌዴሬሽን አስተዳደር ስሙም ሆነ ግብሩ ከታሪካችንና ከባህላችን የራቀ ለጠላት መሣርያ ከመሆን በስተቀር ለሕዝባችን የማይጠቅም መሆኑን ተረድተነው፤ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሕዝብ ለው ሠራሽ በሆነ ባዕዳዊ ድርጅት መመራት እጅግ የሚጐዳው መሆኑን ተገንዝበን የሕዝባችንን ሀሳብና ምኞት ገላጮች ሆነን ይህን ፌዴሬሽን የተባለ አስተዳደር ከላያችን አንስተን ከዛሬው ዕለት ጀምሮ ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር ተዋህደናል..."*[105]

ቢትወደድ አሥፍሐ እስከ እለተ ሞታቸው በአቋማቸው ጸንተው ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት የደከሙ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ባለውለታ ናቸው። የኢትዮ-ኤርትራ ፌዴሬሽን የተመሠረተው በዋናነት ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት ታስቦ እንዲሁም የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ለመተግበር እንደነበር ከላይ

[104] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) ዝኒ ከማሁ 95, ገጽ 417.

[105] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) ፤ዝኒ ከማሁ 95, ገጽ 539.



ተገልፆአል። የፌዴሬሽን መፍረስ የአራቱ ኃያላን አገራትና የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ፌዴሬሽኑን ሲመሠርቱ እነዚህ ሁለት መሰረታዊ ዓላማዎችን አጠናክሩ እንጂ አልሻሯቸውም። ስለሆነም ፌዴሬሽኑን ያፈረሰው የኤርትራ ሕዝብን የሚወክለው አካል ከመሆኑም በላይ ፌዴሬሽኑ የተመሠረተባቸው መሠረታዊ ዓላማዎችን ስለማይጻረር መፍረሱ ሕገ ወጥ ነበር ማለት አይቻልም።

ለማጠቃለል ያህል የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ብሎም አሰብ ቢያንስ በሁለት መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ታጥፎአል፤ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትም ተረጋግጦአል።

1. በጦርነቱ አሸናፊ የነበሩና ኤርትራን ከጣልያን ተረክበው የጉዳዩ ባለቤቶች የሆኑት የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይና ሶቭየት ሕብረት ተወካዮችና የተባበሩት መንግሥታት ጣልያንን ጨምሮ በ1947 ዓ.ም አሰብ ወደ ኢትዮጵያ መጠቃለል እንደሚገባው በውሳኔ ሃሳብ ደረጃ ተስማሙ።
2. አራቱ ኃያላን አገራትን ወክሉ የተባበሩት ምንግሥታች ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁጥር 390 (V) በተለይ በዋናነት ሕጋዊና ፍትሐዊ የኢትዮጵያን የባህር በር መብት ለማረጋገጥና የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ገቢራዊ ለማድረግ ኤርትራና ኢትዮጵያ በፌዴሬሽን ተቀላቀሉ። ይህም ፌዴሬሽን ሊጣስ በማይችል የኤርትራን ባለአደራ በነበሩት በአራቱ ኃያላን አገራት ወኪሎች በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ፤ በኢትዮጵያና በጣልያን ሲፈረም ኢትዮጵያ የባህር ባለቤት ሆነች።

## ምዕራፍ 4

# 4. የኤርትራ በጦር ኃይል መገንጠል ኢ-ሕጋዊነትና በኢትዮጵያ የተሰጣት ዕውቅና

የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት በማያጠራጥር መልኩ በሕግ የተረጋገጠው ከሦስት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ ሲኖር ነው። እነዚህም አንድ በቅኝ ግዛት ሥር የሚገኝ ሕብረተሰብ ራሱን ከቅኝ ግዛት መውጣትና ነፃ መንግሥት ማቋቋም መብቱ ሲሆን ይህንን ለማሳካት ኃይል መጠቀም ከመቻሉም በላይ ሌላውም የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ድጋፍን እንዲሰጠው ዓለም አቀፍ ሕግ ይደነግጋል*።

ቀጥሎም አንድ ሕብረተሰብ በባዕድ ጦር ኃይል ተይዞ ከሆነ ይህንን ጦር ከአገሩ ለማባረርና ሉዐላዊነቱን ለመጐናጸፍ መብት አለው። በመጨረሻም ብዙ ዘሮች ባሉበት አገር አንዱን ዘር ከሌላው ሕዝብ እኩል ተሳትፎ ከተነፈገ ይህንንም በሰላማዊ መንገድ በውይይት ይህንን መብቱ ማስከበር ካልቻለ የመገንጠል መብት እንዳለው የዓለም አቀፍ ሕግ ይደነግጋል[106]። ሆኖም የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚባለው መርህ ነፃና ሉዐዓላዊ አገራትን ለመበታተን መጠቀም ስለማይቻል ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር ዓለም አቀፍ ሕግም ሆነ የዓለም ሕብረተሰብ አንድ ሉዓላዊ አገር ተከፋፍሎ አንዱ ከሌላው በኃይል ተገንጥሎ የራሱን መንግሥት ማቋቋም አይደግፍም። ብሔሮች በዘፈቀደ ከአንድ ሉዓላዊ አገር እንዳሰኛቸው ቢገነጠሉ በዚህ ዓለም ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጥቃቅን አገራት ከመፈጠራቸውም ባሻገር የዓለምን ሰላምና ጸጥታ ሊያናጋ የሚችል ሁኔታ ይፈጠራል በሚል የዓለም ሕብረተሰብ የአገራት የግዛት አንድነትን ይደግፋል።

---

* ሕወሓት ለሻቢያ ድጋፍ የሰጠውም ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ከሚለው ተነስቶ ሲሆን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አልነበረችም እንጂ ቅኝ ግዛት ብትሆን ኖሮ ድጋፉ ትክክልና ሕጋዊ በሆነ ነበር።

[106] Antonio Cassese, supra note 93, p.62-63



ስለሆነም በሎሜ ቶጐ እ.አ.አ. በ2000 ዓ.ም የተደነገገው የአፍሪቃ ሕብረት መሠረታዊ ሕግ (Constitutive Act) አንቀጽ 3 ከአፍሪቃ መሠረታዊ ዓላማዎች አንዱ የአባል አገርን "ሉዐላዊነት፣ የግዛት አንድነትና ነፃነት ማረጋገጥ" መሆኑን ይገላጻል። እንዲሁም በአንቀጽ 4 የአፋሪቃ አገራት ነፃ ሲወጡ የነበራቸው ወሰን መከበር እንደለበት የድርጅቱ እምነት መሆኑን ያስገነዝባል። በአፋሪቃ ቢያፍራስ፣ናይጀርያ፣ካታንጋ፣ከኮንጐሬፑብሊክ፣ኤርትራ፣ከኢትዮያ ሣህራዊ አረብ ሬፑብሊክ ከምሮኮ፣አዲሲቱ ደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን ለመገንጠል የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ብዙ ደም ያፋሰሱ ስለሆነ የአፍሪቃ አገርት መገንጠልን አይደግፋም፣ እንዲያውም በአብዛኛው ይቃወሙታል። ስለሆነም በአፍራቃ ሕብረትም ሆነ በሌሎች ዓለም አቅፍ የሕግ መሠረታዊ ሰነዶች ወይንም የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድንጋጌዎች በአንዱም ከአንድ ነፃና ሉዐላዊት አገር የመገንጠል መብት እውቅና የተሰጠበት ቦታ የለም።

በአንድ አገር መንግሥቱ በግዛቱ የሚገኘውን መላውን ሕዝብ ሳያበላልጥ በእኩልነት ከአስተዳደረ የሕዝቡ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብቱ እስከተከበረለት ድረስ የአገሪቱ የግዛት አንድነት እንዲከበር ሕጉ ጥበቃ ያደርግለታል[107]። ይህንን በማጠናከር የዓለም ሕግ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ሲያረጋግጥ በዚህ መብት መጠቀም የሚቻለው በሉዐላዊ አገር ማቀፍ ውስጥ ሆኖ የአገሪቱ የግዛት አንድነት ተጠብቆ መሆን እንዳለበት ያረጋግጣል[108]። እንዲሁም እ.አ.አ በ1970 ዓ.ም "የወዳጅነት ግንኙነት" መርሆችን የደነገገው መግለጫ (1970 Declaration on Principles of International Law Concerning Relations between States)የራስን ዕድል በራስ መወሰን ማለት ነፃናሉዓላዊ አገራት እንዲገነጣጠሉ መፍቀድ ወይንም ማደፋፈርናና የግዛት አንድነታቸውን ማናጋት ማለት አይደለም ይላል[109]።

---

[107] Supreme Court of Canada in Reference to Secession of Quebec, cited in Antonio Cassese, supra note p.93, P.68

[108] Canadian Supreme Court "The case of Quebec " Cited by Medhane Tadele``The Scope of powers of the Security Counicil to decide on Imumities and. Previleges of Head of States/Governments with Special Emphasis on Sudan`` LLM Thesis ,Faculty of Law,Addis Ababa universislty june 2011

[109] Malcolm Shaw, supra note 69, P.140

የኤርትራ ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በመሠረቱ አንድ ቋንቋ የሚናገር አንድ ኃይማኖት የሚከተል አንድ ወጥ ዘር አይደለም። በኤርትራ በአብዛኛው ሕዝቡ ክርስቲያንና ሙስሊም ሲሆን ከዘጠኝ የማያንሱ ቋንቋዎች ይነገራሉ እነዚህም ትግርኛ ትግረ፣አረብኛ፣አፋር፣ሳሆ፣ቢለን፣ቤጃ፣ ባርያናኩናማ ናቸው። እነዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች በተለያዩ የኢኮኖሚ ደረጃ የሚገኙ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በራሳቸው የቆሙ መሆናቸውና እራሳቸውን እንደ አንድ ሕዝብ ይቆጥራሉ። ስለዚህ እነዚህ ሕዝቦች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ሕዝብ ተቆጥረው የመገንጠል ጥያቄ ቢያነሱ ጥያቄው የኤርትራ ሉዐላዊነት ለሚገረስስ የዓለም አቀፍ ሕግ ድጋፍ ሊኖረው አይችልም።

ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ጋር በነበሩበት ጊዜ በተለያዩ ከተሞች ተሰማርተው የንግድ ሥራ ሲያካሄዱ በቢሮክራሲውም ገብተው ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው ነበር። በአጼ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ዘመን ከማንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት ከመታየታቸውም በላይ እንዲያውም የኤርትራውያኑን ልብ ለማግባል ሲባል የኤርትራ ሕዝብ ከሌላው ጠቅላይ ግዛት ሕዝብ በተሻለ ተጠቃሚ ነበር የሚሉም አሉ። ያም ሆነ ይህ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የአስተዳደር ዘመን ኤርትራውያን ተለይተው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚአዊም ሆነ ሰብአዊ በደልና ጥቃት አልተፈጸመባቸውም። በነበረው ነባራዊ ሁኔታ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን እኩል የሕግ ጥበቃና ከለላ አልተነፈጉም።

በ1960ዎቹ አካባቢ ኤርትራውያን በክልላቸው ሆነ በመላው ኢትዮጵያ በተለይም በአዲስ አበባ በኢኮኖሚ ከየትኛውም ብሔረሰብ አባል በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኙ ነበር ማለት ይቻላል። ስለዚህ ኤርትራውያን ኢትዮጵያውያን ዜጎች በነበሩ ጊዜ ከሌላው ኢትዮጵያዊን በእኩልነት ኖረዋል። በመሆኑም የመገንጠል ጥያቄአቸው በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም። በኤርትራዊነታቸው ተለይተው ሰብአዊም ሆነ ፖለቲካዊ መብቶቻቸው አልተነፈጉም ነበር። እንዴ ሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የፊውዳል ሥርዓት ያመጣው ጉዳትም ሆነ ጥቅም ገፈት ቀማሾች ነበሩ። ስለሆነም እንደማንም ኢትዮጵያዊ ሥርዓቱን ለመለወጥ በሰላማዊ መንገድ



መታገል እንጂ ሁኔታው የመገንጠል መብት አያጎናጽፋቸውም ነበር።

በደርግ የአገዛዝ ዘመን በኤርትራ የእርስ በርስ ጦርነት ይካሄድ ስለነበር ብዙ ኤርትራውያን ለጦርነቱና ለኤርትራ መገንጠል ድጋፍ ይሰጣሉ በሚል በመሃል አገርም ሆነ በኤርትራ የሚኖሩ ኤርትራውያን ላይ ይደርስ የነበረው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን በላይ የከፋ ነበር ማለት ይቻላል። ሆኖም ግን ኤርትራውያንን በኤርትራዊነታቸው ብቻ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ጥቃት እንዲፈጸምባቸው የተወጠነ ዓላማ ነበር የሚል የለም።

እጅግ አሳዛኝ በሆኑ ጦርነቶች ከአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ጀምሮ በኤርትራም በኢትዮጵያም በኩል ብዙ ሰው አልቆአል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ የጦርነቶቹ ዓላማ መገንጠሉን ለማክሸፍ እንጂ ኤርትራውያንን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት እንዳልነበር ማንም ሊክደው የሚችል አይደለም። ደርግ አንድ የማይታማበት ነገር ቢኖር ዘርን ወይንም ኃይማኖትን ለይቶ ሰዎችን አልገደለም። ይህም ማለት ደርግ ለሁሉም እኩልና ተመሳሳይ ዕድል የሰጠ ገዳይ ወይንም ፈረንጆች እንደሚሉት (Equal Opportunity Killer) ነበር።

ኤርትራውያን የትጥቅ ትግል ያደረጉትና ኤርትራን ለመገንጠል ዋናው ምክንያት ነው ያሉት በ1952 ዓ.ም. ተመሠርቶ የነበረው ፌዴሬሽን ያላግባብ ተሰርዞ፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን መወሰን አልቻልንም ከሚል ተነስተው ሲሆን ጥያቄዎቻቸው በሰላማዊ መንገድና በድርድር መፍታት ሲችሉ እነዚህ መብቶቻቸውን እውን ለማድረግ የግድ ጦር መምዘዝ አስፈላጊ አልነበረም።

በተለያዩ ወቅቶችም ድርድሮች ተጀምረው አንድ ጊዜ የደርግ መንግሥት በሌላ ጊዜ ደግሞ የኤርትራ ግምባሮች ድርድሮቹን ሲያጨናግፉ ቆይተዋል። እነዚህ ውይይቶችና ድርድሮች ማድረግ በራሳቸው ውዝግቡን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ይቻል እንደነበርና መፍትሔው የግድ መገንጠል እንዳልነበረ ያሳያሉ።

ለድርድሮቹ መክሸፍ በደርግና በሻቢያ መሪዎች መሃከል በጐ ፈቃድ መጥፋት እንጂ በመሃከላቸው የነበሩ ቅራኔዎች በድርድርና ሰጥቶ በመቀበል ሊፈቱ የማይችሉ ስለነበሩ አይደለም።

ከመገንጠል በመለስ የኤርትራ ውዝግብ ከመቼውም ይበልጥ ለሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ የሆነ መፍትሔ ሊገኝ ይቻል የነበረው ሻቢያና ሕወሓት ሥልጣን በጨበጡበት በ1983 ዓ.ም. ነበር። እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ለብዙ ዓመታት ደርግን ተፋልመው ለቆሙለት ዓላማ ብዙ ዋጋ ከፍለው ሊጥሉት ችለው ነበረ በዚያን ጊዜ ይኸ የኢትዮጵያ የኤርትራ ግንኙነት የቅኝ ገዢና ተገዢ ነው የሚለውን የጨቅላ አስተሳሰበ ትተው አለአግባብ ፈረሰ ወዳሉት ወደ ፌዴሬሽኑ በመመለስ ሕጋዊነትን ሊይዙ በቻሉ ነበር። ሕወሓት ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች በሚል መሠረተ ቢስ ዕርዮተ ዓለም እራሱን ቀፍድዶ አስሮ ስለነበር ፊዴሬሽን የሚል ሃሳብ ከናካቴው አልመጣላትም ይሆናል። ምክንያቱም የአንድ ቅኝ ገዢና ተገዢ ትስስር ሊበጠስ የሚችለው ቅኝ ተገዢ ተብየው ነፃ ሲወጣ ብቻ ነው። ኢሕአዴግ እስከ ዛሬ ለኤርትራ መሪዎች የፌዴሬሽን ወይንም የኮንፌዴሬሽን ሃሳብ አቅርቦላቸው ነበር የሚል ሃሜት ተሰምቶበትም አያውቅም። እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ትስስር ሕወሓት ይቃወም እንደነበር አንዳንድ ሰዎች ይመሰክራሉ። ስለዚህ የኢትዮጵያ የኤርትራ ውዝግብ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ዕድሉ ሰፊ ስለነበር በኃይል መገንጠሉ የዓለም አቀፍ ሕግ ጥሰት ያደርገዋል[110]።

የኤርትራውያን መገንጠል ከሁሉም በላይ ሕገ ወጥ የሚያደርገው የተባበሩት መንግሥታት የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ቁ. 390 አንቀጽ (V) መጣሱ ነው። የዚህ ውሳኔ ዋናው ሐረግ "ኤርትራ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ሥር እራስዋን የቻለች (autonomous) ሆና ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ትዋሃዳለች" የሚለው ነበር።

ይህ የፌዴሬሽን ትስስር ጣሊያን ኢትዮጵያና የተባበሩት መንግሥታት የወከሉትን አራቱ ኃያላን አገራት የገቡት ውል ወይንም ግዴታ መሆኑን ከላይ ተገልጾአል። ውሉ ትስስርን የሚመሠርት እንጂ ተቃራኒውን መገንጠልን የሚያግፍ አልነበረም። የተባበሩት መንግሥታት ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ቢፈልግ ኖሮ ድሮውንም ሁለቱን አገራት

[110] See Minasee Haile, "Legality of Secession: The Case of Eritrea," 8 Emory Int'l Law Review, 479 (1944).



በፌዴራል ግንኙነት ማስተሳሰር ሳያስፈልግ ኤርትራ ነፃና ሉዐላዊ አገር ባደረጋት ነበር።

ስለዚህ ሻቢያ በ1983 ዓ.ም. ኤርትራን ሲገነጥል በመጀመሪያ አራቱ ኃይላን መንግሥታትን የወከለው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ኢትዮጵያና ጣልያን የተስማሙበት ውል ቀጥሎም የኤርትራ ፖርላማ የወሰነውን ውህደት አፍርሶአል። የፌዴሬሽኑ ዋነኛ ዓላማ የነበረው የኢትዮጵያ ወደ ባህር የመዝለቅ መብትንም ሰርዞአል። ሻቢያ ሕጋዊነት ቢከተል ኖሮ በሁለቱ አገራት መሃከል የነበረው የተባባሩት መንግሥታት መሥርቶት የነበረውን ፌዴሬሽን መልሶ ከዚያ በኋላ ሕዝቡ በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር መቆየት ይፈልግ እንደሆነ አልያም ነጻነቱን መርጦ ሉዐላዊ አገር መሆን ይመርጥ እንደሆነ በኢትዮጵያ ወይንም በተባበሩት መንግሥታት አዘጋጅነት ሕዝበ ውሳኔ (referendum) መካሄድ ነበረበት። ይህ አካሄድ ሊሠራ የሚችለው ግን የፌዴሬሽኑ ሃሳብ በሥልጣን ላይ ያለው ሕዋሐት/ኢሕአዴግ ከተቀበለው ብቻ ነበር።

በግንቦት 1983 ዓ.ም ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሻቢያ አሥመራን ከተቆጣጠሩ በኋላ ኢሕአዴግ የሰላም ጉባኤ ያለውን ስብሰባ ጠርቶ በአብዛኛው የብሔር ብሔረሰቦች፣ ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች በጉባዔው ተገኝተው ከአስተላለፉአቸው ውሳኔዎች አንዱ የኤርትራን ነጻነት ማፅደቅ ማለት ኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል ነበር። ከእነዚህ ሁሉ የስብሰባው ታዳሚዎች የአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ ተወካይ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ብቻ ኤርትራን ለማስገንጠል ሥልጣን የለኝም በማለት ከጉባኤው ውሳኔ እንደተለዩ የሚታወስ ነው።

የፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ* አቋም በፖለቲካውም ሆነ በሕጉ አንጻር ሲታይ በጽኑ መሠረት ላይ የቆመ ነበር። ጉባኤው

* አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በታዛቢነት በተገኙበት በአዲስ አበባው 1983 ዓ.ም "የሰላም ጉባዔ" ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አሰብ በታሪክም ቢሕግም የኢትዮጵያ የባህር በር ስለሆነች ወደ ኢትዮጵያ መከከል አለበት ባሉ ጊዜ አቶ ኢሳያስ "ታሪክና ሕግ የሚሉት ዝባዝንኬ ለትምህርት ቤት ክፍል ይተዉት። ይህ ፖለቲካዊ ጉዳይ በጦር ሜዳ ተፈትቶአል" በማለት ተሳለቁባቸው

አንዳንድ ብሔረሰቦች እንወክላለን ያሉ ግለሰቦች የሲቪክ ማህበራትና የጥቂት ፓርቲዎች መሪዎች ነን ባዮችና በጦርነቱ ደርግን አሸንፈው ሥልጣን የጨበጡ ድርጅቶች ተወካዮች የተገኙበት ሲሆን ማናቸውም በህዝብ የተመረጡ ሕዝቡን የሚወክሉ አልነበሩም:: ይህም በመሆኑ ጉባዔው ምናልባት የአገሪቱን ሰላም ለማስጠበቅ የሽግግር መንግሥት ከማቋቋም ውጭ ሌላ በአገሪቱ ላይ አሳሪ የሆነ ግዴታ ውስጥ የሚከትት በተለይም የአገሪቱን አንዱን ክፍል የሚገነጥል ውሳኔ ለመወሰን ሥልጣን አልነበረውም:: ጉባኤው ግን በሌለው ሥልጣን እንዲያውም የኢትዮጵያ ሕግ በመተላለፍ በሕዝብ ያልተመረጠ ስብስብ ቀርቶ ሕዝብን የሚወክል ፓርላማ እንኳን ሊያደርገው ሥልጣን በሌለው በአገር አንድነት ጉዳይ ውሳኔ ሰጠ:: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ከተደነገገው ከ 1923 ዓ.ም ሕገ መንግስት አንስቶ እስከ ደርግ ሕገ መንግስት አንዳቸውም አንዲት ጋት የኢትዮጵያ መሬት ለሌላ አሳልፎ መስጠት ወይንም ማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ማስገንጠል አይፈቅዱም ነበር:: ምናልባት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የኢትዮጵያ መሬት ለሌላ መንግስት ወይንም አገር ሊሰጥ የሚችለው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕዝበ ውሳኔ (Referendum) ሲስማማ ብቻ ነው::

ጉባኤው የሽግግር መንግሥት መሥርቶ ከተነሳ በኋላ የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚደንት አቶ መለስ ዜናዊ የጉባኤው ውሳኔ ለተባበሩት መንግስታትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት አስተላልፈው ለኤርትራ እውቅና እንዲሰጡ ያሳወቁበት ደብዳቤ ከትጥቅ ትግሉ ያላነሰ ኤርትራን ያዋለደ በጣም ትልቅ ዋጋ ያለውና ሕወሓት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የተዋደቀለት የኤርትራ ነፃነት እውን የሚያደርግና ኤርትራን ሙሉ ሕጋዊ ሰውነት ሊያጎናጽፋት የሚችል ኤርትራ ከዓለም መንግሥታት ተርታ የመሰለፍ ዕድል የከፈተላት ታላቅ እርምጃ ነበር::

ኢትዮጵያ ለኤርትራ እውቅና ለመስጠት የመጀመሪያ አገር ስትሆን ከዚያም አልፋ ለተባበሩት መንግስታትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኢትዮጵያ እውቅና መስጠትዋን ስታስታውቅ በመጀመሪያ በሰላም ጉባኤው ቀጥሎም በሽግግር መንግስቱ የተለያዩ የኢትዮጵያ ህግጋት ተጥሰዋል:: ኤርትራን ማስገንጠል በጊዜው የነበረው የደርግ ሕገ መንግስትን የሚጥስ ቢሆንም የደርግ ሥርዓት



ሲደመሰስ የሥርዓቱ መሠረት የነበረው ሕገ መንግሥትም ተደምስሶ ነበር ማለት ይቻላል:: ሆኖም ሌሎቹ የአገሪቱ ሕግጋት እንደነበሩ ሲሆኑ በተለይም በ1949 ዓ.ም የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በጉባዔው ወቅትም ያገለግል እንደነበር የሚታወቅ ነው:: ይኸው ሕግ ዛሬም ጥቃቅን ለውጦች ተደርገውለት እያገለገለ ነው:: የኢትዮጵያ አካል የነበረችው ኤርትራን ማስገንጠል የዚሁ የወንጀል ሕግ ቁጥር 253 የሚጻረር ድርጊት ነው*::

ይህ ኤርትራን አስገንጥሎ እውቅና የሚያሰጥ እርምጃ ኢትዮጵያ የተቀበለችውና የዓለም አቀፍ ሕግ አካል የሆነው የአፍሪካ አንድነት ቻርተርንም ይጥሳል:: ቻርተሩ በአንቀፅ 2 እንደ ደነገገው ከድርጅቱ ዓላማዎች አንዱ "የአባል አገራት ሉዓላዊነት፣ የግዛት አንድነትና ነፃነትን ማክበርና ማስከበር" ሲሆን የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትን የሚንድ የሽግግር መንግሥቱ ኤርትራን አወቀልኝ ጥያቄ በኢትዮጵያ መንግሥት ጠያቂነት ባይቀርብ ኖሮ ጥያቄው በተባበሩት መንግስታት ወይንም በአፍሪቃ አንድነት ድርጅትና በሌላውም ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ተቀባይነት አግኝቶ ኤርትራ ሕጋዊ ሰውነት ባልተጎናጸፈችም ነበር:: የተባበሩት መንግሥታ ድርጅት አገራት እውቅና ለሰጡአቸው መንግሥታት በአባልነት መቀበል እንጂ እውቅና አይሰጥም:: ስለሆነም የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚዳንት አቶ መለስ ዜናዊ ይሰጥ በማለት ለተባበሩት መንግሥታት የጻፉው ደብዳቤ የተባበሩት መንግሥታት የሕግ አማካሪን ሳያስገርም አይቀርም:: ስለዚህ ኤርትራ በተባበሩት መንግሥታት እውቅና አገኘች ሳይሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ነው የሆነችው::

በጊዜው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የነበሩት ታንዛንያዊው ሚስተር ሳሌም ሳሌም ኤርትራ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት እውቅና እንዲሰጣትና የድርጅቱ አባልም እንድትሆን

---

* አንቀጽ 253 እንዲህ ይላል "ማንም ሰው የህዝብን ያንድነት ሕብረት እንዲፈርስ የሚያደርግ ተግባር በመሥራት ወይንም ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት አገር ወይንም ሕዝብ ወይም ከፌዴሬሽኑ ተከፍሎ ወደ ሌላ መንግስት ሥርዓት ሕገ ወጥ በሆነ በማናቸውም ሁኔታ ይህን የመሰለ ተግባር ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ እድሜ ልክ ለማደርስ በሚችል ፅኑ እስራት ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ ከሆነ በሞት ፍርድ፣ [illegible] ይሳል::"

ኢትዮጵያ ጥያቄ ባቀረበች ጊዜ ዋናው ጸሐፊ ጭንቀት ውስጥ ገብተው እንደነበር ረዳታቸው የነበሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ለዚሁ ጸሐፊ አጫውተውት ነበር። ዋና ጸሐፊ ሆነው የተመረጡት ቻርተሩ የሚያዝዘው የአባል አገራትን የግዛት አንድነትና ነፃነት ለማስከበር ሲሆን ይህንን ቻርተሩን የሚጥስ የአንድን አባል አገር መገንጠል እንዴት ሊያስተናግዱ እንደሚችሉ ግር ብሎአቸው ነበር። ቻርተሩ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ማስተናገጃ አንቀጽ ስለሌለውና ከዚህ በፊትም ተመሳሳይ ነገር ገጥሞአቸው ስለማያውቁ የሚያደርጉት ነገር ቢያጡ ጥቂት የአፍሪቃ መሪዎችን ያሉበት ቡድን አማከሩ። የመሪዎቹም ቡድን የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራን አስገንጥሎ እውቅና ሰጥቶ ኤርትራ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት አባል እንድትሆን ካመለከተች መፈቀድ እንደሚኖርበት አሳሰቡ።

ልክ ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት ከሶማሊያ ተገንጥላ ነፃነትዋን ያወጀችው ሲማሌላንድ ኢትዮጵያ በፍጹም የተሳናት ነፃ ምርጫ አድርጋ ገዢው ፖርቲ ተሸንፎ ፕሬዚዳንቱ ለላንዳች ማንገራገር፤ እንኳን የ200 ሰው መገደል ቀርቶ አንድ ሰው ሳይታሠር ሥልጣናቸው ለተቃዋሚአቸው አስረከቡ። ይህም ቢሆን ዛሬ ሱማሌላንድ በአፍሪቃ የዴሞክራሲ ተምሳሌት ብትሆንም ምስቅልቅሏ የወጣው የሶማሊያ ሉዓላዊ አንድነት ሳለመጋፋት ሲል የዓለም ሕብረትሰብ ሱማሌላንድን እስከዛሬ ዕውቅና ነፍጎአታል። የኤርትራ መገንጠልና ዕውቅና ማግኘት እንደ ዳቦ መቁረስ ቀላል ያደረገውና ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ሉዐላዊነቷ ያስከበረች አገር ባንድ ቀን ጀምበር ሉዐላዊነቷ የተገረሰሰው የአገሩ መንግሥት ማለትም ሕወሐት/ኢሕአዴግ ለተገነጠለው አካል እውቅና ሰጥቶ ሌለውም የዓለም ሕበረተሰብ እውቅና እንዲሰግሳት በመማጠኑ ነው። ስለሆነም በኤርትራ መገንጠል ኢትዮጵያ ከተስማማችና ከገፋፋች አማራጭ ስለሌለ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትም ሆነ በጠቅላላው ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ የኢትዮጵያ የእውቅና ጥያቄ እንዲቀበሉ ተገድደው ጉዳዩ በዚሁ ተዘጋ።

ኤርትራ በተገነጠለችበት ጊዜ ከነበረችበት ሁኔታ ዛሬ ሱማሌላንድ ከአለችበት ጋር ሲነፃጸር በማንኛውም መስፈርት በዴሞክራሲ ምሥረታ ሕግና ሥርዓትን በማስፈን ሶማሌላንድ በጣም በተሻለ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ያም ሆኖ ሶማሌላንድ እውቅና



ተነፍጋለች። ስለሆነም ኢትዮጵያ ኤርትራን እውቅልኝ ጥያቄ ባታቀርብ ኖሮ ኤርትራ እውቅና ተነፍጓት ዛሬ እንደ አገር ልትቆጠር አትችልም ነበር።

በኤርትራም በኩል ጦርነቱ ተጠናቀቀ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል በኤርትራ ሕዝብ ምርጫ ሳይሆን በአንድ ነፃ አውጪ ግንባር ውሳኔ ነው። ይህ ነፃ አውጪ ግንባር ሌሎች ተቀናቃኝ ቡድኖች በተለይም ጀብሃ በውሳኔው ሲሳተፍ አልፈቀደለትም።

ሻቢያ ኤርትራን ሲያስገነጥል የአገሪቱን ሰላም ከማስከበር ውጭ ሌላ ማንኛውም ውል ለመዋዋል የሚያስችል ሕጋዊ ሰውነት አልነበረውም። ኤርትራ ሕጋዊ ሰውነት ልትጐናጸፍና ውል ለመዋዋል የምትችለው ከዓለም ሕብረተሰብ ማለት ከመንግሥታት እውቀና ካገኘች በኋላ ብቻ ነበር። ነፃ አውጪው ግንባር ሻቢያ በራሱ ማንም ሳይወክለው በኤርትራ ሕዝብ ውሳኔ (Referendum) የማደራጀት ሥልጣን አልነበረውም። የኤርትር ጉዳይ በሕዝብ ውሳኔ እስኪወሰን ድረስ የኢትዮጵያ አካል በለነበረች ሕዝበ ውሳኔ ለማዳራጀት ሥልጣን የነበራት ኢትዮጵያ ስትሆን እንደ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የአፍሪቃ ሕብረት የመሳሰሉ ገለልተኛ አካለትም ሊያደራጁት ይችሉ ነበር ። ሕዝበ ውሳኔውን ሻቢያ ሲያደረጅ ለሕዝቡ ያቀረበው ጥያቄ ራሱ ሻቢያ የፈለገው መልስ ያሚያስገኝ ስለነበር ነፃነቱ መላው የኤርትሪ ሕዝብ የተስማማበት ስመሆኑ ምንም ማስረጃ የለም።

ሻቢያ በሕገ ወጥ አካሄዱ ቀጥሎበት እንደ አውሮፖ አቆጣጠር በኤፕሪል 23-25, 1991 ዓ.ም በኤርትራ ውስጥ ለሕዝቡ ሌላ አማራጭ ሳይሰጠው "ነፃ መሆን ትፈልጋለህ አትፈልግም" የሚል ጥያቄ ብቻ ቀርቦለት ሕዝቡ በ99.8% (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫን ይመስላል) ድምጽ ለመገንጠል ይሁንታውን ሰጠ ተባለ።

ከኢትዮጵያ ጋር በአንድ መልኩ ወይም በሌላ ተሳስረው ሲኖሩ የፈለጉ ኤርትራውያን ፍላጎታቸውን ሊገልጹ ሳይችሉ ስለቀሩ ሪፈረንደሙ በውን የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐት ሙሉ በሙሉ ያንጸባረቀ ነበር ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም። በተጨማሪም የኤርትራ መገንጠል ሌሎች ኢትዮጵያውንም የሚመለከት ጉዳይ እንደ መሆኑ መጠን ድምጽ መስጠቱ ኢትዮጵያውንን በሙሉ መሸፈን ነበረበት የሚሉም አሉ። የካናዳ አካል የሆነችዋ ኩዌቤክ ከካናዳ "ትለይ አትለይ" በሚባልበት ጊዜ

ድምጽ የሰጠው መላው የካናዳ ሕዝብ ነበር። በተጨማሪም በኤርትራ ጽምጽ የሰጠው ሕዝብ የቀረበለት አማራጭ "ነፃነት ወይንም ባርነት" የሚል እንድምታ ስለነበረው ለሕዝቡ ምንም ዓይነት አማራጭ ስላልተሰጠ ውሳኔው ሕጋዊ አልነበረም የሚሉ አሉ።

ምናልባትም የኤርትራ መሪዎች የግድ መገንጠልን ከመረጡ ሕግና ሥርዓት ተከትለው ነፃ ቢወጡ አዲሱ መንግሥት የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ከበሬታ ይቸራቸው ነበር። ለዘለቄታውም ቢሆን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያቀያይም ምንም ነገር አይኖርም ነበር። ያም ሆነ ይህ ኤርትራ ከህግ ውጭ ከኢትዮጵያ ተገንጥላለች፤ የኢትዮጵያ የባህር በርም ተዘጋ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የኤርትራውያን ከኢትዮጵያ መለየት ምርጫቸው ከሆነ የወንድምና የእህት መለያየት እንደሚያሳምመው ያህል ኢትዮጵያውያን ቢያምማቸውም ተቀብለውታል። በጣሬው በወጣቶች ቋንቋ "ይመቻቸው" ከማለት ሌላ ምንም ማድረግ ስለማይችል ኤርትራውያን የወሰዱት እርምጃ ኢትዮጵያውያንን እንዳሳዘነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

የኤርትራ መገንጠል ለብዙ ኢትዮጵያውያን ጉዳያቸው የሚያደርገው ወንድምነቱና እህትነቱ ከመቅረቱ በተጨማሪ የባህር በራቸው እሰብን መነጠቃቸው ነው። በዚህ ጽሑፍም የኤርትራ መገንጠል የተነሳው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ በማድረጉ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ከዚህ ውጭ ከኤርትራውያን ጋር የሚያቃቅራቸው ምንም ነገር የለም።

ሆኖም የሁለቱ ወንድማማችና እህትማማች መለያየት ጉዳይ እንደሆነ ብዙ ምክንያቶችን አስደግፎ መናገር ይቻላል። የአንድን አገር ክፍል ከሌላው መገንጠል የሚያስከትለው ጉዳት በመገንዘብ ይሆናል የኤርትራው ፕሬዝደንት አቶ ኢሣያስ አፈወርቂ ደቡብና ሰሜን ሱዳንን አስመልክቶ ለአንድ ጋዜጠኛ በሰጡት አስተየየት ከዚህ የሚከተለውን ብለዋል።

*"ከደቡብና በሰሜን ሱዳን መሃከል የተፈጠረው ሁኔታ በሰዎች ስህተት የመጣ አደጋ ነው ብዬ ነው የማስቀምጠው። ለሜንና ደቡብ ሱዳን መለያየት አልነበረባቸውም። የደቡብ ሕዝብ በሬሏ ደርሶበታል። እንደ አንደኛ ዜጋ የሚቈጠር አልነበረም። ሱዳኖች ይህ መብቱ እንዲከበርለት መታገል መብቱ ነው። ከትግሉ ውጤት በኋላ በአዲሲቱ ሱዳን ከሰሜኑ ጋር አብሮ ቢኖር ጥሩ ነበር። ይህ የሆነው ለሱዳናውያን ታስቦ ሳይሆን ሱዳንን ለመበታተን ነው[111]።*



ይህ የአቶ ኢሣያስ አፈወርቂ አባባል ሕግን የተከተለ የበሰለ የአንድ የፓለቲክ ምሁር አስተያየት ነው። እንዲህ ዓይነት የበሰለ አቋም ምነው ወንድማማች ለሆነው ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባመቻቹለት። በትልቅ ክብርና በፍቅር፣ በአንደኛ ደረጃ ዜግነት (ደረጃ ካለ) ከኢትዮጵያውያን ጋር ይኖሩ የነበሩ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ እንዲገነጠሉ ለብዙ ዓመታት የተዋጉ አቶ ኢሣያስ የኤርትራ መገንጠልና የሁለት ወንድማማች ሕዝቦች መለያየት ትክክል ነው ሲሉ፤ ተንቀው፣ ከሰው በታች ተቈጥረው አንዳንዴም በባርነት ይሸጡ የነበሩ ደቡብ ሱዳናውያን ነፃነታቸውን መጐናጸፍ አልነበረቸውም ማለታቸው በጣም አስገራሚ ነው። አቶ ኢሣያስ ምናልባት የኢትዮጵያና የኤርትራ መለያየት ስህተት ነበር፤ መለያየት አይገባቸውም ነበር፤የሚሉ ከሆነ አሁንም ኢትዮጵያውያን ኤርትራውያንን በእኩልነትና በወንድማማችነት መንፈስ እጃቸውን ዘርግተው እንደሚቀበሉአቸው ጥርጥር የለውም። እርሳቸውም እንዳሉት እንደ ሱዳኖች መለያየት ሁሉ የኢትዮጵያና የኤርትራ መለያየት በእርግጥም "በሰዎች ስህተት የመጣ" ነው እንጂ ሁኔታው አስገድዶ አይደለም። ምናልባት በዚህ ዓለም በፍጹም መለያየት ያልነበረቸውና የማይገባቸው ሁለት አገራትና ሁለት ወንድማማች ሕዝቦች ቢኖሩ ኤርትራና ኢትዮጵያ ናቸው ማለት ይቻላል።

[111] <u>አዲስ አድማስ</u> ቅጽ 10 ቁ 590 ቅዳሜ ሚያዝያ 29 ቀን 2003 ዓ.ም

# ምዕርፍ 5

## 5. የአልጀርስ ስምምነት ኢ-ፍትሐዊነት ሲገመገም

እ.አ.አ በ2000 ዓ.ም በኢትዮጵያና በኤርትር መሃከል የተካሄደው ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት ከተደመደመ በኋላ የኤርትራ ወራሪ ጦር ከኢትዮጵያ ሲባረር የኢትዮጵያ ጦር በክትትል መጠነ ሰፊ ከሆነ ኤርትራ ግዛት ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ቦታዎችን ይዞ መቆየት ሲችልና ኤርትራንም አንዳንድ ግዴታዎች ውስጥ ሳያስገባት በሩጫ እንዲወጣ የታዘዘበት ምክንያት እስከ ዛሬም ምስጢር ሆኖ ቆይቶአል። ሆኖም ምናልባት ውስጠ ምስጢሩን ግልጥልጥ አድርጐ ሊያወጣው ባይችልም ቀደም ሲል ሕወሓት አመራር ውስጥ የነበሩና በአሁኑ ወቅት ደግሞ የዓረና ትግራይ ፓርቲ አመራርና የመድረክ አባል ወይዘሮ አረጋሽ አዳነ <u>አውራምባ ታይምስ</u> በሰጡት አስተያየት አንድ ጠቃሚ ነገር ሰንዝረዋል። እሳቸው እንዳሉት፣ "ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ፊት እየገሰገሰ በነበረበት ጊዜ ጦርነቱ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ይቆማል ብለው በሚድያ (በመገናኛ ብዙሃን) ብማወጃቸው ነው ሠራዊታችን ወደ ኋላ እንዲመለስና የሻቢያ ሠራዊት ከሞትና ከመቃብር እንዲድን የሆነው"[112]።

ከዚያም የኢትዮጵያ መንግሥትም እንደዚሁ በአስቸኳይ አልጀርስ ሄዶ የወሰን መካለል ስምምነቱን መፈረሙ ለወሰን መካለሉ መሠረት ኢትዮጵያና ጣልያን በ1900፣በ1902 እና በ1908 ዓ.ም የተፈራረሙአቸው የቅኝ ግዛት ውሎች አግባብነት ያላቸው አለም አቀፍ ሕጐችና እንዲሁም የአፍሪቃ

[112] ወይዘሮ አረጋሽ አዳነ <u>አውራምባ ታይምስ</u>, ቅዳሜ ሚያዝያ 1 ቀን 2003 ዓ.ም



ከዚህ በላይ ቢገለጽም ለማስታወስ ያህል እዚህ ላይ እንደገና ማንሳት አስፈለገ።

የመካለሉ ውሳኔ በእነዚህ ውሎች፣ በዓለም አቀፍ ሕግና በአፍሪቃ አንድነት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ በውሳኔው ወቅት ፍትሐዊነት ርዕታዊነት ወይንም አዘኔታ ወይንም እመክንዮት የመሳሰሉ ለፍትሐዊነት ግብአት ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ነገሮች ሁሉ (ex aequa et bono) ከእሳቤ እንዳይገቡ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተው አምስት አባላት የሚገኙበት የድምበር ኮሚሽን ሆላንድ ዘሔግ ውስጥ ተቋቋመ።

### 5.1. ተዋዋዮቹ

አንድ የአገር ሉዐላዊነት የሚነካ ይሁን ተራ የበሬ ሽያጭ ውል ቢያንስ በሁለት ወይንም ከዚያ በበለጡ ውል የመዋዋል ችሎታ ወይንም ሕጋዊ ብቃት (Legal capacity) ባላቸው ሰዎች ወይንም አካላት መሃከል መፈጸም ይኖርበታል። ውሉም የሚያስረው በሌላ መልኩ ካለተገለጸ በስተቀር ተዋዋዮቹን ወይንም በሕግ የወከሉትን ብቻ ሲሆን ሌላ ሰው ወይንም አካል ባልተደራደረበትና ባልተስማማበት ውል ሲጠቀምም ሆነ ሊጠየቅ አይችልም።

ኢትዮጵያና ጣልያን የፈረሙአቸው ውሎች እንደውልነታቸው ብዙ ማሟላት የነበረባቸው ሕጋዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም ለጊዜውም ቢሆንም ሕጋዊ ውሎች ናቸው ብለን ብንቀበላቸውም እንኳን አሳሪነታቸው ተዋዋዮቹን ጣልያንና ኢትዮጵያን እንጂ በውሉ ውስጥ ያልነበረችው ኤርትራን አይመለከትም ውሎቹ በተፈረሙበት ጊዜ ኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች ውል ለመዋዋል የሚያስችል ሕጋዊ ሰውነት አልነበራትም።

እዚህ ላይ በጊዜው ኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር የገባችው ግዴታም ሆነ መብት ኤርትራ ነፃ ስትወጣ ወርሳለች ወይ የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። አንድ አገር ከቅኝ ግዛት ነፃ ሲወጣ ቅኝ ገገርው የገባቸው ግዴታዎችን እንደገና ተደራድሮ ግዴታውን ካላደሰ ቅኝ ገገርው ከገባው ግዴታ አዲሱ አገር ነፃ መሆኑን ወይንም እንደማይመለከተው ስለአገራት

የተቀበሉት የ1978 ዓ.ም የቪየና ኮንቬንሽን አንቀጽ 16 ይደነግጋል[113]::

ይህንኑ በማረጋገጥ አምባሳደር ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ በቅኝ ገዢዎች ቀድሞ ይተዳደር የነበረ ግዛት ለአዲሱ መንግሥት ሲተላለፍ አዲስ ኢንተርናሽናል ሕይወት መጀመሩ ስለሆነ ከማናቸውም ግዳጅ ነፃ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባሉ::[114]

እንዲሁም የኔሬሬ ዶክትሪን የተባለው የሕግ መርሆ ቅኝ ግዛት የነበሩ አገራት ነፃ ሲወጡ የቅኝ ገዢዎቻቸው የገቡት ግዴታ አይወርሱም የሚል ሲሆን በቪየና ኮንቬንሽንም ሆነ በኔሬሬ ዶክትሪን መሠረት ቅኝ ገዢዎች የገቡባቸው ግዴታዎች በአዲሱ አገር ላይ አሳሪ የሚሆኑት አዲሱ አገር እንደገና ተደራድሮ አዲስ ግዴታ ውስጥ የገባ እንደሆነ ብቻ ነው[115]:: ስለሆነም በ1900 ዓ.ም. በ1902 ዓ.ም እና በ1908 ዓ.ም. ጣልያንና ኢትዮጵያ የተፈራረሙአቸው ውሎች በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ለተፈጠረው ውዝግብ አግባብነት ስለሌላቸው ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት ሊሆኑ አይችሉም:: በእነዚህ ውሎች ተመርኩዞ የሚሰጥ ማንኛውም ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ውሳኔው በሕግ ፊት ዋጋ አይኖረውም::

## 5.2. የተዋዋዮች አቅም አለመመጣጠንና ኢትዮጵያ በውሉ ለሰጠችው ምንም አለማግኘቷ

ጣሊያንና ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱ ውሎችን በፈረሙ ጊዜ በኢኮኖሚ አቅም፣ በወታደርና ትጥቅ ዝግጅት፣ እንዲሁም በየአገራቱ ላይ ሊያሳርፉ የሚችሉት የዲኘሎማሲ ጫና የሚመጣጠኑ አልነበሩም:: ውሎቹ በተፈረሙ ጊዜ ጣልያን በኢኮኖሚ የዳበረች፣ በጦር ኃይሏ የጠነከረች ዘመናዊ አገር ስትሆን ስትሆን ኢትዮጵያ ደግሞ ደካማና ድሀ እንደ መሆንዋ መጠን የሁለቱ አገራት ኃይል የተመጣጠነ ነበር ለማለት ካለመቻሉ ሌላ ጣልያንና ሌሎችም የአውሮፖ አገራት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ የሚጥሩበት ጊዜ ነበር:: የኢትዮጵያ በሁሉም መስክ ደካም ሁኔታ ላይ ሆና ከጣልያን ጋር የገባችው ውል ዋጋ ቢስ ነው::ሁለቱ ተዋዋዮች ኢትዮጵያና ጣልያን በምንም መልኩ የሚመጣጠን ኃይልና አቅም አልነበራቸውም:: ውሎች ሙሉ በሙሉ ወደ አንድ ወገን ያጋደሉ ከመሆናቸውም በላይ ኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛቶችዋን ስታስረክብ በለውጡ ምንም ያገኙችው ነገር ስለሌለ ሕጋዊ ውሎች ነበሩ ለማለት አይቻልም::

## 5.3. ኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛቶችዋን እንድታስርክብ ተገድዳ የፈረመቻቸው ውሎች

ጣልያንና ኢትዮጵያ እነዚህን ውሎች በተፈራረሙበት ወቅት የአውሮፖ ቅኝ ገዢዎች አፍሪቃን በቅኝ ግዛትነት ለመቀራመት ከፍተኛ ትንቅንቅ ውስጥ የገቡበት ጊዜ ነበር:: አጼ ምኒልክ የመጀመርያውን ማለት የ1900 ዓ.ም. ሰነድ የተጫነባችው (ፈርመውት አያውቁም) አውሮፖውያን በጀርመን ዋና ከተማ በበርሊን ተገኝተው አፍሪቃን እንደ ቅርጫ ሥጋ ከተቀራመቱበት ከሁለት ዓመታት በኋላ ነበር:: በዚህ ሽሚያ አንዷም አገር ያልደረሳት ጣልያን ብቸኛዋ ነፃ አፍሪካዊት አገርን ኢትዮጵያን ለመዋጥ ወስና ለዚሁ ግብ እንግሊዝና ፈረንሳይ ሲደግፉአት ቆይተው ነበር::

ስለሆነም ኢትዮጵያ በሰሜኑ በኩል በጣልያን፣ በምሥራቅ አሁንም በጣልያን በፈረንሳይና በእንግሊዝ፣ በደቡብ አሁንም በእንግሊዝ፣ በምዕራብ እንደገና በእንግሊዝ ተከብባ ጭንቅ ውስጥ የነበረችበት ጊዜ እንደነበር ቀደም ሲል ተገልጿል:: እነዚህ ኃይሎች በተለያዩ ጊዜአት የኢትዮጵያን ወሰን ጥሰው በመግባት ጉዳት ያደርሱ ነበር:: የወልወሉ ትንኩሳ ዋነኛው ምሳሌ ሲሆን በሌሎችም አካባቢዎች ተመሳሳይ ጥቃቶች ይሰነዘሩ ነበር::

አጼ ምኒልክ እነዚህን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ግዛቶችን አሳልፈው የሚሰጡ ውሎች የፈረሙት በነበረባቸው ጫና ምክንያት ተገድደው

[113] Vienna Convention on Succession of States in Respect of Treaties, 1978.

[114] ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ (አምባሰደር) ሰለባይ ውሃ ሙግት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኘሬስ, (2001 ገጽ 191.

[115] Vienna Convention on Succession of States, supra note.113.

ተገድደው ለመሆኑ አያጠራጥርም። ኢትዮጵያም በጦር ኃይል፣ በኢኮኖሚና በዲፕሎማሲው በነበራባት ድክመት የጣልያንና የሌሎች የአውሮፓ አገራት ጫና ለመቋቋም የሚያስችል አቅም አልነበራትም። አንድ ተዋዋይ ውል እንዲገባ ወይንም ስምምነት እንዲፈርም ማስገደድ ሕገ ወጥ እንደመሆኑ መጠን እንዲህ ዓይነቱ ስምምነት ከመነሻው በሕግ ፊት ዋጋ አይኖረውም[116]።

አጼ ምኒልክ ተገድደው ባይሆን ኖሮ የኢትዮጵያ የጥንት ግዛቶችን ወደ ጣለያን የሚያጥፉ ውሎችን በምንም ዓይነት ባልተቀበሉም ነበር። ማንም በተለይም እንደ አጼ ምኒልክ ያለ አገር ወዳድና የአገር አባት ተገድዶ ካልሆነ በስተቀር የአገሩን ታሪካዊ ክፍሎች ቆርጦ ለጠላት ሰጥቶ የባህር በርን የሚዘጋ ውል አይፈርምም።

በማስገደድ ወይንም በማስፈራራት የሚፈረም ውል ፍርስ ስለሆነ በተዋዋዮቹ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም። በማንኛውም አገር የውል ሕግም ሆነ በዓለም አቀፍ የውል ሕጎች እንዲህ ዓይነት ውል ፍርስ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ 1 9 9 4 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት የተደነገገው የውል ሕግ አንቀጽ 3 9 አንድ ተዋዋይ ውል ውስጥ እንዲገባ ማስፈራራት የተደረገበት ከሆነና ይህም የተደረገበት ማስፈራራት ሊቋቋመው የማይችል ከሆነ ውሉ ፍርስ ነው ይላል[117]።

በተጨማሪም እ.አ.አ በግንቦት 2 2 ቀን 1 9 6 9 ዓ.ም. የውል ሕጎችን አስመልክቶ በተደነገገው የቪዬና ስምምነት (Vienna Convention) አንቀጽ 5 2 በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የተጠቀሱትን መርሆችን በመጣስ፣ ወይንም በማስፈራራት ወይንም በማስገደድ የተደረገ ውል ዋጋ እንደሌለው ይገልጻል[118]።

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ከተጠቀሱት መርሆዎች አንዱ የአገራት ሉዓላዊንት በሌላው አለመደፈር ሲሆን ጣልያኖች ግን የኢትዮጵያ የጥንት ግዛቶችዋን በመጠቅለል በኢትየጵያ ሉዐላዊነት ላይ በደል ፈጽመዋል ። በተጨማሪም ኢትዮጵያ

[116] Id

[117] Id

[118] Id



ውሎቹን ስተፈርምና ግዛትዋን ስትለቅ ከላይ እንደተገለጸው በለውጡ ያገኘችው ጥቅም የለም። ስለሆነም በዚሁ በቪዬና ኮንቬንሽን መሠረት ውሎቹ አሁንም ፍርስ ናቸው።

የቪዬና ኮንቬንሽን ሕግ ሆኖ የወጣው ውሎቹ ከተፈረሙ በኋላ ቢሆንም አንድ ሕግ ደግሞ አሳሪነት የሚኖረው ሕጉ ከወጣበት ወይንም ከታወጀበት ጊዜ በኋላ ለሚፈጸሙ ድርጊቶች ብቻ እንጂ ሕጉ ወደ ኋላ ሄዶ እንዳይሠራ መደንገግ መሠረታዊ የሕግ መርህ ነው። ይህ የቪዬና ኮንቬንሽን የሚደነግገው ቀደም ሲል ይታወቁ የነበሩት ዓለም አቀፍ ልማዳዊ ሕጎችን (Customary International Law) ስለሆኑ በእነዚህ በአጼ ምኒልክና በጣልያኖች በተፈረሙ "ውሎች" ላይም ተፈጻሚነት አላቸው። ይህ አቋም ከላይ ለተጠቀሰው በ1994 ዓ.ም ለተደነገገው ለተባበሩት መንግሥታት የውል ሕግም አግባብነት አለው።

ስለሆነም እነዚህ በኢትዮጵያና በጣልያን መሃከል የተፈረሙ ሦስቱም ውሎች በእነዚህ በተለያዩ ሕጎች መሠረት ፍርስ ስለሆኑ ለድንበር መካለሉ ሊያገለግሉ አይችሉም። በእነዚህ ሕገ ወጥ ውሎች በመመስረት የተሰጠ ውሳኔም ዋጋ ቢስ ነው።

አምባሳደር ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ሱዳንና ግብጽ ለጥቅማቸው ምቹ ያልሆኑ የቅኝ ግዛት ስምምነቶችን ውድቅ እንዳደረጉ ሁሉ ኢትዮጵያም አባይን አስመልክቶ ተመሳሳይ አቋም መያዝ ምንም የሚከለክላት ነገር እንደሌለ ከገለጹ በኋላ ፍስሐ ይመር (አምባሳደር) የተባሉ የሕግ ባለሙያ ይህንኑ አቋም በአንድ በዋፉት መጣጥፍ እንደሚደግፉ ጠቁመዋል።

በአልጀርስ የድምበር ኮሚሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ መንግሥት ተባባሪ ተወካይ (ሌላው አቶ ሥዩም መሥፍን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲሆኑ) አምባሳደር ፍስሐ ይመር የሱዳንና የግብጽ የቅኝ ግዛት ውሎችን ውድቅ መሆናቸው ሲደግፉ እንዴት ብለው ነው በኢትዮጵያ ላይ ሲሆን የቅኝ ግዛት ውሎች አሳሪና ዋጋ አላቸው በማለት ለድርድሩ መሠረት እንዲሆኑ የተስማሙት?

ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ከመሠረቱ እንደ ውልነታቸው ችግር ደላባቸው ስለሆኑ በውን በሕግ ፊት የተሟሉ ውሎች ናቸው ሊባሉ አይችሉም።

## 5.4. የውሎቹ ጉድለቶችና ውድቅ መሆናቸው።

የድምበር ኮሚሽኑ ውሎች ለውሳኔው መሠረት ካደረጋቸው አንዱ የ1900 ዓ.ም "ውል" እንግሊዝና ጣልያን የተፈራረሙበት ስምምነት ሲሆን ሁለቱ አገራት ከሰቲት እስከ መተማ ያለውን ወሰን ወደ ምሥራቅ በማካለል ከጎንደር ወደ ኤርትራ የሚወስደው የንግድ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ ያደርጋል ይላል። ለዚህም ለኢትዮጵያ ለተሰጠው ሰፊ መሬት ልዋጭ የኩናማ ጎሳ በሙሉ እስከ መረብ ድረስ ለኤርትራ (ለጣልያን) ኢትዮጵያ እንድትለቅ የእንግሊዝና የጣልያን ወኪሎች አጼ ምኒልክን እንዲጠየቁ ይወስናሉ። የኢትዮጵያ ስምምነት እስኪገኝ ድረስ በስምምነቱ የተወሰነው ሁሉ ምስጢር ሆኖ እንዲቆይ እንግሊዝና ጣልያን ተስማሙ[119]።

ይህ ሰነድ ለአጼ ምኒልክ ወይንም ለወኪሎቻቸው ቀርቦ አልተፈረመበትም። ወይንም በሌላ መልኩ ኢትዮጵያ ይህንን ውል ፊርማ የተቀበለችበት ጊዜ የለም። ማንኛውም የውል ረቂቅ ዋጋ እንዲኖራው ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ወይንም አካላት መፈረም ይኖርበታል። ከተፈራረሙም በኋላ የየአገሩ ሕግ በሚደነግገው መሠረት በንጉሡ ወይንም በፖርላማው ወይንም በሌላ ውል ለማጽደቅ ሥልጣን በተሰጠው አካል መጽደቅ ይኖርበታል። ከላይ የተጠቀሰው እንግሊዝና ጣልያን የተፈራረሙት ሰነድ ኢትዮጵያን ሊያስር የሚችል የተሟላ ውል አይደለም። ይህ አቋም በዚህ ጉዳይ ምርምር ያዳረጉ በጀኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት ካህሣይና በአቶ ምገስ ሰለምን የተደገፈ ነው። በጀኔራሉ አስተሳሰብ ሰነዱ ውል ሳይሆን ሁለቱ ወገኖች የተለዋወጡት ማስታወሻ ተደርጎ መታየት አለበት[120]። በዚህ ጽሁፍ በተለያዩ ቦታዎች ይህ ሰነድ

[119] <u>የኤርትራ ቅኝ ግዛት የህግ መጽሐፍ ከአራተኛው ጥራዝ</u> ከገጽ 779-780 በጣልያንኛ የተጻፈው ፤1962 ዓ.ም

[120] Abebe T. Haimanot Kahsay. supra Note 3.



"ውል" እየተባለ ቢጠቀስም ሰነዱ "ውል" ነበር ለማለት አይደለም። ስለሆነም የአልጀርስ የድምበር ኮሚሽን ውሳኔውን የሰጠው በሕግ ፊት በተሟሉ ውሎች ሳይሆን በተራ ማስታወሻ ነው ማለት ነው።

ኢትዮጵያ በኮሎኒያሊስቶች ተከብባ ጭንቅ ውስጥ በነበረችበት ጊዜያት የፈረመቻቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ ኢሕአደግ ሲስማማ ምን አስቦ ነው የሚል ጥያቄ ጉዳዩን በሚያውቀው ሰው ሁሉ አእምሮ የሚጉላላ ጥያቄ ነው። ከአንዳንድ የቀድሞ ሕወሐት አባላት አካባቢዎች እንደተደመጠው ከሆነ ውሎቹ ለኢትዮጵያ ይበጃሉ፣ የኢትዮጵያን ጥቅም በሚገባ ያስጠብቃሉ ከሚለው ተነስተው እንደነበረ ይናገራሉ[121]።

ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛትነት ቀንበር ልታሸክም ትሯሯጥ የነበረችው ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የቅኝ ግዛት ውሎች እንዴት የኢትዮጵያን ጥቅም ሊያስጠብቁ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል? የኢትዮጵያ የጥንት የሰሜን ግዛቶችን የሚነጥቁ የባህር በሮችዋን የሚዘጉ ውሎች ኢትዮጵያን ሊጠቅሙ ይችላሉ ማለት "አይናችሁን ጨፍኑ እናሞኛችሁ" ከማለት አይዘልም። ቅኝ ገዢዋ ጣልያን የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መሠረት የሆኑትን ግዛቶች ከኢትዮጵያ የነጠቀችውና ይህንን ትልቅ አገር ወደብ አልባ ያደረገችው ለእኛው ለኢትዮጵያውያን አስባና ተጨንቃ ነው እንደ ማለት ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያና ጣልያን የተፈራረሙአቸው የድንበር ውሎች አምስት ጊዜ ያህል ሞተዋል፣ ተሰርዘዋል።

- በተለያዩ ሕጋዊ ምክንያቶች ማለትም ውሎቹ በኢትዮጵያ ላይ በግድ በመጫናቸው፣ ኢትዮጵያ፣ ሉዐላዊ ግዛቶችን ለጣልያን ለማስረከብ በመገደድዋ፣ በውሎቹ ተጠቃሚዋ ጣልያን ብቻ ሆና ኢትዮጵያ በልዋጩ ምንም ባለማግኘትዋ ውሎቹን ፍርስ ናቸው።

[121] Ibid

- ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር የፈረመቻቸው ውሎችን በመጣስ ኢትዮጵያን ወርራ ከኢትዮጵያ ጋር የተስማማችባቸው ድንበሮችን አፍርሳ ኢትዮጵያ ኤርትራና የጣልያን ሶማልያን አንድ ላይ አጣምራ "የጣልያን ምሥራቅ አፍሪቃ ግዛት"(Italian East African Empire) በመመስረትዋ ውሎቹን አፍርሳቸለች።
- ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተደምድሞ ድል አድራጊ አገራትና ጣልያን ሌሎችም አገራትን ኢትዮጵያንም ጨምሮ በ1947 ዓ.ም በተፈራረሙት የሰላም ውል አንቀጽ 23 ጣልያን በአፍሪቃ የነበራት ማንኛውም መብቶች ሲሰረዙ ከኢትዮጵያ ጋር የተፈረርመአቸው ውሎቹም አብረው ተሰርዘዋል።
- እ.አ.አ በዲሴምበር 1952 ዓ.ም የተባባሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁ.390 (V) ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ስር በፌዴሬሽን ሲያስተሳስር ቀደም ሲል ጣልያንና ኢትዮጵያ የተፈራረሙአቸው ውሎች ተሰርዘዋል።
- እነዚህ ጣልያኖችና ኢትዮጵያ የተፋረረሙአቸው ውሎች ኤርትራና ኢትዮጵያ እንደገና ተደራድረው አላደሱአቸውም። ስለሆነም እነዚህ ውሎች ምንም በማያጠረጥር መልኩ ~~መሞታቸው~~ እንኳን የሕግ ልሂቃንና የአገር መሪዎች ቀርቶ አንድ የአንደኛ ደርጃ ተማሪ እንኳን ሊረዳው የሚችል ነው።እጅግ በጣም የሚገርመው ደግሞ በአጼ ኃይል ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን እነዚህ ሦስት "ውሎች" በነጋሪት ጋዜጣ በወጣ ትዕዛዝ ቁጥር 6/1952 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተሰረዙ መሆኑኑ እያታወቀ ለአልጀርስ ስምምነት መሠረት መሆናቸውን ነው። "የመርዛም ዛፍ ፍሬ መርዛም ነው" በሚለው የሕግ ብሒል መሠረት ሕገ ወጡ ውሎች የአልጀርሰ ሕግ ወጥ ስምምነትና ውሳኔን ወልደዋል። ስለሆነም እነዚህ ውሎች ለድንብር መካለሉ መሠረት ሲሆኑ ውሎቹ መፍረሳቸው እነዚህ የሕግ ልሂቃንና የአገር መሪዎች አልተረዱም ማለት በፍጽም አይቻልም። ጉዳዩ የሌላ ነው ብሎ ለመደምደም ያስገድዳል ።

ኮሚሽኑ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ፍርስ መሆናቸው ከዚህ በላይ በሰፊው ተብራርቶአል። ሁለተኛው ለውሳኔው መሠረት የሆነው የአፍሪቃ አንድንት ድርጅት የመሪዎች



ጉባዔ በካይሮ ያሳለፈው ወሳኔ ቁ.AHG/Res/16/1 የአፍሪቃ አገሮች ነፃ ሲወጡ የነበራቸው ወሰን ይከበር የሚለው መርህ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ የወሰን ማካለል አግባብነት እንደሌለው ከላይ ተጠቅሶአል። ይህ ውሳኔ ቃሉ እንደሚያስረዳው አግባብነት ያለው ቅኝ ግዛት ለነበሩ አገራት ነው። ከሕወሓትና ሻቢያ በስተቀር ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበርች ያለ ማንም አልነበርም። የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት በጠቅላላው የዓለም ሕብርተሰብ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አድርገው አልቆጠሯትም። በተባበሩት መንግሥት ጸረ ኮሎኒ ኮሚቴም ሆነ በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ጸረ ኮሎኒ ኮሚቴ ኤርትራ እንደቅኝ ግዛት የተመዘገበችበት ጊዜ የለም። እንደ ፕሮፌሰር ንጉሤ አየለ አባባል "………የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት መቼም ቢሆን ሻቢያ በአፍሪቃ ውስጥ ትግል እንደሚያደርግ እንደ የነፃነት ታገይ ቡድን (Freedom fighting group) በመቁጠር እንደ ሌሎች ለነፃነት ታጋዮች" ድጋፍና እርዳታ አደርጎለት አያውቅም[122]። ስለሆነም የድምበር ኮሚሽኑ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አለመሆንዋ እየታወቀ ኮሚሽኑ ይህ የሕግ መርህ ለውሳኔው መሠረት ማድረጉ የሚገርም ከመሆኑም በላይ ግልጽና አውቆ የተደረገ ስህተት ነው።

### 5.5. የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ የአሜሪካ መንግሥት የተጫወተው ሚና

እነዚህ የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ የተመረጡት በቢል ክሊተን (Bill Clinton) አስተዳደር ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፋሪቃ ጉዳይ ኦስፊ በነበሩት በሱዛን ራይስ (Susan Rice) ግፊት እንደነበር በኢትዮጵያው የድርድር ቡድን ውስጥ ተመድበው የነበሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ተሰታፊ ለዚሁ ጸሐፊ ገልጸውለታል።

[122] ንጉሤ አየለ ፕሮፌሰር (የቀድሞ አምባሳደር)፤ "ያቀጋችን ቁራጭ መሬት አይደለችም" ሮፖርተር 15 ሐመሌ 1992 ዓ.ም ,

ኤርትራ ቀይ ባህርን በማዋሰንዋ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለባብኤል መንደብ ባላት ቅርበት እጅግ ስትራተጂክ በሆነ አካባቢ የምትገኝ ስትሆን ይህንኑ በመገንዘብ አሜሪካኖች በአጼ ኃይለ ሥላሴ የአስተዳደር ዘመን አሥመራ አጠገብ የሚገኘው ቃኘው የተባለ የመገናኛና የስለላ ሰፈር አቋቋመው ነበር። አሜሪካኖች አሁንም ይህንን በጣም ስትራተጂክ የሆነችውን ኤርትራን በቁጥጥራቸው ስር ለማስገባት በብዙ ኳትነዋል። የኤርትራው ፕሬዚዳንት አቶ ኢሣያስን፤የኡጋንዳው ፕሬዚዳንት ዮዎሪ ሙሰቪኒ፤ የሩዋንዳው ፕሬዝዳንት ፖል ካጋሜንና፤ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ ቀይቶ ሲቆጫቸው "አዲሶቹ የአፍሪቃ ዴሞክራቲክ መሪዎች" እያሉ አሞካክሸአቸው ነበር። ከእነዚህም መሪዎች በተለይም ከኤርትራ ጋር ቅርበት ለመፍጠር በብዙ ጥርዋል፤ የዛሬዋ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ክሊንተን (Hillary Clinton) የአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ተደማጭ አባል በነበሩት ጊዜ ኢትዮጵያን ከጉዳይ ሳይጥፋ ኤርትራን ጉብኝተው ወደ ኢትዮጵያ ሳይዘልቁ ወደ ሀገራቸው መመላሰቸው የሚታወስ ነው።

ከላይ እንደተገለጸውም ደርግ በኢሕአደግና በሻቢያ ተሸንፎ ኢሕደግ አዲስ አበባ፤ ሻቢያ አሥመራ ለመግባት ጥቂት ቀናት ሲቀራቸው አሜሪካ ኢሕአዴግን፤ ሻቢያንና የኦሮም ነፃነት ግንባርን (ኦነግ) በለንደን አሰባሰባ በማደራደር ኤርትራን በማዋለዱ ሂደት ከፍተኛ ሚና ተጫውታ ስለነበር ኤርትራን የራስዋ ፍጡር አድርጋ በመቁጠር በአንድ ወቅት "ኤርትራ የሹም ዶሮ ነች፤ ክፍ አትበልዋት" ወደ ማለቱ ደርሳ ነበር።

አሜሪካ የኤርትራን እጅግ ስትራቴጂካዊነት በመረዳት በቁጥጥሬ ስር አውላታለሁ በሚል እምነት ይመስላል ቀደም ሲል የአገራት ሉዐላዊነት አጥብቃ ትደግፍ የነበረችዋ አሜሪካ በተባበሩት መንግስታት መድርክ የተናገሩችውን በመለወጥ የኤርትራን መገንጠል በጽኑ ደግፍለች። በአፍሪቃ ቀንድ ሽብርኝነት ብቅ ብሎ ኢትዮጵያ እንደገና የአሜሪካ ጥብቅ ወዳጅ እስከሆነችበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ለአሜሪካ ጠቃሚነትዋ እጅግም ስላልነበረ ወደብ አልባዋን ኢትዮጵያን ትታ ድጋፍዋን ወደ ኤርትራ አዞረች። በአንድ ወቅት እንዲያውም ኢትዮጵያ በአካባቢው ካለ አገሮች በሦስትና በአራት እጅ ስለምትገዝፍ



ይህም ለአካባቢው ሰላምና ደህንነት አደገኛ ስለሆነ፤ ኢትዮጵያ ከአካባቢው አገሮች እኩልና ተመጣጣኝ እንድትሆን ወደ ሦስትና አራት ቦታ መከፋፈል አለባት የሚለው ሃሳብ ሲናፈስ ነበር። ይህን መሳይ አስተሳሰብ በሌሎች አካባቢም ይናፈቅ እንደነበር ፕሮፌሰር መስፍን ጽፋዋል

> *....አንዳንድ ኃያላን አገሮች አደዲስ አገሮች እንዲፈጠሩ ተጽእኖ እንዲሚያደርጉ በቅርቡ በአውሮፓም ሆነ በአፍሪቃ "ያልተሳካለቸው" አገሮች በእንግሊዝኛ "ፌይልድ ስቴትስ" በሚል እርዕስ ከአሜሪካ አንድ ሰነድ ወጥቶ ነበር ። ዓላማው እነዚህ ያልተሳካላቸው፤ የአፍሪቃ አገሮች በጉሣ ለመሸንሸንና ትናንሽ አገሮች ለመፍጠር ነበር። በዓላማው ከአፍሪቃ መሪዎች" ተስማምተዋል ተብለው የተጠቀሱት ዋናው መለሰ ናቸው*[123]

ስለዚህ አሜሪካ በቁጥጥርዋ ስር ለማስገባት ያሰበቻትን ኤርትራን ለመጥቀም ኢትዮጵያን የሚጉዱ ውሎች ለድንበር መካለሉ መሠረት እንዲሆኑ ጫና ብታደርግ አይገርምም።

የቅኝ ግዛት ውሎች ለድንበር መካለሉ መሠረት ይሁኑ ሲባል ኤርትራን ለመጥቀም መሆኑ የአንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሊረዳው የሚችለው ጉዳይ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አገርን የሚያስቀማ፤ የባህር በርን የሚያዘጋ ሕገ ወጥ ውሎች ለድንበር መካለል መሠረት ይሁኑ ሲባል እሺ ብለው መቀበላቸው አንድም ስህተት ሲከፋም ክህደት ነበር ብሎ ከመፈረጅ አማራጭ የለም።

## 5.6. ፍትህና ዕርት ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት እንዳይሆን የተደረገ ገደብ

ኤርትራና ኢትዮጵያ በመሃከላቸው ያለውን ድንበር ለማካለል መሠረት ያደረጉአቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ፤አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕግጋትና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ ብቻ መሆናቸው ይታወሳል። በማካለሉ ጊዜ የሚገጥሙ አንዳንድ ኢፍትሐዊ ሁኔታዎቹን ለማረም የሚያስችል ፍትሕ ርትዕ፤ሰብአዊ እርህራሄ (ex aequa et

[123] መስፍን ወልደ ማርያም፤ፕሮፌሰር፤ ዋሽ ከማሁ 3ኛ ገጽ 25

bono) ከግንዛቤ እንዳያገቡ ስምምነቱ ይከለክላል። ስለሆነም ከነኚሁ ከተጠቀሱት ሕግጋትና መመርያ ውጭ በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ምንም ዓይነት ችግር ቢፈጠር ኮሚሽኑ ለፍትሕና ለርትዕ ሲል አስተያየት አድርጎ ውሳኔውን ሊያርመው አይችልም። ወሰኑ በሚካለልበት ጊዜ በቅኝ ግዛት ውሎችና በተጠቀሱት መመርያዎች መሠረት ብቻ ይሁን ሲባል የወሰኑ መስመር የሚያርፍባቸው ቦታዎች ምድረ በዳዎች ሳይሆኑ ለብዙ ዘመናት ሕዝብ የሰፈረባቸው ቦታዎች መሆናቸውን መዘንጋት አይገባውም ነበር። የኢትዮጵያ ጠበቆች ወይንም ተወካዮች በምዕራቡ በኩል በአንደንድ ቦታዎች መስመሩ ትምህርት ቤትን፤ ቤተክርስቲያንና የመቃብር ቦታዎች ለሁለት ሊከፍል እንደሚችል ማወቅ ነበረባቸው።

እንደዚህ ዓይነት ተራማይሌ ሁኔታ በተፈጠሩ ጊዜያት የድንበር ኮሚሽኑ ይህንኑ የሕግ መርሆ (ex aequa et bono) ተከትሎ ፍትሕ ርትዕ ወይንም አመክንዮ ተጠቅም የድንበሩን ማስተካከል አይፈቀድለትም። ይህ ሁኔታ የሚጉዳው ኢትዮጵያ ነው። ምክንያቱም የድምበር ኮሚሽኑ ያስመረው የማካለል መስመር ከላይ እንደተጠቀሰው ቤተክርስቲያን ከመቃብር ቦታ ይልያል ተማሪ ቤትን ለሁለት ይከፍላል። በስምምነቱ መሠረትም ኮሚሽኑ እነዚህን ውጥንቅጥ ሁኔታዎች አርሞ ትምህርት ቤቱም ሆነ ቤተክርስቲያኑ ወደ አንዱ አገር ማጠፍ አይችልም። በጠቅላላው ኮሚሽኑ ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎችንም ሆነ ተመሳሳይ ጉረማይሌ ሁኔታዎችን ለማስተካከል አይፈቀድለትም። በዚህም ተጉጂ የሚሆኑት የድምበር መስመሩ በሚያርፍበት አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ያለው አማራጭ ሁለቱ ወገኖች ተስማምተው እርምት ማድረግ ብቻ ነው። እርምት ለማድረግ ስምምነት ሳይደርሱ ውሳኔው እንደወረደ ሥራ ላይ ማዋል ሊኖር ነው። በኢትዮጵያና በኤርትራ ባለሥልጣናት መሃከል ባለው ግትርነት ጥላቻ ምክንያት እንዲህ ዓይነቱ መግባቡት ደርሰው እርምት ለማድረግ ይስማማሉ ብሎ መጠበቅ አዳጋች ነው።

በኤርትራና በኢትዮጵያ ድምበር ኮሚሽን ውስጥ ይሠራ የነበር በኋላም ወደ ናይጂሪያ ካሜሩን የድምበር ኮሚሽን ተዛውሮ የዚህ ጸሐፊ የሥራ ባልደረባ አሚሪካዊ የሁለቱን አገራት



ባለሥልጣናት ሲገልጽአቸው "እንደ ሚስማር የጠጠሩ" (tough as nail) ናቸው ብሎአል። ከሁለቱም መግባበት መጠበቅ ስህተት መሆኑን ገልጾአል።

የኢትዮጵያ ተወካዮች ወደ ፊት እንደምናየው ዋና ዋና የአገሪቱ ጥቅምችን አስረክበው በጭፍጫፊ ላይ ግትር መሆን ጠቃሚነቱ እምን ላይ መሆኑ እነርሱ ብቻ ናቸው የሚያውቁት።

## 5.7. የውሉ አፈፃፃምና የኢትዮጵያ የተዛባው አካሄድ

•በናይጀርያና በካሜሩን መሃከል የድምበር ችግር ተፈጥሮ ጉዳያቸው ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወስደው ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ የድምበሩ መስመር አንዱን ከተማ ለሁለት ሲከፍል ከዚህያም አልፎ አንድን ቤት ግማሹን በናይጀርያ በኩል ሲያስቀመጠው ሌላው ግማሽ በካሜሩን በኩል ሲሆን ሁለቱ ወገኖች ተስማምተው መስመሩን አስተካክለው ቤቱና የከተማው ክፍል ወደ ካሜሩን እንዲታጠፉ ሆነ። የካሜሩንና የናይጀርያ የወሰን ድርድር መግባባት የነበረበትና በሰለጠነ መንገድ የተስተናገደ ስለነበረ ከነዚህም የከፉ ውስብስብ ችግሮችን ወደ ፊት እንደምናየው በመግባባት ፈትዋትል[124]።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረው ጦርነት እንደተጠናቀቀ በየትኛው አገር ጠያቂነት እንደሆነ አይታወቅም ለግልግል ደኝነት ወደ አልጀርስ ማቅናታቸው ከዚህ በፊት ተገልጾአል። የሌሎች በጦርነት ውስጥ የነበሩት አገሮች ተሞክሮ እንደታየው ከሆነ በአንድ ጦርነት አሸናፊ የሆነ አገር የጠላትን ግዛት ይዞ እንደሆነ በዚያው በያዘው ቦታ አረግቶ ተሸናፊው ተኩስ አቁም ስምኖ ለግልግል አስቀድሞ ጥያቄ ያቀርባል። ግልግሉ ተጠናቅቆ ስምምነት እስኪደርሱ ድረስ አሸናፊው የያዘው መሬት ለወደታደራዊ እንቅስቃሴ ጠቃሚነት ያለው ገነር መሬት ከሆነ

[124] Case Concerning the Land and Maritime Boundary between Cameroon and Nigeria (Cameroon V. Nigeria and Equatorial Guinea Intervening) 10 October 2000 Judgment.

ወይንም ለወደፊቱ ጠላት ጥቃት ሊሰነዝርበት አመቺ የሆነ ቦታ ከሆነ ጠላቱ በድጋሚ እንደማይወረው ዋስትና ሲሰጠውና ሌሎች ሌሎች ግዴታዎችም ውስጥ ካስገባው በኋላ የያዘውን የሰው መሬት ለቅቆ ይወጣል፡፡

ለምሳሌ እስራኤል እ.አ.አ በ1967 ዓ.ም በአረቦች ከተወረረች በኋላ በጦርነቱ አሸንፋ ከያዘቻቸው የአረብ ግዛቶች አንዱ ኢየሩሳሌም አናት ላይ ያለው የሶርያ ግዛት ጐላን ሃይትስ ነው፡፡ ጐላን ኃይትስ ላይ ሆኖ በቀጥታ ኢየሩሳሌምን መቆጣጠር ስለሚያስችል ሶርያ ለእሥራኤል አውቅና እስከትሰጥ ድረስ እስራኤል ጐላን ሃይትስን አለቅም ብላ እነሆ ለአርባ አራት ዓመታት ይዛባት ትገኛለች፡፡ ዓለም አቀፍ ሕብረተ ሰብም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ጐላን ሃይትስን ከእሥራኤል ለማስለቀቅ የወሰደው ምንም እርመጃ የለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያም ለደህንነትዋ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን አሳብ ወደ ኢትዮጵያ እስኪታጠፍ ወይንም ከኤርትራ ጋር አሰብን አስመልክቶ ሌላ ስምምነት እስኪደረግ ድረስ ከያዘቻቸው የኤርትራ ግዛት አልወጣም ብትል ድሮውንም ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት በደገፈው ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ወቀሳ አይደርስበትም ነበር፡፡ ስለዚህ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማጠፍ ከሚያስችሉ ብዙ ዕድሎች አንዱ ይኸው ሲሆን በዚህና በተመሳሰይ ወደፊት በሚጠቀሱ እድሎች ኢትዮጵያ ሳትጠቀምባቸው አልፏአል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል በተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያ እንደ አሸናፊነትዋ ከአሸናፊነት የሚመነጩ መብቶች አልተጠቀመችባቸውም፡፡ ይልቁንም በሕገወጥ አልጀርስ ስምምነት ምክንያት ለጉዳት ተዳረገች፡፡



## ምዕራፍ 6

## 6. በአልጀርስ ስምምነት መሠረት የተቋቋመው የድምበር ኮሚሽን አመሠራረትና ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ሲገመገም

በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል የነበረው ቁጥራቸው እስከ ዛሬም በሁለቱም ባላጋራዎች ያልተገለፀ በጣም ብዙ ኢትጵያውያንና ኤርትራውያን ወንድማማቾችና እህትማማቾች የተላለቁበት ጦርነት፤ ብዙ ዋጋ ብትከፍልም በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተደምድሞ የሁለቱም አገሮች መሪዎች በወቅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀ መንበር በነበሩት በአልጀሪያው ፕሬዝደንት በአብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ አደራዳሪነት ሰላም ለማውረድ፤የድምበር ስምምነት ለመፈራረምና ሰመካሰል ወደ አልጀሪያ ዋና ከተማ አልጀርስ አቀኑ፡፡

ድርድሩ በአጭር ቀናት ውስጥ ተጠናቅቆ በተኩስ አቁም ስምምነት፤ የድምበር ኮሚሽንና የካሣ ኮሚሽኑ በሚያቋቁመው ሰነድ ላይ የሁለቱም አገሮች መሪዎች አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ፈርመው ጥላቻና ቂም በሚያንፀባርቅ መልክ ተጨባብጠው በሌላ ወቅት እንደተለመደው ሳይተቃቀፉና አንዲት ቃል ሳይለዋወጡ ተለያዩ፡፡

በሁለቱ ወንድማማች "የሐበሻ" መሪዎች (አቶ ኢሣያስ ቢክዱም) አንድ የአረብ አገር መሪ መሃል ገብቶ ሲያጨባብጣቸው ማየት ሕሊናን የሚሰብር ትዕይንት ነበር፡፡ እ.አ.አ. በዲሴምበር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሁለቱ መሪዎች ድንበር ማካለሉ በቅኝ ግዛት ውሎችና በሌሎች ሕጐች መሠረት እንዲሆን ተስማምተው ሲጨባበጡ የተላለፈው መልእክት የኢትዮጵያ የባህር በር ተዘጋ፤ "ብቃ ተዘጋ" የሚል ለኢትዮጵያውያን አስደንጋጭ መልዕክት ነበር፡፡

የአልጀርስ ስምምነትና ውሰኔ ከውጫሌው ውል ባልተናነሰ ምናልባትም በከፋ መልኩ በአገር ላይ ጉዳት ያደረሰ ውል ስለሆነ ከድርድሩ ቀጠና (Venue) አመራረጥ ጀምሮ የሊቀ መንበሩ አሰያየም፣ለድርድሩ መሠረት የሆኑ ሕጎችንና የዳኞቹ አመራረጥና ገለልተኛነት የድርድሩ አካሄድ መመርመር ያስፈልጋል።

እነዚህን የ1900ዓ.ም፣ 1902ዓ.ም እና የ1908ዓ.ም ስምምነቶችን በሥራ ላይ ለማዋል በአልጀርስ የተፈረመው ስምምነት በኢትዮጵያ ላይ ዘላቂ ጉዳት የሚያስከትል የኢትዮጵያን የባህር በር የሚዘጋና አሰብን ለኤርትራ የሰጠ ስምምነት ሲሆን፤ ይህ የአልጀርስ ስምምነት አጼ ምኒልክ እንደፈረሙአቸው "ውሎች" በኢትዮጵያ ላይ በግድ የተጫነ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግስት ሕወሓት/ኢሕአዴግ ፈቅዶ (ምናልባትም ለምኖ) ዳኛ መርጦ፣ ሥልጣናቸውና የሚዳኙበት ሕግ ወስኖ የገባበት ስምምነት ነው።

የዚህም ውል ዋናው ዓላማ የኢትዮጵያና የኤርትራ የጋራ ድምበር የሚያካልል አምስት ዳኞች የያዘ ኮሚሽን አቋቁሞ ኮሚሽኑ የተባበሩት መንግሥታት፤ የአውሮፖ ኅብረት፤ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትና የአሜሪካ ተወካዮች በአስፈጻሚነት በተገኙበት የተቈረጠ ይግባኝ የሌለበት ውሳኔ መስጠትና ድምበር ማካለል ነበር።

## 6.1. የየአገራቱ ተወካዮች ማንነት

በኮሚሽኑ ፊት የኢትዮጵያን ቡደን የመሩ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ክብረ ወሰን የያዙት በጊዜው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት የሕወሓት መሥራች አባል አቶ ሥዩም መስፍን ሲሆኑ በተባባሪነት ደግሞ የህግ ባለሙያ የሆኑት አምባሳደር ፍሰሐ ይመር ተመድበው ነበር። እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አባል የሆኑ አንድ የሕግ ባለሙያ የመንግሥት ባለስልጣን በቡድኑ ተጨምረው፣ ሌሎች አስራ አንድ የውጭ አገር ዜጎችን ጨምሮ በጠቅላላው ኢትዮጵያ አስራ አራት አባላትን በሚያካትት ቡድን ተወክላ ነበር። ወሳኝ በሆነው በሕግ አማካሪነትና በጥብቅናው ዘርፍ ማንም ኢትዮጵያዊ አለመመደቡ ሊሠመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ናቸው ክርክሩን አዘጋጅተው በድምበር ኮሚሽኑ ፊት ቀርበው



የሚሟገቱት ። ሌሎቹ የቡድኑ አባላት አማካሪዎች ናቸው ማለት ይቻላል። የአንድ ኢትዮጵያዊ እንኳን በቡድኑ መካተት ወደ ፊት እንደሚታየው ግልጽ የሆኑ የኤርትራና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ የተሠሩ ስህተቶችን ማረም ያስችል ነበር።

የኤርትራው ቡድን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አለ. ሰይድ አብደላ ሲመራ ተባባሪአቸው ደግሞ ፕሮፌሰር ሊያ ብሬልሜየር ( Lea Brilmayer) ነበሩ። የኤርትራ ቡድን በውስጡ ሦስት የመንግስት ባለስልጣናትና አንድ የኤርትራ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ያቀፈ ሲሆን፤ እንዲሁም አስር የውጭ ዜጎች አካትቶ በጠቅላላው ኤርትራ በአሥራ አራት ሰዎች ስትወከል በሕግ አማካሪነትና በጥብቅናው ዘርፍ ከውጭ አገር ዜጐች በተጨማሪ የአሥመራ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰር የማነ ምሾጊና ተመድበው ነበር[125]።

ሁለቱ ቡድኖች ሲነፃፀሩ ኢትዮጵያ በኮሚሽኑ ውስጥ አስራ አራት ሰዎች ስታሠማራ ኤርትራም እንደዚሁ አስራ አራት ሰዎችን መድባ ነበር። በኢትዮጵያ በኩል ሁሉም የመንግሥትን አቋም የሚያቀነቅኑ ግለሰቦች ሲሆኑ የአልጀርስን ስምምነት የተቀበሉና የኢትዮጵያ የባህር በር እንዲዘጋ የተስማሙ ነበሩ ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያን የባህር በር መዘጋት የሚቃወሙ ቢሆኑ ኖሮ ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የኢትዮጵያ የባህር በር በእርግጠኝነት የሚዘጉና የፈረሱ የቅኝ ግዛት ውሎችን ተቀብለው ኢትዮጵያን ወክለው በድርድሩ ባልተገኙም ነበር።

ሁለቱ ቡድኖች የሚለያቸው ነገር ቢኖር የኤርትራ ዜጎች በኮሚሽኑ ውስጥ የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ ሲሆን የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ አነስተኛ ነበር ማለት ይቻላል። ከላይ እንደተጠቀሰው ኤርትራ ከውጭ አገር ዜጎች ሌላ በሕግ

125 Eritrea-Ethiopia Boundary Commission Decision Regarding Delimitation of the Border between the State of Eritrea and the Federal Democratic Republic of Ethiopia, The Hague 13th day of April 2002 (unpublished)

አማካሪነትና በጥብቅናው ዘርፍ አንድ ኤርትራዊ ስትመድብ በዚህ እጅግ ወሳኝ በሆነ ዘርፍ ማንም ኢትዮጵያዊ ካለመመደቡም ሌላ ኢትዮጵያን የወከሉ የውጭ አገር ዜጎች እንዳቸውም በኢትዮጵያ ጥናት ማለት በሕግ፣በኢትዮጵያ ታሪክና ባሕል እውቀት የተካኑ ነበሩ ለማለት የሚያስደፍሩ አልነበሩም። ይህም ስለኢትዮጵያ የዕውቀት ማነስ በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ እንዴት እንደተንፀባረቀ ወደፊት እናየዋለን። በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ በህግ ፣በታሪክና በሥነ መንግሥት እውቀታቸውና በሥራ ተሞክሮአቸው የታወቁ በትላልቅ ዩኒቨርስቲዎችና ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት የላቀ ሚና የሚጫወቱ ሌላው ዓለም ግልጋሎታቸውን የሚፈልገው ኢትዮጵያውያን በዚህ ትልቅ አገራዊ ጉዳይ እርዳታቸውን እንዲለግሱና በሐራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለምን እንዳልተጠየቀ ኢሕአደግ ብቻ ነው የሚያውቀው። እነዚህ ኢትዮጵያውያን እንደ ፈረንጆቹ ዘጠኝ ሚልዮን ዶላር ወጪ ሳያስወጡ አገራቸውን በዚህ ጉዳይ በነፃ ለማገልገል ፈቃደኛ ይሆኑ እንደነበረ መጠረጠር አይቻልም።

## 6.2. የድርድሩ የጊዜ ሰሌዳ

ሁለቱም አገራት ስምምነቱ በተፈረመ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ዳኞች መርጠው ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ማሳወቅ እንደሚጠበቅባቸው ውሉ ይደነግጋል ። ከዚያም በኋላ በሰላሳ ቀናት ውስጥ የኮሚሽኑ ሊቀ መንበር መመረጥ ሲኖርበት በተከታዩ አርባ አምስት ቀናት ውስጥ ደግሞ እያንዳንዱ አገር አለኝ የሚለውን መብትና ማስረጃዎቹን አሰባስቦ በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ፀሐፊ ያቀርባል።

ኮሚሽኑ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ተሰብስቦ ሥራውን እንዲጀምርና ውሳኔው በስድስት ወራት ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበት በስምምነቱ ተደንግጓል[126]። ይህ ወሳኝና የኢትዮጵያን የባሕር በር የሚዘጋና የኤርትራ ዳር ድንበርን የሚያረጋግጥ ውሳኔ በተፈረመ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ስምምነት ላይ ተደረሰ።

ኮሚሽኑም ይህንን የጊዜ ሰሌዳ ጠብቆና አክብሮ ውሳኔውን ሰጠ። ከመጀመሪያውኑ ኢትዮጵያ ጦርነቱን ባሸነፈች ማግስት ኢሕአዴግ ለድርድር ተጣድፎ አልጀርስ የሄደበት ምክንያት ግልጽ እንዳልነበረ ሁሉ አሁንም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚነካ በብዙ አንፃሩ የወደፊት የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ የሚወስንና የኢትዮጵያን የባህር በር የሚዘጋ እጅግ በጣም ትልቅ አገራዊ ጉዳይ በአምስት ግለሰቦች በሆይ ሆይታ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ የኢሕአዴግ መሪዎች እንዴት ሊስማሙ እንደቻሉ ግር ይላል።

ጦርነቱ ተደምድሞ የህይወት መጥፋትና የንብረት መውደም ከቆመ በኋላ ለድርድር መጣደፍ ለምን እንዳስፈለገ ግልፅ አይደለም። ሆኖም ለዚህ ሁሉ ጥድፊያ በጊዜው ኢሕአዴግ የሰጠው ሊታመን የሚያዳግት ምክንያት የጦርነቱና የድምበር ውዝግቡን ዘግተን ፊታችንን ወደ ልማቱ ማዞር እንፈልጋለን የሚል ነበር።

የድንበሩን ጉዳይ የሚከታተሉ ዳጎስ ያለ ገንዘብ የሚከፈላቸው ጥቂት የውጭ አገር ዜጎችና ጥቂት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረቦች በኮሚሽኑ ሥራ መጠመድ የልማቱን እንቅስቃሴ በምን መልኩ ሊያደናቅፍ እንደሚችል ግልጽ አይደለም።

መንግሥት ጊዜ ወስዶ ሕዝብ እንዲወያይበት ዕድል ሰጥቶ በዓለም አቀፍ ሕግና በወሰን አካለል ተሞክሮ ያላቸው ኢትዮጵያውያንን አማክሮ ቢሆን ኖሮ ምናልባትም የኢትዮጵያን የባህር በር የሚዘጋ አሳዛኝ ስምምነት ተፈራርሞ ኮሚሽኑ የሰጠውን አሳፋሪ ውሳኔ በኢትዮጵያ ላይ ባልተጫነም ነበር። ባድመንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶችን ኮሚሽኑ ለኤርትራ ሲፈርድ ኢሕአዴግ "ሱሪ ባንገት" ሆኖበት የውጭ ጉዳይ ሚኒስተሩ በጠራራ ፀሐይ ባድመ ለኢትዮጵያ ተፈርዶላታል ሲሉ ሕዝቡን አሳሳቱ።

[126] Eritrea-Ethiopia Border Commission Decision, Ibid

በሌሎች አገራት የተከሰቱ የመሬት ይገባኛል ጥያቄዎችና የድምበር ውዝግቦች እልባት ለማግኘት ከአምስትና ስድስት አንዳንዴም ስምንት ዓመታት እንደሚፈጁ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡

በካሜሩንና በናይጄርያ መሃከል የነበረው ይህ ጸሐፊ በህግ አማካሪነት የተሳተፈበት የመሬት ይገባኛል ጥያቄ የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመስጠት ስምንት ዓመታት ሲፈጅ፤ ውሳኔ ከሰጠም በኋላ የተባበሩት መንግስታት፣ የካሜሩንና የናይጄርያ ወኪሎችን ያቀፈ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ኮሚቴው ሕዝቡን አወያይቶ ወሰን ለማካለል ሌላ ሦስት ዓመት አስፈልጕታል፡፡

በጠቅላላው በናይጄርያና በካሜሩን መሃከል የነበረውን የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ለመዝጋት ከአሥር ዓመታት በላይ ፈጅቶአል፡፡ እንዲሁም በቻድና በሊቢያ መሃከል የነበረውን የወሰን ውዝግብ እልባት ለመስጠት ከሦስት ዓመታት በላይ ወስዶአል፡፡

የባህር በርን የሚዘጋ፣ ባድመን፣ኢሮብን፤ጾረናና ከፊል አፋርን ሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶችን ለኤርትራ አሳልፎ የሚሰጥ ውዝግብ በሁለት መቶ ሳማንያ አምስት ቀናት ውስጥ ሲጠናቀቅ በእንዓሩ በበግ ሽያጭ የተነሳ የፍርድ ቤት ክርክር እንኳን መጌቶቱ የማይደገፍም ቢሆን ከአስራ ሁለት ወራት በላይ እንደሚወስድ ይታወቃል፡፡

## 6.3. የድርድሩ ቀጣናና የአደራዳሪው ማንነት

ኢትዮጵያና ኤርትራ ተደራድረው ስምምነቱን የፈረሙት በአልጄርያ ዋና ከተማ በአልጄርስ መሆኑ ይታወሳል፡፡ አልጄርያ የአረብ አገርና የዓረብ ሊግ አባል ስትሆን በኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ ገና ከጥንስሱ እስከ ድምዳሜው ድረስ ለሻቢያና ለጀብሃ የማቴርያልና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ትሰጥ እንደነበረች ለኢሕአዴግ የተሰወረ አልነበረም፡፡ ከዚህ በረከትም ሕወሓትም ሳይቋደስ እንደልቀረ በእርግጠኝነት መናገር ይችላል፡፡



በዚሁ ድርድር ዋናው አጋፋሪ የነበሩት ሚስተር አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ የወቅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር አገራቸውን ለረጅም ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነትና በፕሬዝደንትነት አገልግለዋል፡፡ አልጄርያ ከሻቢያና ከጀብሃ ጋር ለነበራት ግንኙነት ፖሊሲ ቀራጺና (አርኪቴክት) ለኤርትራ መገንጠል ሌት ተቀን የሠሩ ሰው ናቸው፡፡

እኚህ ሰውዬ የአልጄርያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ቢሮ ከአዲስ አበባ እንዲነሳ ሲጥሩ የነበሩ ሲሆን በዚህ ጉዳይ በጊዜው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከነበሩት ክቡር ከተማ ይፍሩ ጋር አንድ ስብሰባ ውስጥ የኃይል ቃል ተለዋውጠው እንደነበር በስብሰባው ተገኝተው የነበሩ አንድ የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ለዚሁ ፀሐፊ ገልጸውለታል፡፡ ስለሆነም ድርድሩ የተካሄደው በገለልተኛ አገር ሳይሆን ከኢትዮጵያ ጋር በጠላትነት የተሠለፈ አገር ውስጥ ነው፡፡ እንዲሁም አደራዳሪው ታማኝና ገለልተኛ ሳይሆኑ እንዲያውም ኢትዮጵያ እንድትፈርስ ይፈልጉ ከነበሩት አረባዊ ባለስልጣናት አንዱ ነበሩ ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያና ኤርትራ ሁለቱም የጥቁር ሕዝብ አገሮችና የጥቁር አፍሪካ አካል መሆናቸው እየታወቀ በአደራዳሪነት ከፍተኛ ተሞክሮ ያላቸው አፍሪካውያን እያሉ ለድርድር ለምን አረብ አልጀርያዊ ተመረጠ? የአረብ መሪዎች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው አስተያየት እየታወቀ አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ ገለልተኛና ታማኝ አደራዳሪ ሊሆኑ እንደማይችሉ ለምን ተዘነጋ?

ምናልባትም አብዱል አዚዝ ቡተፍሊካ ለድርድሩ ሊቀ መንበርነት የተመረጡት በጊዜው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀ መንበር ስለነበሩ ነው የሚል መልስ ይሰጥ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድርድሩም ሆነ ስምምነቱ የግድ አልጄርያ ውስጥ፤ አደራዳሪውም የግድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀ መንበር መሆን ነበረባቸው የሚል ህግ የለም፡፡ ብዙ የአፍሪካ አገራት በመሃከላቸው የሚነሱ ውዝግቦች ከአፍሪካ አንድነት ውጭ ተደራድረው ወይንም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቀርበው ውዝግቦቻቸውን የቋጩባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው፡፡ ምናልባትም ድረድሩ አልጄርስ ከተማ ውስጥ

በመሆኑ አደራዳሪውም አረባዊ ፕሬዝደንት መሆናቸው በስምምነቱ ውጤት ላይ ተጨባጭ አሉታዊ ውጤት ይኑረው አይኑረው በውል ማረጋገጥ አይቻል ይሆናል። ሆኖም ግን ጥርጣሬው ተገቢ ከመሆኑም በላይ አጅግ ቢያንስ ስምምነቱን ገና ከመነሻው የጥርጣሬ ድባብ የለበሰ፤ለኤርትራ የሚያደላ የሚመስል፤ ተአማኒነቱ የሳሳ አድርጉታል።

## 6.4. የድንበር ኮሚሽኑ ዳኞች ማንነት

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረውን የድንበር ውዝግብ መርምረው ፤ የቅኝ ግዛት ውሉችን ቃኝተው አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕጎችንና የአፍሪቃ አንድነት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔን ዋቢ በማድረግ ይግባኝ ሊባልበት የማይቻል ውሳኔ እንዲሰጡ ኤርትራና ኢትዮጵያ ሁለት ሁለት ዳኞች መድበው እነዚህ አራት ዳኞች ሊቀ መንበር እንዲመርጡ ስምምነት ላይ መደረሱ ከለይ ተገልጾአል።

ባለጉዳዩቹ ለዳኞቹ የሰጡአቸው መመሪያዎች በስምምነቱ በአንቀጽ 4 የተቀመጡ ሲሆን፤ እነዚህም ኢትዮጵያ ከጣልያን ጋር የተፈራመቻቸው የ1900 ዓ.ም፤የ1902 ዓ.ም እና የ1908ዓ.ም "ውሎች" አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕጉች እንዲሁም በካይሮ በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት በ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባኤ በቁጥር AHG (Res16(1) የአፍሪካ አገራት ነፃ በወጡበት ወቅት የነበራቸው ድንበር መከበር አለበት የሚለውን መርህ ተከብሮ ወሰኑ እንዲካለል ተስማሙ። ዳኞቹ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ሰብአዊ ርህራሄ፣ ፍትሐዊ አስተያየት አመክንዮ (ex acqua et bono) የመሳሰሉት ከግንዛቤ እንዳያስገቡ መመሪያው አገደ[127]። በዚህም መሠረት ወሰኖቹን ለማካለል ሊረዱ ይችሉ የነበሩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፤ ዓለም አቀፍ ልምዶች፤ የሰለጠኑ አገራት የተቀበሉአቸው የሕግ መርሆች፣ የህግ ጠበብት የደረሱአቸው ጽሁፎችና የተለያዩ የፍርድ ውሳኔዎች መጥቀስ አይቻልም ማለት ነው።

[127] Eritrea-Ethiopia Border Commission Decision, Ibid.



ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የካይሮው የመሪዎች ጠቅላላ ጉባዔ የ1964 ዓ.ም ውሳኔ አግባብነት ያለው ከቅኝ ግዛት ነፃ ለሚወጡት አገራት ሲሆን የኤርትራና የኢትዮጵያ ግንኙነት የቅኝ ገዢነትና ተገዢነት ስላልነበር ይህ መርህ ለኮሚሽኑ ውሳኔ በሌላ ቦታ እንደተብራራው ግብአት ሊሆን አይችልም ነበር።

ከአራቱ ዳኞች ኤርትራ ሚስተር ጃን ፓልሰን (Mr Jan Paulson) እና ዳኛ ስቴፈን ሽዌብል (Judge Stephen Schwebel ) ስትመርጥ ኢትዮጵያ ደግሞ ልዑል ቦላ አዴሱምቦ አጂቦላ (H.E Prince Bola Adesumbo Ajibola) እና ሰር አርተር ዋትሰን (Sir Arthur Watts) መደበች። ጥቂት ቆይቶ ኢትዮጵያ ባልታወቀ ምክንያት የሚስተር ጃን ፓልሰን የኮሚሽኑ አባልነት ስለተቃወመች ሰውየው ከኮሚሽኑ አባልነት እራሳቸውን አገለሉ።[128]። የኮሚሽኑ ዳኞች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።*

1. ፕሮፌሰር ኤሊሁ ሉተርፓክት -ፕሬዚዳንት

   Pro. ElihuLauterpacht President

2. ልዑል ቦላ አዴሱምቦ አጂቦላ

   Prince Bola Adesumbo Ajibola

3. ፕሮፌሰር ማይክል ራይስማን
   Prof.Michael Reisman.
4. ሰር አርተር ዋትስ
   Sir Arthur Watts.
5. ዳኛ ስቴፈን ሽዋብል
   Judge Stephen Schwebel

[128] Ibid

* የዳኞቹ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፤ ቀደም ሲል በኃላፊነት የተመደቡባቸው ሥራዎች ከኢንተርኔት አይቶ ከሙሉቱ ቡድን የትኛው እንደሚሻል መገመት ይቻላል።

ኮሚሽኑ የዳኝነት ሥርዓቱ አጠቃላይ ወጪዎች የዳኞቹ ክፍያንም ጨምሮ የሁለቱ አገራት መንግስታት እንደሚሸፍኑ ሲደነግግ ኮሚሽኑ ከተባበሩት መንግስታት የገንዘብ እርዳታ ከተለገሰው እንዲቀበል በስምምነቱ ተፈቅዶለታል። የተባበሩት መንግስታት የካርታ ክፍል ኃላፊ (U.N.Cartographer) የኮሚሽኑ ፀሃፊ ሆነው እንዲያገለግሉ ሲመደቡ የቋሚ ግልግል ፍርድ ቤት (Permanent Court of Arbitration) ዋና ጸሃፊ ደግሞ በሬጅስትራርነት እንዲያገለግሉ ተመርጠው ኮሚሽኑ ሥራውን ወዲያውኑ ጀመረ።

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በኮሚሽኑ ገለልተኛነትና አወቃቀር ቅሬታቸውን አሰምተዋል። ፕሮፌሰር ተኮላ ወርቅ-ሐጎስ የኮሚሽኑን አወቃቀር ሲነቅፉ የኮሚሽኑ አባላት ቀራ ጠበቆች ሲሆኑ እንደማንኛውም ጠበቃ ገንዘብ የሚከፈላቸው ጉዳዩ እምብዛም የሚያሳስባቸው አይደሉም"[129]ይላሉ። ፕሮፌሰር ተኮላ በመቀጠል ሰብሳቢው ዳኛ ፕሮፌሰር ሉተርፓክት ገለልተኛነታቸውና የግል ታማኝነታቸው አጠራጣሪ ስለሆነ ከኮሚሽኑ አባልነትና ሰብሳቢነት መነሳት እንዳለባቸው በጊዜው አሳስበው ነበር። እንዲሁም ኢትዮጵያና ኤርትራ ያዋቀሩት ኮሚሽን በቋሚ የግልግል ፍርድ ቤት (Permanent Court of Arbitration) ስር ሆኖ የሚሠራ ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት የተቋቋመበት ኮንቬንሽን ኤርትራ እ.ኤ.አ. በ1997ዓ.ም ተቀብላው ስትፈርም ኢትዮጵያ ስላልፈረመች ዳኞቹ ለኤርትራ ያደላሉ በማለት ፕሮፌሰር ተኮላ ስጋታቸውን ገልጸው ነበር[130]።

## 6.5. ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወይስ የግልግል መድረክ

አብዛኞዎች አገራት ከጎረቤቶቻቸው ጋር የድንበር ውዝግብ በሚፈጠርበት ጊዜ ጉዳያቸው የተባበሩት መንግሥታት ዋነኛ

[129] Tecola W. Hagos, Professor "Aklilu Habtewold: In the Footsteps of a great International Law Jurist, Disqualification of Lauterpacht, 30 Oct. 2003

[130] Ibid



የፍትሕ አካል ቋሚ ቢሮው ሄግ ወደ ሆነው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) ወስደው ተከራክረው ዳኝነት ያገኛሉ። ጉዳዩን የሚያዩ 15 ዳኞች በችሎት ተሰይመው ሲሆን እያንዳንዱ ዳኛ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔና በጸጥታው ምክር ቤት የተሾመ ነው። በተጨማሪም የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ደንብ አንቀጽ 31 ፓራግራፍ 2 እና 3 በሚደነግገው መሠረት በችሎቱ ላይ እያንዳንዱ አገር ከዜጎቹ አንዳንድ ተወካይ ጊዜያዊ ዳኛ (Judge ad hoc) የሚሰይም ሲሆን ይህ ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር እኩል ሥልጣን ያለው ነው[131]። የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለመድረስ የጊዜ ገደብ ሳያስቀምጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ጊዜ ወስዶ ውሳኔ ይሰጣል።

ዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለዳኝነቱ መሠረት የሚያደርጋቸው ብዙ ሕግጋት አሉ። እነዚህም፤ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሃገራቱ መሃከል የተደረጉ ውሎች ካሉ፣ ዓለም አቀፍ ልምዶች፣ የሰለጠነው የዓለም ሕዝብ የተቀበላቸው የህግ መርሆዎች፣ ቀደም ሲል የተሰጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች፣ የሕግ ልሂቃን የደረስዋቸው ጽሁፎች፣ ሲሆኑ በተጨማሪም ባለጉዳዩቹ ከተስማሙ- ፍትሕና ርትዕ፣ ሰብአዊ እርህራሄ (ex acquo et bono) ለዳኞቹ ውሳኔ ግብዐት ሊሆኑ ይችላሉ። የእነዚህ ለውሳኔ መሠረት የሚሆኑ የተለያዩ ሕጎች ዳኞች ፍትሕ ላይ እንዲደርሱ ይረዱአቸዋል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የአልጀርሱ ስምምነት ግን በዋነኛነት ለውሳኔው ግብአት ያደረገው የቅኝ ግዛት ውሎች ሲሆኑ በእነዚህ በኢትዮጵያ ላይ በግድ በተጫኑ ውሎች መሠረት ኢትዮጵያ ፍትሕ አገኘታለች ማለት አይቻልም። ለዚህም ነው ውሳኔው ፍጹም ኢፍትሐዊ በመሆኑና ባድመንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች አሳልፎ ለኤርትራ የሚሰጥ ስለሆነ ኢሕአዴግም ይህ ሁኔታ ለሥልጣኑ አደገኛነቱ ስለተረዳ በመርህ ደረጃ ተቀብዬዋለሁ ቢልም ውሳኔውን ሊተገብረውና ከኤርትራ ጋር ምስሶ ወይንም ችካል ለመትከል ፈቃደኛ አልሆነም። ውሳኔውን በመርህ ደረጃ ተቀብዬአለሁ ማለት ደግሞ ትርጉም የሌለው አባባል ነው።

[131] International Court of Justice, Article 31, para. 2 and 3.

የኢትዮጵያና የኤርትራ የወሰን ውዝግብ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቢቀርብ ኖሮ ኢጣልያና ኢትዮጵያ የተፈራረሙአቸው ውሎች ፍርድ ቤቱ ውድቅ እንደሆኑ ተረድቶ ሌሎች ከላይ የተጠቀሱትን ሕግጋት ተጠቅሞ ለኢትዮጵያ የቆመ ተከራካሪ ኖሮ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ቢጠይቅ ኖር ውሳኔው የኢትዮጵያን የባህር በር ሳይዘጋ ይችል ነበር። ይልቁንም ፍርድ ቤቱ ፍትሐዊና ሰብአዊ አስተያየትና አመክንዮን ከግምት ስለሚያስገባ 90 ሚሊዮን ሕዝብ ቀደም ሲል በታሪክ፤ አሁንም ለአርባ ዓመት መግቢያ መውጫ የነበረውን አሰብን ኮሚሽኑ ለኤርትራ ሰጥቶ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ትሁን ብሎ መፍረድ እጅግ አስቸጋሪ ይሆንበት ነበር።

## 6.6. የክርክር ፍሬ ነገሮች

የሁለቱ አገራት ጠበቆችና ዳኞች መደበኛ ችሎት ባልሆነ ስብሰባ የክርክሩ አካሄድ እንዴት መሆን እንዳለበት ከተስማሙ በኋላ እ.አ.አ ከዲሴምበር 10 እስከ 21, 2001 ዓ.ም. የፍርድ ቤት መቀመጫ በሆነው "በሰላም ቤተመንግሥት" (Peace Palace) በሄግ የመጀመርያ የቃል ክርክር ከኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ክአቶ ስዩም መስፍንና ከኤርትራው አቻቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሚስተር አሊ ሳይድ አብደላ ከተደመጠ በኋላ በመከተልም በጠበቆቻቸው መሃከል የቃል ክርክር ተደረገ። እርትራ ባቀረበችው አቤቱታ (Memorial) በአያያዘችው ማስረጃ መሠረት ያመለከተችው ድንበር ይፅደቅልኝ የሚል ሲሆን የኢትዮጵያ ተወካዮች በተደጋጋሚ የ1900፣ 1902፣ 1908 ዓ.ም. ውሎች የሚጠቅሱአቸውን ወሰኖች እንዲፀድቁላቸው ጠየቁ።

የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ የኢትዮጵያ ተወካዮች አንዳቸውም አንድም ጊዜ ትንፍሽ አላሉም። በኢትዮጵያ ተመርጠው የኮሚሽኑ አባል የነበሩት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት አገራቸውን የወከሉና እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት በሶማሌናና በናይጀርያ በጋራ ኮሚሽን የአገራቸውን ቡድን የመሩ ልውል ቦላ አጂ ቦላ በጣም የሚቀልዱ ሰው ሲሆኑ ከዚህ ጸሐፊ በተገናኙ ቁጥር "አሰብን፤ እሰጥሃለሁ" እያሉ ይቀልዱበት ነበር።



ፀሐፊውም የኢትዮጵያን መጻኢ እድል የሚወስን ከባድ ጉዳይ እንደሆነ ልዑሉን ከማስገንዘብ አልቦዘነም።

ኮሚሽኑ በመግቢያ ምዕራፍ ውስጥ የድንበር ውዝግቡን መሠረትና ታሪካዊ አመጣጡ በሚተነትንበት ጊዜ አንዳንድ ስህተቶችን አስፍሮአል። ስለኤርትራ ታሪክ በሚያትትበት ጊዜ አብዛኛው ኤርትራ እ.አ.አ ከ1880 ዓ.ም. በፊት የአቶማንና የግብጽ ይዞታ እንደነበረች ገልጾ ከዚያ በፊት እጅግ ቢያንስ የማያጠራጥረው ደጋው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስለነበራት ግንኙነት አንድም ቃል አላሳረፈም። ጣልያን በመጀመሪያ አሰብን ይዞ ከዚያም ከአሥር ዓመታት በኋላ ወደ ምጽዋ መስፋፋቱን ኮሚሽኑ አልጠቀሰውም።

መግቢያው በመቀጠልም እ.አ.አ. በ1933 ዓ.ም የጣልያን ጦር ከኢትዮጵያ እንደተባረረ ሲገልጽ የኢትዮጵያ አርበኞች ጣልያኖችን በማባረር የተጫወቱት ሚና ከቶም አልተነሳም። እንዲሁም የእንግሊዝ ወታደሮችና የኢትዮጵያ አርበኞች ጣልያኖችን ካባረሩ በኋላ የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ኤርትራና ኢትዮጵያን አጣምሮ ያስተዳድር እንደነበረ ገልጾአል። ሆኖም እንደሚታወቀው ሁሉ እንግሊዞች በአገሪቱ አስተዳደር የተወሰነ ሚና ቢጫወቱም ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያንና ኤርትራን አጣምረው ያስተዳደሩበት ጊዜ የለም። ኮሚሽኑ ኢትዮጵያ እ.አ.አ. በሴፕቴምበር 1952 ዓ.ም የ1900፣ የ1902 እና የ1908 ዓ.ም. ውሎችን መሰረዝዋን ገልጾ፤ በተጨማሪም የኢትዮ-ኤርትራ ፌዴራል ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያ ስለሰረዘችው በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረውን ፌዴሬሽን ኢትዮጵያ አፈረሰችው ይላል። እስከ አሁን ባለው መረጃ ግን ፌዴሬሽኑ የፈረሰው በኢትዮጵያ ሳይሆን በኤርትራ ፓርላማ ሙሉ ድምጽ ነው። እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው ኮሚሽኑ ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ሁለቱም ተዋዋዮች ሰርዘዋቸዋል ካለ በኋላ እንዴት ለውሳኔው መሠረት ሊያደርጋቸው እንዲቻለ ግር ይለል ውሎች ሁለቱም ተዋዋዮች ከሰረዙአቸው በኋላ መልሰው አድሰዋቸዋል የተባለበት ጊዜ የለም።

የኮሚሽኑ ሃተታ በመቀጠል እ.አ.አ. በሜይ 1998 ዓ.ም. በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ግጭት ተፈጠረ በማለት የአፍሪካ የዲፕሎማቶች ኮሚቴ ባድመና አካባቢውን ጐብኝቶ በአጠናቀረው ዘገባ ኤርትራ ወሰን ጥሳ ገብታ ወረራ እንደፈጸመች ቢያረጋግጥም ኮሚሽኑ ይህንን ሐቅ በማድበስበስ በሁለቱ አገሮች መሃከል ግጭት ተፈጠረ በማለት ያልፈዋል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የኮሚሽኑ ግድፈቶች ምናልባት ለመጨረሻም የፍርድ ውሳኔ የማጠቅሙም የሚጐዱም አይደሉም ቢባል እንኳን እጅግ ቢያንስ ኢትዮጵያ በጠበቆችዋ በአግባቡ እስመወከልዋን ይጠቁማሉ። የዚህ ችግር ምንጭ ምናልባትም እነዚህ ስህተቶች እንዲታረሙ የሚያሳስቡ ኢትዮጵያውያን የሕግ ባለሙያዎችና የታሪክ ምሁራን በቡድኑ አለመካተታቸው ነው። እነዚህ ኢትዮጵያን የወከሉ የውጭ አገር ዜጐች እንደዚህ ዓይነት ዝርዝር ሁኔታዎች እንዲያውቁም አይጠበቅባቸውም።

ኮሚሽኑ የቅኝ ግዛት ውሎቹ መሠረታዊ ጉድለት አላቸው ኢትዮጵያና ጣልያን ስለሰረዙአቸው በሥራ ላይ ሊውሉ አይችሉም በማለት ፈንታ በትርጉም ስም የወንዞችና የተራሮችን ስም እያስተካከለ፣ ተራሮችን ወደ አልተባለ ቦታ "እያንፏቀቀ" ወይንም ውሉ ባላስቀመጣቸው ቦታ እያስቀመጠ በመሠረቱ ውሎቹን እንደገና ጽፎአቸዋል በሚያሰኝ መልኩ ዋጋ እንዲኖራቸው አድርጐአል። ለምሳሌ "በለሳ" እና "ሙና" የሚባሉ ወንዞች ውሉ ሲፈረም እንዳልተጠቀሱ እየታወቀ ኮሚሽኑ ግን ለውሳኔው መሠረት አድርጎአቸዋል።

ግልጽ የሆነ የውል አንቀጽ በተዋዋዮቹ የቃል ስምምነት ብቻ ሳይሆን በድርጊትም ሊለወጥ እንደሚችልና ለውጡም ተቀባይነት እንደሚኖረው በግብጽና በእሥራኤል መሃከል በነበረው የድምበር ጉዳይ ተረጋግጦአል። በግብጽና በእሥራኤል መሃከል የተደረገው ውል በሁለቱ ድንበር ላይ ወሰናቸውን ለመለየት ትይዩ የሆኑ ምሰሶዎች ይተከላሉ ይላል። ከእነዚህ ምሰሶዎች አንዱ በትይዩ ሳይሆን ወጣ ብሎ ተተከለ። ግብጽም ሆነች እስራኤል ስህተቱን ለማረም ምንም ሳያደርጉ ቆይቶ ጭቅጭቅ ሲፈጠር ግብፅ ምሰሶው ትይዩ ሆኖ አልተተከለም፣ ስለዚህ ተቀባይነት



አይኖረውም ስትል ተከራከረች። ከመስመር ወጥቶ የተተከለው ምሰሶ አንዱ ወገን እንዲስተካከል ባለመጠየቁ የግልግል ዳኞች ግብፅ እንደተቀበለችው ይቆጠራል በማለት ወሰኑ[132]።

በተመሳሳይ መልኩ ባድመ በ1900 ዓ.ም. ውል መሠረት በኤርትራ ውስጥ ብትሆንም ለብዙ ዘመናት እንደ ኢትዮጵያ ግዛት ተቆጥራ ሕዝቡ ለኢትዮጵያ መንግሥት ቀረጥ ሲከፍል፤ በኢትዮጵያ መንግስት በተሾመ አስተዳዳሪ ሲተዳደር ሕዝቡ ተወካዮችን መርጦ ወደ ኢትዮጵያ ፓርላማ ሲልክ ኢትዮጵያ ግዛቴ ነው በማለት እነዚህን ሁሉ የሉዓላዊነት ተግባራት ስትፈፅም የጣልያን መንግሥትም ሆነ ኤርትራ ከተገነጠለች በኋላ አዲሱ የኤርትራ መንግሥት ተቃውሞ አሰምተው አያውቁም ነበር። ስለሆነም ኤርትራ አሁን ተነስታ ባድመ ሉዐላዊ ግዛቴ ነው ልትል አትችልም።

ሆኖም እነዚህን ሉዓላዊ መብቶች የሚገልጹ ተግባራት ኢትዮጵያ እየፈጸመች ሳለ ጣልያኖችም ሆኑ ኤርትራውያን ነፃ ከወጡ በኋላ ሳይቃወሙ በመቀጠላቸው ኮሚሽኑ ይህንን የሚገልጸው የህግ መርህ ኢፌክቲቪቴ (Effectivite') አልቀበልም በማለት ባድመን ለኤርትራ ሰጠ። አንድ አገር በአንድ ግዛት ላይ ግዛቱ ይገባኛል የሚለው አገር እያወቀ በይዞታው ያለው አገር የሉዓላዊነት ተግባራት ሳያቋርጥ እየፈጸመ ለብዙ ጊዜ የተባለው ግዛት በእጁ ያቆየው ከሆነ ይህ አገር ግዛቱን ለራሱ ሊያደርገው ይችላል የሚል የሕግ መርህ ኢፌክቲቪቴ (Effectivite') ይባላል[133]። የ1900 ዓ.ም የቅኝ ግዛት ውል መስመር ወደ ኤርትራ ቢያጥፈውም እንኳ ከላይ በተለገጸው የሕግ መርህ ምክንያት ባድመ ወደ ኢትዮጵያ መካለል ነበረበት። ሆኖም ኮሚሽኑ ኢፌክቲቪቴ የሚለው የሕግ መርህ ቢቀበልም ኢትዮጵያ ሉዐላዊነትን የሚያመላክቱ ተግባራት በቅጡ አስረድታ አሳማኝ ማስረጃዎችን አላቀረበችም በማለት ባድመን ወደ ኤርትራ አካለለ።

---

[132] See "Arbitral award in the Dispute Concerning certain Boundary Pillars between Arab Republic of Egypt and the State of Israe"l, 80 ilr 226 (27ilm 142 (1421) 1998.
[133] Malcolm Shaw supra note 69 ገ. 140.

ምናልባትም ይህ ግልጽ የሆነ የሕግ መርህ ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ያላካለለው ኮሚሽኑ እንዳለው አንድም በኢትዮጵያ በኩል አሳማኝ ክርክርና በቂ ማስረጃ ባለማቅረቡ ወይንም ዳኞቹ ሆነ ብለው ለኤርትራ አዳሉ ማለት ይቻላል። በተጨማሪም ባድመ የጦርነቱ መንስኤ (Casus Belli) እንዳሆነችና ብዙ ኢትዮጲያውያን የተሰውለት መሆኑ ኮሚሽኑ ከግንዛቤ ሳያገባው አልፎታል።

ለኢሕአዴግ ደግሞ ይህ ውሳኔ እጅግ አሳፋሪና አሸማቃቂ እንደነበር ይባስ ብሎም ኮሚሽኑ ውሳኔውን ባስተላለፈ ማግስት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቀርበው "የጦር ሜዳው ድል በዓለም አቀፍ መድረክም ተደገመ፤ባድመ ለኢትዮጵያ ተፈርዶላታል፤ ባድመ የኢትዮጲያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋ ተረጋገጠ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደስ ይበልህ፤ደስታህን አደባባይ ወጥተህ ግለጽ" ማለታቸው ይታወሳል። ይኸ ደግሞ ሳይውል ሳያድር ፈጽሞ ሐሰት ሆኖ ባድመ ወደ ኤርትራ መታጠፉ ተረጋገጠ፤ ሃፍረቱ እጥፍ ድርብ የሚያደርገው ኢሕአዴግ በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኤርትራን አሸነፍን ከማለት ውጭ የኢትዮጲያ ሉዐላዊ ግዛት አሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍና የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት አንድም ቃል ትንፍሽ አላሉም።

ኢትዮጵያ በጦርነቱ ከአሸነፈች፡ በኋላ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መግለጫ በሰጡባቸው ጊዜያት ሁሉ በኢትዮጵያ በኩል የጦርነቱ ዋናው ዓላማ አቶ ኢሣያስን ሕግና ሥርዓትን ማስተማርና ሕገ ወጥነትን መቀልበስ እንጂ በኤርትራ የተያዙ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛቶችን ማስመለስ ነው ያሉበት አንድም ጊዜ የለም።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አባባል "ወረራውን የመመከት ጉዳይ የመሬት ጉዳይ አይደለም፤ የሕግ የበላይነት የሚያረጋግጥና አጉራ



ዘለልነትን የማስወገድ ጉዳይ ነው"[134] እንጂ በጠላት የተያዙ መሬቶች የማስመለስ ጉዳይ አይደለም።

ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ምሁራን ያቀረቡለትን ሐሳብ አልቀበልም ያለው ኢሕአዴግ በመጨረሻ አልጀርስ ሄዶ አሳሪ ውል ፈርሞ ይግባኝ በሌለበት ግለሰቦች በሰጡት ውሳኔ ለመታሰር ፈቃደኛ መሆኑ ስህተት እንደሆነ የተረዳ ይመስላል። ምክንያቱም ኮሚሽኑ የሰጠው ይግባኝ ሊባልበት የማይቻለው ውሳኔ አክብሬ ፍርዱ የሚያዘውን እፈጽማለሁ ካለ በኋላ ቃሉን በማጠፍ አንድ ጊዜ በውሳኔው ላይ ማብራርያ ይሰጠኝ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጉዳዩ እንደገና በሦስተኛ አካል ይታይልኝ ማለቱ በውሳኔው አለመስማማቱን ይገልጻል። ዓለም በሙሉ በሚያውቀው የፍርድ ውሳኔ ላይ እንዲህ መዋዠቅ አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ኢሕዴግ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም እንደማያውቅ ወይንም ሆነ ብሎ ችላ ብሎት እንደነበር ያመለክታል።

[134] ስብዮታዊ ዴሞክራሲ መጽሄት ግንቦት 1995

# ምዕራፍ 7

## 7. በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ኢትዮጵያን የወከለው ቡድን ለኤርትራ ያስረከባቸው የኢትዮጵያ መብቶች

በአልጀርስ የድምበር ኮሚሽን ክርክር ወቅት የኢትዮጵያ ተወካዮች ወይ ለክርክሩ ትኩረት ካለመስጠት ወይንም ደግሞ ሆነ ብሎ ኤርትራን ለመጥቀም በመፈለግ ወይንም በቀጣሪዎቻቸው በኢሕአዴግ ትዕዛዝ ኢትዮጵያን በግልጽ የሚጐዱ ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ላይ እንዲወሰኑ የጠየቁባቸው ሁኔታዎች አሉ። እነዚህ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች አንዳንድ ክርክር የተነሳባቸው ቦታዎች ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል በሚፈልጉበት ጊዜ እንኳን ሽንጣቸውን ገትረው ከዳኞቹ ጋር ክርክር ገጥመው አንዳንድ ቀበሌዎች ወደ ኤርትራ እንዲታጠፉ አድርገዋል።

### 7.1. በምስራቅ በኩል

#### ጠረፍ "Coast" ምን ማለት ነው?

የድምበር ኮሚሽኑ በተሰረዙና በሞቱ የቅኝ ግዛት ውሎች ላይ በመመሥረት የኢትዮጵያ የምስራቅ ወሰን ከጠረፍ ወደ ውስጥ በሚካለልበት ክርክር ጊዜ "ጠረፍ" (Coast) ከየት ይጀምራል የሚል ጥያቄ አንስቶ ነበር[135]።

[135] Eritrea-Ethiopia Boundary Commission Decision, Supra note 124 p.122.



ከ1908 ዓ.ም ውል በፊት አጼ ምኒልክ ከጣልያኑ ተወካይ ከሻለቃ ኔራዚኒ ጋር በተደራደሩበት ወቅት ወሰኑ ከጠረፍ ወደ ኢትዮጵያ ማለት ወደ ምዕራብ 60 ኪሎ ሜትር እንዲገባ ለሻለቃው ሃሳብ አቅርበውለት ይህ 60 ኪሎ ሜትር በሁለቱ ተዋዋዮች መካከል መግባቢያ ሆኖ ከ1897 ውሉ እስከ ተፈረመበት 1908 ዓ.ም ድረስ ወሰን ሆኖ አገልግሎአል[136]። በዚህ ውል ድምበሩ "ከጠረፉ" ይጀምራል ከማለት ሌላ ጠረፍ ከየት እንደሚጀምር "ጠረፍ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተገለፀም ነበር።

የዚህ የ1908 ውል ስለጠረፍ የሚያወሳው አንቀፅ 1 የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች አንስተውት "ጠረፍ" ምን ማለት እንደሆነ ከየትስ እንደሚጀምር እንዲያስረዱ ባለጉዳዮቹን ጠየቁ። የድምበር ኮሚሽኑ ጥያቄውን በማብራራት "ጠረፍ" የሚለው የሚጀምረው ከደሴቶቹ ነው ወይስ ባሆሩ አልቆ በቀጣይነት ካለው መሬት ነው? የሚል ጥያቄ ለባለጉዳዮቹ አቀረቡላቸው።

የኤርትራ ተወካዮች የኢትዮጵያ ድንበር ከባህሩ ጠርዝ 60 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ይገባል የሚለው፤ መሬቱ ከውሃ ጋር ከሚገጣጠምበት በቀጣይነት ወደ ውስጥ ማለት ወደ ምዕራብ ተለክቶ ነው እንጂ ከደሴቶች አይጀምርም ሲሉ ተከራከሩ። የኢትዮጵያ ተወካዮች በውሉ 60 ኪሎ ሜትር የተባለው የሚነሳው ከደሴቶቹ ጀምሮ ነው ብሎ ከመከራከር ፈንታ ከደሴቶቹ ሳይሆን ባህሩ ከመሬቱ ከሚገጣጠምበት ጀምሮ ነው በማለት ኤርትራ ከጠየቀችው ጋር በመስማማታቸው ኮሚሽኑ ወሰኑ የሚጀምረው ከደሴቶቹ ሳይሆን መሬቱ በቀጣይነት ከሚጀምርበት ነው በማለት በመሬቱና በደሴቶቹ መሃከል ያለውን እርቀት ለኤርትራ ሰጠ[137]።

ስለሆነም ከደሴቶቹ ጀምሮ ወደ ምዕራብ ቢለካ የኢትዮጵያ ድምበር እርቀቱ ከ60 ኪሎ ሜትር ትንሽ ያንሳል። አሁን በኤርትራ እጅ የወደቁ 160 ደሴቶች በቀይ ባህር ሲገኙ አንዳንዶቹ ከመሬቱ እርቀው የሚገኙ ናቸው።

[136] ዶ/ር ተወልደ ትኩእ ዝኒ ከማሁ 31 ገጽ 59

[137] Eritrea-Ethiopia Border Commission, supra, 124 p.123.

በኮሚሽኑ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች የወሰዱት አቋም ከቶም ልክ ሊሆን እንደማይችል የህግ ሀሁ የቆጠረ ሰው ሊያውቀው የሚችል ነበር። ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር በ1908 ዓ.ም የፈረመችው ውልና ሌሎችም ኤርትራንና በአቅራቢያዋ የሚገኙት ደሴቶችን ቅኝ ግዛት ሲያደርጉ መላውን ኤርትራ ማለት ደሴቶችንም ጨምሮ ነበር እንጂ ኤርትራን በከፊል አልነበረም። የኢትዮጵያ ተወካዮች "ጠረፍ" ማለት ምን ማለት ነው ከየትስ ይጀምራል ለሚለው ጥያቄ መልሱ እ.ኤ.አ. በ1982 ዓ.ም በወጣው የባህር በር ስምምነት (1982 Maritine Convention) በግልፅ ስለተቀመጠ ይህንን ፈልጎ ማግኘት አዳጋች አልነበረም። ይኸ ስምምነት አንድ ከባህር ጋር የሚዋሰን አገር ግዛቱ ከመሬቱ 12 ኖቲካ ማይልስ (Nautical miles) ወደ ባህሩ ዘልቆ እንደሚገባ ይገልፃል[138]። አሰብን የሚያካልለው ቀይ ባህር ከሚዶ ካሉት አረብ አገሮች በተለይም ከየመን ጋር የሚጋሩት በመሆኑ ባህሩ ለሁለት ተከፍሎ ግማሹ ወደ አፋር ግማሹ ወደ የመን መካለል ይኖርበታል። "ጠረፍ" የሚለው ከመሬቱ መጀመርያ ከሆነ ኤርትራ ከሚገባት ውጭ ቢያንስ ወደ ምዕራብ 12 ኪሎ ሜትር የኢትዮጵያን መሬት ይዛለች ማለት ነው።

"ጠረፍ" "coast" ማለት በደሴቶችና በመሬቱ መሃከል ያለው እርቀት ደሴቶችንም ይጨምራል። አጼ ሚኒልክ ተስማምተውበታል የተባለው 60 ኪሎሜትርም መለካት ያለበት ከደሴቶቹ ተነስቶ መሆን ይገባዋል በማለት ተከራክረው ኮሚሽኑ ውሳኔ ይሰጥበታል እንጂ ከኮሚሽኑ ውሳኔ በፊት የኢትዮጵያ ጠበቆች ቀድመው የኤርትራን ጥያቄ መቀበላቸው ማንን ይወክሉ ነበር የሚል ጥርጣሬ ያነሳል። አንድ ጠበቃ የወከለውን አካል ጥቅም ለማስጠበቅ ክርክሩን አቅርቦ ዳኝነቱን ለተመደቡት ዳኞች ይተዋል እንጂ እራሱ ዳኛ ሆኖ የተቃራኒውን ጥቅም አያራምድም። እንዲህ አይነቱ አሠራር ከጥብቅና ተግባር ውጪ ሲሆን ምናልባትም

138 Hand book on the Delimitation of Maritime Boundaries, Division for Ocean Affairs and the Law of the Sea, office of Legal affairs, united nations, Newark, (2000) P.3



ጠበቃ ሆኖ ከመሠራት ሲያጣግድም የሚችል የስነ-ምግባር ጥሰትም ሊሆን ይችላል።

የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች "ጠረፍ" "coast" የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆን መጠየቃቸው እራሱ ኤርትራን ለመጥቀም ተብሎ የተነሳ ጥያቄ ይመስላል። ዳኞች "ጠረፍ" "Coast" የሚለው ቃል ከደሴቶች ተነስቶ መለካት እንዳለበት ጠንቅቀው ያውቃሉ። አንድ ባህር የሚያዋስን አገር ግዛቱ እጅግ ቢያንስ 12 ኖቲካል ማይልስ ወደ ባህሩ ዘልቆ እንደሚገባ ወይንም ሁለቱ አገራት ትይዩ ከሆኑ ደግሞ በመሃከላቸው ያለው እርቀት ከ24 ኖቲካ ማይልስ ካነሰ ባህሩን እኩል እንደሚካፈሉት ዳኞች ሊያጡት አይችሉም።

## 7.2. ከአሰብ በስተ ምዕራብ ያለው ቡሬ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን ሊሆን እንዴት ቻለ ?

ቡሬ በአሰብ መስመር የመንገድ ትራፊክ መቆጣጠሪያ መሆኑ ይታወቃል። ቡሬ ከባህሩ ጠረፍ ከ60 ኪሎ ሜትር ይበልጣል። በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ወቅት የኤርትራ ተወካዮች ቡሬ የኢትዮጵያና የኤርትራ ድምበር እንዲሆን ኢሕአዴግና ሻቢያ እንደተስማሙ ማስረጃ አቀረቡ።

ማስረጃውም "ከአዲስ አበባ እስከ መተሓለፊያ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ጥናት" ይላል። በዚህም ጥናት ላይ ተስማምተውበት ኢሕአዴግና ሻቢያ ተስማተውበት እ.ኤ.አ.በ1994 ፈርመውበታል።

ጥናቱ የትራንስፖርት የቁጥጥር ጣቢያዎችን ሲዘረዝር "ቡሬ የኢትዮጵያ ወሰን" "ቡሬ የኤርትራ ወሰን" ብሎ አስቀምጦታል። ስለሆነም ኮሚሽኑ ቡሬ የሁለቱም አገራት የወሰን ከተማ ነው ሲል ወሰነ። ይህም ማለት በቡሬ በኩል የጣልያኖች ውል ከመደበው ከ60 ኪሎ ሜትር በላይ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቃ ገብታለች ማለት ነው።

የድምበር ኮሚሽኑ ጥናቱ ለድንበር መካለስ ውሳኔ መሠረት ከማድረግ ፊንታ የጣልያን 60 ኪሎ ሜትር ስምምነት ማጽደቅ ነበረበት። አንድ ጥናት ሁለት ወገኖች በውል የተስማሙበትን ጉዳይ ሊሽር በፍጹም አይችልም። የድምበር ኮሚሽኑ ይህ ጥናት ተብየው ኢትዮጵያና ኤርትራ ሁለቱም ባለጉዳዮች የተስማሙበት አዲስ ውል ነው የሚል አቋም ነው የያዘው።

## 7.3. ምዕራብ ትግራይ

በምዕራብ በኩልም የተደረገው መካለል ኤርትራ ያነሳቻቸው አንዳንድ የይገባኛል ጥያቄዎች ኢትዮጵያ የበኩልዋን ክርክር አቅርባ ኮሚሽኑ ውሳኔ እንዲሰጥበት ከመተው ፊንታ የጥብቅና ሥርዓት በማይፈቅደው መንገድ የኢትዮጵያ ጠበቆች የኤርትራን ጥያቄ አምነው ተቀበሉ። በኮሚሽኑ ችሎት የኢትዮጵያ ወኪሎች የተጠቀሙችባቸው ቃላት እነዚህ ነበሩ።

"ፎርት ካርዶና፣ ሞኖክሲቶ፣ ጉና ጉና እና ጸረና የማያጠራጥሩ የኤርትራ ግዛቶች ናቸው።" ሞኖክሲቶና ጉና ጉናን የውሉ መስመር ኤርትራ ውስጥ ሲያደርጋቸው ለኮሚሽኑ የቀረቡት ማስረጃዎች ግን ጸረናና ፎርት ካርዶናን የውሉ መስመር ኤርትራ ውስጥ አያደርጋቸውም።

በተለይ ጸረናን በተመለከተ ኢትዮጵያ ለኮሚሽኑ ባቀረበችው ጽሑፍ ጸረና የኤርትራ ግዛት ነች በማለት ወደ ኤርትራ እንዲካላል የኢትዮጵያ ወኪሎች ኮሚሽኑን ጠየቁ።

ኮሚሽኑ ጸረና የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑን ተረድቶ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካላል በሚወስንበት ጊዜ የኢትዮጵያ ጠበቆች ጸረና የኤርትራ ሉዐላዊ ግዛት ነው ብለው ተከራከሩ።

ስለሆነም ኮሚሽኑ ይህንን ጸረና ወደ ኤርትራ ይታጠቃ የሚለው የኢትዮጵያ ጥያቄ ሊዘልለው ስላልቻለ ጸረናን ወደ ኤርትራ በማካለል የድምበሩ መስመር መለወጥ አስፈላጊ ሆኖአል ሲል ኮሚሽኑ ደመደመ። የድምበር ኮሚሽኑ ጸረናን ወደ ኤርትራ ለማካለል ሲል የድምበር መስመሩ ሃደቱን ቀይሮ ጸረናን እንዲሸፍን እንዴት እንዳጠረው ቀጥሎ ያለው ማፕ በግልጽ ያሳያል።

Map 11



ኮሚሽኑ ውሉ የሚደነግገውን ግልጽ የድምበር መስመር አክብሮ ውሳኔ መስጠት እንጂ፤ ክርክር ያልተነሳበትን ጉዳይ የድምበር ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት ማስተናገድ አይገባውም ነበር። ኮሚሽኑ ምንም ያላከራከረው ጾረና ወደ ኢትዮጵያ መካለል ይገባው ነበር ወይንም አይገባውም ብሎ መጠየቅ ተገቢ አልነበረም። አንድ ዳኛ አንድን የውል አንቀጽ ወይንም ክፍል አሻሚ ከሆነበት ወይንም ግልጽ ካልሆነለት የሁለቱም ወገኖች ጠበቆችን የየበኩላቸው አቋም ጠይቆ ዳኛው ከብዙ ዓይነት የትርጉም ስልቶች በአንዱ ተጠቅሞ አንቀጹን ሊተረጉም ይችላል። ይህ ጾረና ወደ ኢትዮጵያ የሚያጥፈው የውሉ አንቀጽ ግልጽ ስለነበር ውሉ የሚለውን በቀጥታ ማስፈፀም እንጂ መተርጉም ወይንም ሌላ ጥያቄ ማስተናገድ አልነበረምበትም። ኢትዮጵያ ብትፋልግ ከኮሚሽኑ ውጭ ጾረናን ለኤርትር ትስጥ እንጂ በዚህ ግልፅ በሆነ ነገር ኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ጠበቆች ጥያቄ ማድመጥ አስፋላጊ አልነበረም። በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ተወካዮች መቀሌንም ለኤርትር ይስጥ ብለው ቢጠይቁ ኮሚሽኑ ሊቀበል ነው ማለት ነው? እንዲያውም የኢትዮጵያ ተወካዮች የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ለኤርትራ ይስጥ በሚሉበት ጊዜ ድርጊቱ የጥብቅናን ሥነ-ምግባር የሚጥስ ተግባር እንደመሆኑ መጠን ኮሚሽኑ ጉዳዩ መመርምር ይገባው ነበር። ምክንያቱም አንድ ጠበቃ አላፊነቱ የቀጠረው የደምበኛውን ጥቅሙን ወይንም መብቱን ማስከበር እንጂ ለባላጋራው እንዲሰጥበት አይደለም።

“ይህ የድምበር ኮሚሽን የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑ” ያወቀላትን የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት ለሌላ አገር አሳልፎ መስጠት ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች ውሳኔ ብቻ ሊሆን አይችልም። ጠበቆቹን የቀጠረው የኢሕአዴግ መንግሥት መመርያ ተከትለው መሆን አለበት። ይህ ጾርና በስጦታ ለኤርትራ የተሰጠው በጠበቆቹ ውሳኔ ከሆነ ኢትዮጵያ ጠበቆችዋን ማባረርና ጉዳዩን ለኮሚሽኑ ማቅረብና ማስመርመር ይገባት ነበር። በኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት ትዕዛዝም ከሆነ ይህንን የኢትዮጵያ

ሉዐላዊ ግዛትን አሳልፎ ለሌላ መስጠት በሕግም ሊያስጠይቅ ይችላል።

ይህንን የመሰለ ከጥብቅና ሙያ ስነ ምግባር ውጭ የሆነ ድርጊት ጠበቆች በራሳቸው ተነሳሽነት ያደርጉታል ለማለት ይቸግራል። ጉዳዩ ከፍተኛ ኃላፊነት የሚያስከትል ስለሆነ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት ለጠላት አሳልፎ ማን እንደሰጠ ተጣርቶ ውሳኔ በሰጠው ሰው ላይ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ የግድ ይላል። ከእነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች ሌሎችም ኢትዮጵያን የጎዱ ስህተቶች እንዳሉ ማስታወስ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ከዘጠኝ ሚልዮን ዶላር[139] በላይ ክፍላ የቀጠረቻቸው ጠበቆች ጾረናን ከሚሽኑ ከወሰነው በተቃራኒ ለኤርትራ አሳልፈው ሲሰጡ "በቆረጥከው ዱላ ብትመታ፣ በመረጥከው ዳኛ ብትረታ" መገረም የለብህም የሚለው የአበው አባባል ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ ደረሰ።

## 7.4. የደብር ቢዘን ገዳም

በምጽዋ መንገድ ከአሥመራ ትንሽ ወጣ ብላ የምትገኝ ጥንታዊት ገዳም ነች። ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር የቆየ ትስስር ስላላት እ.አ.አ ግንቦት 2ቀን በ1889 ዓ.ም በኢትዮጵያና በጣልያን በተፈረመው በውጫሌው ውል በአንቀጽ 4 ገዳሚቱ እስከ ምጽዋ ከሚደርሰው እርስተ ጉልትዋ ጋር የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ሆና እንደትቆይ ስምምነት ተደርሶ ነበር። በተጨማሪም ደብረ ቢዘን ገዳምን በምንም ዓይነት መልኩ ኢትዮጵያ ለወታደሪዊ ጥቅም እንዳታውለው ውሉ ይከለክላል።

የአልጀርስ ስምምነትም ሆነ የድምበር ከሚሽኑ ስለዚህ ስምምነት ምንም ያሉት ነገር የለም። በድምበር ኮሚሽኑ ፊት

[139] ኢትዮጵያ ለድምበር ኮሚሽኑ ሥራ ዘጠኝ ሚልዮን ዶለር መክፈልዋን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ይገልጻሉ። ኢትዮጵያ የባህር በርዋን አሰብን ለኤርትራ ለመስጠት ጾረናና ባድመንና ሌሎችም ግዛቶችዋን በፍርድ ለኤርትራ ለማስረከብ ዘጠኝ ሚልዮን ዶላር ወጪ አስወጥቶአታል



ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆችም ስለደብረ ቢዘን ምንም ያመለከቱት ነገር አልነበረም።

በእርግጥም ኤርትራ ውስጥ የምትገኝ አንዲት ገዳም ኤርትራ ነፃነትዋ ስትጐናጸፍ ገዳምዋ የኢትዮጵያ ግዛት ሆና የምትቆይበት መንገድ የለም። ሆኖም ግን አማራጩ በገዳሙ ምትክ ኤርትራና ኢትዮጵያ ተደራድረው ለኢትዮጵያ ማካካሻ መስጠት ፍትሐዊ አካሄድ በሆነ ነበር። አለብ ቀደም ቢል የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋ ቢረጋገጥም ለሰላምንና ለመልካም ጉርብትና ሲባል ለደብር ቢዘን ማካካሻ ብትሆን ለሁለቱም አገር ሰላም ጥሩ መፍትሔ ነበር ሆኖም በተደጋጋሚ እንደታየው ኢትዮጵያን የሚወክሉ ጠበቆች አሁንም የኢትዮጵያ መብት አሳልፈው ሰጥተዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የአልጀርስ ስምምነትም ሆነ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ እ.አ.አ በ1900 በተፈረመው ውል የተደነገገው ጣልያን በማንኛውም ምክንያት ኤርትራን ለቅቃ ብትወጣ መላዋ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ትታጠፋለች የሚለውን አንቀጽ የኢትዮጵያ ጠበቆች ሳያነሱት በዝምታ አልፈውታል። ይህም ማለት የድምበር ኮሚሽኑም ሆነ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች ሆነ ብለው ኢትዮጵያን የሚጎዱ አንቀጾችን ነቅሰው አውጥተው ተፈጻሚ ሲያደርጉ ለኢትዮጵያ አንዳንድ መብቶችን የሚያጎናጽፉ አንቀጾችን ደግሞ ሆነ ብለው ሲዘልሉአቸው በተደጋጋሚ ተስተውሉአል።

## 7.5. የህግ አመራረጥ

ከላይ እንደተገለጸው የድምበር ኮሚሽኑ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸው ጣልያንና ኢትዮጵ "የተስማሙባቸው" የቅኝ ግዛት ውሎች ሆነው በተጨማሪም አግባብነት ያላቸው የዓለም አቀፍ ሕጎችንና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ እንዲሆኑ የኢትዮጵያ ተወካዮች መስማማታቸው ይታወሳል። የኢትዮጵያ ተወካዮች ጣልያን ለጥቅሟ ስትል በኢትዮጵያ ላይ በግድ የጫነቻቸው ውሎች ለኢትዮጵያ

ይጠቅማሉ ብለው በዚህ መስማማት "አይናችሁን ጨፍኑ እናሞኛችሁ" ዓይነት ነው። ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች እነዚህ የቅኝ ግዛት ውሎች ደንበኞቻቸውን ኢትዮጵያ የሚጎዱ መሆናቸው ለደንበኞቻቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት ማስታወቅ የጥብቅና ተግባር የሚጠይቀው ሃለፊነት ነበር። ይህንን ካላስታወቁ የጥብቅና ሥነ ምግባር ጥሰዋል።

ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በእነዚህ በተሻሩ ውሎች ይመርኮዝ ከማለት ይልቅ የዓለም ሕብረተሰብ የሚጠቀምባቸውና ከዚህ በፊትም የተጠቀመባቸው የተፈተኑ የዓለም አቀፍ ህግጋት፤ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች፤ የታወቁ ምሁራን ትንታኔዎች ወዘተ.....ፍትሕን ለማስፈን ይበልጥ ይጠቅሙ እንደነበር መገንዘብ ይገባቸው ነበር። ውሳኔዎቹ በቅኝ ግዛት ውሎች ይመሥረቱ ብሎ ክርክር ማቅረብ ሌላውን ወገን ለመጥቀም ታስቦ ካልሆነ በስተቀር እንዴት እንዲህ ዓይነት በኢትዮጵያ ላይ በግድ የተጫኑ ውሎች ደንበኞችንን ይጠቅማሉ፤ፍትሕ ያሰፍናሉ ተብሎ ይታሰባል? ደንበኞቻው ኢሕአዴግም የኮሚሽኑ ውሳኔ እነዚሁ በፈረሱ የቅኝ ግዛት ውሎች መመሥረት አለበት ብሎ ድርቅ ካለም ጠበቆቹ ሥራውን ትተው መሰናበት ይገባቸው ነበር እንጂ ሕገ ወጥ በሆኑ "ውሎች" ተመርኩዘው በመከራከር የሕዝብን መብቶች ማስረከብ አይገባቸውም ነበር።

## 7.6. ሁለት ወደ አይሆንም

የድምበር ኮሚሽኑ ለውሳኔው መሠረት ካደረጋቸው ሕጎች በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባኤ በካይሮ በ1964 ዓ.ም በውሳኔ ቁ AHG/Res 161(1) የተደነገገው አንዱ ነበር። ይህም ውሳኔ ቅኝ ግዛት የነበሩ አገራት ነፃ በሚወጡበት ጊዜ በቅኝ ግዛት ወቅት የነበረውን ወሰን (ድንበር) ማክበር እንዳለባቸው ይደነግጋል[140]።

[140] የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ቁ ውሳኔ AHG/Res 16(1)



በመጀመሪያ ደረጃ ኤርትራ ከቅኝ ግዛት ነጻ የወጣችው በ1952 ዓ.ም በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ስትቀላቀል ሲሆን ኤርትራ ከኢትዮጵያ በተገነጠለች ጊዜ በሁለቱ አገራት የነበረው ግንኙነት የቅኝ ገዢና ተገዢ አልነበረም። ስለሆነም ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ወሰን መካለል አግብባነት የለውም።

ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባኤ ውሳኔ ከቅኝ ግዛት ነፃ ለሚወጡትና በተጨማሪም ለሌሎች በመገንጠልም ይሁን ወይንም በሌላ መንገድ ነፃነት ለሚጎናጸፉ አገራት አግባብነት አለው ከተባለ ኤርትራ ነፃ ስትወጣ የነበራትን ግዛት ይዛ ትሄዳለች እንጂ ነፃ በወጣች ጊዜ በግዛትዋ ውስጥ ያልነበረውን አሰብን ልትወስድ አትችልም። ይህ እጅግም አስቸጋሪ ያልሆነ ግልፅ የህግ ነጥብ የኢትጵያ ተወካዮች እንዴት ዘነጉት? ጉዳዩ የዝንጋታ ሳይሆን የሌላ ይመስላል።

ስለሆነም ኤርትራውያን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበርን ካሉ ነፃ ሲወጡ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ትተው የያዙትን መሬት ብቻ ይዘው ይገነጠሳሉ። የለም የኢትዮጵያ አካል እንጂ ቅኝ ግዛት አልነበረንም ካሉም ደግሞ ሊገነጠሉ የሚችሉት አንዳንድ ግዴታዎችን ካሟሉ በኋላ ብቻ ነበር።

## 7.8. "በያዝከው እርጋ" (UTI POSSIDETIS JURIS)

በቅኝ ግዛት ስር የነበረ አንድ አገር ነፃ በሚወጣበት ጊዜ ወሰኑ የትኛው መሆን አለበት የሚለው ጥያቄ በመጀመርያ የተነሳው በ19ኛው ምዕተ ዓመት የስፔን ቅኝ ግዛት የነበሩ የላቲን አሜሪካ አገራት ነፃ በወጡበት ጊዜ ነው። እነዚህ የቀድሞ የስፔን ቅኝ ግዛቶች ነፃ ሲወጡ ወሰናቸው ቅኝ ገዢዋ ስፔን የመሰረተቻቸው ድንበሮች መሆን አለበት ተብሎ "በያዝከው እርጋ" UTI POSSEDETIS የሚል አንድ የሕግ መርህ ተፈጠረ። ይህ መርህ ይበልጥ ጉልቶ የወጣው የአፍሪካ አገራት ከቅኝ ግዛትነት ነፃ ሲወጡ ወሰናቸው የትኛው መሆን አለበት ለሚለው ጥያቄ፤ በ1964 ዓ.ም. በካይሮ, ተሰብስቦ የነበረው የአፍሪካ አንድነት የመሪዎች ጉባዔ ይህንኑ መርህ ተቀብሎ አንድ አገር

ነፃ በሚወጣበት ጊዜ ቅኝ ገዢዎች የመሠረቱት አንድ ቋሚ ወሰን ስላለው ያ ወሰን ሳይለወጥ የአዲሲቱ አገር ድምበር እንዲሆን ተወሰነ::[141]

ይህንኑ ውሳኔ በማጽደቅ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል አገራት ነፃ የቅኝ ግዛት ወሰኖችን ላለመለወጥ ቃል ገቡ። ይህንን መርህ በመጣስ በቤልጂያን ኮንጐ፣ በናይጄርያና በሱዳን ከግዛቶቻቸው ውስጥ አንዳንዶቹ ክፍሎች የቅኝ ግዛት ወሰኖችን በመለወጥ ሲገነጠሉ በሞከሩ ጊዜ በአፍሪካ አገራት ተቃውሞ ገጠማቸው[142]::

ይህ "ባያዝከው እርጋ" የሚለው የሕግ መርህ በሂደት ተስፋፍቶ የሚመለከተው ከቅኝ ግዛት ነፃ የወጡ አገሮች ብቻ ሳይሆን በማንኛውም መንገድ ለምሳሌ በአገሪቱ መከፋፈል ተፈጥሮ ነፃ ለሚወጡ አገራት አግባብነት እንዲኖረው ሆኖአል። ነፃ የወጣው አገር ወሰኑ በውስጥ አስተዳደር የተመሠረተ ወይንም የቅኝ ግዛት ወሰን ሊሆን ይችላል። አዲሱ አገር ነፃ በሚወጣበት ወይንም በሚገነጠልበት ጊዜ ያ የአስተዳደር ወይንም የቅኝ ግዛት ወሰን በዚህ የህግ መርህ መሠረት የጸና ይሆናል ማለት ነው።

ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን እንዲችል የብሔረሰቦች እኩልነት ለማረጋገጥ የአካባቢው የራስ በራስ አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ የልማት ተግባሮችን ለማከናወን የአካባቢው ብሔረሰቦች ቋንቋ እንዲደብሩ እንዲስፋፋና በጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሲባል የትግራይ፣የአሰብ፣የድሬዳዋና የኦጋዴን ክፍለ ግዛቶች በአዋጅ ቁ. 16/1980 ዓ.ም ራስ ገዝ ተብለው ተቋቋሙ። እነዚህ ክልሎች የራሳቸው ወሰን ያላቸው[143]:: የኢትዮጵያ የውስጥ አስተዳደር ወሰን መለወጥ ሉዓላዊ መብቷ ሲሆን እነዚህ ራስ ገዝ አስተዳደሮች ወይንም ክልሎች የራሳቸው ወሰን ከመሠረቱ ከአሥር ዓመታት በላይ ሲሆን እነዚህ ወሰኖች የረጉ መሬት የጨበጡ ሆነው ነበር::

ኤርትራ ነፃነትዋን በተጐናጸፈች ጊዜ ይህ ጸንቶ የቆየው ኤርትራንና አሰብን የሚለየው የአስተዳደር ወሰን ጥሳ በጊዜው የኤርትራ አካል ያልነበረችውን አሰብን ስትይዝ ክልካይ

[141] ዝኒ ከማሁ.

[142] Malcolm Shaw, Supra note 69. P. 447.

[143] የትግራይ፣የአሰብ፣ የድሬዳዋና የኦጋዴን ራስ ገዝ አካባቢዎች ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ <u>አዋጅ ቁ.16/1980</u> ዓ.ም.



አልነበረባትም ። በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ያለውና የነበረው የወሰኑ ሁኔታ በሶቭየት ሕብረት በዩጐዝላቪያና በቼኮስሎቫቢያ ከተከሰተው ጋር ይመሳሰላል። ሶቭየት ሕብረት ፈርሳ የህብረቱ አባል የነበሩ አገራት ተከፋፍለው ነፃ በወጡበት ጊዜ ቀደም ሲል ሶቪየት ህብረት መስርቶት የነበረው ወሰን ተከትለው ነፃ ወጡ። እንዲሁም ዮጐዝላቪያ ስትከፋፈል ቀደም ሲል በዮጐዝላቭ አስተዳደር የተመሠረቱ ድምበሮች እንደጸኑ ሆነው ሰርቢያ፣ ሽርሲጐቪ፣ ክሮዌሽያና ሞንቲኔግሮ ሲለያዩ የቀድሞውን ድምበሮቻቸው አልለወጡም። ሞንቲኔግሮ ቀደም ሲል ግዛትዋ ያልነበረውን ክፍል ከሰርቢያም ሆነ ከሌሎቹ አልጠየቀችም::

በአጠቃላይ ዩጐዝላቪያ በመባል ይታወቁ የነበሩ አያሌ አገራት ወይንም ክልሎች ነፃ በወጡበት ጊዜ የነበረውን ድምበር ጥሰው የሌላውን ግዛት የያዙበት ሁኔታ አልነበረም። ዩጐዝላቪያ በተበታተኑቹ ጊዜ የግዛቶቹ ወይንም የክልለሉቹ ወሰን እንዲያካልል የተቋቋመው የግልግል ኮሚሽን (Arbitration Commission) "ሁኔታ ምንም ይሁን ምንም የራስን ዕድል በራስ መወሰን በጊዜው የነበሩ ወሰኖችን ሊለውጥ አይችልም::"[144] ብሎ ውሳኔ ሰጠ። ይህ መርህ በጊዜው ያለው ድምበር እንዴት ተፈጠረ ሳይባል የተረጋጋውንና መሬት ላይ ያለውን ማጽደቅ እንደሚገባ የዓለም አቀፍ ሕግ ያስገነዝባል። ስለዚህ ኤርትራ ከአሰብ ጋር የነበራትን ወሰን ጥሳ አሰብን ስትይዝ በሁለት መንገዶች የዓለም አቀፍ ሕግን ጥሳለች ማለት ነው።

ሕወሓትና ሻቢያ በዚህ ጉዳይ አስተሳሰባቸው የጨቅላ ቢሆንም ኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት በመሆንዋ ነፃ መውጣት ይገባታል በማለት ለዚህም እኩይ ዓላማቸው ስኬታማነት ብዙ ዋጋ ከፍለው ኤርትራ ነፃ ወጣች ወይንም ከኢትዮጵያ ተገነጠለች። እንግዲህ ኤርትራ ከኢትዮጵያ "ቅኝ ተገዢነት" ነፃ ስትወጣ ቅኝ ግዛት የነበሩ አገራት ነጻ በሚወጡባት ጊዜ በወቅቱ የነበራቸው ግዛት የቅኝ ግዛቱ ወሰን ሳይለውጡ ነፃነታቸውን እንደሚጎናፀፉና ይህም የህግ መርህ በካይሮ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ጸድቆ በአፍሪካ ተፈጻሚነት አግኝቶ የአለም አቀፍ ሕግ አካል ሆኖአል። ስለዚህ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነፃ ስትወጣ "የኢትዮጵያ ቅኝ

[144] Shaw, Malcalm supra, note 69. p 447.

ግዛት" በነበረችበት ጊዜ አሰብ ራስ ገዝ እንጂ የኤርትራ አካል አልነበረችም። ስለሆነም ኤርትራ ነፃ ስትወጣ የአሰብን ራስ ገዝ ሳይጨምር ከአሰብ ራስ ገዝ ሰሜን የሚገኘውን አገር ይዛ መሄድ ይገባት ነበር። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ የዓለም አቀፍ ሕግ አካል የሆነውን የ1964 ዓ.ም. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔን ጥሳ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት አሰብ ራስ ገዝን ይዛለች ማለት ነው።

ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ከተባለ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነጻ ስትወጣ የኢትዮጵያ የውስጥ አስተዳደር ድምበሮችን ማክበር ይኖርባት ነበር። ይኸም ማለት ራስ ገዝ በነበረችው በኤርትራና በሌላዋ ራስ ገዝ በአሰብ መሃከል የነበረው ኢትዮጵያ መሠርቶት የነበረው ድምበርን ኤርትራ ማክበር ነበረባት። ኤርትራ ይህ ከአሰብ ጋር የሚለያትን ወሰን ጥሳ አሰብን ጠቀለለች። ይህ ኤርትራ የፈጸመችው ጥሰት "በያዝከው እርጋ" (UTI POSSIDETIS) የሚደነግገውን የሕግ መርህንና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የ1964 ዓ.ም የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔን ይሽራል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የህግ መርሆች ማለት የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የካይሮ ውሳኔና "በያዝከው እርጋ" የሚለው መርህ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው ስንል እውነትም ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ወይንም ነበረች የሚለውን አምነን ተቀብለነው ሳይሆን ሻቢያና ሓወሓት/ኢሕአዴግ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ካሉ ውጤቱን በፀጋ መቀበል ነበረባቸው ለማለት ነው።

እነዚህን ሁለት የሕግ ጥሰቶችንና የአሰብ እራስ ገዝ በኤርትራ መነጠቅን በድምበር ኮሚሽኑ ችሎት ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች አላነሱትም። ምናልባት አሰብ የኢትጵያ አካል ነች ብሎ መከራከር የአሰብ ኢትዮጵያዊነት በተነሳ ቁጥር በቁጣ የሚገነፍሉ አንዳንድ ኢሕአዴጐችን ስለሚያስከፋ ሆን ብለው ዘልለውት ወይንም በክርክሩን ውቅት ነጥቡን እንዳያነሱ መመርያ ተሰጥቶአቸው ሊሆን ይችላል።

የኢትዮጵያን ጥቅም ተከታትሎ የሚያስጠብቅ አካል ቢኖርና ይህ ምናልባት አዋጪ ሊሆን ይችል የነበረ ክርክር ለድምበር ኮሚሽኑ ቢቀርብ ምናልባትም አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛትና



የባህር በር ሆና ልትቀርና የቀይ ባህር አፋሮችም አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ሊከበርላቸው በተቻለ ነበር። ይህን አብይ የሕግ ክርክር በድምበር ኮሚሽኑ ችሎት አለማንሳት አሁንም የኢትዮጵያ መብት አሳልፎ መስጠት ነው።

የድምበር ኮሚሽኑ ዳኞች ይህን የመሰለ የሕግ መፈናፈኛ ቢቀርብላቸው ኖሮ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ዓለም የደገፈው ጉዳይ ስለነበርና 90 ሚልዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ በእግር መንገድ እርቀት ወደብ አልባ ማድረግ ፍጹም ኢፍትሐዊ ስለሆነ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ ዳኞቹ ሊወስኑ ይችሉ ነበር፡

## 7.9. የድምበር ኮሚሽኑ መሬታቸውን ወደ ኤርትራ ያካለለባቸው ኢትዮጵያውያን የዜግነት መብት

በአልጀርስ ስምምነት የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ኮሚሽን የሞቱ የቅኝ ግዛት ውሎችን ከመቃብር ቆፍሮ አውጥቶ በሥራ ላይ አውሎ በሰጠው ውሳኔ መሰረት የቀይ ባህር አፋርን በከፊል ኢሮብን ኩናማንና ጾረናን ለኤርትራ መስጠቱ ከዚህ በላይ በዝርዝር ተገልፀአል።

የድምበር ኮሚሽኑ እነዚህን አካባቢዎች ለኤርትራ ሲሰጥ በቦታው ነዋሪ የሆነውን ሕዝብ ታሪክ መመዝገብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የያዘውንና እትብቱ የተቀበረበትን መሬት ነጥቆ ኢትዮጵያዊነት ዜግነቱን ገፍፎ ኮሚሽኑ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ሕዝቡን ኤርትራዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ብሎታል። እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከአያት ከቅድመ አያቶቻቸው ከዚያም በፊት የቀድሞዎቹ የጣላት ወረራዎችንና የቅርብ የሻቢያንም ጭምር ሲመክቱ ኖረዋል። በአድዋ ጦርነት ጣልያንን ካምበረከከው የኢትዮጵያ ጦር ውስጥ የአፋር ጀግኖች ጉልህ ሚና እንደተጫወቱ አዛዦቻቸው ልዑል ራስ መኰንን በሕይወት ቢኖሩ በመሰከሩላቸው። የኢሮብም ሕዝብ የጣልያኖች ቅኝ ግዛት ከነበረችው ኤርትራ ጋር ስለሚጐራበት ዘወትር የወራሪዎቹ ገፈት ቀማሽ ሆኖ (የሻቢያንም ጭምር) ለአገሩ ነፃነት ብዙ መስዋትነት የከፈለ ሕዝብ ነው።

ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ቅንጣት ያህል እውቀት የሌላቸውና ስለኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና የባህር በር መከበር ጉዳያቸው ያልሆነው ፈረንጆችና አንድ አፍሪቃዊ፤ ዛሬ ተነስተው የኢሮብን፣የአፋርንና የኩናማን ሕዝብ ኤርትራዊ ነህ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ብለውታል። ስለሆነም ወሰኑ በሚካለልበት ጊዜ እነዚህ ኢትዮጵያውያኑ ያላቸው አማራጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ይዘው ወደ መሃል ኢትዮጵያ አገር ይሰደዳሉ፤ ወይንም የሻቢያ መልካም ፈቃድ ከሆነ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን እንደያዙ የኤርትራ ፖስፖርት አውጥተው በኤርትራ ውስጥ እንነደውጭ አገር ዜጋ በመሬታቸው ላይ ሊኖሩ ይችላሉ።

ይህም የኤርትራ መንግሥት ፈቃድ ከሆነ ነው እንጂ የኤርትራ መንግሥት የእነዚህ ኢትዮጵያውያን የጸጉር አቈራረጥ ካላስደሰተው ከነበሩበት አስነስቶ ኤርትራ ውስጥ ሌላ ቦታ ቢያስፍራቸው ሉዐላዊ መብቱ ነው።

ይህ ኢትዮጲያውያን ዜግነታቸውን ጥለው የኤርትራ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስገድደው የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ "የሰብአዊ ሁሉ አቀፍ መብት መግለጫ" (Declaration of Human Rights) አንቀጽ 15ን በግልጽ ይጥሳል። ይህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 1 "ማንም ሰው የዜግነት መብቶቹ በዘፈቀደ አይገፈፍም" በማለት ይደነግጋል። ይህንን መሠረታዊ መብት በሌሎች የሰበአዊ መብት ሰነዶችም ሰፍሮአል። በ1948 ዓ.ም. የወጣው የላቲን አሜሪካና የሰሜን አሜሪካ የሰው ልጆች መብት መግለጫ (American Declaration of the Rights of Man) "ማንኛውም ሰው ሕግ የሚያጐናጽፈው ዜግነት እንዲኖረው መብቱ ነው። ዜግነቱን የሌላ አገር ዜግነት ሊሰጠው ፈቃደኛ በሆነ አገር ዜግነት ሊለውጠው" እንደሚችል መግለጫው ይደነግጋል። የአንድ ሰው የዜግነት መብት በዓለም አቀፍ ሕግ የተከበረና በጣምም ዋጋ ያለው መብት ለመሆኑ እነዚህ ሕግጋትና ሌሎችም ያመለክታሉ።

የኢሮብ ሕዝብ በተደጋጋሚ ኤርትራዊ እንዳልሆነና ለኢትዮጲያዊ ዜግነቱ እስከ ሞት እንደሚታገል በተለያዩ ጊዜአት አስታውቆአል። እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. "የዛላምበሳና ኢሮብ አካባቢ ኮሚቴ" በሚል ስያሜ የተቋቋመ ቡድን ለተባበሩት መንግሥት ድርጅትና የአልጀርስ ስምምነት በማስፈፀም ተሳታፊ ለሆኑት መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሬታቸው ወደ



ኤርትራ እንዳይከለልባቸውና ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው እንዲከበርላቸው ተማጽነዋል። እንዲሁም በኤርትራ ወረራ መሬታቸው በተያዘበት ወቅት በኤርትራ ሠራዊት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ የኢሮብ ተወላጆች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ እንዲደረግ ኮሚቴው ቀይ መስቀል ማህበርን ጠይቋል[145]።

ኢሕአዴግ አልጀርስ ላይ በተፈራረመው ውል ኢትዮጵያና ኤርትራ ወሰን በሚከለሉበት ወቅት ሁለቱም አገራት በስሩላቸው በየጠረፋቸው ጸጥታውን እንዲያስጠብቁ ተስማምተዋል ። የኢሮብ ሕዝብ ደግሞ መሬቱንና ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን በምንም ዓይነት እንደማይለቅ ለዚህም መብቱ ለመሞት ዝግጁ መሆኑን በተለያዩ ጊዜአት አስታውቆአል። ድንበር በሚከለልበት ወቅት የኢሮብ ሕዝብ በዚሁ አቋሙ ቢጸና መንግሥት ምን ሊያደርግ ነው? የጸጥታ አስከባሪ ኃይሎች ፈረንጆች አለአግባብ የሰጡትን ውሳኔ ለማስፈጸም በግፃ ሕዝቡ ላይ እንደማይተኩሱ እንተማመናለን። የድምበር ኮሚሽኑ ወደ ኤርትራ ባጠፋቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የኢሮብና የዛላምበሳ፤ የአፋርና የኩናማ ሕዝቦች ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ከመገፈፉ በፊት ኤርትራዊነት ወይንም የኢትዮጵያ ዜግነት ይመርጡ እንደሆነ በሕዝብ ውሳኔ ማረጋገጥም በተቻለ ነበር። ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያን የወከሉ ጠበቆች ይህንን ግልጽ የሆነ የሕግ መርህ በክርክራቸው ወቅት አላነሱትም። ስለሆነም ይህን ክርክር በድምበር ኮሚሽኑ ፊት አለማቅረባቸው ሌላው የኢትዮጵያ መብት ለኤርትር አሳልፎ እንደመስጠት ይቆጠራል።

## 7.10. ከጦርነቱን በፊትም ሆነ በኋላ አሰብን ማስመለስ የሚያስችሉ የነበሩ ሁኔታዎች

የኤርትራ ጦር ጥቃቱን የሰነዘረውና ባድመንና አካባቢውን የያዘው አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች ኤርትራ ለጦርነቱ ዝግጅት እያደረገች መሆኑ የሚያረጋግጡ አንዳንድ ማስረጃዎች

[145] "ከዛላምበሳ ኢሮብ ቀጣና ጊዜያዊ ኮሚቴ የቀረበ የምድረ ኢሮብ አቤቱታ፤ ለኢትዮ-ኤርትራ ድምበር ኮሚሽን የቀረበ ጥሪ"፤ጦቢያ 9ኛ ዓመት ቁ.7 2000 ዓ.ም

ቢደርሳቸውም "የኤርትራ መሪዎች አይወሩንም፣አላበዱም" በማለት በእንዝህላልነት ችላ በማለታቸው መሆኑን ከስይ ተገልጽአል። ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ባድመ እንዲያዝና አገር እንድትደፈር ያደረጉ የፖለቲካ መሪዎች እነማን እንደሆኑ፣ መንግሥትስ ለዚህ እንዝህልልነታቸው ምንስ እርመጃ እንደወሰደ ሕዝቡ የሚያውቀው ነገር የለም።

መሪዎቹ እንደዚህ ተደጋጋሚ ትንኮሳዎችን ችላ ባይሉና እንዝህላልነት ባይንሰራፋ ኖሮ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ወዲያውኑ እርምጃ ወስዶ አሰብ ዘልቆ ወደቡንና አካባቢውን ሊቆጣጠር በቻለ ነበር።

ኤርትራ ባድመንና አካባቢውን ወርረ ከያዘች በኋላ ለቅቃ እንድትወጣና ቀደም ሲል በነበረችበት እንድትረጋ በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ መንግሥትና በተለያዩ የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ብትጠየቅ አሻፈረኝ አለች። እንዲያውም "ጅራፍ እራሱ እየመታ እራሱ ይጮሃል" እንዲሉ ኤርትራ በኢትዮጵያ ተወረርኩ በማለት ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅትና ለሌሎችም ስሞታ በማቅረብዋ የጦርነቱ ቀስቃሽ ኢትዮጵያ ትሁን ኤርትራ እንዲመረምር በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ተወክሎ እቦታው ድረስ በመሄድ ያጣራው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ቡድን የሚከተለውን ሪፖርት ለድርጅቱ አቀረበ። "ከ1998-2000 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ውስጥ በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል በተደረገው ጦርነት ኤርትራ በጠብ አጫሪነት የጀመረችው ሲሆን ኤርትራ ራስዋ የቀሰቀሰችው ጦርነት የአልሞት ባይ ተጋዳይነት መከላከል ነበር ልትል አትችልም[146] ብሎ ነበር።

ከሁለት ዓመት ዝግጅት በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ጥቃት ሰንዝሮ ከባድመና ከአካባቢው የኤርትራን ጦር ከማስወጣቱም በላይ ዓለም አቀፍ የጦርነት ደንብ (Rulesof Engagement) በሚፈቅደው መሠረ ወራሪውን ጦር ከአገሩ አስወጥቶ ጦሩን በክትትል ኤርትራ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ በጥቂት ቀናት ውስጥ ሸንበቆን፣ ባሬንቱን፣ አፋቤትን፣ ጸረን፣ መንደፈራን አዲቋላን መያዙን ለኤርትራ ሕዝብ

[146] African Cmmittee of Diplomats, Cited in Abebe Tekle Haimanot Supra Note 3



ቅርብ የሆነው የቦስተን ዩኒቬርሲቲ ጋዜጠኛ ዳን ኮኔል ዘግቦት ነበር። የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል የኤርትራን ሦስት አራተኛ ግዛት ከያዘ በኋላ ልቅቆ እንዲወጣ ታዘዘ[147]።

ጦሩ ግስጋሴውን ቀጥሎ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ያስችለው የነበረው ሁኔታ በፖለቲካ መሪዎች ድክመት ወይንም ሆነ ብሎ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ለማድረግ በመፈለግ የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሰብ ዘልቆ በቁጥጥሩ ስር ማድረግ አልቻለም።

የኢትዮጵያ ጦር በያዛቸው በኤርትራ ግዛቶች ውስጥ እረግቶ አካባቢዎችን ለቅቆ ስመውጣት አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ቅድመ ሁኔታ ቢያደርገው ኖሮ ኤርትራ ይህንን ቅድመ ሁኔታ ከመቀበልና አሰብን ለኢትዮጵያ ከማስረከብ አማራጭ አይኖራትም ነበር።

የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ከመነሻው ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጀምሮ አራቱ ኃያላን አገራትና ሌሎችም የሚደግፉት ነገር ስለነበር በዚህ እርምጃዋ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ነቀፌታ አይደርስባትም ነበር።

በአንዳንድ ጉዳዩን በተከታተሉ ሰዎች ግምት የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሥመራ ዘልቆ የኤርትራን ዋና ከተማ ሊይዝ ይችል እንደነበረ ይናገራሉ። ኤርትራ የዓለም ሕብረተሰብ እውቅና የሰጣት ሉዐላዊ አገር እንደመሆንዋ መጠን የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሥመራን ቢይዝ ኖሮ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤትና ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ በኢትዮጵያ ላይ ውግዘት ከመሰንዘሩም በላይ ሌላም አስገዳጅ እርምጃ ሊወስድ ይችል ነበር። የጦሩ ወደ አሥመራ ግስጋሴ በአሜሪካኖች ማስጠንቀቂያና ዛቻ ምክንያት እንደቆመም አንዳንድ ውስጥ አዋቂዎች ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሥመራን ሊይዝ ከቻለ ፋቱን ወደ ምሥራቅ አዙሮ አሰብን ነፃ ማውጣት አያዳግተውም ነበር ማለት ነው። ይህንን ቢያደርግ ኖሮ መከላከያ ኃይሉ በአገሩ ላይ ወደር የሌለው ውለታ ጥሎ ነበር። ይህንን ማስፈጸም ይቻል አይቻል እንደነበረ የአገሩ ህልውናና ደህንነት አምኖ ለሰጣቸው የጦሩ አዛዦች አንድ ቀን ሃቁን ለኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚነግሩት ተስፋ ይደረጋል።

[147] ሪፖርተር እሁድ ሚያዝያ 2 ቀን 2003

የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል በቡሬ ግንባር ከጠላት በሚፋለምበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ፓርላማ ተገኝተው ለፓርላማ አባላት ስለጦርነቱ መግለጫ በሰጡበት ወቅት የመከላከያ ኃይላችን በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለና ዘልቆ አሰብን ከመያዝ የሚያግደው ምንም ነገር እንደሌለ የኢትዮጵያ ሕዝብና የፓርላማ አባላትን ባስደመመ፤ በጭብጨባ በታጀበ ንግግራቸው አብስረው ነበር።

ኮሎኔል ተወልደ ገብረ ተንሣይም ስለምሥራቁ ግንባር ሲጽፉ ይህንኑ የጠቅላይ ሚኒስትር አባባልን አረጋግጠዋል። ኮሎኔሉ "የኤርትራ መንግሥት ሰኔ 4 ቀን 1990 ዓ.ም. በቡሬ ግንባር በከፈተው ድንገተኛ ማጥቃት የአፋር ሕዝብ ከሠራዊታችን ጐን በመሰለፍ ወራሪውን በጀግንነት ሲገጥም የ52ኛው የኤርትራ ኮማንዶ ክፍል ጦር በውጊያው ተሸንፎ መበተን ሲጀምር በየመንገዱ እያደፈጠ አንድ በአንድ ለቅመውታል" ብለዋል[148]።

ኮሎኔል ተወልደ ገብረ ተንሳይ በመቀጠል የካቲት 7ቀን 1991 ዓ.ም ከንጋቱ 12:30 ላይ በቡሬ ግንባር የተጀመረውና ኢትዮጵያ በአየር ጥቃት ያፋፋመችው ውጊያ የኢትዮጵያ ሚግ 21 ተዋጊ ጀቶች ከኢትዮጵያ ደንበር ወደ ውስጥ 51 ኪሎ ሜትር ዘልቆ በመግባት ከአሰብ 20 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው በርስሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በኤርትራ ጦር ላይ ድል መቀዳጀቱና በቦታው ተከማችቶ የነበረው የጦር መሣርያና ተሽከርካሪዎች ማውደሙን የኤርትራ ተከላካይ ጦር የኢትዮጵያ ጀቶችን ለመጣል ያደረገው ጥረት እንዳልተሳካለት የኢትዮጵያ መንግስት ቃል አቀባይና አዣንስ ፍራንስ ሬድዮ አረጋግጠው እንደ ነበረ ገልጸዋል። ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ ጦር ቢፈቀድለት ኖሮ አሰብን ለመያዝ የሚያግደው ምንም ነገር እንዳልነበር ነው። በዚህ አይነት የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አሰብ ደርሶ ተመለሰ ማለት ያቻላል።

መከላከያ ኃይላችን ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳረጋገጡት ይህንን ያህል እየቀናው አቅሙም እያለው የኢትዮጵያ ሕጋዊ መብት ወይንም በተባበሩት መንግሥታ አባባል የኢትዮጵያ "ሕጋዊና

[148] ተወልደ ገብረ ትንሳይ (ኮሎኔል) ባድመ እንደ ምክንያት ፤የኛ፡ዋናው መፃፎ (የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እውነተኛ ታሪክ) አዲስ አበባ (2009) ገፅ 312



አስፈላጊ" የሆነውን የባህር በር ከጠላት እጅ ፈልቅቆ ነፃ ሳያወጣ የቀረበትና ይህንን የኢትዮጵያ የባህር በር መብት የሰቀቀበት ምክንያት ሕዝቡ ከፖለቲካ መሪዎች መልስ ይፈልጋል።

## 7.11. "ኢትዮጵያ ሽንፈትን ከድል መንጋጋ አወጣች" (ፕሮፌሰር ክላፋም)

እ.አ.አ በ1991 ሻቢያ አሥመራን ሕወሓት/ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ በኋላ ኤርትራውያን በኢትዮጵያውያን ጉዳይ ፈላጭ ቆራጭ፤አዛዥና አናዛዥ ሆነው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ኢትዮጵያውያን በገዛ አገራቸው ባዕዳን ሆነው የባንክ ብድርም ሆነ የሥራ ዕድል ለማግኘት ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን ቅድሚያ የሚያገኙበት ሁኔታ ነበር። ሕወሓትን ያማለለው የኤርትራ ፍቅር በተለያዩ ምክንያቶች ሲያረጅ የአፍሪቃ የዲፕሎማቶች ኮሚቴ እንደዘገበው በኤርትራ ቀስቃሽነት ጦር ተማዛው ጦርነቱ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ቢደመደምም ከጦርነቱ ተጠቃሚ ኤርትራ ሆነች። የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ መምህር ፕሮፌሰር ክሪስቶፎር ክላፋም ስለድንበር ኮሚሽኑ የተዛባ ውሳኔ ሲጽፉ "ውሳኔው ኢትዮጵያ የተጐናጸፈችውን ድል ዋጋ አሳጥቶት ኢትዮጵያ ሽንፈትን ከድል መንጋጋ ፈልቅቃ እንድታወጣ ተገደደች"[149] (Ethiopia pulled defeat from the jaws of victory) በማለት በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ክስረት ገልጸዋል። ከእነዚህ ክስረቶች ዋና ዋናዎቹ አንዳንድ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች በኤርትራ እጅ መውደቅና የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ብቻም አይደለም።

ኤርትራ ግን ጦርነት በመቀስቀሰዋ የአሰብ የባህር በር በሕግ ጸደቀላት፤ ጾረና እና ሌሎችንም የኢትዮጵያ ግዛቶች ወደ ኤርትራ ታጠፋ። ሁለቱም አገራት በጦርነቱ ጉዳት ደርሶብናል ብለው

[149] Christopher Clapham, Professor, "Notes on the Ethio-Eritrea - Boundary Demarcation," East Africa Forum, http://www.cfeestees.org/code/claph.htm. Visited on Feb. 2, 2010

ለአልጀርስ የካሳ ኮሚሽን ያቀረቡት ጥያቄ የሁለቱም ጉዳት ተሳልቶ ኢትዮጲያ ለደረሰባት ጥፋት አሥር ሚሊዮን ዶላር ብሎሚ ኤርትራ እንድትከፍላት ኮሚሽኑ ወሰነ። ኤርትራ አሥር ሚልዮን ዶላር ብልሚ ለኢትዮጵያ እንድትከፍል ቢወሰንባትም ገንዘቡ እንደማትከፍልና ለመክፈልም አቅሙም እንደሌላት በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የካሣ ኮሚሽኑም ለሁለቱም ካሣ ሲወስን አገራቱ ሊከፍሉ እንደማይችሉ በመረዳት ነበር በጣም ዝቅተኛ ካሣ የቆረጠው። ኤርትራና ኢትዮጵያ በሰውና በንብረት ላይ ላደረሱት ካሣ ለእያንዳንዳቸው እንዲከፍሉ ታዝዞ የኢትዮጵያ ድርሻ በ10 ሚሊዮን ቢበልጥም የካሣ ኮሚሽኑ ኤርትራ ጦርነት በመቀስቀስዋ ለኢትዮጵያ የቅጣት ካሣ (Punitive damage) እንድትከፍል አልተቆረጠላትም። ኢትዮጵያ በካሣ ኮሚሽኑ ክርክር ባዶዋን ወጣች ማለት ይቻላል ፤ ምክንያቱም ኤርትራ የአይደር ትምህርት ቤትና ከጦርነት ውጭ መሆን የሚገባቸውን አካባቢዎች በቦምብ ስትደበድብ ለዚህ ሁሉ የተፈረደበት የጦር ካሣ አሥር ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ካሣ በአሜሪካና አውሮፖ ፍርድ ቤቶች ለስድብ ለሚያህል ትንሽ ነገር ይቆርጣሉ። በአንድ ወቅት በአሜሪካ ውስጥ አንዲት ሴትዮ አንድ ሬስቶራንት ገብታ ቡና አዝዛ ትኩሱ ቡና ጭኗ ላይ ስለፈሰሰ ክስ አቅርባ ሬስቶራንቱ አሥር ሚልዮን ዶላር ካሣ እንዲከፍላት ፍርድ ቤቱ ቆረጠላት።

ምናልባት ወራሪዋ ኤርትራ ወረራ በመክፈትዋና በሽንፈትዋ የከፈለችው ዋጋ ቢኖር በአልጀርስ ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያን የሚያዋስነው 25 ኪሎ ሜትር የኤርትራ ግዛት የሰላም ቀጣና ሆኖ የተባበሩት መንግሥት የሰላም አስከባሪ ኃይሎች እንዲሰፍሩበትና እንዲቆጣጠሩት መደረጉ ነበር። ያም ቢሆን የሰላም ቀጣናው ኤርትራ በኃይል መልሳ በእጇ አስገባችው።

ኤርትራ ጦርነት ጭራ ስትሸነፍ የኤርትራ መንግሥት መቀጣትና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት መረጋገጥ ነበረበት። ክጠላት ሲከላከሉ ለወደቁት በአሥር ሺዎች ለሚቈጠሩ ውድ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት ዜጐች፣ ለጠፋው የግልና የሕዝብ ንብረት ኤርትራ መክፈል ነበረባት። ኤርትራ ግን ለእነዚህ ጥፋቶችዋ ቤሳ ቢስትኒ ሳትከፍል ይልቁንም በከፈቶችው ወረራ ተጠቃሚ ሆ



# ምዕራፍ 8

## 8. የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኢትዮጵያ መሰረዝ ይገባታል

### 8.1 የተኩስ አቁም ስምምነት መጣስ

አልጀርስ ስምምነት ውስጥ ከተካተቱት ከዋና ዋናዎቹ አንቀጾች አንዱ ስለተኩስ አቁም የሚደነግገው ነው። የዚህ አንቀጽ መጣስ ከሌሎች ጥሰቶች ሁሉ የከፋ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የተኩስ አቁም ጥሰት የስምምነቱ ዋነኛውና አንኳር ዓላማ ስለሚጥስ ነው። ተኩስ ካልቆመ ስምምነቱ ምንም ዋጋ አይኖረውም ማለት ነው።

የተኩስ አቁም ስምምነት ከተደረሰና የአልጀርስ ስምምነት ከተፈረመ በኋላ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታ የኤርትራ ጦር በኢትዮጵያ ጦር ላይ ትንኩሳ ያካሄድ እንደነበር ኢሕአዴግ በተደጋሚ ከስሶ ነበር።

የኤርትራ ጦር በእውነትም ኢሕአዴግ እንደሚለው በተለያዩ ጊዜያት በኢትዮጵያ ጦር ላይ ትንኮሳ ሰንዝሮ ከሆነ ይህም ድርጊት የስምምነቱ ዋናውና አንኳር የሆነውን ተዋዋዮቹ የገቡትን ግዴታ ስለሚጥስ ኢሕአዴግ ስምምነቱን መሻር ይገባው ነበር።

### 8.2. ምሰሶ ወይንም ችካል በወሰኑ ላይ ስለመትከል

የድምበር ኮሚሽኑ የጦርነቱ መንስኤ (Casus Belli) የሆነችውና ከሻቢያ እጅ ለማስለቀቅ እልፍ አእላፍ ኢትዮጵያውያን የተሰዉለት ባድመ ለኤርትራ በመስጠቱ በኢሕአዴግ ሰፈር ከፍተኛ መደናገጥ ተፈጥሮ እንደነበር የሚታወስ ነው። ውሳኔው

የመጨረሻ ይግባኝ የሌለበት መሆኑን እያወቀ ኢሕአዴግ የኮሚሽኑ ውሳኔውን አስመልክቶ ማጣሪያ ጠየቀ።

የማጣርያው ጥያቄው ጉዳዩ እንደገና ይታይልኝ ማለት ስለሆነ ኮሚሽኑ ከእንግዲህ ወሰን አካልሎ ችካል ከመትከል በስተቀር የቀረው ነገር እንደሌለ ገልፆ በኢትዮጵያ ቀርቦ የነበረውን አንድ ጊዜ ይብራራልኝ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደገና በሦስተኛ ወገን ይታይልኝ ብሉ ለተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ም/ቤት ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሆነ።

በሁለቱ ባላጋራዎችና ስምምነቱን በታዘቡ አካላት መሃከል ብዙ ውይይቶች ከተደረጉ በኋላ ኢሕአዴግ ውሳኔውን "በመርህ" ደረጃ መቀበሉን ገልጾ ድንበር ማካለሉ (Delimitation) ቢጠናቀቅም ምሰሶ ከመቆሙ ወይንም ችካል (Demarcation) ከመተከሉ በፊት የሰዎች አሰፋፈርና የመሬት አቀማመጥ ከግምት ውስጥ አግብቶ "ሰጥቶ በመቀበል" መካለል አለበት ሲል ተከራከረ። ሻቢያ ደግሞ የኮሚሽኑ ውሳኔ የመጨረሻ እንደመሆኑ መጠን ምንም ዓይነት ማስተካከል ሳይደረግ እንደውሳኔው ቃል መፈፀም አለበት በማለት በወሰኖቹ ላይ ችካል እንዲተከል አጥብቆ ጠየቀ። ኮሚሽኑ ሁለቱም መንግሥታት ይስማሙ እንደሆነ በሚል በቂ ጊዜ ከሰጠ በኋላ ሁለቱም በአቋማቸው ጸኑ።

ኮሚሽኑ ዘመናዊ የአካላል ስልት ተጠቅሞ የድምበር መስመሩ የሚያርፍበት መሬቱ ምን እንደሚመስል ከሰማይ በአይሮፕላን በተነሱ ፎቶግራፎች አይቶ ችካል የሚተከልባቸው ነጥቦችን ለይቶ የማስመሰል ማካለል (Virtual Demarcation) አድርጌ ሥራዬንም አጠናቅቄአለሁ ሲል እ.አ.አ ሕዳር 30ቀን 2007 አስታወቀ። ኤርትራ ይህንን ማካለል በደስታ ስትቀበልው ኢትዮጵያ በጽኑ ተቃወመችው። ኢትዮጵያ ይህንን የማካለል ዘዴ "የሕግ ልብ ወለድ" (Legal Fiction) ነው በማለት እንደማትቀበለው አስታወቀች። ለዚህም የኢትዮጵያ እምቢታ ኤርትራውያን አሜሪካንን ተጠያቂ አድርገዋል። በኤርትሪረውያን እይታ ኢትዮጵያ ለመካለል ፈቃደኛ ያልሆነችውና የኤርትራ ሉዐላዊ ግዛት የያዘችው የአሜሪካ የገንዘብና የዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ተማምና መሆኑን ኤርትራውያን ሲገልጹ ለዚህም ተወቃሽ ያደረጉዋቸው በቡሽ



አስተዳደር ጊዜ የአፍሪቃ ክፍል ረዳት ሚኒስትር የነበሩትን ወይዘሮ ጀንዳይ ፍሬዘርን (Jendayi Fraser) ነው።

ኤርትራ በታላቅ ደስታና ጉጉት የተቀበለችው "የማስመሰል ማካለሉ" ባድመንና ሌሎችም አካባቢዎች ወደ ኤርትራ በማጠፉና ኢትዮጵያን ወደብ አልባ አድርጎ ስለሚያስቀር ነበር። ይህንን መሠረት በማድረግ የኤርትራው ፕሬዘዳንት አቶ ኢሣያስ አፈወርቂ በተለያዩ ጊዜያት በአፍሪቃ ከተደረጉ የድንበር መካለሎች ሁሉ የኤርትራና የኢትዮጵያ ያህል የተዋጣለት አካለል የለም ሲሉ ተናግረዋል። በመቀጠልም በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የድንበር መካለል ችግር የለም፤ ተካልሎ ተጠናቋአልና ብለዋል። በአቶ ኢሳያስ አባባል አሁን የቀረው ኤርትራ በፍርድ የተሰጠት ሉዐላዊ ግዛቶቿዋን በኢትዮጵያ መያዛቸው ነው። ኤርትራ ይህንን ለማስፈጸም ደፋ ቀና የምትል ሲሆን እስከ ዛሬ ሰሚ አግኝታ ኢትዮጵያ በኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት ባድመንና ሌሎችም ለኤርትራ የተወሰኑ ግዛቶች እንድታስረክብ የተደረገባት ግፊት የለም። ኤርትራ በአቶ ኢሣያስ አባባል ኢትዮጵያ በድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት ባድመንና ሌሎችም ለኤርትራ ግዛቶች እንድታስረክብ ያልተገደደችው አሜሪካን ከላላ ስለሆነቻት ነው በማለት አሜሪካን እጅግ አምርረው በመውቀሳቸ በዚህም ምክንያት አሜሪካና ኤርትራ በጣም የተበላሸ ግንኙነት አላቸው። በተጨማሪም የአሜሪካና የኤርትራ ግንኙነት የተበላሸው አሜሪካ ኤርትራ የሱማሌ አሸባሪዎችን ትረደለች ከሚልም ጭምር ነው።

የድምበር ኮሚሽኑ የተሰጠው ኃላፊነት ድንበሩን (delimit) ማካለሉም እንደተጠናቀቀ ምሰሶ ማቆም ወይንም ችካል መትከል (demarcate) ነበር። ኮሚሽኑ ያደረገው ግን በኢትጵያና በኤርትራ ካርታ ላይ ከላይ እንዲተገለጸው አንዳንድ ምሰሶ የሚተከልባቸው ነጥቦችን በማስቀመጥ በማስመሰል አካልዬአለሁ፣ ሥራዬንም፤ አጠናቅቄአለሁ በማለት ፋይሉን ዘግቶ ተነሳ።

የድምበር ኮሚሽኑ በአልጀርስ ስምምነት አንቀጽ 4 መሠረት ለኮሚሽኑ የተሰጠው ሥልጣን የሁለቱ አገራት ድንበር ማካለልና ከዚያም በኋላ ምሰሶ በመሬት ላይ ማቆም እንጂ ማስመሰል (Virtual Demarcation) ብሎ ነገር ለኮሚሽኑ አልተሰጠም።

አሁን ኮሚሽኑ ያደረገው የኮሚሽኑ አባላት ወይንም ወኪሎቻቸው መሬቱን ሳይረግጡ በስምምነቱ ያልተጠቀሰው በካርታው ላይ ነጥቦችን ማመላከት ምሰሶን መትከል አይተካም።

ኮሚሽኑ በመሬት ላይ ምሰሶ ማቆም እንጂ በወረቀት ላይ ማመልከት ስምምነቱ ከሰጠው ኃላፊነት ውጭ ከመሆኑም በላይ በማስመሰል መካለል (Virtual damarcation) ምሰሶ በሚቆምበት ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ማረም አይቻልም። በሁለት አገሮች መሃከል ወሰን ተካልሎ ምሰሶዎች በሚተከሉበት ጊዜ አንዳንድ ያልተጠበቁ የመሬት ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ለምሳሌ ምሰሶ የሚቆምበት ሥፍራ እልም ያለ ገደል ሆኖ ምሰሶውን መትከል በፍፁም የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ምሰሶውን ትንሽ ፈቀቅ አድርጎ መትከል የተለመደና በብዙ አገሮች የሚሠራበት ነው። ይህም ማድረግ የሚቻለው በቦታው ተገኝቶ እርምት በማድረግ ሲሆን በወረቀት ላይ የሚደረገው ምልክት ይህ መታረም ያለበትን ጉራማይሌ ሁኔታ ሊያሳይ አይችልም።

የድምበር ኮሚሽኑ በዚህ ሕጉ በማያውቀውና ስምምነቱ ውስጥ ባልተገለፀ የማስመሰል ማካለል አድርጌአለሁ ማለቱ ከተሰጠው ኃላፊነት ውጭ ስለሆነ ስምምነቱን መጣስ ነው። ስለዚህ ስምምነቱ በሚያዝዘው መሠረት በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የድምበር ምሰሶ አልተተከለም ማለት ሲሆን ኮሚሽኑም ምሰሶዎችን ከመትከሉ በፊት ሥራውን በማቆም ስምምነቱን ስለጣስ ኢሕአዴግም ስምምነቱንም ሆነ የድምበር ኮሚሽኑን ውሳኔ መሻር ሙሉ መብቱ ነው።

ከዚህ በላይ የተዘረዘረው "የማስመሰል" ምሰሶ ተክዬአለሁ በማለት የድምበር ኮሚሽኑ በአልጀርስ ስምምነት የተሰጠውን ኃላፊነት መጣሱና ስምምነቱን ማፍረሱ እንዳለ ሆኖ ኤርትራም ስምምነቱን ከአራት ጊዜ ባላነሰ ስትጥስ ኢሕአዴግ ለድምበር ኮሚሽኑም ይሁን ስምምነቱን ለማስፈጸም ለተመደቡ አካላት አንድም ጊዜ ይፋዊ ተቃውሞ ሲያሰማ አልተደመጠም።



## 8.3. አንዳንድ የሰላም አስከባሪ ኃይል አባላት ከኤርትራ መባረር

የሁለቱን አገራት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት ከተቋቋመው የሰላም አስከባሪ ኃይል (United Nations Mission in Ethiopia and Eritrea) (UNMEE) ውስጥ ኤርትራ አንዳንድ አሜሪካኖችን፣ አውሮፓውያንን ካናዳውያንና ሩሲያውያንን ከአገር አባረረች[150]።

ሁለቱ አገራት ተካልለው ወሰኖቻቸውን ለመለየት ምሰሶ እስኪያቆሙ ድረስ የሰላም አስከባሪው ኃይል በሰላሙ ቀጣና እንዲቆይ ስምምነት ተደርሶ ነበር። ሆኖም ምሰሶዎች ተተክለው የድምበር መካለሉ ሥራ ከመጠናቀቁ በፊት ኤርትራ አንዳንድ የሰላም አስከባሪ አባላትን ማባረሯ ስምምነቱን መጣስ ነው። ስለሆነም አሁንም ስምምነቱን ኤርትራ መጣስዋን ኢሕአዴግ እያወቀ ስምምነቱና ውሳኔውን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት እያለ በዝምታ ማለፍን መረጠ።

ኤርትራ እነዚህን ጥሰቶች በመፈጸምዋ ስምምነቱ ተሰረዘ ማለት አይደለም። ኤርትራ ስምምነቱን ስትጥስ ኢትዮጵያ ስምምነቱን የመሰረዝ መብት ይሰጣታል እንጂ ስምምነቱ ተሰረዘ ማለት አይደለም። ኢሕአዴግ የድምበር ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔና ስምምነቱ በግልጽና በይፋ ሽሮ መሻሩንም ለድምበር ኮሚሽኑና ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አስታውቆ ውሉን የሻረበት ሰነድ በተባበሩት መንግሥታት አርካይቭ ሲቀመጥ ብቻ ስምምነቱ እንደተሻረ ሊቆጠር ይችል ይሆናል። ኢሕአዴግ ስምምነቱ በሻቢያ መጣሱ በተለያዩ ጊዜያት በሚዲያ ቢገልጽም ራሱ ኢሕአዴግ

[150] Afop News, 7 December 2000.

ስምምነቱን ስለመሰረዙም ሆነ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ስለመሻሩ ያለው ነገር የለም። እንዲህ ዓይነት ክርክር በሚነሳበት ጊዜ "ዝምታ" በሕግ ፊት የሌላውን አቋም እንደመቀበል ይቆጠራል። (Silence is acceptance)። ስለሆነም ኤርትራ የአልጀርስ ስምምነቱም ሆነ ውሳኔውን ምን ጊዜም ልታነሳው ትችላለች።

በግልግል ዳኝነት የተወሰኑ እንዲያውም ከግልግል ዳኝነት በላይ ክብርና ክብደት ያላቸው በተባበሩት መንግሥታት ዋና የፍትሕ አካል በሆነው በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት (Internaitonal Court of Justice) የተወሰኑ ጉዳዮች እንኳን መሻር ወይንም ውሳኔውን አልቀበልም ማለት የተለመደ ነው።መንግሥታቱ በመረጡአቸው ዳኞች ፊት ቀርበው ከተከራከሩ በኋላ ወይንም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ቀርበው ከተረቱ በኋላ የግልግል ዳኞች ወይንም የፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሠረታዊ ጥቅሞቻቸውን የሚጻረሩ ከሆኑ ውሳኔዎቹን አንቀበልም ያሉባቸው አያሌ ጊዜአት አሉ።

መንግሥታት እንደዚሁ መሠረታዊ ጥቅሞቻቸውን የሚጐዳ መስሎ በታያቸው ጉዳይ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በተከሰሱ ጊዜ ክሱን ተቀብለው ፍርድ ቤት መቅረብ እንኳን ፈቃደኛ ያልሆኑባቸው ጊዜያትም አሉ። አንድ ያውል ግዴታን ወይንም የፍርድ ቤት ውሳኔ አክብሮ መፈጸም አገሪቱን የሚያጠፋ ከሆነ የውል ግዴታን ከመፈጸም በፊት ሕልውናን በማስቀደም ውሉን መሰረዝ ይችላል የሚለው የቆየ የሕግ መርሆ አለ ።[151]

ላለመግባባቱ መንስኤ የሆነው ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት እይታ ለዓለም ሰላምና ጸጥታ አስጊ መስሎ ካልታየ የተባበሩት መንግሥታት የፍርድ ቤትንም ወይንም የግልግል ዳኞች ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ እንዲፈጽሙ ማስገደድ አይቻልም። ስለሆነም መንግሥታት የግልግል ዳኝነት ወይንም የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መጥሪያም ሆነ ውሳኔ አንቀበልም ያሉባቸውና በዚህም ምክንያት ምንም ችግር ያልገጠማቸው አገራት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

[151] See Jefferson Opinion on the French Treátires (Qpr.28,1793) in Merril D.Peterson,Ed, The Politcal Writings of Thomas Jefferson,113-114 (Thomas Jefferson Memorial Foundation:1993) p.113-114



እ.አ.አ በ1974 ዓ.ም ፈረንሳይ በፖሊፊክ ውቅያኖስ በኒውዚለንድና በአውስትራልያ አካባቢ የኑክሌር ቦንብ ሙከራ ልታደርግ በወሰነች ጊዜ እነዚህ ሁለቱ አገራት ሙከራው እንዳይደረግ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ክስ መሠረቱ። ፍርድ ቤቱ የሁለቱንም ክርክር ከሰማ በኋላ ፈረንሳይ የኑክሌር ሙከራውን እንድታቆም ቢበይንም ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታ ውሳኔውንም እንደማትቀበል ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አስታወቀች። የኑክሌር ፍንዳታ ሙከራም አደረገች[152]።

እንዲሁም የደቡብ አሜሪካዊት አገር ኒካራግዋ አሜሪካ ወታደራዊና ሌላም ሌላም ጥቃት አድርሳብኛለች በማለት በ1984 ዓ.ም በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ክስ አቅርባ ነበር። ፍርድ ቤቱም አሜሪካ የኒካራግዋን የተለያዩ መብቶች መጣስዋ ጠቋሚ ማስረጃዎች ቢኖሩም አሜሪካ እንዲያውም የፍርድ ቤቱን ሥልጣን አልቀበልም ብላ ለክሱ ፍሬ ነገር መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነችም። በሌለችበት የተሰጠውንም ውሳኔ አልቀበልም አለች።

አንድ የጀርመን ዜጋና ወንድሙ አሜሪካ ውስጥ በሠሩት ወንጀል እ.አ.አ. በ1998 ዓ.ም በአሜሪካ ፍርድ ቤት የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ጉዳያቸው ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወስደው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሞት ቅጣቱ እንዲታገድ ቢያዝም አሜሪካ ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታ ሁለቱም ወንድማማች በሞት ተቀጡ[153]።

ኢትዮጵያ የድምበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ብትሰርዝ ተጨባጭ የሆነ ምንም ዓይነት ጫና ወይንም ቅጣት የሚደርስባት አይመስልም። ዛሬ ሻቢያ በተለይም በአሜሪካና በአውሮፖ እንደ ወንበዴ መንግሥት (rogue state) በተቆጠረችበትና ከዚያም አልፎ

[152] Tekola W.Hagos, Professor, "Aklilu Habtewold: In the Footsteps of a Great International Law Jurist Disqualification of Lauterpacht: Nullification of Algiers Agreement, and Rejection of the Decision of the Border Commission." Phineaus Claire Washington DC October 30, 2003,

[153] Ibid

የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ኤርትራ በሱማልያ ያለውን መንግሥት ለመጣል ለሚሠሩ ቡድኖች ድጋፍ ታደርጋለች፣ከጅቡቲ ጋር ያላት የድምበር ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመጨረስ ፋቃደኛነት አላሳየችም በማለት እ.አ.አ በፌብርዋሪ 25 ቀን 2010 ዓ.ም የጦር መሣርያ እቀባ፣ የአገሪቱን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከአገር ውጭ እንዳይዘዋወሩ እንዲሁም ባለሥልጣናቱ በውጭ ያላቸው ንብረት እንዳያንቀሳቅሱ በተደረገበት ሁኔታ ኢትዮጵያ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ሽራለችና ማዕቀብ ይጣልባት ብትል ኤርትራ ሰሚ አታገኝም። ለዚህም የብሪታንያ የውጭ ጉዳይና በኮመንዌልዝ የአፍሪቃ ዲሬክተር ሚስተር ጀምስ በሻንን መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ ባትቀበል የብሪታንያ መንግሥት ማዕቀብ የመጣል እቅድ አለው ወይ ተብለው ለተጠየቁት ቀጥሎ ያለውን መልስ ሰጡ። "የድምበር ኮሚሽኑ ያስተላለፈው ውሳኔ ለመቀበል ኢትዮጵያ ሊክብደትና እሉታዊ ጐኑ ያመዘነ ጠንካራ ስሜት ሊፈጥር ይችላል። የብሪታንያ መንግሥት በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ ማዕቀብ የመጣል አቋም የለውም፤ ምክያቱም ማዕቀብ መጣል ምንም ፋይደ የለውም። ስለዚህ የብሪታንያ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት ከዛሬ ጀምሮ የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ካልተቀበልክ ምንም ዓይነት የገንዘብ እርዳታ አልሰጥህም የሚል አቋም የለውም"[154]። በተለይም ኢሕአዴግ ሽብርተኛነትን በመዋጋት የምዕራባዊያን ምርጥ ወኪል በሆነበት በአሁኑ ሰዓት ውሳኔውን ቢሽር ማንም ደፍሮ የኢኮኖሚ እቀባም ሆነ የኃይል እርምጃ ይወስድበት የሚል የለም። የድምበር ኮሚሽኑ በወሰነው መሠረት ኢትዮጵያ ለኤርትራ እንድታስረክብ የተፈረደባትን ባድመንም ሆነ ሌሎች አካባቢዎችን እንድታስረክብ አምርሮ የጠየቃት እንኳን የለም። ምናልባት ሁኔታው ከፍቶ በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ እቀባ ይደረግባት ቢባል እንኳን ከዚህ ቀደም በአገራት ላይ የተጫኑ ማዕቀቦች ውጤት አልባ ሆነው የተፈለገው ዓላም ማስፈፀም አልቻሉም። ለዚህም ከኤርትራ የተሻለ ምሳሌ አይገኝም። ኤርትራ በሱማልያ ሽብርተኞችን ትረዳለች በሚል በአብዛኛው በኢትዮጵያ ቀስቃሽነት የተጣለባት የኢኮኖሚ እቀባ ያደረሰባት ጉዳት አይታይም። የኤርትራው ፕሬዚዳንት የተጣለው ማዕቀብ

[154] ኒሽን ጥቅምት 28 ቀን 1996 ዓ.ም



በኢኮኖሚአቸው ላይ ምንም ዓይነት ጫናም ሆነ ጉዳት እንዳላደረሰ ብዙ ጊዜ ተናግረዋል።

አቶ መለስ ስምምነቱን ቢሽሩት በኢትዮጵያ ላይ የሚደርስ ጉዳት እለመኖሩን በአንድ ወቅት ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪቃ ክፍል እርዳት ሚኒስትር ለወይዘሮ ጀንዳይ ፍሬዘር (Jendayl Fraser) ገልጸውላቸዋል። ወይዘሮዋ አዲስ አበባን ጐብኝተው ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር ተገናኝተው ስለ ሰላም አስከባሪው ኃይል ከኤርትራ መባረር ባደረጉት ውይይት ወይዘሮ ፍሬዘር ኢትዮጵያ የአልጀርስ ስምምነትን ብትሰርዝ ምን ይደርስባታል ብለው አቶ መለስን ጠየቋቸው።አቶ መለስም ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ኢትዮጵያ ውሉን ብትሰርዘው "በመንግሥታቸው ውስጥ ያሉት ተቃዋሚ አክራሪዎችን ያጠናክራል። እነዚህ አክራሪዎች በኤርትራ ላይ ጠንክር ያለ እርምጃ እንዲወሰድ ይፈልጋሉ፤ኤርትራውያንም ግራ ይጋባሉ"[155] በማለት ጥያቄውን መለሱ። በመልሱ፤ አክራሪዎች ይጠናከራሉ ሲሉ ለአቶ መለስና ለቡድናቸው ሥልጣን ስጋት ይሆናሉ ማለታቸው ግልጽ ነው። በዓለም ሕብረተስብ ኢትዮጵያ የድምበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ባለማክበርዋ ምናልባት ሊደርስባት የሚችለው ጫና አላነሱም።

## 8.4. የሰላም ቀጣናው በኤርትራ ጦር መወረር

ኤርትራ ስምምነቱን ስትፈርም ጦርዋ የኢትዮጵያ ጦር ከነበረበት ከኤርትራ ወሰን 25 ኪ.ሎ ሜትር እርቆ በኤርትራ ምድር እንዲሰፍርና ላይ ታቹ ስፋቱ 25 ኪ.ሎ ሜትር የሚሆን የሰላም ቀጠና በመሬትዋ ላይ ተመስርቶ የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ወታደሮች (United Nations Mission in Ethiopia and Eritrea) እንዲሰፍሩበት ተስማምታ ነበር። ኤርትራ እራስዋ በቀሰቀሰችው ጦርነት በመሸነፍዋ የከፈለችው በጣም ትንሽ ዋጋ ቢኖር ይህ የሰላም ቀጠና በመሬትዋ ላይ መቋቋሙ ነበር።

[155] See .http://danielberhane .wordpress.Com Accessed on 6 june 2011

ይህ መሬት በተባበሩት መንግስታት በተቋቋመው የሰላም አስከባሪ ኃይል ቁጥጥር ሆኖ ኃይሉ እንደፈለገ እንዲንቀሳቀስና የሰላሙን ሁኔታ እንዲቆጣጠር በስምምነቱ ተፈቅዶለት ነበር። ሆኖም ኤርትራ የሰላም አስከባሪውን ኃይል እንቅስቃሴን በመገደብና የተለያዩ ጫናዎችን በማድረግ፣ ለምሳሌ ነዳጅ እንዳይገዙ መከልከልን የመሳሰሉ ድርጊቶች በመፈጸም የሰላም አስከባሪው ኃይል ተግባሩን እንዳያከናውንና አሳፊነቱን እንዲይወጣ ብዙ እንቅፋቶች ተጋረጡበት። በመቀጠልም ኤርትራ የሰላም ቀጠናውን ጥሳ ገብታ በጦር ኃይል በመቆጣጠሯ በሁለቱ አገራት ወሰኖች ምስሶ ቆም እስኪጠናቀቅ በቦታው መቆየት ይገባው የነበረው የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪው ኃይል ሥራውን አቋርጦ እ.አ.አ በጁላይ 2008 ዓ.ም የሰላም ቀጣናውን ዘግቶ እንዲወጣ ተገደደ። አሁንም ኤርትራ የሰላም ቀጣናውን ስትቆጣጠር ስምምነቱን እንዳገና ጥሳዋለች። ይህንን ጥሰት ተከትሎ ኢሕአዴግም ስምምነቱንና ውሳኔውን ሲሽር ቢችልም አሁንም በዝምታ አልፎታል።



# ምዕራፍ 9

## 9. የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን አስመልክቶ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሲቪክ ማህበራትና የሕዝባዊ ድርጅቶች አቋምና ያደረጉአቸው ትግሎች

### 9.1 የፓለቲካ ፓርቲዎች

ኢሕአዴግ አሰብ የኤርትራ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋና ለባለቤትዋ ለኢትዮጵያ እንድትመለስ አሁንም ሆነ ወደፊት ዲፕሎማሲያዊ ጥረትም ሆነ ከኤርትራ ጋር ድርድር እንደማያደርግ በተለያዩ ጊዜያት በግልፅና በማያሻማ መልኩ አረጋግጧል። የኢሕአዲግን አቋም እንደፓርቲነቱ ከለይ በዝርዝር ስለተብራራ አሁን እዚህ አንመለስበትም።

በምርጫ 97 የተወዳደሩና ከዚያም በኋላ የተፈጠሩ ፓርቲዎች በፕሮግራሞቻቸው ካሰፈሩአቸው ከዋና ዋና ተግባሮቻቸው አንዱ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመልስ መሥራት መሆኑን አረጋግጠዋል። በምርጫ 97 የአሰብ ወደ ኢትዮጵያ መካለል ፓርቲዎች ከሕዝቡ ድጋፍ ለማግኘት በሰፊው ከተጠቀሙባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ኢሕአዴግ ስለ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ያለው እጅግ የላላ አቋምና አሰብን ለኤርትራ አሳልፎ መስጠቱ ነበር ቢባል የተሳሳተ ግምት አይሆንም። አሁንም ቢሆን ብዙዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪክ ማህበራትና፣ሕዝባዊ ድርጅቶች አሰብን የማስመለስ ጉዳይ ሊሸሹት የማይችሉት ነገር ሆኖ በየፕሮግራሞቻቸው ቀርጸው ለዚሁ ግብ እንደሚሠሩ ቃል ገብተዋል።

## 9.2. በ1997 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ አሸንፎ የነበረው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ (ቅንጅት) በሕዝብ ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ሰዎች ለቅንጅት ድል ሞትን እንኳን የተጋፈጡበት ከብዙ ምክንያቶች አንዱ በብሔር ወይንም በዘር ያልተከፋፈለ በአንድነት የተሳሰረ ሙሉ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ያንፀባርቅ ስለነበር ነው። የዚህም መገለጫው በኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና የኢትዮጵያን ጥቅም በማስጠበቅ ቅንጅት የነበረው ጠንካራ አቋም ነበር። ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብን ከዳር እስከ ዳር ካንቀሳቀሰባቸው ከዋነኛ ፕሮግራምቹ አንዱ ሉዐላዊነትን የማስከበር ዓለማ የሆነውን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል የነበረው ቁርጠኝነት ነበር ቢባል ስህተት አይሆንም። ቅንጅት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለአሰብ ኢትዮጵያዊነት የነበረው ቁርጠኝት ሕዝቡ ጠንቅቆ ከማወቁም በላይ በሕዝቡ እንዲሰርጽ ለማድረግ ችሎ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በአገሩ ሉዐላዊት የሚነሳ ጥያቄ ያህል የሚቀሰቅሰው ምንም ነገር ያለ መኖሩን ያህል በዚሁ ምክንያት ቅንጅትን ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ አቀፈው። ከምርጫው ትንሽ ቀደም ብሎ በኢሕአዴግና በቅንጅት ተወካዮች መሃከል በተደረጉት ክርክሮች ለኢሕአዴግ በዝረራ መሸነፍ አንዱ ምክንያት ኢሕአዴግ በሉዐላዊነት ላይ የነበረው የተለሳለሰ አቋም በተለይም አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች በማለቱና አሰብንም ለማስመለስ ምንም ጥረት እንደማያዳርግ ግልጽ በማድረጉ ነበር።

በምርጫ 97 እና ከዚያም ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ የህዝቡ ጥያቄ ለዲሞክራሲ ለፍትሕና ለእኩልነት ብቻ አልነበረም። በይበልጥም የኢትዮጵያ ሉዐላዊነት መከበርንም ይጨምር ነበር። በዚያን ጊዜ በራፋችን ደርሰው በኢሕአዴግ የተቀለበሱት እነዚህ የዴሞክራሲ እሴቶች ጥያቄ እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከእነዚህ ጎን ለጎንና መሳ ለመሳ የቆመው የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ ነበር ማለት ይቻላል። በየምርጫ ወረዳዎች ከምርጫ መፈክሮችና ከተለጠፉ ፖስተሮች ውስጥ አሰብን ወደ ኢትጵያ የማስመለስ ጥያቄ ጎልቶ ይታይ ነበር። ለናሙና ያህል በጉራጌ ዞን በቸሀ ወረዳ በእምድር ከተማ ምርጫው ሁለት ቀን ሲቀረው የሆነውን እንጥቀስ ። ከሊቅ እስከ ደቂቅ የእምድብር ሕዝብ



የቅንጅት ተወዳዳሪዎችን ለመደገፍ ተነቅሎ ወጥቶ የቅንጅት ተወዳዳሪዎችን ያሳሰብ የነበረው የምግብ ወይንም የውሃ ወይንም የጤና አገልግሎት ጥያቄ ሳይሆን ሕዝቡ እዚያችው በፈጠረው ስንኝ

*የዛሬ ዓመት የዛሬ ዓመት*
*አሰብ የእኛ ናት*

እያለ በሚዘምረው ማሳሰቢያ ነበር። ሕዝቡ ይህንን ያዜም የነበረው ቅንጅት አሸንፎ ሥልጣን እንደሚይዝ እርግጠኛ ስለነበር፣ ቅንጅት ሲያሸንፍም አሰብን ያስመልሳል ከሚል ፅኑ እምነት ከመነሳት ነበር። የቅንጅት አመራሮች ይህንን የሕዝብ ስሜት ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር የምረጡኝ ዘመቻ ከመጀመሩ በፊት ባወጡት የቅንጅት የምርጫ ማኒፌስቶ የሚከተለውን አስፍረው ነበር።

*"የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ ሕጋዊና የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብም በሚገባ የሚገነዘበው ቢሆንም የገዢው ፓርቲ በያዘው የተሳሳተ አቋም ለውይይት እንኳን የሚቀርብበት እድል ተዘግቶአል። ስለዚህ ይህ ጥያቄ ከሉዓላዊነትና ከብሔራዊ ሕልውና ጋር የተያያዘ ሕጋዊ ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩ በሰላማዊ መንገድና በሁለቱ ሕዝቦች ስምምነት መፍትሔ እንዲያገኝ ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ድጋፍ እንዲሰጥ ጥረት ያደርጋል"*[156]

በማለት ቅንጅት አሰብን ለማስመለስ የወደፊት ትግሉን ቀይሶ ነበር። በግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ የሕዝቡ ድምጽ ዋጋ ተሰጥቶት ውሳኔው ተከብሮ ቅንጅት እንደ ሕዝቡ ውሳኔ ሥልጣን ቢረከብ ኖሮ ከቀዳሚ የቅንጅት አጀንዳዎቹ አንዱ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት የሆነችውን አሰብን ወደ ባለቤቱ ወደ ኢትዮጵያ ማስመለስና የቀይ ባህር አፋሮች አንድነት በማረጋገጥ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ማስከበር ነበር።

አሰብን ለማስመለስ የቅንጅት እንቅስቃሴ የሚጀምረው ከዲፕሎማሲ አቅጣጫ ይሆን ነበር። ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት በተለያዩ መድረኮች ይደግፉ የነበሩ

[156] የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የምርጫ ማኒፌስቶ፣ አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም

አሜሪካ፣ ፈረንሳይ ታላቋ ብሪታንያና ራሽያ አሁንም በቃላቸው ተገኝተው የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዲደግፉ መጠነ ሰፊ ዘመቻ ይከፍት ነበር። እንዲሁም በአፍሪቃ ተመሳሳይ ዘመቻ ተከፍቶ አገራቱ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ ይጠየቁ ነበር። ከዚያም መግባቢያ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ አማራጮች* ለኤርትራ አቅርቦ መደራደር በተቻለ ነበር።

ቅንጅት የዲፕሎማሲ ጥረቶችን አሟጦ ለኤርትራ የሚቀርቡ አማራጭ ሐሳቦች በኤርትራ ተቀባይነት ካላገኙ የመጨረሻው ሰላማዊ መንገድ ጉዳዩ ወደ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) በመውሰድ ከፍርድ ቤቱ ፍትሕ መጠየቅ ሌላው አማራጭ በሆነ ነበር።

ቅንጅት በምርጫ ማኒፌስቶውና በፕሮግራሙ የተገለጹት ለኢትዮጵያ ብሩህ ቀን ያፈነጥቃሉ የተባሉት ተግባራት በሥራ ላይ ሳያውል ሁሉም እንደሚያውቀው በኢሕአዴግ፤ በተለያዩ አካላትና ግለሰቦች በተፈጸመበት ደባ ምክንያት እጅግ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ፈረሰ። ከቅንጅት መፍረስ ጋርም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የማስመለስ ዕድል ለጊዜው ያከተመ ቢመስልም ወቅቱን ጠብቆ አንድ ቀን መነሳቱ ግን አይቀርም። ምክንያቱም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቁጥሩ ከመቶ ሚልዮን በላይ የሚሆነው ሕዝብ በእግር መንገድ እርቀት የሚገኘው ብቸኛ የባህር በሩ ተዘግቶበት ፀጥ ብሎ እንዲኖር መጠበቅ ከፍትሕና ከመልካም ጉርብትና ጋር የማይጣጣምና በተቃርኖ የሚቆም ሁኔታ ነው የሚሆነው። ከፍትሕ በተቃርኖ የቆመ ሁኔታ ሁሉ፤ጊዜ ይወሰድ እንደሆን ነው እንጂ በፍትሕ መሸነፉ የማይቀር ነው።

## 9.3. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት መድረክ

መድረክ እራሱና የመድረክ አባል ፓርቲዎች በኢትዮጵያ የባህር በር መብት ላይ የፀና አቋም ያላቸው ሲሆን ሁሉም በግልፅና በማያሻማ መልኩ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ እንደሚሠሩ በየፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ቀርፀውት ይገኛል።

*አንዳንድ አማራጮች በጽሑፉ መጨረሻ ተዘርዝረው ተተንትነዋል



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) በመለስተኛ ፕሮግራሙ የሚከተለውን አስፍሮአል።

*"ኤርትራውያን [ከወደብ] ጋር በተያያዘ ሊኖራቸው የሚችለውን ስጋት ለመቅረፍ እና ሁለቱም ወገኖች ተጠቃሚ ሆነው የሚወጡበትን የመፍትሔ አማራጮችን (መድረክ) ያፈላልጋል። ኢሕአዴግ መንግስት ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ላይ ያላት ከታሪክ ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እና ከፍትሐዊነት አንጻር የባለቤትነት መብትዋን ሳያስከብር ቀርቷል። ይህም በመሆኑ ሃገራችን ወደብ አልባ በመሆንዋ ምክንያት በአስከፊ ኢኮኖሚያዊና የፀጥታ ችግሮች ውስጥ እንድትገባ አድርጓል። ስለዚህ የአሰብ ወደብ ለኢትዮጵያ የምትገባ የባህር በር መሆንዋን በመገንዘብ በዚሁ ጉዳይ ከኤርትራ ጋር የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ጠንካራ ዘላቂ ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚገባ መድረኩ በፅኑ ያምናል። ለዚህ ስኬት ኢትዮጵያውያን በጽናት እንዲቆሙ ያለመታከት ይሠራል"*[157] በማለት ዕቅዱን ገልጸአል።

በአንድ ወቅት የአሁኑ የመድረኩ ሊቀመንበርና የአረና ፓርቲ መሪ አቶ ገብሩ አሥራት "አሰብ የኢትዮጵያ ንብረት እንደሆነ ሕጋዊም ታሪካዊም መረጃ አ ለን። .....በህጋዊና በፖለቲካዊ መንገድ ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ማድረግ እንፈልጋለን። መንግስቱ (ኢሕአዴግ) የአሰብን ጉዳይ ማንሳት ሰላምን ያናጋል፤ ጦርነት ይቀሰቅሳል ፤ኢትዮጵያን ከጎረቤቶችዋ ጋር ማቡጣበጥ ነው ብሎ ያምናል። መንግስት የሚከራከረው ለእኛ ነው ወይስ ለኤርትራ የሚለው ጉዳይ መነሳት ያለበት ይመስለኛል" በማለት መድረክ ስለ ባህር በር ያለውን አመለካከት አብራርተዋል። የመድረኩ አቋም ጠንካራና የማያወላውል መሆኑ ግልፅ ሲሆን ለባህር በር ያለ መታከት እንደሚሠራ ቃል ገብቶአል። ሆኖም ይህ መለስተኛ ፕሮግራም ከተዘጋጀ ወዲህ መድረክ አሰብን አስመልክቶ ምንም ያደረገው ነገር የለም። ምናልባት በአገራችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሰላማዊ ሰልፍ የመሳሰሉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን የማይፈቅድ ቢሆንም ከሰላማዊ ሰልፍ መልስ፣ ፅሁፎችን አውጥቶ ሕዝቡን ስለአሰብ ግንዛቤ ማስጨበጥ የባህር በር ጥያቄ ከሕዝቡ ሕሊና እንዳይወጣ የመሳሰሉ ነገሮችን በመሥራት የመሪነት ግዴታውን መወጣት ይጠበቅበታል።

[157] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ መለስተኛ ፕሮግራም አዲስ አበባ 2001ዓ.ም

## 9.4. የዓረና ትግራይ ለደሞክራሲና ሉዐላዊነት ፓርቲ (ዓረና)

የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋትና ወደብ አልባ መሆን ከሚቆጠቁጣቸው ኢትዮጵያውያን ውስጥ የዓረና ትግራይ ለዲምክራሲና ሉዐላዊነት (ዓረና) ፓርቲ መሪ አቶ ገብሩ አሥራትና አባላቱ ናቸው። በሚድያ አማካይነትም ይሁን በሌላ አጋጣሚ ወደ ሕዝብ በሚቀርቡበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ብሉም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የማጠቃን ጉዳይ ሳያነሱ ያለፉባቸው ጊዜያት የሉም ማለት ይቻላል። የዓረና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊም አቶ አስራት አብርሃም በጻፉት ከአገር በስተጀርባ 2003 ዓ.ም በተሰኘው መጽሐፋቸው ለኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ትኩረት በመስጠት የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የሚያስከትለውን ጉዳት በብዙ ቦታዎች ይተነትናሉ[158]። አቶ ገብሩ አሥራት ከሕወሓት መሪዎች አንዱ በነበሩበት ጊዜ ከተደረጉ ጥፋቶች ሁሉ የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን በቀዳሚነት ያስቀምጡታል። ከዚህ ቀደምም ለዚህ ጥፋት ከአንዴም ሁለቴ በድፍረት ወጥተው፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቃቸው ያስመሰግናቸዋል።

ዓረና ስለኢትዮጵያ የባህር በር መብት በፕሮግራሙ ሰፊ ቦታ ሰጥቶ አስተናግዶታል። በዚህ መሠረት ዓረና "ከዓለም አቀፍ ሕግጋትና ከታሪክ አንጻር [ኢትዮጵያ] ራስዋ ባለቤት ሆና የምታስተዳድረው የባህር በር እና መተላለፊያ (ኮሪደር) የማግኘት መብት እንዳላት ዓረና ያምናል[159]። የባህር በር ጠቃሚነቱ "ለኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን የአገር ደህንነትና ሕልውና ጉዳይ መሆኑንም ይገነዘባል"[160] ዓረና የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ለማስከበር የሚሠራ ሲሆን "በዴብልጥ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ በዲፕሎማሲያዊና ሰላማዊ ትግል [አሰብን ለማስመለስ] በጽናት እንዲቆም ያለ መታከት"[161] እንደሚሠራ ቃል ገብቶአል።

[158] አሥራት አብርሃም ዝኒ ከማሁ 16

[159] የዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉዐላዊነት ፕሮግራም ነሐሴ 22 ቀን 2002 ዓ.ም

[160] ዝኒ ከማሁ



## 9.5. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፖርቲ (ኢዴፖ)

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፖርቲ አሰብ በኤርትራ እጅ ወድቆ የኢትዮጵያ የባህር በር ተዘግቶ አገሪቷ ወደብ አልባ መሆን በአገሪቱ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከሁሉም ፖርቲዎች ቀደም ብሎ የተገነዘበ ሲሆን በተለያዩ ወቅቶች መግለጫዎችን በማውጣት ሰላማዊ ሰልፎች በተደረጉበት ጊዜያት ሁሉ የባህር በር መብትን በተለይም የአሰብን ኢትዮጵያዊነት አጉልቶ በማሳየት የሕዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር በብዙ ደክሞአል። የፖርቲው ሊቀ መንበር አቶ ልደቱ አያሌው በ1983 ዓ.ም. ለሪፖርተር ጋዜጣ እንደገለጹት "ይህን ፍትሐዊ ጥያቄዋን [አሰብ ወደ ኢትዮጵያ መታጠፍ ይገባዋል የሚለውን ማለት ነው] በአግባቡ በጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ሊታገል የሚችል ኃይል ባለመኖሩ እንጂ የኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት ዝግ አገር አትሆንም ነበር" በማለት ቁጭታቸውን ገልጸው የዛሬው ትውልድ ትግሉን ይጀምር፤ ቀጣዩ ትውልድ ደግሞ ይጨርሰዋል ሲሉ ተሰፋቸውን ገልጸዋል። ኢዴፖ እንዳጀማመሩ ሳይሆን በአሁን ጊዜ እንደሌሎቹ ፓርቲዎች ሁሉ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማጠፍ ምንም እንቅስቃሴ ሲያደርግ አይታይም። ይህም ፖርቲ በመጀመርያ የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት እንዳሳሰበውና እንዳስጨነቀው ያህል አሁንም በትግሉ አመራር እንዲሰጥ ይጠበቅበታል፡

## 9.6. የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር

አሰብ ወደ ኤርትራ እንዳይካለል ከፍተኛ ጥረት ካደረጉት የአፋር ሕዝብ የፖለቲካ ድርጅቶች የአፋር አብዮታዊ ዴመክራሲያዊ አንድነት ግንባር አንዱ ነው። የድርጅቱ ሊቀመንበር አቶ ማህሙድ ጋአስም በአውሮፖና በአሜሪካ እየተዘዋወሩ የአፋር ሕዝብ ከተቀሩት ኢትዮጵያውያን

[161] ክብሪት የካቲት 7 ቀን 1994

ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን የራሱ የሆነውን አሰብን ከነጣቂዎች ለማዳን ቆርጦ እንደተነሳና የአሰብ ጥያቄ የአፋሮች ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደሆነ አቶ ማህሙድ በተለያዩ ጊዜአት አስገንዝበዋል። አቶ ማህሙድ በመቀጠል "አፋር ኢትዮጵያዊ ነው። አሰብም የአፋር ነው" በማለት የኢትዮጵያ መንግሥት በቅኝ ግዛት ውሉች ተመስርቶ አሰብን እስከ ወዲያኛው አሳልፎ በመስጠቱ መብረጃ የሌለው ደም መፋሰስ እንዲከተል ከማድረጉ በፊት በኢትዮጵያዊነታችን የምናምን ዜጐችና ሰላም የሚሹ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ድምጻቸውን ሊያሰሙ የሚገባ የመጨረሻው ሰዓት ቢኖር አሁን መሆኑን አቶ ማህሙድ ጋአስም አሳስበዋል። አቶ ማህሙድ በመቀጠል ዘሔግ ተሰይሞ የኤርትራና የኢትዮጵያን የወሰን ውዝግብ የሚዳኘው ኮሚሽን የአፋርን ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና መብት ከግምት ሳያስገባ የሚያስተላልፈው ውሳኔ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ሊያሰፍን እንዳማይቻል ቀደም ሲል ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊና ለጸጥታው ምክር ቤትና ለሌሎችም ዓለም አቀፍ ተቋማት መልእክት ማስተላለፋቸውን ገልጸዋል[162]።

## 9.7. የኦሮም ብሔራዊ ኮንግሬስ ፓርቲ

የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ ሊቀ መንበር ተባባሪ ኘሮፌሰር መራራ ጉዲና የፓርቲአቸውን አቋም ሲገልጹ "የቅኝ ግዛት ውሎችን በተመለከተ የኢሕአዴግ መንግሥት የሚያቀርባቸው ክርክሮች አስደናቂና የሚያስገርሙ ናቸው። የፈረንጅ ጠበቃ ገዙም አልገዙም [ክርክሮቹ] የኤርትራ መሪዎች ቢያቀርቡአቸው ያምርባቸዋል" በማለት በተለመደው አዝናኝ አገላለጻቸው አስረድተዋል[163]።

[162] ክብረት የካቲት 7 ቀን 1994

[163] ጉኩሳት የካቲት 27 ቀን 1994 ዓ.ም ገፅ 3



## 9.8. የቀይ ባህር አፋር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት

የቀይ ባህር አፋር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ያሲን ሞሃመድ አብደላ የአሰብ ወደብ፣ የዳህላቅ ደሴቶችና ምጽዋን ጨምሮ በኤርትራ መያዛቸውን በመቃወም እነዚህ ግዛቶች በሙሉ የቀይ ባህር አፋሮች ንብረት መሆናቸውን የአውሮፓና የአሜሪካ ባለስልጣናትን አስገነዘቡ።

## 9.9. የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ

የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ ሊቀ መንበር ኢትዮጵያ የባህር በር እንደሚያስፈልጋት ከገለጹ በኋላ የአፋር ሕዝብና የመልክአ ምድር አቀማመጥ በኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ አሰብ የኢትዮጵያ ነውና ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነትዋን ማረጋገጥ እንደሚገባት ገልጸው ወደፊት በሰላማዊ መንገድ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ፓርቲአቸው እንዲሚሠራ ቃል ገቡ።

## 9.10. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር

አቶ ግርማይ ሐደራ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ ግንባር ሊቀ መንበር በ1985 ዓ.ም. በኤርትራ በተካሄደው ሬፈረንደም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይጠየቅ የኤርትራ ጉዳይ ሲወሰን ኢትዮጵያ በባህር በር ባለቤትነቷ እንዲያበቃለት መደረጉ ሕዝብን ያሳዘነና አንገት ያስደፋ ጉዳይ እንደነበረ እያስታወሱ ፓርቲአቸው አሰብን ለማስመለስ የሚታገልበት ስልት መንደፉን ገልጸዋል[164]።

## 9.11. የአፋር አብዮታዊ ዴምክራቲክ ግንባር (አርዱፍ)

- የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራቲክ የተባበሩት ግንባር (አርዱፍ) ሊቀ መንበር አቶ ሞሃመድ ገአዝ የኢትዮጵያና የኤርትራ የወሰን

[164] ዝኒ ከማሁ

ውዝግብ ጉዳይ የያዘው ዘሔግ የሚገኘው የድንበር ኮሚሽን የአሰብን የኢትዮጳያና የአፋር የተፈጥሮ የባህር በርነት ከግምት ውስጥ ካላስገባ ዳግመኛ ስህተት መፈጸሙን መረዳት እንዳለበት አስገንዝበዋል። [የመጀመርያው ስህተት የቅኝ ግዛት ውሎች ለውሳኔው መሠረት ማድረጉ ነው]። በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ድርጅቶችንና ተቆርቋሪ ዜጐችን አውሮፖና አሜሪካ በመመላለስ ሲቀሰቅሱ የነበሩት አቶ ሞሃመድ ገአዝ የድንበር ኮሚሽኑ አሰብን ወደ ወራሪዋ ኤርትራ ካካለለ የአፋር ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጳያውያን ወንድሞቹ ጋር በመሆን የተነጠቀው ወደቡን ለማስመለስ መስዋዕትነት ለመክፈል እንደሚገደድ ከአስገነዘቡ በኋላ ይህ ከመሆኑ በፊት ግን የድምበር ኮሚሽኑ አሰብን አስመልክቶ የማያሻማ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት አሳስበው ነበር። ድርጅታቸው አርዱፍም የአሰብን ጥያቄ ፍትሐዊነት ባለው መልኩ ካልተመለሰ ትግሉን እንደሚቀጥል ለመንግሥታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጸፉት ደብዳቤ ማስታወቃቸውን አቶ ሞሃመድ ገአዝ ገልጸዋል[165]።

## 9.12. የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅት

አቶ መለስና መንግሥታቸው የአሰብ ጉዳይ ያለቀለት ስለሆነ አትከራከሩ ቢሉንም ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት ሲመሠረት ጥያቄው መነሳቱ የማይቀር መሆኑ የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅት ዋና ጸሐፊ ገለጹ ።ዋና ጸሐፊው አቶ ቦጋለ አሰፋ ከአዲስ አድማስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የአሰብ ኤርትራዊነት ተቀበሉ ማለት መራራ ኮሶ እንደመጋት ነው ሲሉ ገልጸውታል። አቶ መለስ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውን ያልወገኑ መሆናቸውን የገለጹት ዋና ጸሐፊው አቶ መለስ የአንድን አገር አካል ቆርሶ ለሌላ የመስጠት መብት እንደሌላቸው አቶ ቦጋለ አስረድተዋል[166]።

---

[165]ጦቢያ የካቲት 14ቀን 1994 ዓ.ም

[166]አዲስ አድማስ ሚያዝያ 12 ቀን 1994



## 9.13. የሲቪክና፣ የኃይማኖት ተቋማት በውጭ አገር ያደረጉአቸው ትግሎች

### 9.13.1 በተለያዩ አካላት የተደረጉ ትግሎች

በውጭ አገር በተለይም በአሜሪካ የሚገኙ ልዩ ልዩ ኢትዮጵያውያን፤ የሲቪክና ሕዝባዊ ድርጅቶችና ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፤ ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አቢያተ ክርስቲያናት ካህናት፣ ሞአ አንበሳ የኢትዮጵያ የዘውድ ምክር ቤት አባላት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ የተግባር ሊግ ወኪሎች፣ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ተወካዮች፤ የትግራዊያን የዓለም አቀፍ የአንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ አባላት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሕብረት ፖርቲ ተወካዮች፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፖርቲ አባላት እንዲሁም ብዙ ኢትዮጵያውያን የተገኙበት በተባበሩት መንግሥታት ጽህፈት ቤት ደጃፍ እ.አ.አ የካቲት 8ቀን 1994 ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጐ ነበር። በዚህ ሰልፍ ተሰላፊዎቹ "የኢትዮጵያ የባህር በር አይዘጋም" "አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊት ግዛት ነች" "የአፋር ሕዝብ አንድነት ይከበር" "የአፋር ሕዝብ የራሱን ዕደል በራሱ የመወሰን መብቱ መከበር አለበት" የሚሉ በእንግሊዝኛ የተፃፋ መፋክሮችን ይዘው ነበር። በዚሁ ሰልፍ ኢዴፖ አሰባስቦት የነበረ 158 ሺህ ኢትዮጵያውያን የፈረሙት የኢትዮጵያ በባህር በር እንዳይዘጋ የተማጽኖ ዳብዳቤ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለሚስተር ከፊ አናን ተሰጠ፡

ከሰልፉ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ በቡድን በቡድን በመከፋፈል የጸጥታው ምክር ቤት አባላት ተወካዮች ቢሮ ድረስ በመሄድ የኢትዮጵያ የባህር በር በተመለከተ ታሪክን፤ ሕግንና የአካባቢውን ሰላም በዋቢነት በመጥቀስ ሰፊ ማብራሪያ ሰጡ። ይህ ጸሐፊ የአሜሪካና የፈረንሳይ ተወካዮችን ያነጋገረውን ቡድን በመምራት

ለብዙ ዘመናት ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሲኳትኑ የኖሩት አቶ ቸሩ ተረፈንና ሌሎችንም ጨምሮ አሜሪካኖች ቢሮ በማምራት ከአሜሪካኑ ባልሥልጣን ጋር በተደረገው ውይይት የአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ ኢፍትሐዊነት፣ ሊያስከትለው የሚችል መዘዝ እንዲሁም ለአሜሪካ መርከቦች ሰላማዊ እንቅስቃሴ ከአካባቢው ካሉ ወደቦች በሙሉ በኢትዮጵያ እጅ ያለች አሰብ ብቻ መሆንዋን አስረዳን። የአካባቢው ወደቦች በሙሉ ለሽብርተኞች የተጋለጡ ሲሆኑ ይህም ለአሜሪካ መርከቦች አደገኛ መሆኑን ገልፀን ከጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ዩኤስኤስ ኮል (USS Cole) የተባለው የአሜሪካን የጦር መርከብ በየመን ወደብ በኤደን አሸባሪዎች አፈንድተውት 17 አሜሪካኖች ሞተው 39 ቆስለው እንደነበረ አስገንዝበን፡ ስለዚህ በአካባቢው ለአሜሪካኖች አስተማማኝ ወደብ አሰብ በኢትዮጵያ እጅ ስትገባ መሆኑን ለማሳመን ጥረት አደረግን። የአሜሪካኑ ተወካይ በተመሰጦ ካዳመጠን በኋላ ይህንኑ በጽሁፍ እንድናቀርብለት በጠየቅን ጊዜ ጥያቄአችንን አስመልክቶ ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ የነበረ ጽሁፍ በእጃችን ስለነበር በሰጠነው ጊዜ የመገረም ስሜት በፊቱ ይታይ ነበር።

ያነጋገርናቸው የሌሎቹ አገራት የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት አባላት የአሜሪካኑም ጨምሮ የሰጡን መልሶች የሁሉም ተመሳሳይ ነበሩ ማለት ይቻላል። የተባበሩት መንግሥታት የነፃና ሉዐላዊ አገራት ተወካዮች ማለት የአምባገነኖችም ይሁን የዴሞክራሲያዊ መንግሥታት ስብስብ እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩ በኢትዮጵያ መንግሥት ለድርጅቱ እስካልቀረበ ድረስ ጥያቄዎቻችን ክብደት ያላቸው መሆናቸው ቢቀበሉም ለጥያቄዎቻችን አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጡን እንደማይችሉ ገለጹልን

## 9.13.2. የቀይ ባህር ድንበር አስጠባቂ ኮሚቴ

ይህ ኮሚቴ በአቶ በላይ አባይ አስተባባሪነት እ.አ.አ በ1993 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ተቋቋመ። የዚህ ኮሚቴ ዋና ዓላማውና ተግባሩ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን አስመልክቶ ለዓለም ሕብረተሰብና ለአሜሪካ ኮንግሬስ አባላት ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ በተለይም በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዲያስከብሩ



በኢሕአዴግና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሬፑብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ላይ ግፊት ለማድረግ ነበር። በዚሁ መሠረት ኮሚቴው "ጣልያን እራሱ ያፈረሳቸው ውሎች በሥልጣን ያለው መንግሥት እንደ ሕጋዊ ማስረጃ መጥቀሱን ትቶ በታሪክና በሕግ የአገሪቱ ንብረት የሆነውን የአሰብ ራስ ገዝ የቀይ ባህራችን ከሻቢያ ጋር በሚያደርገው ድርድር ወደ ኢትዮጵያ ማስመለስ እንደሚኖርበት በአጽንኦት በማሳሰብ" ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለምክር ቤቶቹ ደብዳቤ ጽፎ ነበር። ኮሚቴው በፋክስ ከዋሺንግተን ለተላከው ደብዳቤ ከጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች መልስ አለማግኘቱን ገልጾ መብቱን የተገፈፈ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነገ እንደሚጠይቃቸው አሳሰበ። በመቀጠልም ኢትዮጵያ በሕግና በታሪክ የራስዋ የሆነውን ወደብና እውራጃ እንደቀላል እቃ ለኤርትራ ሲሰጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም አለምንም ድርድርና ሕዝባዊ ውይይት ለሌላ ለጥቶ ኢትዮጵያ ለጥቃት ስትጋለጥ ኮሚቴው ዝም እንደማይል አሳሰበ። የተወካዮች ምክር ቤትም በታሪክና በሕግ የአገሪቱ የሆነውን ራስ-ገዝ አስተዳደር ቀርቶ የሕዝብ ንብረት የሆነውን ሁሉ የማስጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ኮሚቴው ጠቅሶ ከዚህ የበለጠ ኃላፊነት ሊኖር ስለማይችል ከሻቢያ ጋር በሚደረገው ድርድር የቀይ ባህራችንን ለማስመለስ የምክር ቤቱ አባላትና ምክር ቤቱ ይህንን ታሪካዊና ሕጋዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ኮሚቴው ጥሪውን አቅርቦአል[167]።

## 9.13.3. የኢትዮጵያውንና የአሜሪካውያን መድረክ (Ethiopian American Forum)

የኢትዮጵያንና የአሜሪካውያን መድረክ (Ethiopian American Forum) በአሜሪካ የተቋቋመ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና አሜሪካውያንን በአባልነት ያቀፍ ድርጅት ሲሆን እነዚህ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የአሜሪካን ዜጐች በአሜሪካ ለሚደረጉ የፌዴራልም ሆነ የክልል ምርጫዎች ገንዘብ

[167] "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀይ ባህር ድምበራችንን ለማስመለስ ግዴታቸውን እንዲወጣ ተጠየቀ" ሬፖርተር ህዳር 28 ቀን 1993 ዓ.ም

ስለሚያዋጡና ድምጽ ስለሚሰጡ በአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣናት ተሰሚነት ያላቸው ናቸው።

ይህም ድርጅት የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ያሳሰበው መሆኑን የዚህ ቡድን አባል ዶ/ር አርአያ ወልደጊዮርጊስ በጻፉት መግለጫ ገልጸዋል። በጹሁፋቸው ኢሕአዴግ ስህተቱን አምኖ አሰብን እንዲይዝ ያሳስባሉ። ይህንን ለማድረግ ኢሕአዴግ በአሁኑ ጊዜ እድል እንዳለውም ያመለክታሉ። አሰብን ለማስመለስ ኢሕአዴግ በሌላ መንግሥት እስኪ.ተካ መጠበቅ ሳይኖርብን አሁኑኑ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያስመልስ ኢሕአዴግን መማጠን አለብን ይላሉ፡ ኢትዮጵያ አሸባሪነትን ለመዋጋት እጅግ በጣም አስፈላጊአቸው ስለሆነች ምዕራባውያን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ድጋፋቸውን እንደሚለግሱ ዶ/ር አርአያ ያምናሉ። ስለሆነም ኢሕአዴግ ኤርትራን ከኢሣያስ አፈወርቂ የጭቆና ቀምበር ነፃ አውጥቶ መላው የአፋር ሕዝብ ውሳኔ እንዲያደርግ ቢፈቀድለት የአፋር ሕዝብ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር እንደሚቀላቀል አይጠራጠሩም። በመሆኑም ዶ/C አርአያ ኢትዮጵያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አሜሪካኖች ኢሕአዴግ ከላይ የተጠቀሱትን እርምጃዎች እንዲወስድ እንዲማጠኑ ያሳስባሉ።[168]

## 9.13.4. የዛላአንበሳና የኢሮብ አካባቢ ጊዜያዊ ኮሚቴ

ይህ ኮሚቴ በበኩሉ ባወጣው መግለጫ የአልጀርስ ስምምነት የኤርትራን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ያለመ ነው ብሎታል። የኢሮብ፣ የጾረና፣የኩናማ፣ የዛላአምበሳን እና የአፋርን ሕዝብ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የባህር በር ባለቤትነት መብት ያላወቀ ውሳኔ በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ያለው ችግር በዘላቂነት እንደማይፈታ በመግለጫቸው አስገንዝበዋል[169]።

---

[168] See www.ethiopianamerikcanforum.com, Accessed on 29 April 2011

[169] ዝኒ ከማሁ



## 9.13.5. የትግራውያን ዓለም አቀፍ ትብብር ለፍትሕና ለዴሞክራሲ

የትግራውያን ዓለም አቀፍ ትብብር ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በጻፈው ደብደቤ የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በተለይም የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የሚቃወም መሆኑን ገልጾአል[169]።

በአሁኑ ወቅት እነዚህ ድርጅቶችና ተቋማት የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እውን ለማድርግ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የቀዘቀዘ ነው። ሆኖም ግን ይህ ጉዳይ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሥነ ልቦና ተቀርጾ የሚገኝ ነገር ነው። ምናልባትም ይህ ችግር በአንድ ጀምበር የሚፈታ ሆኖ ኢትዮጵያ በቅርብ ቀን የባህር በር ባለቤት ላትሆን ትችላለች። ሆኖም ግን ጊዜ የሚያመጣው አይታወቅም ዋናው ነገር ይህንን የባህር በር ባለቤትነት ጉዳይ ጊዜ እስኪፈታው ኢትዮጵያውያን ከልባቸው እንዳይፍቁትና የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ያስፈልጋል። የዚህም ኣላፊነት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነው።

---

[169] ሪፖርተር ዝኒ ከማሁ 166.


HAP15
502
43E

## ምዕራፍ 10

# 10. አሰብ - የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር

## 10.1 አሰብና ታሪኳ

በአንድ ጉዳይ በፍሬ ነገሩ ለመስማማት በቃላት ትርጉም የጋራ ግንዛቤ መጨበጥ የግድ ይላል፤ ስለሆነም "አሰብ" ስንል ምንን እንደሚያካትት፣ "የባህር በር መብት" ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ መግለፅ ያስፈልጋል። በተለምዶ አነጋገር "አሰብ" ሲባል ብዙዎች ቃሉ ወደቡን ብቻ የሚሸፍን አድርገው ይወስዱታል። በዚህ ፅሁፍ "አሰብ" ስንል ግን ከወደቡ ዓለም አቀፍ የባህር በር ሕግ እንደሚደነግገው 12 ኖቲካል ማይልስ ወደ ባህር ዘልቆ ገብቶ ላይ ታቹን የባህርና የመሬት አካባቢን (Red Sea littoral) የሚሸፍን ሲሆን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት "የአሰብ አውራጃ"፤ በደርግ ዘመን ደግሞ "የአሰብ ራስ ገዝ" ይባል የነበረውን ውሀውና መሬቱን ደሴቶቹንም ያጠቃልላል።

እንዲሁም በተለያዩ ፅሁፎች፤ በተባበሩት መንግስታ ሰነዶችም ጭምር "የኢትዮጵያ ወደ ባህር የመዝለቅ መብት" (access to the sea) የሚል ሐረግ ይነበባል። ይህም ማለት ኢትዮጵያ በራስዋ ወደብ በአሰብ አድርጋ ወደ ባህር መዝለቅ ማለት እንደሆነ አንባብያን ሊገነዘቡት ይገባል። ወደብ አልባ አገር ባለወደቡ አገር የሚጠይቀውን ክፍያ እስከ ፈፀመና ሌሎችም ባለወደቡ አገር የሚያስቀምጣቸውን ሕጋዊ ግዴታዎችን እስካሟላ ድረስ በሌላው አገር ወደብ የመጠቀም መብት በተለያዩ [illegible] አቀፍ ሕጎች የተደነገጉ ስለሆነ ኢትዮጵያም ይህ መብት ከመላው ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ጋር የምትጋራው በመሆኑ በጅቡቲ አድርጋ ወደ ባህር ለመዝለቅ የተለየ ፈቃድ አያስፈልጋትም[171]።

[171] See Vienna Convention on the Law of the Sea, Article 25, 1982



ስዊዝ ካናል በወደብነት ተዘጋጅቶ ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ የጣልያን መርከቦች የሚያርፉበት አንድ የንግድ ማዕከል፤የሽቀጣሽቀጥ፤ የነዳጅና የከሰል መጋዘን፣ ወደ ሩቅ ምስራቅ ለሚመላለሱ መርከቦችም ማረፊያ የሚያገለግል ወደብ በቀይ ባህር ማግኘት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተረድቶ አመቺ ወደብ ፍለጋ ቀይ ባህርን ሲያስስ የነበረው የካቶሊክ ቄስ ጁሴፔ ሳፔቶ ከጓደኛው ከአክተን ጋር በ1869 አሰብ ደረሰ[172]። በታው ለፈለጉት ግልጋሎት ተስማሚ ሆኖ ስለአገኙት ከመሬቱ ባለቤቶች ከወንድማማቾቹ ከሱልጣን ኢብራሂም በን አህመድ እና ከሱልጣን ሀሰን በን አህመድ በአሰብ የሚገኝ አንድ ትንሽ ቦታ በስድስት ሺህ ማርያ ቴሬዛ ብር ለመግዛት ተስማሙ። ገዥው የተከናወነው በሩባቲኖ ኩባንያ ስም ነበር[173]።

ከአሰብ ፊት ለፊት የሚገኙ ደሴቶችንም ከአሰብ ጋር መቀላቀል ቄሱ አስፈላጊ ሆኖ ስለአገኙት ከደሴቶቹ ባለቤት ከሱልጣን አብደላ ሃሺም ጋር ተስማምተው ሦስቱም ሱልጣኖች እኩል የሚካፈሉት 8100 ማርያ ቴሬዛ ብር ሲቀበሉ የሩባቲኖ ኩባንያ ወዲያውኑ ከራስ ሉማህ አላላህ ተብሎ ከሚጠራው የባህር ዳርቻ እስከ ጋንጋ ተራራ ድረስ ያለውን መሬትና ደሴቶቹን ተረከበ። የጣልያን ባንዲራም ተሰቅሎ 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ። የቀረው ነገር ከአሰብ ፊት ለፊት ይገኙ የነበሩት ሌሎችም ዋና ዋናዎቹ ደሴቶች ጣልያኖች መያዝ ስለፈለጉ የደሴቶቹ ባለቤት ብርሃን ከሚባለው የራሄይታ ሱልጣን ጁሴፔ ሳፔቶ ደሴቶቹን ገዛ። ሳፔቶ በ1870 ዓ.ም ወደ አገሩ ሲመለስ ጥሩ አቀባበል ቢያገኝም ቅሉ የጣልያን ጋዜጦች፤ መፅሔቶችና የፖለቲካ ሰዎች አሰብ የተቃጠለ አገር ነው፤ ሙቀቱም ኃይለኛ በመሆኑ ሰው ሊኖርበት አይችልም፤ ዕጽዋትም አያበቅልም እያሉ ተዘባበቱበት[174]።

[172] ዶ/ር ተወልደ ትኩዕ ዝኒ ከማሁ 31 ገፅ 195.

[173] ዝኒ ከማሁ

[174] ዝኒ ከማሁ ገፅ 196

አሰብ ለ10 ዓመት በሙሉ ተረስቶ ከቆየ በኋላ የኢጣልያ መንግስት ከሩባቲኖ ኩባንያ ተረክቦት በአፍሪካ ቀንድ የመጀመሪያዋ የጣልያን ቅኝ ግዛት ሆነች፡፡

አሰብ የሩባቲኖ ኩባንያ ሲገዛው ከዚያም በኋላ ለብዙ ጊዜ ትንሽ መንደር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ጣልያኖች ሲገዙት በቀይ ባህር ለሚተላለፉ የጣልያን መርከቦች ከሰል ለማቅረብ አስበውት ስለነበር ለወደብነት እምብዛም ትኩረት አልሰጡትም ነበር፡፡ በአካባቢው ከነበሩ ወደቦች የጣልያኖችን ትኩረት የሳበው ምፅዋ ስለነበር ምጽዋን በወደብነት ማሳደግ ተያያዙት፡፡ በ1920ዎቹ አካባቢ በአሰብና በዙርያው ይኖር የነበረው ሕዝብ ከሦስት ሺህ የማይበልጥ ሲሆን ከእነዚህም አውሮፓውያን በተለይም ጣልያኖች ከ100 እስከ 140 ይደርሱ እንደነበር ተዘግቦአል[175]፡፡

የጣልያኑ ካቶሊክ ቄስ ሳፔቶ ለሩባቲኖ ኩባንያ አሰብን በገዛበት ጊዜ አሰብ የኢትዮጵያ አካል እንደነበረች አንድ የአፋር ፀሀፊ ዘግቦአል[176]፡፡ አፄ ምኒልክም የኢትዮጵያን ዳር ድምበር ለዓለም ሕብረተሰብ ለማስታወቅ ለንግሥት ቪክቶሪያ በፃፉት ደብዳቤ የአፋሩ ሱልጣን "ጥንታዊ ዜጋቸው" መሆኑን ግዛታቸውም በምሥራቅ በኩል የቀይ ባህርን ይዞ ደቡብ እንደሚደርስ አስታውቀው ነበር፡፡

በጊዜው በነበረው የመገናኛ ችግሮች የአፋር በረሃማነትና ከማዕከሉ በመራቅ እንደዛሬው የኢትዮጵያ መንግሥት በአፋር ላይ ሙሉና የቀን ተቀን ቁጥጥር ነበረው ማለት ባይቻልም የአፋር ባላባቶችን ግብር ማስከፈሉ አፋር የኢትዮጵያ አካል ነበረች ሊያሰኝ የሚችል በቂ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም የአፋር ሱልጣን አሰብን ለሌላ መንግስት አሳልፎ የመስጠትም ሆነ የመሸጥ መብት አልነበረውም፡፡ ሱልጣን ኢብራሃምም አሰብን ለጣልያኖች በመሸጡ "ሱልጣን ኢብራሂም አሰብን የሸጠ" በመባል በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ ከሃዲ ተቆጥሮአል፡፡ በጊዜው በዚሁ በምሥራቅ ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ይሯሯጡ የነበሩት የቱርኮች ተጠሪዎች ግብጾች

[175] Richard Pankhurst, An Introduction to the Economic History of Ethiopia From Early Times to 1800 (1961), p.307

[176] የግርጌ ማስታወሻ ቁ.36 ማየት ይቻላል



የአፋር ሱልጣን አሰብን የመሸጥ መብት የለውም በማለት ሽያጩን ተቃውመውት ነበር፡፡

አሰብን የገዛው የሩባቲኖ ኩባንያ አሰብንና ደሴቶቹን በሙሉ ለጣልያን መንግስት አስረክቦ "የጣልያን ቅኝ ግዛት" ተብለው በጣልያን መንግሥት እጁ ገቡ፡፡ በዚህ ጊዜ ጣልያን በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ ሁለት ቅኝ ግዛቶች ነበሯት ማለት ነው፡፡ ሩባቲኖ ኩባንያ አሰብን ከገዛ ከአሥር ዓመታት በኋላ "አሰብ የጣልያን ቅኝ ግዛት" የሚለውን ስም ቀርቶ እ.ኤ.አ. በጃንዋሪ 1ቀን 1890 ዓ.ም በቀይ ባህር የሚገኙ የጣልያን ይዞታዎች "የኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች" ተብለው አንድ ላይ ተጠቃለሉ፡፡ በጊዜው አሰብ በጣልያን እጅ እንዳትገባና የጣልያን ቅኝ ግዛት እንዳትሆን የተቃወሙ ጣልያኖችም ነበሩ[176]፡፡

የሩባቲኖ ኩባንያ አሰብንና ደሴቶቹን ሲገዛም ሆነ ወደ ጣልያን መንግሥት ሲያስተላልፈው ኢትዮጵያ የምታውቀው ነገር አልነበረም፡፡

አሰብ ከቀረው ኤርትራ ተለይታ ጣልያኖች ቅኝ ግዛት ሲያደርጉአት ከኤርትራ በባህልም ሆነ በዘር ወይንም በቋንቋ የተለየች አገር ነበረች፡፡

አሰብ ከምፅዋ ወይንም ከዘይላ ጋር ስትወዳደር በዕድሜ ለጋ ወደብ ነች ማለት ይቻላል፡፡ እድገትዋም ከስዌዝ ካናል መከፈትና ከአፄ ምኒልክ የግዛት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው[177]፡፡

አሰብ ኤርትራ በጣልያን ግዛት ስር በነበረች ጊዜ ሳይቀር ትስስርዋ ከወሎ ጋር እንጂ ከኤርትራ ጋር አልነበረም፡፡ ጣልያን ኤርትራን በሚያስተዳድርበት ጊዜ ሁሉ የቀይ ባህር አፋሮች በሙሉ ግንኙነታቸው ከሃይማኖት መሪአቸው ከአውሳው ሱልጣን ጋር ሆኖ በመሃከላቸው የወሰንም ሆነ የአስተዳደር ልዩነት እንዳልነበረ የአፋር አዛውንቶች ይናገራሉ፡፡ አሰብ ከደሴ ጋር

[176] Moges Solomon, supra note 91.

[177] ዶ/ር ተወልደ ገዛ ከማሁ 31 ገፅ 158.

በመኪና መንገድ ስትገናኝ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከአሥመራ ጋር የሚያገናኛት መንገድ ስላልነበረ ከአሰብ አሥመራ ለመሄድ ከአሰብ ወደ ደሴ ተመልሶ ከዚያ በኋላ ነበር ወደ አሥመራ ማቅናት ይቻል የነበረው።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንግሊዞች ኤርትራን ለአሥር ዓመታት ከአስተዳደሩ በኋላ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መሃከል ፌዴሬሽን ተመሥርቶ ኤርትራን ለቅቀው ሲሄዱ ፋብሪካዎችን ነቃቅለው ሕንጻዎችን አፈራርሰው ሊሸጥ የሚቻለውን ሁሉ ለጐረቤት ሱዳን ሲሸጡ የባቡር ሃዲዱም አልቀራቸውም ነበር። የወደብ መሣርያዎችንም ከምጽዋና ከአሰብ እየነቃቀሉ ወስደው የደረቅ ወደብ መገልገያዎችን (dry docks) በታትነው ለሱዳን ስለሸጡ አሰብ በፌዴሬሽን ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ስትዛወር ምንም ዓይነት የወደብ ግልጋሎት ልትሰጥ የማትችል "የወደብ ምድረ በዳ" ነበርች ማለት ይቻላል[179]።

## 10.2. የአሰብ እድገት

አሰብ ከኢትዮ-ኤርትራ ፌዴሬሽን በፊት እዚህ ግባ የማይባል ጥቅም ብቻ የምትሰጥ ማንም ትኩረት ያልሰጣት ትንሽ ወደብ ነበረች። የተሟላች ወደብ ሆና ማገልገል የጀመረችው ከአርባ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ እጅ ከገባች ወዲህ ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራ ፌዴሬሽን እንደፈረሰ አሰብን በሰፊው መገንባትና ማስፋፋት ተጀምሮ በመጀመርያ ሞግራድ በሚባል የየጉዝላቪያ ኩባንያ ሥራው ሲጠናቀቅ ለዚህም ሥራ 26 ሚሊዮን ብር በዛሬው ተመን ምናልባት ከ260 ሚሊዮን ብር በላይ ኢትዮጵያ ወጪ አውጥታለች[180]።

በደርግ አገዛዝ ዘመንም ወደቡ ከፍተኛ መሻሻል ተደርጎለት እንደነበርና ለዚህም ከመነሻው ጀምሮ ኢትዮጵያ ለአሰብ ግንባታ እስከ 3 ቢልዮን ዶላር የሚደርስ ወጪ እንዳደረገች በአንድ ወቅት የአሰብ አውራጃ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ጌታቸው በቀለ ለዚሁ ጸሐፊ ገልጸውለታል። ቀጥሎም ወደ አንድ ሚልዮን የሚጠጉ

[179] Shumet Sishagne,Professor, supra 43 P.53
[180] Ibid



ኢትዮጵውያን ያሰቁበት ትልቁ ረሃብ በተከሰተ ጊዜ የእርዳታ እህል ለማስተላለፍ ብቁ እንዲሆን አሰብ በብዙ ሚልዮን ደላር የሚጠጋ መሻሻል ተደርጐለታል[181]። በተጨማሪም ኢሕአዴግና ሻቢያ በፍቅር እፍ ባሉበት ወቅት ኢትዮጵያ ከሚሌ እስከ አሰብ ድረስ የሚወስደውን መንገድ በራስዋ ወጪ አሠርታ መንገዱን የሠራው የፈረንሳይ ኩባንያ ገንዘቡ ስላልተከፈለው ኢትዮጵያን ከስሶ እንደነበረ ይታወሳል። ለዚህ መንገድ ኢትዮጵያ ወደ 25 ሚልዮን ዶላር ወጪ እንዳደረገች ይነገራል። ኢትዮጵያ በአሰብ ከተማ የተለያዩ የመንግሥት ሕንፃዎችን፣ መንገዶችን፣ ተማሪ ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችንና መርከብ ማሳረፊያዎችን እንዲሁም አንድ ትልቅ የነዳጅ ማጣርያ አሠርታ ነበር። ለእነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያ በብዙ ቢልዮን ዶላር የሚገመት ወጪ ያወጣች ሲሆን ለዚህ ሁሉ ንብረት ኤርትራ አሰብን ስትወስድ ቤሳ ቤስቲኒ ለኢትዮጵያ አልከፈለችም። እንዲያውም አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት እስከ ዛሬ አሰብን በነፃ ስተጠቀምንበት ኤርትራውያን ሂሳብ እናወራርድ እንዳይሉን ስጋታቸውን ገልጸዋል። አሰብ ከፌዴሬሽኑ በኋላ በተደረገላት መሻሻል ትላልቅ መርከቦችን ለማስተናገድ ችላ ለመሃሉና ለደቡብ ኢትዮጵያ ዋናዋ የባህር በር ሆና ታገለግል ነበር።

ወደቡ ከነበረበት በጣም አድጎ ኢትዮጵያ ለቅቃው ስትወጣ በዓምት 2.8 ሚሊዮን ቶን ጭነት ሊያስተናግድ የሚችል አቅም ነበርው። በአሁን ወቅት አሰብ ዘመናዊ ከተማ ስትሆን በውስጥዋም ብዙ መስኪዶችና ቤተክርስቲያናት፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የሕዝብ መገልገያዎች፣ የተሟሉ መንገዶች ሲኖሩአት፣ ከኢትዮጵያም ጋር በአስፋልት መንገድ ተያይዛለች። የአሰብ ወደብ በአሁን ጊዜ ሰባት ትልልቅ መርከቦች ሊያቆም ሲችል ባህረ ሰላጤው በጣም ትራፊክ ከሚበዛባቸው የዓለም ባህረ ሰላጤዎች አንዱ ነው። አብዛኛዎቹ በቀይ ባህር የሚያልፉ መርከቦች በአሰብ በኩል አድርገው ሲሆን በዓመት ወደ 20,000 የሚጠጉ መርከቦች

[181] Panel Vallily "Assab, "The Life line that could Feed Ethiope, Report from Assab", May 1, 2000.

7,000 ሚልዮን ቶን (ሰባት ቢልዮን) የሚጠጋ ጭነት ይዘው ይገዛሉ[182]።

## 10.3. ጁቡቲ አሰብን አትተካም

የጅቡቲን ወደብ መጠቀም ከብዙ ችግሮች ጋር ተያይዞ ይመጣል። በመጀመርያ የጅቡቲ እርቀት ከአሰብ ጋር ሲመዛዘን ለመሃል አገሩ በይበልጥም ለሰሜን ኢትዮጵያ በጣም ሩቅ ከመሆኑም በላይ ይኸም ለመኪና ሹፌሮች አድካሚ ሲሆን የትራንስፖርት ወጪውንም ያንረዋል። የጅቡቲ የወደብ አገልግሎት ታሪፍ በሌላ ቦታ እንደተጠቀሰው እለት በእለት እየጨመረ መሄድ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋ አስወድዶአል። በአሁኑ ወቅት ለተከሰተው እና ሕዝብን ለከፍተኛ ስቃይ የዳረገው ከውጭ ለሚገቡ ዕቃዎች የዋጋ ንረት የወደብ ታሪፍ መጨመር አስተዋጽኦ እንዳለው አያጠያይቅም። በጅቡቲና በኢትዮጵያ መካከል ታሪፍን አስመልክቶ የጋራ ስምምነት ቢኖርም ጅቡቲ ስምምነቱ ከመጤፍ ሳትቆጥር የወደብ አገልግሎት ታሪፍ የጨመረችባቸው ጊዜአት አሉ። በአንድ ወቅት ይህንን ጭማሪ ለማሰረዝ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር እራሳቸው ጅቡቲ ድረስ በመሄድ የተጣለው ታሪፍ እንዲነሳ ማድረጋቸው ይታወሳል።

ለጉምሩክ ሠራተኞች 'ትርፍ ሰዓት እየተባለ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉ ነው። በጅቡቲ ወደብ ላይ ስለሚሰረቁና ብልሽት ለሚደርስባቸው የኢትዮጵያ ዕቃዎች የወደቡ ሠራተኞች ኃላፊነቱን አይወስዱም[183]። ጭነት ወደ ኢትዮጵያ በሚያጓጉዙ ሹፌሮች ላይ የሚደርሰው ወከባና እንግልት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ የዘር መድልዎ እንደሚደረግባቸው ሹፌሮቹ በተለያዩ ጊዜአት ተናግረዋል[184]። ጌት ፓስ (gate pass) ዴመሬጅ (demurrage) ስቶሬጅ (storage) እያሉ የሚያስከፍሉት በየ15 ቀናት ይቀይሩታል። ሱር ታክስ፣ ባጌጅ ታክስ፣ ሪቬንዩ ታክስ፣ የክሬን ኪራይ እያሉ በየጊዜው የሚጨምሩት ክፍያ ጅቡቲ ወደብን የሚያስተዳድረው ዱባይ ወርልድ ኩባንያ በቀውስ ውስጥ በመሆኑ በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀስ ሲሆን እንቅስቃሴው የዘረፋ ዓይነት መሆኑን አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ አስገንዝበዋል[185]።

ከዚህም አልፎ የጅቡቲ ወደብ በአሁኑ ወቅት በችግር ላይ መሆኑ ይነገራል። ወደቡን ለማስተዳደር እ.አ.አ. ጁን 20 ቀን 2000 ዓ.ም የሃይ ዓመት ውል ከጅቡቲ ባለሥልጣናት ጋር የተፈራረመው የዱባይ የዓለም ወደብ ኩባንያ ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቁ ተዘግቦአል። ውሉ እንዲሰረዝለት የጠየቀበት ምክንያት በእርግጠኝነት ባይታወቅም ኩባንያው ለጅቡቲ ባለሥልጣናት የገባቸው ቃል አክብሮ ባለመገኘቱ ነው ይባላል[186]።

## 10.3. ኢትዮጵያ የባህር በር (አሰብ) እንዳይኖራት የሚጠነሰሰው ሤራ

ግሬጎሪ ኮፕሌይ (Gregory Kopley) የተባለ የአፍሪካ ኤክስፐርት ጋዜጠኛ ስለ ኢትዮጵያና ግብጽ ግንኙነት ሲጽፍ የሚቀጥለውን አስፍሮአል። "የግብጽ የአፍሪካ ቀንድ ዋነኛው ፖሊሲ ኢትዮጵያ በአካባቢው የበላይነት እንዳይኖራት ከባህሩ ዙርያ ማግለል ነው። ይህም ዓላማዋ በኤርትራና በኢራን አማካይነት እያስፈጸመች ነው። ግብጽ የኤርትራ የነፃነት ንቅናቄዎችን በመርዳት ቀደም ሲል የኢትዮጵያ የባህር ኃይል ይቆጣጠረው የነበረው የቀይ ባህር ደቡብ ክፍል ከኢትዮጵያ እጅ በማውጣት ኤርትራ ነፃ እንድትወጣና ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር አካባቢ ተገልላ በተፈጥሮም ሆነ በባህልም መቼም የኤርትራ አካል ሆና የማታውቀው አሰብንም እንድታጣ አደረገቻት[187]። ግብፅ

---

182 Araia Tseggai የኤርትራ ወደቦች አላፊ ሀአንድ ኤርትራ የወሬ ወኪል የሰጡት ማብራርያ

183 በዛብህ አስፋው ዶ/ር ከፍጥጫው በስተጀርባ አዲስ አበባ የነቲት 1997 ገጽ 83-84.

184 ከአቶ በለጠ ማሞ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፤አዲስ አበባ (ጥቅምት 20 ቀን 2003) ዓ.ም

185 አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብርአናንያ ዝኒ ከማሁ: 24.

186 "Djiboutl Port may Dirorce DPWorld, Capital Vol. 13. No 65 1 june 15,2011.

187 Copley Gregory R. "Transforming the Åge of Gas Begins in Earnest""http://oibprice_.com_geo_politics/Africa_Energy_and_Security, Accessed 21 February 2011.

የአረብ መሪነትዋ በመጠቀም ሱዳን ፣ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ የመን፣ ሊብያና ሳውዲ አረቢያን በማቀነባበር ኢትዮጵያን ለማዳከም በመጣር ላይ ነች። ግብጽ ይህንን የምታደርገው ጠንካራ ኢትዮጵያ በአባይ ውሃ ላይ ያላት መብትና የባህር በር መብትዋን ልታስከብር ትችላለች ከሚለው ፍራቻ በመነሳት ነው። ግሬጉሪ ኮኘሌይ በመቀጠል እንደሚሉት አሁን ኢትዮጵያ ምንም ነገር ወደ አገርዋ ለማስገባት ብትፈልግ የጅቡቲ በጎ ፈቃድ ያስፈልጋታል። ስለሆነም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ጦርነት ቢፈነዳ ግብጽ በጦርነቱ በግልጽ በመግባት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የነበራትን ሥፍራ መልሳ እንዳትይዝ መከላከልዋ አይቀርም በማለት ይገልጻሉ።[188]

በመቀጠልም አሰብ አካባቢ የሚገኘው የአፋር ህዝብ የግድ ከኤርትራ ጋር በመቀላቀሉና በኤርትራ ቁጥጥር ስር በመዋሉ ከፍተኛ ቅሬታ እንደተሰማውና ከኤርትራ ቁጥጥር ለመውጣት ብረት አንስቶ እንደሚፋለም ኮፕሌ ፅፈዋል።[189] በጥቅምት 2003 ዓ.ም አቶ መለስ ዜናዊ ግብጽ በአባይ ወንዝ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ብትከፍት እንደማታሸንፍና ጦርነት የከፈቱም እንዳላዘለቀላቸው ከገለጹ በኋላ ግብጽ የኢሕአዴግ መንግስትን ለማናጋት ተቃዋሚዎችን ትረዳለች በማለት በከሰሱ ማግስት የኤርትራው ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ግብፅ ሄደው ከግብጽ ፕሬዝዳንት ሙባራክ ጋር በካይሮ ተገናኝተው መመካከራቸው የኮፕሌን አባባል አመኔታን ያጐናፅፈዋል።

ከሞምባሳና ለኢትዮጵያ ግልጋሎት እየተዘጋጀች ነች ከምትባለዋ የኬንያ ወደብ ላሙ በስተቀር ሌሎች ኢትዮጵያ ልትጠቀምባቸው የምትችል ወደቦች በሙሉ በአረብ ሊግ ውስጥ ሲሆኑ በድንበር አቋራጭ ወንዞችዋ ወይንም በሌላ ምክንያት ኢትዮጵያ ከአንድ አረብ ጋር ,በተለይም ከግብጽ ጋር ውዝግብ ውስጥ ብትገባ ግብጽ በአረብ አገሮች ላይ ባላት ተሰሚነትና የአረብ ሊግ አባላት ባላቸው ስምምነት መሠረት የአካባቢው ወደቦች በሙሉ ለኢትዮጵያ ዝግ ሊሆኑ ይችላሉ፡

[188] Ibid

[189] Ibid



የጅቡቲ ወደብ የሚተዳደረው በአንድ የዱባይ ኩባንያ ሲሆን ነገ የወደቡ አስተዳደር ወደ ግብጽ ቢዞርስ የሚለውን ማሰብ ብቻ ብቻ ለኢትዮጵያ ዝግ ቢሆን በኢትዮጵያ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ችግር መገመት አስቸጋሪ አይደለም።

ኢትዮጵያ በሕዝብም ቁጥር ብዛት ፣ባላትም የመሬት ስፋት በጠቅላላው ተፈጥሮ በለገሳት እምቅ ሃብትና በሕዝብዋ ታታሪነት የራስዋ የባህር በር ቢኖራት ታላቅ አገር የመሆን እድል ይኖራት ነበር። ወደብ አልባ ሆና ግን ድህነትን እንኳን ማሸነፏ እጠራጣሪ ሲሆን ድህነትን ብትቀንስም እንኳን በዘለቄታ እይታ ታላቅ አገር ልትሆን አትችልም። ወደብ አልባ ሆኖ ታላቅ የሆነ አገር የለም።

ኦስትሪያ፣ ስዊዘርላንድና ሉክሰምቡርግ ወደብ አልባ ቢሆኑም ሀብታም እንጂ ታላቅ የሚባሉ አገራት አይደሉም። እነዚህ አገራትም ቢሆኑ ጐረቤቶቻቸው ሃብታሞች በመሆናቸው በቅርባቸው ሰፋፊ ገበያ ከመኖሩም በላይ የመገናኛ አውታሮቻቸው የደረጁ ሲሆኑ ግንኙነታቸውም በሰለጠነ መንገድና በሕግ ተደንግጐ የተያዘ ስለሆነ እነዚህ ሦስት አገራት በወደብ አልባ ከሆኑ አገራት ጐን ማሰለፍ አይገባም።

## 10.4. አሰብ ፣ሰላምና ልማት፣ የቀይ ባህር አፋሮች ኢትዮጵያዊነት

የልማት ሊቃውንት ለአንድ አገር መበልጸግ በአገሩ ለረጅም ዓመታት የሰላም መስፈን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ይገልጻሉ። ለልማት ሊውሉ የሚችሉ ግብዓቶች እንደልብ ቢገኙ ሰላምና መረጋጋት ከሌለ ልማትና ብልጽግና ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ነው። ኢትዮጵያ ሳያቋርጥ ተያይዞ ለረጅም ዓመታት ይቅርና ለአምሳ ዓመታት እንኳን ሰላም አጣጥማ እንደማታውቅና ለዚህ ኢትዮጵያ ለተጫናት ድህነት ከዋናዎቹ ምክንያቶች አንዱ ከጦርነት አዙሪት መውጣት አለመቻሏ መሆኑን የታሪክ ምሁራን ይነግሩናል።

የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ምሁራንና ሌሎችም በኢትዮጵያ ለሰላም መደፍረስና ለግጭት መንስኤዎች የአባይ ወንዝ ውሀ

ፍትሐዊ አጠቃቀምና የኢትዮጵያ የባህር በር በተለይም የአሰብ ባለቤትነት ጉዳይ እንደሚሆን ሳያመነቱ ይናገራሉ። በፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው እይታ ኢትዮጵያ በራስዋ ወደብ አድርጋ ወደ ባህር የመዝለቅ መብት በሰላም መፍትሔ ካልተሰጠው ወደ ፊት ብሔራዊ ስሜት ያለው መንግሥት መንበሩን ሲይዝ አሰብ ለጦርነት መንስኤ እንደምትሆን አያጠራጥርም ይላሉ።ይህንን አደገኛ ሁኔታ ለማስቀረት ለጋስ አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ድርድር መደረግ እንዳለበት ፕሮፌሰር ጌታቸው ያሳስባሉ።[190]

የድርድሩም ውጤት መሆን የሚገባውን አሰብን አለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ሲሆን ይህም ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን የጦርነት መዓት ያስቀራል ይላሉ ፕሮፌሰር ጌታቸው። አያድርገውና ለወደፊቱ በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ግጭት ቢፈጠር መንስኤው የወሰን መከላከል ጉዳይ ሳይሆን በአሰብ ባለቤትነትና በአፋር ህዝብ አንድነት ላይ ያጠነጠነ እንደሚሆን የተለያዩ ምሁራን ያስገነዝባሉ። አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ የፕሮፌሰር ጌታቸው አቋም በማጠናከር የሚከተለውን ብለዋል።

*"የአሰብ ጉዳይ የተደፈነ እሳት ማለት ነው። አማራጭ እያለህ ዝም ብለህ የምታካሄደው ጦርነት (War of Choice) የምርጫ ጦርነት ሊሆን አሁን ያጋጠመን ግን ልንሸሸው የማንችል አስገዳጅ ጦርነት (War of necessity) ነው። ምርጫ የሌላት አገር አስገዳጅ ጦርነት ለማካሄድ ትገደዳለች። የኢትዮጵያና የኤርትራ ችግር አሁን የድምበር ብቻ አይደለም፣ የመሬትም ጉዳይም አይደለም፣ ዋናው አንኳሩ የባህር ወደብ ጉዳይ ነው።ሁላችንም ቁጭ ብለን ችግራችንን መፍታት ያለብን በተለይም ደግሞ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ይሄ ችግር መኖሩን አውቀው ከኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጋር በግልጽ መነጋገር አለባቸው። ምክንያቱም እነርሱም ወደ ሥልጣና የመ... እንደሆን ከእነርሱም ጋር ጦርነት መግጠማችን አይቀርም። ሊሕአዴግ ካላደረገው ቀጥሎ የሚመጣው መንግሥት ይሄንን ጥያቄ እንደሚያነሳና ሊሕአዴግንም እንደሚወቀስ አምናለሁ።[191]*

---

[190] Getachew Begashaw, supra note 6

[191] ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ ዝኒ ከማሁ 24.



አሰብ ጥንትም አሁንም የአንድ ብሔረሰብ የአንድ ኃይማኖት ተከታይ የሆነውን ከጥንታዊቷ ከሱሲ (ድንቅነሽ) ብንጀምር ምናልባት የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን መሬት ነች። በአፋሮች ዘንድ የኢትዮጵያ፣ የኤርትራ፣ አፋር የሚባል ነገር የለም። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል የተፈጠረው ክፍፍል አፋሮች በጽኑ ይቃወሙታል። የሃይማኖትና የዓለማዊ ጉዳዮች አላፊ የአሳይታው ሱልጣን ሲሆኑ እኚህ ሰው የአፋሮች ሁሉ አባትና መሪ ተደርገው የሚቆጠሩ ከቅርብ ሳምንታት በፊት ያረፉትና የጅቡቲው ጠቅላይ ሚኒስትር በክብር የቀበሩአቸው ቢትወዳድ ሱልጣን አሊሚራህ ሀንፋሬ ናቸው። ክቡር ቢትወደድ በአፄ ኃይለ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን የአውሳ (አሰብ) አውራጃ አስተዳደሪ ቢሆኑም ከሌሎች የኢትዮጵያ አውራጃ አስተዳዳሪዎች የተለየ ሥልጣንና ለንጉሠ ነገሥቱ ቀረቤታ ነበራቸው። የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትም በአፋር ውስጣዊ ጉዳዮች ጣልቃ አይገባም ነበር[192]።

አሰብ ምን ጊዜም በታሪካም ጭምር ከኤርትር የተለያች ብትሆንም ጣልያኖች ከኤርትራ አካል በግድ ቢቀላቅልዋትም ምን ጊዜም ቢሆን ሕዝቡ የኤርትራ አካል መሆኑን አልተቀበለውም። በኤርትራ የሚታየው ከፍተኛ የሆነ የኤርትራዊነት ብሔራዊ ስሜት በአፋሮች ዘንድ አይታይም። ክቡር ቢትወደድ ሱልጣን አሊ ሚራህ ሌሎችም የአፋር መሪዎች በተለያዩ ወቅቶች እንደገለፁት ኢትዮጵያዊነታቸውን አጥብቀው የያዙ ሕዝቦች ናቸው።

ክቡር ቢትወደድ አሊ ሚራህ ለዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ በሰጡአቸው ቃለ ምልልስ እንዲህ ብለው ነበር። "የአፋር ሕዝብ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን ወዳድ ነው በታሪኩና በባህሉም ይኮራል። ኢትዮጵያዊነታችንም ማንም ሊነፍገን አይችልም የአፋር ሕዝብ ጠላቶች ብቻ ናቸው አፋርን የተለዩች አድርገው የሚቆጥሩት። እነኚህ ጸረ ሕዝቦችን እናጋልጣቸዋለን። ይኸም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲባል መደረግ አለበት"[193]። እንዲሁም

---

[192] የአንድ አፋር አዛውንት ለፀሐፊው የነገሩት ፣ አዲስ አበባ ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

[193] ክቡር ቢትወደድ አሊ ሚራህ በሐምሌ ወር በ1983 ዓ.ም አዲስ አበባ በተደረገው የሰላም ጉባዔ የተናገሩት

ክቡር ቢትወደድ አሲ. ማሬ.ራህ በሐምሌ ወር 1983 ዓ.ም ኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ለማደራጀት በጠራው ጉባዔ ላይ ተገኝተው አቶ መለስና አቶ ኢሣያስ ባሉበት "የአፋር ሕዝብ ወሰን ቀይ ባህር ነው። ግመሎቻችን እንኳን የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውቁአታል" ብለው ነበር[194]። እንዲሁም በሽግግሩ ቻርተር ስብሰባ ላይ ለቀድሞው ቺፍ አብ ስታፍ ሌተና ጀኔራል ጻድቃን ገብር ትንሣኤ በሰጡት ቃለ ምልልስ የቀይ ባህር አፋሮች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው እንዲወስኑ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው እንደ ነበር ጀኔራል ፡ሰበበ በጽሁፋቸው ገልጸውታል[195]። የራሴን ዕድል በእራሴ እወስናለሁ በማለት ለብዙ ዓመታት ተዋግታ ይህንኑ ያስከበረችው ኤርትራ የቀይ ባህር አፋሮችን የግድ ከኤርትራ ስር ትሆናላችሁ በማለትዋ እንደማንኛውም ለመብቱ ተቆርቋሪ ሕዝብ የአፋር ሕዝብም ነፃ ለመውጣትና ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል ያለው መብት ማንም ሊገድበው አይችልም።

ከላይ በቱለያዩ ምሁራን እንደተገለጸው ወደፊት በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ግጭት ቢነሳ መነስኤው ኤርትራ እዚህ አንድ ኪሎ ሜትር እዚያ ሌላ አንድ ኪሎ ሜትር የኢትዮጵያን ወሰን ጥሳ ገባች በሚል ሳይሆን (ያም የማይፈቀድ ቢሆንም) ኢትዮጵያ የባህር በር ተዘግቶባት ልማቷ፣ ደህንነትዋና ሉዓላዊነትዋ አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ነው። ኢትዮጵያ ለ40 ዓመታት በከፍተኛ ወጪ የገነባቻቸው የባህር በሮች አንድ የነበረ አገር ለሁለት ተከፍሎ አንዱ ሁለቱንም የባህር በሮች ጠቅልሎ ሲይዝ ሌላው ደግሞ ባዶውን ይቅር ማለት ፍትሕና መልካም ጉርብትና የማይቀበለው ጉዳይ ስለሆነ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሰላም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ በማካለል ላይ መንጠልጠሉ ያለ ማመንታት መተንበይ ይቻላል።

በመጨረሻም ኤርትራውያንስ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን በተለይ አሳብን አስመልክቶ ምን ይላሉ የሚለው ጥያቄ መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ነው፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ነች እያሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጽሁፎች ሲያወጡ በየአጋጣሚው ሲከራከሩ ኤርትራውያን ለዚህ ለኢትዮጵያውያን አቋም መልስ ሲሰጡበት ብዙ ጊዜም

194 ዝኒ ከማሁ

195 Abebe, T. Kahsay, supra note 3



አልተደመጠም። ይህ ጽሑፉ አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ነች በማለት ለጻፈው ወሎ ተወልደው ያደጉትና የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የአንትሮፓሎጂ መምህር የነበሩት በአሁኑ ጊዜ የሻቢያ አባልና የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር አሥመሮም ለገሠ መልስ ሲጸፉ የሚከተለው ብለው ነበር።

> *"አሰብ ወደብ የኢትዮጵያ ነው ብለው በአሁኑ ጊዜ የሚከራከሩት ትምህርት የሚይለውጣቸው ጊዜ የማያስተምሯቸው የአማራ ባለሥልጣናት የነበሩ ናቸው። አሰብ የኢትዮጵያ ነው እያሉ የሚከራከሩ ነፍጠኞች አንዳንድ የወያኔ መሪዎችን በመስበክ ኢትዮጵያና ኤርትራ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑና የትግራይ ልጆች እርስ በርሳቸው ተናንቀው ተባልቀው ሲያበቁ የአመራር ክፍተት ስለሚፈጥር ምንም ሳይዋጉ ወደ ሥልጣናቸው የመመለስ ድብቅ አጀንዳ ያላቸው ናቸው"* [196]

ፕሮፌሰሩ የኢትዮጵያ ችግሮች በሙሉ በአማራ ላይ ማላከክ ልማድ ሆኖባቸው ነው እንጂ ጸሐፊው ኢትዮጵያዊ እንጂ የአማራ ነፍጠኛ የሚባል ነገር ካለ "የአማራ ነፍጠኛ" እንደልሆን በተገነዘቡ ነበር። ለኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መከራከር ነፍጠኛ የሚያሰኝ ከሆነ በ1997 ዓ.ም በኢሕአዴግና በተቃዋሚዎች በተደረገው ክርክር ነፍጠኛነቱን እንዳገለጸ ሁሉ ይህ ጽሐፊ አሁንም ነፍጠኛ ነው።

ይህ አቋም የፕሮፌሰሩ የግላቸው ሲሆን በአቶ ኢሣያስ ተቃዋሚዎች በኩል ምንም የተደመጠ ነጋር የለም። ሆኖም የአቶ ኢሣያስ ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ መንግሥት እንደመደገፋቸው ወደብን አስመልክቶ ከኢሕአዴግ ጋር አንድ መግባቢያ እንደቀየሱ መገመት ይቻለል።

196 <u>ዕትኩሮት</u> ጥቅምት 14 ቀን 1993 ዓ.ም

# ምዕራፍ 11

## 11. በአግባቡ የተስተናገደ የካሜሩንና የናይጄርያ የድንበር ውዝግብ

ብዙ አገራት ድምበር ውዝግብ ውስጥ ገብተው ጦር ከተማዘዙ በኋላ እንኳን ውዝግቡን ሕግና ሥርዓትን በተከተለና በሰለጠነ መንገድ ፈትተው በመሃከላቸው የኢኮኖሚ የሰላልና የፖለቲካ መስተጋብሮችን ፈጥረው በመልካም ጉርብትና ይኖራሉ። ከዚህ በታች ያለው የናይጄርያና የካሜሩን የወሰን ውዝግብ አፈታት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። በካሜሩንና በናይጄርያ መሃከል የነበረው የድምበር ውዝግብ አፈታት በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ከነበረው የድምበር ውዝግብ አፈታት ፍፁም የተለየ ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራው ውዝግብ ገና በጅምሩ የተሰረዙ የቅኝ ግዛት ውሎች መሠረት አድርጎ ሲነሳ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን ሲሰርዝ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ጥቅሞችን ያላገናዘበ መሆኑ ግልጽ ነበር። ስለሆነም ውሳኔውና አፈጻጸሙ ችግር ቢገጥመው አያስገርምም። የአገሩ መሠረታዊ ጥቅሞችን አገናዝበ ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ በትክክለኛ መድረክ በየአገሮቻቸው ተወላጆች የተመራ የካሜሩን፣ የናይጄርያው የድንበር ውዝግብ ክርክር ምን እንደሚመስል ከኢትዮጵያውና ከኤርትራው ጋር ማወዳደር እንዲቻል በዚህ ፁሁፍ አካትቼዋለሁ[197]።

እ.አ.አ በ1970ዎቹ የናይጄሪያ አንዷ ክልል የሆነችውን ቢያፍራን ለመገንጠል በተሞከረ ጊዜ የናይጄርያው ፌዴራል መንግሥት በመቃወሙ የእርስ በእርስ ጦርነት ተቀስቅሶ ካሜሩን በጦርነቱ የፌዴራል መንግሥቱን በመርዳትዋ የወቅቱ የናይጄርያ

[197] ስለካሜሩንና ናይጄርያ የወሰን አካለል የተወሰደው ከዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔ አጠቃለይ ዝርዝር ዘገበ 94 (International Court of Justice, General list 94), International Court of Justice, The Case Concerning The Land and Maritime Boundary Between Cameroon and Nigeria, (Cameroon Vs Nigeria, Equatorial Guinea intervening, 10 October 2002



መሪ የነበሩት ጄኔራል ያኮቡ ጋዋን ሁለቱ አገራት በይገባኛል ይጨቃጨቁበት የነበረው በተለያዩ ጊዜያት ጦር የተማዘዙበት ባካሲ የተባለ የባር ሰላጤ (Peninsula) ለካሜሩን ሰጡ። በዚሁ ቁጭት የተነሳ የናይጄሪያ የጦር ኃይል ጋዋንን ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከሥልጣን አባረሩአቸው። ጄኔራል ጋዋንን የተኩት ጄኔራል ሙርታላ መሃመድ ስምምነቱን ወዲያውኑ ሰርዘው የናይጄሪያን ጦር አሰፈሩበት።

በሙርታላ መሃመድ እግር የተተኩት ኘሬዚዳንት አባሳንጆም ደግሞ በዚሁ ስለጸኑ ካሜሩን ውዝግቡ ዘሔግ ወደሚገኘው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በከሳሽነት አቀረበችው።

ከስምንት ዓመታት ሙግት በኋላ ለውሳኔው አርባ ቀናት ሲቀር የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሀፊ ኮፊ አናን የሁለቱን አገራት ፕሬዚዳንቶች ስለ ባካሲ ለመወያየት ፓሪስ ጋብዙአቸው በውይይቱ መሃከል ኮፊ አናን ሁለቱን ፕሬዚደንቶች የፍርድ ቤት ውሳኔ ምንም ይሁን ምንም እንዲያከብሩ ቃል አስገቡአቸው።

ፍርድ ቤት እ.አ.አ 10 ኦክቶበር 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ባካሲ ለካሜሩን ተሰጠ። የታወቀው ንቁ የናይጄርያ መገናኛ ብዘሃን በተለይ ጋዜጠኞች ውሳኔውን አውግዘው በሰፊው ጻፉ በሕዝቡም በኩል ከፍተኛ ቅዋሜ ቢነሳም አባሳንጆ በቃላቸው እረጉ።

የባካሲ ነዋሪዎችም በበኩላቸው "ለእኛ ባካሲ ሕያው ነው። ባካሲ ወንዶች፣ ሴቶችና ሕፃናት ማለት ነው.......የናይጄርያ ዜጐች ነን። በቤታቸውና በመሬታቸው ላይ ስለሚኖሩ ሰዎች ነው የምንነጋገረው ሲሉ፣ ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ ተቃውመዋል። የእነርሱ አቋም የገለፁበት ቋንቋ እንግሊዝኛው በቅጡ ይገልጸዋል። "For us Bakasi is real. It is men, women and children. It is people living in their homes, on their land. We are Nigerian citizens. We do not have any other place to go." የእነዚህ ሰዎች አባባል በድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ወደ ኤርትራ የተጠቃለሉት የኩናማ፣የባድመ፣ የአፋርና የኢሮብ ሕዝቦች ከሚሉአቸው ጋር ተመሳሳይነታቸው አስገራሚ ነው።

በዚሁ ፍርድ ቤት በጊዜያዊ ዳኝነት (Judge ad hoc) በናይጀርያ ተመድበው ከአሥራ አምስቱ ዳኞች አንዱ የነበሩት በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረው ውዝግብ ስመዳኘት በኢትዮጵያ የተመረጡት ናይጀርያዊ ልዑል ቦለ አጂቦላ (Prince Bola Ajibola) ነበሩ። ባካሲ የማን ነው በሚለው ክርክር አጂ ቦላ እንግሊዝና ናይጀርያንና ፋረንሳይ ካሜሩንን የተካፋፋሉበት የቅኝ ግዛት ውል ውድቅ በማድረግ ከሌሉች ዳኞች በመለየት ባካሲ ለናይጀርያ ትገባለች በማለት ለአገራቸው ለናይጀርያ ፈረዱ።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል በነበረው የድምበር ኮሚሽን ክርክር ጊዜ ግን እኚህ ሰውዬ ኢትዮጵያ መርጣቸው በዳኝነት ተቀምጠው የቅኝ ግዛት ውሉችን በማጽደቅ የ90 ሚልዮን ሕዝብ የባህር በር ሲያዘጉ ቅርም አላላቸውም። "በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት" ዓይነት ሲሆን ለነገሩ እርሳቸው ምን ያድርጉ? "ባለቤቱ ያቀለለው አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም" እንዲሉ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ከመጤፍ ያልቆጠሩት የባህር በር ጉዳይ የውጭ ዜጋ ለምን አልተጨነቀለትም ብሎ መውቀስ ትክክል አይደለም። ውሳኔ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ወሰን አካልሎ ችካል ለመትከል አልተሄደም። ተቃውሞውን ለማብረድ ሲበል የተባበሩት መንግሥታት ወኪሎች ይህንኑ ጸሐፊ ጨምሮ የናይጀርያና የካሜሩን ተወካዮች የሚገኙበት አንድ የጋራ ኮሚቴ ተቋቋመ።

በኢትዮጵያና በኤርትራ፤ በናይጀሪያና በካሜሩን የወሰን መከለል የዳኝነት ጉዳይ የጐሉ ልዩነቶች አሉ። ዋነኛው በካሜሩንና በናይጀሪያ መሃከል የነበረው ውዝግብ ከጅምሩ አንስቶ እስከ ድምዳሜው ድረስ ሕዝብ የተወያየበት፤ አሳፊነቱ በውጭ አገር ዜጐች ላይ ሳይሆን በአብዛኛው በየአገራቱ ዜጐች ላይ የተጣለበት ሁኔታ ሲሆን በኢትዮጵያ ግን መንግሥት የአልጀርስን ስምምነት ሲፈርም ሕዝቡ ሳይወያይበት የኢትዮጵያ ምሁራን አስተያየት ተንቆ ሥራው በሙሉ ማለት ይቻላል ለውጭ አገር ዜጐች የተተወበት ሁኔታ ነበር።

ሌላው ልዩነት በአብዛኛው በዓለም ዙርያ እንደሚደረገው የመሬት ይገባኛል የወሰን ውዝግብ ካሜሩንና ናይጀርያ እንዳደረጉት ለዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ይቀርባል እንጂ ብዙም ጊዜ ምንም ተጠያቂነት ለሌለባቸው ግለሰቦች አይተውም። በአመዛኙ የድንበር ውዝግብ ለግልግል ኮሚሽን የሚቀርበው ጉዳዩ ብዙም አጨቃጫቂ ሳይሆን ግልጽ ሆኖ በተለይም ጉዳዮ በቶሎ እልባት እንዲሰጠው ሲፈለግ ወይንም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነው።

የተኩስ አቁም ታውጆ የሕይወት መጥፋትና የንብረት መውደም እስከሌለ ድረስ ኢትዮጵያ ለውሳኔ የምትጣደፍበት ምንም ምክንያት አልነበረም። በተለይም ኢትዮጵያ የባህር በር ከሚዘጋ የሚበልጥ ያህል ትልቅና ወሳኝ ብሔራዊ ጉዳይ ይገጥማታል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው። ስለሆነም ጉዳዩ ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መሄድ ሲገባው ለማንም ተጠያቂ ባልሆኑ ግለሰቦች ለተቋቋመ ኮሚሽን ተሰጠ። ለአብነት ያህል የወሰን ውዝግባቸው ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከወሰዱ አገራት ጥቂቶቹ ኒካራጓ፣ ኮሎምቢያ፣ ሆንዱራስ፣ ኢንዶኒዝያ፣ ማሌዥያ፣ ናሚቢያ፣ ቦትስዋና፣ ቻድ፣ ሊብያና ሌሎችም ብዙዎቹን መጥቀስ ይቻላል።

ኢትዮጵያ ግን ለማንም ግልጽ ባልሆነና ማንም ሊገባው ባልቻለ ፍጹም እንቆቅልሽ በሆነ ምክንያት ማንም ሳያስገድዳት የምትገኝበት ሕግን (በተለይ የቅኝ ግዛት ውሉች) መርጣ ይግባኝ ሊባል በማይቻልበት መድረክ ዳኞችን ሰይማ ውሳኔውን የተባበሩት መንግሥታት፣ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት፣ የአሜሪካ መንግሥት፤ የአውሮፖ ሕብረትና ሌሎችም እንዲያስፈጽሙ ተስማምታ ራስዋን በማይፈታ ማነቆ እግር ተወርች ተብትባ በሉዓላዊነቷ ላይ እንዲወስኑ በአላፊነት ሊጠየቁ ለማይችሉ ግለሰቦች አስረከበች። ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል እንደሚባለው ውጤቱም ለጦርነቱ መንስኤ የሆነው፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን ያለቁበት ባድመንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች ኮሚሽኑ ለኤርትራውያን ጋር ሲሰጥ ውዝግቡ እልባት ሳያገኝ እነሆ ተንጠልጥሎ ከኤርትራዊያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር መልካም ጉርብትና ከመፍጠር ፋንት ደመኛ ጠላትነት ተመሠረተ።

ናይጀራያ የተባበሩት መንግሥታት ፍርድ ቤት ውሳኔ ከብዙ ማመንታት በኋላ ተቀብላ ባካሲን ለማስረከብ ፈቃደኛ ብትሆንም እንኳን ጉዳቱ ለናይጀሪያ እምብዛም ነበር። ምክንያቱም ከባካሲ በተጨማሪ ናይጀርያ ብዙ ትላልቅ ሕደቦች ያሉአት አገር ናት።

ባካሲ የናይጀርያ ብቸኛ ወደብ ብትሆን ኖሮ በምንም ዓይነት ባካሲን ለካሜሩን እንደማታስረክብ የዚሁ ጸሐፊ አንድ የሥራ ባልደረባና ከኮሚሽኑ የናይጀሪያ ተወካዮች አንዱ አረጋግጠውለታል። ሌላው ልዩነት ናይጀርያና ካሜሩን የፍርድ ቤቱ ውሳኔዎቹ በሕዝቡ በኩል ተቀባይነት እንዲያገኙ የተደረጉ ጥረቶች ናቸው።

በካሜሩንና በናይጀሪያ መሃከል የነበረው የፍርድ አፈጻጸም ለመከታተል የናይጀርያ፣ የካሜሩንና የተባበሩት መንግሥታት ባልደረቦች የሚገኙበት የተለያዩ የጋሪ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ኮሚቴዎቹ ወደ ድንበሮቹ በመሄድ ውሳኔውን ለሕዝብ እያስረዱና፣ እያረጋጉ እንዲሁም የድንበሩ መስመር የሚያርፍበት ቦታ ተማሪ ቤቶችን፣ መስጊዶችንና ቤተክርስቲያናትን የመሳሰሉት የሚከፋፍል ከሆነ ኮሚቴዎቹ ይህንን እያስተካከሉ አንድም ቀን ውዝግብ ሳይፈጠር እነዚህ ኮሚቴዎች 22 የናይጀርያ ትናንሽ የድምበር ከተሞችና ባካሲን ለካሜሩን አስረከቡ። እነዚህ ኮሚቴዎች በካሜሩንና በናይጀሪያ ወሰኖች ለሚገኙ ሕዝቦች የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስረዳትና ሕዝቡን ለማረጋጋት ለሳምንታት እየተጓዙ ያልረገጡት የሁለቱ አገራት ድምበሮች የሉም ማለት ይቻላል። ወደ ሕዝቡ ለመድረስ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር የመኪና ጉዞ ይደረግ እንዳነበራና እነዚህም ጉዞዎች ምን ያህልም አድካሚ እንደነበሩ ይህ ጽሐፊ ያስታውሰዋል። የኮሚቴው አባላት በእነዚህ በሁለት እህትማማች አገራት መሃከል በአፍሪቃ እንድተለመደው ውዝግባቸው በጦር ኃይል መፍታት ሳይሆን በጠርጴዛ ዙርያ እንዲፈቱ በመርዳታቸው በሥራቸው እጅግ ይኮሩና ይረኩ ነበር።

በኢትዮጵያና በኤርትራ ድምበር አካለል በነበረው ግን ድምበር እንዲያካልል ሕዝቡን እንዲያግባባ ጉራማይሌ ሁኔታ ሲያጋጥም እርማት እንዲያደርግ ሁለቱም ወገኖች ሥልጣን የሰጡት የጋራ ኮሚሽን ሳይኖር የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በቀጥታ በሕዝብ ጉሮሮ ውስጥ እንዲሸነቆር ተወሰነ። ቆይቶም የናይደርያን የካሜሩንና የተባበሩት መንግሥታት የጋር ኮሚሽን ምሳሌነት በመከተል ይመስላል አቶ መለስ የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ድንበር አካልሎ ችካል ይትከል የሚል ሃሳብ ቢያቀርቡም ኤርትራ በመቃወምዋ በኮሚሽኑ በኩል ጥያቄችው ተቀባይነት አላገኘም።



የባካሲ ሕዝብም ቢሻው ናይጀሪያዊ ዜግነቱን እንደያዘ ቢሻው ደግሞ ካሜሩንያዊ ሆኖ በነበረበት መሬት እረግቶ እንዲኖር ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው እስከ ዛሬ አንድም ሰው ከቤት ንብረቱ ሳይፈናቀል ሕዝቡ በሰላም ይኖራል።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ባለው፣ የድንበር ኮሚሽኑ የሚያካልለው መሬት ሕዝብ የሰፈረበት እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ ችግሮች መፈጠራቸውና የኮሚሽኑ ውሳኔ ቃል በቃል ለመተግበር ችግር እንደሚፈጥር ባለመረዳት ወይንም ችላ በማለት የኮሚሽኑ ውሳኔ በግርድፉ በሕዝብ ጉሮሮ ውስጥ ለመሸንቆር ተሞክሮአል። ስለሆነም የኤርትራና የኢትዮጵያ የወሰን መካለል ችግር ላይ መውደቅ እጅግም አያስገርምም።

የናይጀርያና የካሜሩን ውዝግብ ሕግን ተከትሎ ሕዝብን አሳትፎ በሰለም በመጠናቀቁ ሁለቱም አገራት በዓለም አቀፍ ሕብርተሰብ ዘንድ ክብርና ሞጋሰ ያጐናጸፋቸው ሲሆን ኤርትራንና ኢትዮጵያ ግን ለሕግ ተገዢ ሆነው የድምበር ውዝግቡ ለመፍታት ብቃቱም ሆነ ፍላጐቱ ስላላሳዩ በዓለም አቀፉ ሕብረተስብ ፊት እንደሚዋረዱበት አያጠራጥርም።

ምዕራፍ 12

## 12. የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ መደምደሚያና አንዳንድ የመፍትሔ ጥቆማዎች

ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን በደም፣ በቋንቋ፣ በባህልና በሃይማኖት የተሳሰሩ ለመሆኑ ተደጋግሞ የተባለ ነገር ነው። ምናልባት ተደጋግሞ ያልተባለ ነገር ቢኖር ስውርም ይሁን ግልጽ በቃላት አይገለጥ እንጂ ሁለቱም ሕዝቦች አንዱ ላንዱ ያለው የውስጥ ትስስርና የወገናዊነት ስሜት ነው። ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ቀጥሎ የሚቀሰቅሳቸው ነገር ቢኖር ከሌላ ከየትኛውም አገር በፊት የኤርትራ ጉዳይ ነው። ምናልባት ብዙ ኢትጵያውያን የኤርትራ መገንጠል ጊዜያዊ ቁጣ ቢያሳድርባቸውም የነበረው ችግር ከመገንጠል በመለስ ሊፈታ ይችል ነበር የሚል እምነት ቢኖራቸውም መገንጠሉ ያ ልዩ ውስጣዊ ስሜትን ሊሰርዘው አልቻለም። ስንቶቻችን ነን ከኤርትራውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር አንድ ክፍል ቁጭ ብለን የተማርን፣ ስንቶቻችን ነን አንድ ማዕድ ቁጭ ብለን እንጀራ የቆረስን፣ ከዚያም አልፎ ስንቶቻችን ነን በራሳችን ወይንም በልጆቻችን የደም ስር ኤርትራዊ ወይንም ኢትዮጵያዊ ደም የሚንቆረቆረው?

ኢትዮጵያውያን ይሸሽጉት እንደሁ እንጂ ለኤርትራውያን ያላቸው ስሜት ለኬንያውያን፣ ለሱዳናውያን ወይንም ለሶማሊያውያን ካላቸው ስሜት ፍፁም የተለየ ነው። ኤርትራውያንም እንዲሁ ጊዜያዊ ጥላቻው የወንድማማች ስለሆነ አንዳንዴ በከረረ መልኩ ቢገለፅም ዘላቂነት ግን የለውም። ይህ ስሜት በሳይንስ መርምሮ ተንትኖ ምን እንደሚመስል ማስረዳት አይቻልም፤ ስሜት ስለሆነ። ሆኖም ስሜቱ ምን እንደፈጠረው ግን መረዳት ይቻላል። "ዘር ከልጓም ይስባል" የሚለው ብሂል የኢትዮጵያንና ኤርትራውያን ሁኔታ እውነትነቱን ሲያረጋግጥ ታሪክ፣ ባህል ቋንቋ ወዘተ... ለትስስሩ ገመድ ተደራቢ ናቸው። ኤርትራን በውል ለመደምሰስ የሚቃጣ ኃይል ቢነሳ ኤርትራን



ለመታደግ ኢትዮጵያውያን ወደ ዘማቾች ማግኘት አይቸግርም። በኤርትራውያን በኩልም ይኸው ነው። ነበርም። ለዚህም ዘርአይ ድረስ፣ አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም ሌሎችም ለኢትዮጵያ ነፃነት የተዋደቁት እጅግ ብዙ ኤርትራውያን ሕያው ምስክሮች ናቸው። በኤርትራ ሙዚቃ ስሜቱ የማይነካ ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ሙዚቃ መንፈሱ የማይረካ ኤርትራዊ ይገኛል? ምናልባት ከአረብ አገራት ውጪ እንደ ኢትዮጵያውያንና እንደ ኤርትራውያን ለሁለት የተከፈል ተመሳሳይ ሕዝብ በአፍሪቃ የለም ማለት ይቻላል። ተመሳሳይ ፊደል፣ ተመሳሳይ ቋንቋ፣ ተመሳሳይ አለባበስ፣ ተመሳሳይ ምግብ፣ ተመሳሳይ የፀሎት ስርዓት፣ ተመሳሳይ የሙዚቃ መሳሪያና ሙዚቃ፣ ተመሳሳይ መልክ፣ ተመሳሳይ ስሞች፣ ተመሰሳይ አቱራረስ፣ ተመሳሳይ የኑሮ ዘይቤና ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያላቸው ሁለት አገራት በዓለም ጥቂቶች ሲሆኑ በአፍሪቃ ከኤርትራና ከኢትዮጵያ ውጭ ሌሎች የሉም ማለት ይችላል። ይህም ሲባል በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ ከዚህ በተመሳሳይነት ከተሰለፉት ሕዝቦች ውጭ ሌሎች ለየት ያሉ ቋንቋም ሆነ ባህል ያላቸው ሕዝቦች የሉም ማለትም አይደለም።

የእነዚህ የሁለቱ አገራት የዘለቄታ መፃኢ እድል የተሳሰረ መሆኑ ግልፅ ነው። "በሃበሽ" ላይ ከተሰነዘረ ጥቃት ይውል ያድር እንደሆን እንጂ ኤርትራም አታመልጥም። በኤርትራም በኩል እንዲሁ። የአንዱ ጠላት የሌላው ጭምር መሆኑ የአረብ ካባ የደረበ ጊዜያዊ ማሞካሸት ሃቁን አይሸረውም።

ከአፍንጫቸው አርቀው ሊያዩ ባልቻሉ ወይንም ሕሊናቸውን ሥልጣን በጋረደው አንዳንድ መሪዎች ምክንያት በሁለቱ ወንድማማችና እህትማማች ህዝቦች መሃከል የተሸነቆረው ጠላትነት በሕዝቡ ውስጥ ሊሰርጽ አለመቻሉ አላፊነት በጎደለው መልኩ አንዳንድ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ በተባረሩ ጊዜ ሕዝቡ ሊያስጥላቸው ሳይችል ሲቀር በእምባ እየተራጨ እንደሸኛቸው በቂ ማስረጃ ነው። እንዲሁም ፍጹም ሰብአዊ እርህራሄ በራቀው መልኩ ሻቢያ አሥመራን በተቆጣጠረ ማግስት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ ሲያባርር ሕዝቡን አማክሮ ሳይሆን እንዲያውም ከሕዝቡ ሸሽጎ ነው።

የሁለቱም አገራት መሪዎች ይህንን ወንድማዊና እህታዊ ትስስር እንደማይፈልጉት ከአንድ ምሳሌ ማረጋጥ ይቻላል። የኤርትራ ሕዝብ "ነፃነት" ትመርጣለህን ተብሎ ለሚቀርብለት ጥያቄ ማለትም ለሬፈረንደሙ ጥቂት ቀናት ሲቀሩ የሕዝቡን ትስስርና ታሪኩን በጥልቀት የሚያውቁ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን "በሰላምና ልማት ኮሚቴ" አዘጋጅነት በቪዲኦ (video) የተቀረጸ ውይይት አድርገው ነበር። እነዚህ ታዋቂ ግለሰቦች ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ፣ ዶክታር ደጃአዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም፣ አቶ ተፈሪ ብርሃኔ፣ ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋና አቶ ሣሙኤል ዓለማየሁ ሲሆኑ ውይይታቸው ያተኮረው በኢትዮጵያ ሕዝብና በኤርትራ ሕዝብ መሃከል በነበረውና ባለው ትስስር ላይ ሆኖ ይህንኑ እጅግ በሚመስጥ መልኩ ካስረዱ በኋላ ይኸ ትስስር በጊዜው ሆይ ሆይታ እንዳይበጠስ በእጅጉ ተማፅነው ነበር። በመቀጠልም ሁለቱ አገራት ለጊዜው በነበረው ትስስር የማይቀጥሉ ከሆነ መተላለቅ እንዳይኖር ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተማጽኖአቸውን አቀረቡ። ይኸ በጥልቅ እውቀት የተከሸነ ስሜትን የሚቀሰቅስ ምልጃና አቤቱታ በከፍተኛ ወጪ በቪዴዩ ከተቀረጸ በኋላ በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ መገናኛ ብዙሃን ለሕዝቡ እንዳይተላለፍ ታገደ።

የታገደውም ቀደም ሲል በመሪዎች ተወስኖ የነበረው ኤርትራን የመገንጠል ሂዲት ያደናቅፋል ከሚል ነበር። እንዲያውም ይህንኑ ውይይት ባዘጋጀው በዚሁ ጸሐፊ ላይ ከፍተኛ ወቀሳና ውግዘት ደርሶበታል።

ለኤርትር ሕዝብ የቀረበለት ጥያቄ በራሱ የኤርትራና የኢትዮጵያ መሪዎች የፈለጉት ውጤት የሚያስገኝ ሲሆን ሕዝቡ በመገንጠሉ ሊከተል የሚችለው አደጋ፣ የሚቀርበት የጋራ ጥቅም፣ እንደ አገርነቱና እንደ ሕዝብነቱ ምን ያህልስ እንደሚያሳሳው በሚገባ ባልተገለፀለት ሁኔታ ሕዝቡ መገንጠልን ቢመርጥ ምንም አያስገርምም። አርቆ አስተዋይ መሪዎች ኖረው ሁለቱ አገራት በሆነ ትስስር ተያይዘው ወይንም ተዋህደው የኤርትራ አምስት ሚሊዮን ህዝብ ከኢትዮጵያው 90 ሚሊዮን ጋር ተደምሮ ሁለት ስትራተጂክ የሆኑ የባህር በሮች፣ ሰፊ ለም



የእርሻ መሬት፣ መጠነ ሰፊ የውሃ ሃብት ያለው ይህ ፌዴራላዊ ወይንም አሃዳዊ አገር ምንኛ ጠንካራ፣ የማይበገርና የበለጸገ አገር ሊሆን ይችል እንደነበር በምናባችን ስንቃኘው በራሱ ያማልላል።

በቅርብ ጊዜ አንዳንድ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር የኢትዮጵያና የኤርትራ የወዳጅነት መድረክ አቋቁመው ይህ የሁለቱ አገራት መሪዎች የበጠሱት የትስስር ገመድ እንዴት መቀጠል እንደሚቻል በሰከነ መንፈስ የጀመሩት ውይይት ደብል የሚያሰኝ ነው። የዚሁ ውይይት ዋነኛ ቀስቃሽ የሆኑት ፕሮፌሰር ተስፋ ፅዮን መድሃኔ በአንድ ወቅት የኢትዮጵያና የኤርትራ ትስስር መቀጠል አለበት በማለት የዓፋት አይደፋም" በሚል የመልስ ምትና ሌሎችም ጸረ አንድነት ኃይሎች ፕሮፌሰሩን ማብጠልጠላቸው ፕሮፌሰር ተስፋ ፅዮን ከቁብ ሳይቆጥሩት ዛሬም ይህንኑ ትግል በግምባር ቀደምትነት ሲጀምሩት በአርቆ አሳቢነታቸውና በድፍረታቸው እናደንቃቸዋለን። ይህ ዓላማ ቢሳካ የኢትዮጵያን የባህር በር መዘጋት ሊያመጣ የሚችለው አሰቃቂ መዘዝ ከማምከኑም በላይ ምናልባትም በምሥራቅ አፍሪቃ አንድ የበለጸገች የታፈራችና የማትበገር ፌዴራላዊ ወይንም አሃዳዊ አገር ብቅ ትል ይሆናል።

አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያሳየን ኢትዮጵያ የባህር በር ተዘግቶባት ሕልውናዋና ልማትዋ አደጋ ላይ ወድቆ ይገኛል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ኢትዮጵያውያን የባህር በርን በተመለከተ አፋቸውን ዘግተው መቀመጥ ለአገራቸው ያለባቸው ግዴታ መጣስና አባቶቻቸውና እናቶቻቸው የጣሉባቸውን አደራ መብላት ነው በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ምክንያት ኢትዮጵያውያን የሚያሰሙትና የሚያንፀባርቁት እጅግ የከረረ ምሬትና ቁጭት ኤርትራውያን ከፍትሃዊነት ከወንድማማችነትና ከመልካም ጉርብትና አንፃር ማየት ይጠበቅባቸዋል። ኤርትራና ኢትዮጵያና አንድ አገር ሆነው ለአርባ ዓመት አብረው በቆዩበት ጊዜ ሁለት የባህር በር የነበራት አገር ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ በተባበሩት መንግስታት ፊት ቆመው አድማጩን ባስደመመ ንግግራቸው ኤርትራ ሁለት የባህር በር ሲኖራት ኢትዮጵያ

እንዴት ወደብ አልባ ትሁን ብለው የጠየቁት ጥያቄ ዛሬም አግባብነት ያለው ሆኖ ብቅ አለ።

ለመሆኑ ኢትዮጵያውያን በኤርትራ መገንጠል ምን ይሰማቸዋል ቢባል የእያንዳንዱ ግለሰብ ስሜት ለአገሩ ካለው ፍቅር ጋር የሚመጣጠን ነው ማለት ይቻላል። ለአንዳንዱ የአገር መቁረስ ከዳቦ መቁረስ አስበልጦ የማያየው ሲሆን ሌላው ደግሞ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም እንዳሉት "ብዙ ሰዎች [መገንጠልን] በጣም ይጠላሉ፤ እንደሞት ይፈሩታል"[198]።" ስለሆነም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የወንድሞቹችንና የእህቶቻችን መለየት አሳዝኖታል ቢባል በበቂ አይገልፀውም። ያም ሆኖ ግን ዛሬ የኤርትራን መገንጠልን ብዙ ኢትዮጵያን ተቀብለውታል። አምባሳደር ዘውዴ ረታ ስለኤርትራ ነጻ መንግሥት ሆኖ መቋቋም ያሉት ዛሬ የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ስሜት ያንጸባርቃል ማለት ይቻላል። አምባሳደር ዘውዴ ኤርትራውያን በቅጡ አስበውበት ከሆነ "ኢትዮጵያዊነት ጎድቶናል፤ ነፃ መሆን ይጠቅመናል ብለው ለብዙ ዓመታት ተዋግተው መለየትን የመረጡት ወንድሞቻችንና [እህቶቻችን] ኤርትራውያኖች ስለሆኑ ምርጫቸውን እንቀበለዋለን"[199]። ሆኖም ኢትዮጵያውያን አንድ የማንቀበለው ነገር ቢኖር ከቀይ ባህር በእግር መንገድ እርቀት የሚገኘውን አሰብን ለቅቀን ሕልውናችንና እድገታችን ለአደጋ ለማጋለጥ ፈቃደኛ ባንሆን ተወቃሽ አንሆንም።

በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ከኢትጵያውያን የሚደመጠው ምሬት ኤርትራውያንን ማስከፋት አይገባውም። ኤርትራውያን ስለ አገራቸው የሚሰማቸውን ያህል ሁሉ ኢትዮጵያውያንም ይሰማናል። እኛም እንደ ኤርትራውያን አገራችንን እንወዳለን። አቅማችን በፈቀደ መብትዋና ሕጋዊ ጥቅሞችዋን ለማስጠበቅ እንጥራለን። በተለይም አንዲት ጋት መሬት በሌላው የማያስነካው የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ስለሌላት ብቻ የባህር በር ይቀርቀርባት ማለት ኢትዮጵያውያን መቼም ቢሆን የማይቀበሉት በደል ከመሆኑም

[198] መስፍን ወልደ ማርያም፤ ፕሮፌሰር፤ ዝኒ ከማሁ 37. ገፅ 96
[199] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር)፤ ዝኒ ከማሁ 95. ገፅ 79



በላይ ለዘለቄታውም ቢሆን ለኤርትራም የማይበጅ ነገር ይሆናል። ኢሕአዴግን የሚተካው መንግስትም ቢሆን ቅንጣት ያህል ብሔራዊ ፍቅር ካለው የባህር በር ጉዳይ እንደ ኢሕአዴግ በቸልታ ሊያልፈው ሕዝቡ አይፈቅድለትም። የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ዋነኛ አጀንዳው ካላደረገው በስልጣን ሊቆይ የሚችለው በጠመንጃ ኃይል ብቻ ይሆናል። ስለዚህ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን አሰብ ወደ ኢትዮጵያ የሚታጠፍበት ሰላማዊና ፍትሐዊ መንገድ ቀይሰው አቋማቸውን ይፋ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አማራጩ ከዚህ በፊት እንደታየው አሳስፈላጊ የሆነ የወንድማማቾችና የእህትማማቾች መተላለቅና እንደገና እንዳለፈውም የዓለም ሕብረተሰብ መሳለቂያና መዘባበቻ መሆን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብን ጥያቄ ሊመልሱ የሚችሉ ሦስት ፍትሐዊ አማራጮችን መጠቆም ይቻላል። በእነዚህ በሦስት አማራጮችም ሆነ በሌሎች መፍትሔዎች ዙርያ ኢትዮጵያውያን ተወያይተው አንድ የጋራ አቋም ቢይዙ ለጥያቄአቸው ጥንካሬ ይሰጣል።

12.1. አሰብን ከነደሴቶቿና ሕጉ የሚፈቅደው 12 ኖቲካል ማይልስ ወደ ባህሩ ገባ ብሎ ያለው ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍና ሁለቱም አገሮች ጤናማ ግንኙነት መሥርተው ሕዝቡ ከአንዱ አገር ወደ ሌላው በነፃ እንዲንቀሳቀስና ሰፊው የኢትዮጵያ ገበያ ለኤርትራውያን ክፍት ሆኖ ኤርትራ የኤሌትሪክ ኃይልና የምግብ ሰብሎች ወዘተ ከኢትዮጵያ በዘመድ ዋጋ እንድትገዛ መፍቀድ። እንዲሁም ኢትዮጵያ የኤርትራ ምርቶችን እንድትገዛ መስማማት አንዱ አማራጭ ነው።

12.2. ኤርትራ የእርሻ መሬት እንደሚያስፈልጋት ሁሉ ኢትዮጵያም የባህር በር ያስፈልጋታል። አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋ ከላይ የተዘረዘሩት ሕጎች ቢደነግጉም ለሰላምና ለመልካም ጉርብትና ሲባል ሁለቱም ሃገራት የወሰን መሸጋሸግ አድርገው ኤርትራ የተወሰነ የእርሻ መሬት ተሰጥቶአቶ አሰብ ከላይ በተገለጸው መልኩ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ሌላው

አማራጭ ነው። እዚህ ላይ በአጽንኦት መነገር ያለበት ይህ አማራጭ ሃሳብ የቀረበው ለሰላምና ለመልካም ጉርብትና ሲባል እንጂ የአሰብ ኢትዮጵያዊነት በምንም መልኩ ጥያቄ ውስጥ አያገባም።

12.3. አሰብ ከነደሴቶቹ ሁለቱም አገራት ማለት ኢትዮጵያና ኤርትራ በጋራ ይዘውት ሁለቱም ጣምራ ሉዓላዊነት (Joint Sovereignty) እንዲኖራቸው መስማማት ይችላሉ። የጣምራ ሉዐላዊነት ዝርዝር ከሌሎች አገራት ተሞክሮ በመነሳት ምን ምንን እንደሚያጠቃልል በቅድሚያ በድርድር ሊወሰን ይችላል። ይህ ጣምራ ሉዐላዊነት ተመሳሳይ ችግር ባላቸው አገሮች የባህር በሮችንና ደሴቶችን አስመልክቶ የሚሠራበት ሲሆን ጥቂት ምሳሌዎችንም መጥቀስ ይቻላል።

አሰብን አስመልክቶ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ያለው አቋምና ስሜት በእስራኤሎችና በፍልስጤማውያን መሃከል ካለው አቋምና ስሜት ጋር ይመሳሰላል። ኢየሩሳሌም በይሁዳውያን ልብ ሰርፃ እንደገባ ሁሉ አሰብም በኢትጵያውያን ዘንድ በተመሳሳይ ስሜት ይንፀባረቃል። ስለሆነም እስራኤላዊያን ኢየሩሳሌምን በምንም ዓይነት ለፍልስጤማውያን እንደማያስረክቡ ሁሉ ኢትዮጵያውያንም መቼም ቢሆን አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች ብለው አይቀበሉም።

እስራኤልና ፍልስጤምን አስመልክቶ ብዙ ሰዎች ሁለቱ አገራት በሰላምና በመልካም ጉርብትና እንዲኖሩ ከተፈለገ በኢየሩሳሌም ላይ ጣምራ ሉዓላዊነት የሚሰጣቸው ቀመር ያስፈልጋል ይላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያና ኤርትራ በሰላምና በመልካም ጉርብትና እንዲኖሩ ከተፈለገ በአሰብ ላይ ጣምራ ሉዓላዊነት ኖሮአቸው የአሰብ ውስጣዊ አስተዳደር ራሱን በቻለ በሕዝብ በተመረጠ ካውንስል እንዲተዳደር ማድረግ ይቻላል። በዓለም ዙርያ በሁለት አገራት ጣምራ ሉዓላዊነት ስር የሚተዳደሩ ብዙ ከተሞች ወይንም ክልሎች ይገኛሉ። ለምሳሌ ቻንዲጋር (Chandigarh) የተባለ ከተማ የሕንድ ሁለት ክልሎች



(States) ዋና ከተማ ሆኖ ሁለቱም ክልሎች በከተማው ላይ ያልተከፋፈለ ጣምራ ሉዓላዊነት አላቸው[200]።

እንዲሁም ሕንድና ፓኪስታን ካሽሚር ይገባኛል በሚል ውዝግብ ምክንያት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወታደሮች በየወሰኖቻቸው አሰልፈው የኑክሌር ጦርነት ለሰባ ከመሆን፤ ብዙ ሰዎች ካሽሚርን ሁለቱም አገራት በጣምራ መያዝ ይበጃቸዋል ይላሉ። በተመሳሳይ መልኩ አንዶራ የተባለ አገር ፈረንሳይና ስፔን በጣምራ ከያዙት ከ700 ዓመታት በላይ ሆኖአል[201]።

አገራት ሌላው አጎራባች ወደብ አልባ አገር የባህር በር ባለቤት እንዲሆን ከግዛታቸው እንኳን ቆርጠው የሰጡባቸው ሁኔታች አሉ። የተባበሩት መንግስታትም ሆነ መላ ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ አገራት በሰላማዊ መንገድ የባህር በር ባለቤት እንዲሆኑ ይደግፋሉ። ምክንያቱም ፍትሐዊ ስለሆነ ነው። በዓለም ዙርያ አገራት በተለያዩ ምክንያት የባህር በር ባለቤት ሆነዋል። ዙርያዋን በመሬት ተከብባ የነበረችው የዛሬዋ የዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ወደ ባህር የሚያሸጋግር ከአንጎላ መሬት ተቈርጠ ተሰጥቶአት ዛሬ ኮንጎ ሪፐብሊክ የባህር በር ባለቤት ሆናለች።

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በቬርሳይ ውል መሠረት ፖላንድ ወደ ባህር የሚያዘልቃት መሬት ከጀርመን ተቆርሶ ተሰጥቶአት ወደብ አልባ የነበረችው ፖላንድ የወደብ ባለቤት ሆናለች። እነዚህ አማራጮች የምንጠቁመው ከሁሉም የተሻሉ መፍትሔዎች ናቸው በሚል እምነት ሳይሆን የግድ ሳንወድ የምንገባባቸው አማራጮች ናቸው። ከሁሉም የተሻለው መፍትሔ ግን እነዚህ ሁለት እህትማማች አገራት ከመለያየታቸው በፊት ወደ ነበረው፣ ያም ካልሆነ ወደ ፌዴሬሽኑ ያም ካልሆነ በኮንፌዴሬሽን ተሳስረው ቢቆዩ ለዘላቂ ሰላማቸውና ለብልጽግናቸው የተሻለ መሆኑ ማንም አይስተውም።

[200] Fred E.Foldvary, Senior Editor of Progress Report, http:// progress. Org / fold 250. html
[201] Ibid

ኢትዮጵያ በአንድ ወይንም በሌላ መንገድ አሰብ ካልተመለሰላት ችግሩ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው እየተላለፈ በቦሊቪያ እንዳለው ሁኔታ ቁስሉ እያመረቀዘ ይሄዳል እንጂ ኢትዮጵያውያን መቼም የሚተዉት ጉዳይ አይሆንም። ቦሊቪያ በ1883 ዓ.ም ከቺሊ ጋር ባደረገችው ጦርነት የባህር ጠረፍ ግዛትዋ በቺሊ ተወሰደባት። ቦሊቪያ የባህር በር ሲወሰድባት ነፍሷ ከዚያው ጋር ሄደ እያሉ ቦሊቪያውያን ይገልጹታል። ቦሊቪያ የባህር ጠረፍ ግዛትዋ ከተወሰደባት ጊዜ ጀምሮ ወደ አምስት ሺህ የሚጠጋው የባህር ኃይሏ አንድ ቀን የባህር ጠረፍ ግዛታችን እናስመልሳለን በሚል ተስፋ እስከ ዛሬ በቲቲካ ሐይቅ የባህር ላይ ጦርነት ልምምድ ያደርጋሉ። እንደ ቢቢሲ ዘገባ ያቦሊቪያ ዜጋ ሁሉ ከልጅነቱ ጀምሮ ያደገው ቺሊ የባህር ጠረፋችን ሰረቀችን ሲባል እየሰማ ሲሆን እርሱም በተራው ለልጆቹ ይህንኑ እየነገረ ያሳድጋል። ማንኛውም ቦሊቪያዊ አገርህ ወደብ አልባ ሆነች ሲሉት በምንም ዓይነት የማይቀበለው ሲሆን ሕዝቡም በየዓመቱ "የባህር በር የተወሰደበት" ቀንን ዘክሮ ይውላል። ቅርብ ጊዜ ደግሞ ከ132 ዓመታት በኋላ የባህር በሬ በቺሊ ተወሰደብኝ የምትለዋ ቦሊቪ ጉዳዩን ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንደምትወስደው አስታውቃለች[202]።

የአሰብ ችግርም ለሁለቱም፣ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ በቶሎ ይፈታል አልያም እንደ ቦሊቪያው ችግር ተንጠልጥሎ ይቆያል እንጂ መቼም ቢሆን ኢትዮጵያውያን የሚተዉት ጉዳይ አይደለም። በመሃሉ ግን ለሁለት ወንድማማችና እህትማማች ሕዝብ ለእልቂት መንስኤ ሲሆን መቻሉ ግን አሳዛኝ ነው።

ኢሕአዴግ በዲፕሎማሲም ይሁን ወይንም በሌላ በማንኛውም መንገድ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ ፍላጎቱ እንደሌለውና ብሎም እንዲያውም እንደሚቃወም በከረሩ ቃላትና በብስጭት ስሜት በተደጋጋሚ ገልጾአል። ከዚህም አልፎ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል የሚሞክር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ኃይል

[202] See http://www.bbc.co.uk/news/world_latin_America_12842978. Accessed on 3/3/2011.



ቢነሳ ኢሕአዴግ እርምጃ እንደሚወስድበት ከዚህ ቀደም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአጽንኦት አስጠንቅቀዋል።

ይህም ማለት ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ በሥልጣን እስከቆየ ድረስ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት የመሆን ዕድል ዜሮ ነው ማለት ነው። አልያም ቀይ ባህር የአፋር ክልልን ለሁለት ሰንጥቆ የባህር ሰላጤ የሚፈጥር መሆኑ በጂኦሎጂስቶች ስለተረጋገጠ በኢሕአዴግ ዘመን ኢትዮጵያ የባህር በር የሚኖራት ይህ ስንጥቅ በጥቂት ሺህ ዓመታት ወደ ፊት ማስቀደም ከተቻለ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ በአፋር በኩል በቀይ ባህር በይ ተቆፍሮ ውሃውን ወደ ኢትዮጵያ ማዝለቅ ይቻላል ይላሉ። እነዚህ ለፌዝ ይባሉ እንደሆነ ነው እንጂ ለአሰብ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ለኤርትራም ይሁን ለኢትዮጵያ ይህን ያህል የሚከብድ ጉዳይ አይደለም። ጉዳዩ በኢሕአዴግ ዘመን መፍትሔ ካላገኘም በአገራችን አባባል "እርስት በሺህ ዓመቱ ለባለቤቱ" እንዲሚሆን አንጠራጠርም።

የሃርቫርድ ፕሮፌሰር ሩፐርት ኤመርሰን (Rupert Emerson) እንዳሉት "በአሁኑ ወቅት የአፍሪቃ አገራት ቅኝ ገዢዎች በቀየሱአቸው ወሰኖች መታሰር በቅኝ ግዛት ጊዜ የተተነበየውና የተፈለገውን አያንጸባርቁም። በቅኝ ግዛት ጊዜ የተተነበየው የአፍሪቃ አገራት ነፃ ሲወጡ እነዚህ በኢምፔርያሊስቶች በዘፈቀደ የጂኦግራፊ የኤኮኖሚ ገጠመኞችን በመሻር የተወሰኑ ድምበሮች ተሰርዘው አህጉሪቷ የተፈጥሮ መሰመርዋን ተከትላ የተፈጥሮ ቅርጽዋን ትይዛለች የሚል ተስፋ ነበር[203]"።

ሁለት አገራት አንድ ሆነው የተፈጥሮ ቅርጻቸው መያዝ ከሚገባቸው አገራት ኤርትራና ኢትዮጵያ በቀዳሚነት ማስቀመጥ ይችላል።

ይህ ከዚህ በላይ በሓርቫርድ ፕሮፌሰር ሩፐርት ኤመርሰን የተፃፋው እንግሊዝኛው በተሻለ ይገልጸዋል።

[203] See www.Ethiomedia.com /andanun/2432.htlml.

"The present consolidation of African states within former colonial borders runs counter to much of what had been predicted and desired during colonial era. It was widely assumed that as soon as Africans came to freedom they would sweep aside the abrbitrary boundaries imposed by imperialists which cut across tribes and override the dictates of geography and economics. The continent had been partitioned to meet colonial convenience, but it would be reshaped to realize its natural contours and return to its natural essnce[204]."

Erasing colonial imposed lines between Ethiopia and Eritrea will surely restore the natural contour and essence of this ancient region.

[204] ibd



## ምዕራፍ 13

## ስባሪዎችና የተለያዩ የሕብረተ ሰቡ ክፍሎች አስተያየቶች

### 1. በኢትዮጵያ ሕልውና ላይ የተጋረጠ አዲስ አደጋ[205]

በዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም

ቀድሞውኑም ቢሆን በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ መቅሰፍት የሚታመሰው፤እጅግ አደገኛ በሆነው በአፍሪቃ ቀንድ ከዚህ በፊት ባልነበረና የአካባቢውን ፀጥታና ሰላም ከአሁኑ በበለጠ ሊያናጋ የሚችል በቀጭን ክር የተንጠለጠለው የጂኦፖለቲካውን ይዘት የሚያተራምስ፤ አካባቢውን በኑክሌር ጦርነት ቀለበት ውስጥ የሚዘፍቅ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል አዲስ ክስተት እየተፈጠረ ነው።

ይኸውም የኑክሌር በምብ ባለቤት ለመሆን በግልቢያ ላይ የምትገኘው ኢራን በቀይ ባህር በተለይም በአሰብ ላይ የጦር ሰፈር እንዳቋቋመችና ሚሳይሎችን እንደጠመደች በተለያዩ የዜና ምንጮች ተዘግቦአል።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ትርጉም የለሽ ጦርነት በ1993 ዓ.ም. በኢትዮጵየ አሸናፊነት ተደምድሞ የአልጀርስ ስምምነት ከመፈረሙ ሳምንታት በፊት አሰብ ከሻቀጥ ማስተላለፊያነቱ በበለጠ ለኢትዮጵያ ሕልውናና ነፃነት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትና አስገንዝበን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የማያጥፍ ምንም ዓይነት ስምምነት የኢትዮጵያ ባለስልጣናት እንዳይፈርሙ ብዙዎቻችን አሳስበን ነበር። ከአልጀርስ ስምምነትም በኋላ ከቶም ምንም የማይሳናቸው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር "አሰብ የግመል ውኃ ማጠጫ ይሁን" ብለው ከረገሙ

[205] <u>በአዲስ ነገር</u> ጋዜጣ የወጣ፤ 1998 ዓ.ም (አካባቢ)

በኋላ ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡና ከኢትዮጵያ የሚወጡ ማንኛቸውም ሸቀጣ ሸቀጦች በጅቡቲና በሌሎች የአካባቢው ወደቦች በኩል እንዲገቡና እንዲወጡ ወሰኑ።

የቀይ ባህር ሰላጤ (Red Sea littoral) በአሳ ሀብት የበለፀገች፣ የቱሪስት መስህብ የሆነችና በማህፀንዋ ብዙ ዓይነት ማዕድናት ያቀፈች እጅግ ስትራቴጂክ የሆነችዋ የባህር ሰላጤ ነች ኤርትራ እራስዋ ካልተጠቀመችበት ለሌሎች ሲከፋም ለኢትዮጵያ ጠላቶች አሳልፋ ትሰጥ እንደሁ እንጂ የግመል ውኃ ማጠጫ እንደማትሆን በጊዜው አሳስበን ነገር። ብዬ ነበር ማለቱ ባያስደስተንም የተፈራው ደርሶ እነሆ በቆጣለው መልኩ ምናልባትም የኢትዮጵያ ጠላት መሆንዋ በውል ባይታወቅም ወደጅ መሆንዋ ያልተረጋገጠው ኢራን በአሰብን ላይ ጦር አስፍራ ሚሳይሎች እንዳጠመዳች የዓለም ዜና አውታሮችና ልዩ ልዩ ምንጮች ዘግበዋል። በይዘቱ ይህን መጣጥፍ የሚመስል ቃሁፍ ይኸው ጸሐፊ ለአዲስ ነገር ጋዜጣ አቅርቦ ከታተመ በኋላ በኢትዮጵያ የኢራን አምባሳደር መልስ ሲሰጡ "ያዕቆብ የፅዮናውያን አሽከር ነው" ብለው ከመሳደብ ውጭ የኢራን ጦር አሰብ ላይ አልሰፈረም የሚል ማስተባበሪያ ከአፋቸው አልወጣም። ኤርትራ አሰብ ላይ የኢራን ጦር አልሰፈረበትም ብላ ብታስተባብልም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ለኤርትራ ምንም ጥቅም የማይሰጠው አሰብ እውነትም የግመል ውኃ መጠጫ ሆኖ ሲቀር ኤርትራ ስለማትፈቅድ ለለየላቸው የኢትዮጵያ ጠላቶችም ቢሆን አሳልፋ መስጠትዋ የጊዜ ጉዳይ ነው።

### 1.1 አቶ ኢሳያስ አሰብ ላይ የኢራን ጦር እንዲሰፍርና ሚሳይሎች እንዲጠመዱ ለምን ፈቀድ?

የድንበር ውዝግቡ እንዲዳኝ በኢትዮጵያና በኤርትራ ስምምነት የተሰየመው የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ አለመፈጸሙ ይታወሳል። በሂደትም ኤርትራ በተለያዩ ወቅቶች በኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ላይ ትንኮሳ በማካሄድ፣ የሰላም ቀጣናውን ጥሳ በመግባት የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ኃይል ከኤርትራ በማባረር የአልጀርሱን ስምምነት ጥሳለች። አንድ ዓለም አቀፍ ውል ውድቅ የሚሆነው አንዱ ወገን ውሉን ሲጥስና ሌላው ወገን



ከአንግዲህ ውሉ እንደማይገዛው ሲያስታውቅ ነው። የኢህአዴግ መንግስት በቂ ሕጋዊ ምክንያት ቢኖሩትም የአልጀርስ ስምምነት ውድቅ ሆኗል ለማለት ለምን ወኔው እንደከዳው አይታወቅም። ያም ሆነ ይህ የድንበር ውዝግቡ እልባት ባለማግኘቱ እነዚህ ሁለት አገሮች በጦርነት ይፋለሰጋሉ የሚል ከፍተኛ ስጋት አለ። ጦርነት ቢነሳም በኤርትራ ሽንፈት እንደሚደመደም መገመት ይቻላል። ይህም የሚሆነው የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ከኤርትራ አቻው ጋር በጀግንነት ይበልጣል ለማለት ሳይሆን ሁለቱም ከአንድ ህዝብ አብራክ የመነጩ በመሆኑ የጦርነቱ ውጤት የሚወስነው የህዝብ ብዛትና የኢኮኖሚ አቅም ነው። አሸናፊው የኢትዮጵያ ጦርም ወደ አሰብ ዘልቆ አሰብን ይይዛል የሚል ስጋት በኤርትራውያን ዘንድ መኖሩ አያጠራጥርም። ጦርነት ባይነሳ መልካም ነው፣ ጦርነቱን ማምከን ካልታቻለም ግን የኢትዮጵያ ሕዝቡ ከመከላከያ ኃይሉ የሚጠብቀው ይኸው ነው።

አቶ ኢሳያስ በቅርብ ጊዜ የኑክሌር ጦር መሣሪያ ልትታጠቅ ለምትችል ኢራን አሰብ ላይ ጦርዋን እንድታሰፍር ሲፈቅዱ ጦርነቱ ቢነሳ ኢትዮጵያ አሰብ ላይ ኢራንን ልትገጥም አቅሙ አይኖራትም ከሚል ስሌት ተነስተው የኢትዮጵያ ሕጋዊ የአሰብ ባለቤትነትን ለማምከን አስበው ያደረጉት ይመስላል።

አቶ ኢሳያስ የኢራን ጦር አሰብ ላይ እንዲሰፍርና ሚሳይሎችን እንዲያጠምዱ ሲፈቅዱ አሰብ ምንም የማያከራክር ያለቀለት የኤርትራ ግዛት ከመሆን አልፎ እንደፈቀዱ የሚያዙበት፣ ቢሻቸው አሳ የሚያሰግሩበት፣ ቢሻቸው የኑክሌር ሚሳይሎች ለሚያጠምዱበት አገሮች አሳልፈው ሊሰጡ የሚችሉ የግል እርስታቸው አድርገው ቆጥረውት ነው።

አሰብ ከሉሲ (ድንቅነሽ) ብንነሳ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን የአፋሮች የእነ ቢትወደድ ሡልጣን አሊ ሚራህ፣ የእነ ደጃዝማች ሃንፍሬ አገር መሆኑን አቶ ኢሣያስ የዘነጉት ይመስላል። የአሰብ ባለቤትነት ዛሬ የጥቂት ኢትዮጵያውያን ምሁራን ወይንም ፖለቲከኞች ጉዳይ ሳይሆን ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ከምሁሩ እስከ ገበሬው የሚቆጠቁጠው ለመሆኑ አዲስ አበባ ወይንም ገጠር ውስጥ አንድ መንገደኛ ቢጠየቅ የሚያረጋግጠው

ነው። ዛሬ ሕዝቡ በኢህአዴግ ዘመን ከደረሱ ጥፋቶች ሁሉ የትኛው ይበልጣል ተብሎ ቢጠየቅ ሳያመነታ የኢትዮጵያ የባህር በር መዘረጋት ነው እንደሚል በፍጹም አያጠራጥርም። ልክም ነው።

## 1.2. የኢራን ጦር አሰብ ላይ መስፈር ለኢትዮጵያ ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ስጋቱ እምን ላይ ነው?

ተስፈንጣሪዋ ኢራን ለኤሌክትሪክ ኀይል ማመንጫና ለመሳሰሉት ሰላማዊ ግልጋሎቶች ዩራኒየም አብላልታ በማጠናቀቅ ላይ እንደሆነች በተለያዩ መድረኮች በልበ ሙሉነትና በኩራት ተናግራለች። የኑክሌር ሳይንቲስቶች እንደሚያረጋግጡት ለሰላማዊ ግልጋሎት የተዘጋጀ ዩራንየም በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ጦር መሣሪያነት ማሸጋገር ይቻላል። ማን ይሙት አሁን በነዳጅ የተንበሸበሸችው ኢራን ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ከፍተኛ ወጪና ጥበብ የሚጠይቀው የኑክሌር ኃይል አስፈልጎአት ነው የኑክሌር ኘሮግራምዋን የጀመረችው? የኢራን ዓላማ የእስራኤልን የኑክሌር ጥቃት ለመከላከልና የተለያዩ ፍላጎቶችዋን ለመጫን ለምሳሌ አሰብን ከኢትዮጵያ እጅ ለማስጣል የሚያስችላት ጉልበት ለማግኘት መሆኑ ከወዲሁ መገመት ይቻላል። አሰብ ለምሥራቁና ለመሃሉ የአገራችን ክፍሎች እጅግ ቅርብ ስለሆነች በአካባቢው የሚኖረው ህዝባችን በእስራኤልና በኢራን መሃከል የኑክሌር ግጭት ቢፈጠር ህዝባችን ለኑክሌር ልውውጡ (Nuclear exchange) ሰለባ ሆነ ማለት ነው። እስራኤልና ኢራን ጦርነት ውስጥ ባይገቡ እንኳን እስራኤል የኢራን አፍሪቃ ውስጥ መስፋፋት ለማምከን ከኢትዮጵያ ጋር የተለየና የጠበቀ ወዳጅነት ትመሰርት ይሆናል። ይህም ቢሆን ባይሸሹም ዞር እሉ ዓይነት በማያባራው በእስራኤልና በመካከለኛው ምስራቅ ንትርክ አገራችን በምንትዳዋ ትዘፈቅ?

ከጥቂት ወራት በፊት ግብፅም ለሰላማዊ ግልጋሎት የሚውል የኑክሌር ኘሮግራም መጀመርዋ በይፋ ከአስታወቀች በኋላ አሁን ደግሞ ለግንቦታው ጨረታ አውጥታለች። (ሪፖርተር ጥር 15 ቀን 2003 ገጽ 1) ከእስራኤል ጋር በካምፕ ዴቪድ የሰላም ውል የተፈራረመችው ግብፅ ኑክሌር ኃይል ለምን አስፈለጋት የሚለው



በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ ጥያቄ እንደሚጭር ግልፅ ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህ አስተያየት የተጋነነ ነው፤ በዚያ በኩል የሚመጣ አደጋ የለም ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም አበው እንደሚሉት ታምሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ብልህነት ነው።

## 1.3. ኢትዮጵያን ከኑክሌር ስጋት ለማላቀቅ ምን መደረግ አለበት

ኑክሌር መሣሪያ በሰፊው ታጥቃ እንደነበረ ይነገርላት የነበረችው ደቡብ አፍሪቃ ነፃነትዋን ስትጎናፀፊ (አፓርታይድ ሲፈርስ) ማንም ሳያስገድዳት አፍቃሪ ከኑክሌር ነፃ ቀጠና እንድትሆን በማሰብ የኑክሌር መዋቅርዋን አፈራረሰች። አሁንም አፍሪቃ ከኑክሌር መሣርያ ቀጠና ውጭ እንድትሆን ኢራን ከአፍሪቃዊ ግዛት ከቀይ ባህር ጦርዋን እንድታስወጣ የአፍሪቃ ህብረት መጠየቅ ይገባዋል። በኤርትራ አጋዥነት በአፍሪቃ ውስጥ ኢራን የጦር ሰፈር እንዲኖራት መፍቀድ ለኩሩ ኤርትራውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን አሳፋሪ ሊሆን ይገባዋል።

70% በላይ የዓለም ነዳጅ መተላለፊያ በሆነችው በቀይ ባህር የኑክሌር መሳሪያ መኖር ለመርከቦችና ለኢንተርናሽናል የባህር ትራፊክ እጅግ አደገኛ በመሆኑ በኑክሌር ቦምብ የታጠቀች ኢራን ቀይ ባህር ላይ መስፈር ለዓለም ሰላምና ፀጥታ አስጊ በመሆኑ ኢራን አሰብ ላይ ያቋቋመችው የጦር ሰፈር ዘግታ እንድትወጣ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት አስገዳጅ እርምጃ እንዲወሰድ ኬንያ፣ ቢቻል ሱዳን፣ ጅቡቲና ኢትዮጵያ ጥያቄ እንዲያቀርቡና ግፊት እንዲያደርጉ ይገባል። አፍሪቃ ከኑክሌር መሣሪያ ነፃ መሆን አለባት የሚለው መርህ በግብፅ በኩል እንዳይጣስ እነዚህ አገሮች የተባበሩት መንግሥታት ክትትል እንዲያደርግ በየጊዜው ማሳሰብ ይገባቸዋል።

ይዋልም ይደር ኢትዮጵያ ለኑክሌር ጥቃት ልትጋለጥ እንደምትችል ግልጽ እየሆነ መጥቶል። በድንበር ተሻጋሪ ወንዞችዋ፣ በምትገኝበት የጂኦግራፊ አቀማመጥዋ፣ በሶስዮ ፖለቲካ ይዘትዋ (ባህል፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ታሪክ ወዘተ) ምክንያት ኢትዮጵያ በአንድ ጀምበር እንድትፈርስ የሚፈልጉና ለዚህም ሌት

ተቀን በሚሠሩ ጠላቶች ተከብባለች። ስለሆነም ኢትዮጵያ ከጥቃት ለመከላከል የሚያስችላት ከጠላቶችዋ ጋር የሚመጣጠን ትጥቅና ኃይል ማዘጋጀት፣ ከዚህ በፊት ተጀምሮ እንደነበረው በጥናት ደረጃም ቢሆን ዝግጅቱን መጀመር አለባት። ሆኖም ግን የአገር ሉዓላዊነትና ሕልውና ማስከበር የሚቻለው በአንደኛ ደረጃ ሰብአዊ መብቶች ተከብረው የሕግ የበላይነት ተረጋግጦ ሕዝቡ በመንግስት ላይ እምነት ኖሮት ሲገኝ ነው።

ኤርትራውያን ለበጎም ይሁን ለክፉ ሊበጠስ በማይችል ሰንሰለት ተፈጥሮ ከኢትዮጵያ ጋር አቆራኝቶአቸዋል።አንዳንድ ከአፍንጫቸው አርቀው ሊያስቡ የማይችሉ መሪዎች አይገነዘቡት እንደሁ እንጂ የሁለቱም መጻኢ ዕድል አንድና አንድ ነው። ኢትዮጵያውያን ከኤርትራውያን ጋር፣ ሲሆን በጥምረት አልያም በመልካም ጉርብትና በወንድማማችነትና በእህትማማችነት በመረዳዳትና በመደጋገፍ ጠላትን በጋራ በመከላከል መኖርን እንደሚመርጡ በተለያዩ ወቅቶች ለምሳሌ አንዳንድ ኤርትራውያን ኃላፊነት በጎደለው መልኩ ከኢትዮጵያ በተባረሩበት ወቅት አስመስክረዋል። ኤርትራውያን ክፉ ቀን ባጋጠማቸው ጊዜ ሁሉ ወገናቸው ወደ ሆነው ወደ ኢትዮጳያ ነው የሚሰደዱት። ይህም ሲሆን ኤርትራዊያን በኢትዮጵያውያን እግር ተተክተው ሊያዩት የሚገባ ነገር አለ። ይኸውም መቼም ቢሆን ከ 90 ሚልዮን ሕዝብ በላይ በእግር መንገድ እርቀት የባህር መግቢያና መውጫ በር ተዘግቶበት ከዘጊው ጋር በሰላም ለመኖር እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል።

ኢትዮጵያ በአሰብ ላይ ያላት ሕጋዊ መብቶች የዓለም ሕግጋትን፣ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎችን፣ የራሱ የኤርትራ ሕዝብ ውሳኔ በማጣቀስ በሌላ ወቅት በሰፊው የተተቸ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም በዚሁ በቀይ ባሕር በኩል በተደጋጋሚ መወረራችን አሰብ ለኢትዮጵያ ሕልውና ወሳኝነት እንዳላት እንደዚሁ በሌላ ወቅት ተገልጿል። እንደሁም በ1960ዎቹ መባቻ ላይ አሰብን ያስተዳድሩ የነበሩ አንድ አዛውንት ለዚሁ ጸሐፊ እንዳረጋገጡት ኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ ለመገንባት ከሶስት ቢልዮን ዶላር በላይ ወጪ ያደረገች ሲሆን፣ አሰብ በኤርትራ እጅ ከገባች በኋላም የኢህአዴግ መንግስት ከኢትዮጵያ ወሰን አንስቶ



ወደ አሰብ ወደብ የሚያስገባ መንገድ በ56 ሚልዮን ዶላር አሠርቶ ለሻብያ እንዳስረከበ ይነገራል።

ስለዚህ የአሰብ ጉዳይ በግድ ለሁለቱም አገራት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መፈታት አለበት። እነዚህ አገሮች በሰላም እንዲኖሩ ከተፈለገ ፈቃደኛነቱ ካለ ችግሩ የሚፈታበት ብዙ መንገዶች አሉ። (I) አንዱ መንገድ ኤርትራና ኢትዮጵያ ከ1983 ዓ.ም. ማለት ኤርትራ ከመገንጠልዋ በፊት ወደነበረችበት ሁኔታ መመለስ ነው። ኤርትራውያን ይህንኑ ባያስደስታቸው ወደ ፌደሬሽን መመለስ ሌላው መፍትሔ ሊሆን ይችላል። (II) ኤርትራውያን ብቸኝነቱ ከመረጡም ሁለቱም አገሮች አሰብን በጣምራ ሉዓላዊነት (Joint Sovereignty) ይዘው አሰብን ሊያስተዳድሩ ይችላሉ። ይኸ ሁኔታ ለሰላም ሲባል እንደመፍትሔ ሊቆጠር ይችላል እንጂ የኢትዮጵያ የአሰብን ባለቤትነትን አይሽርም። ዛሬ ዴሞክራቲክ ኮንጎ የምትባለው አገር በ1884—1885 ዓ.ም. በተደረገው ኮንፈረንስ ከአንጎላ ወደ ባሕር ሊያዘልቃት የሚያስችላት መሬት እንደተሰጣት ሁሉ ኢትዮጵያም ከወሰንዋ አንስቶ ወደገነባቸው ወደ አሰብ የሚያዘልቃት ካሪዶር ሊኖራት ይገባል። ይህም የሚሆነው የወደቡ ባለቤትነት በኢትዮጵያ እጅ ሆኖ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኋላ በቨርሳይ ስምምነት መሠረት ፖላንድ እንደዚሁ በጀርመን ሙተላሰፊያ ተሰጥቷት ወደ ባህር ለመዝለቅ የሚያሸትላት ሙተላሰፊያና ወደብ እንዲኖራት ሆኗል።

## 1.4. መደምደምያ

የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እስከተረጋጠ ድረስ የኢራን ይሁን ወይንም የሌላ ባዕዳን አገር ጦር አሰብ ላይ የሚሰፍርበት ምክንያት አይኖርም። ስለዚህ የውጭ ኀይሎች ጣልቃ ገብነት ለማስወገድ በሁለቱ አገሮች መሃከል ሰላም ኖሮ ይህንን አሳፋሪ ድህነት በአስቸኳይ እንዲቀረፍ፣ ሁለቱም አገሮች በአንድ ጀምበር ጠፍተው ቢያድሩ ደስ የሚላቸው ኀይሎች በሃፍረት እንዲሟሽሹ፣ ለዚህ ሁሉ ቁልፍ አሰብን ወደ ባለቤቱ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ነው፤ ወይንም በአንድ ወቅት አቶ ኢሣያስ እንዳሉት "የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን በህዋው (Space) ላይ ነው ያሉትን ተከትሎ በሁለቱም መሃከል መኖር የማይገባው ሰው ሠራሽ የድንበር

መሰመር ማጥፋት ነው። ምናልባት ፌዴሬሽን ወይንም ውህደት በቅርብ ጊዜ እይታ ሕልመኛነት ነው ብሎ መፈረጅ ይቻል ይሆናል። ሆኖም ግን ማንኛውም ትልቅ ሃሳብ ከሕልም ይጀምራል። በመጨረሻም ሰሞኑን በአሜሪካ በኢትዮጵያውያንና በኤርትራውያን የወዳጅነት መድረክን የሚደረገው ውይይት ይበል የሚያሰኝ ነው። አዘጋጆችንም በአርቆ አሰተዋይነታቸው ሊደነቁ ይገባል።



## 2. የባህር በር መብትና የፌዴራሉ ምክር ቤቶች ኃላፊነት[208]

የአፋር ሕዝብ አንድነትና የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋትን በተመለከተ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ችግሩንና መፍትሔውን በመጠቆም ያለተፈነቀለ ድንጋይ ያልተማሰ ሥር የለም ማለት ይቻላል። ምናልባትም እንደ የኢትዮጵያ "የባህር በር ይገባኛል" ጥያቄን ያህል፣ ታማኝነታቸው ወዴት እንደሆነ በውል ማወቅ ካዳገቱት ከአንዳንድ የኢሕአደግ ካድሬዎች በስተቀር፣ ሕዝቡ እንዲህ በአንድ አሳብና መፍትሔ የተስማማበትና የደመደመበት ኢትዮጵያዊ ጉዳይ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ስለዚህ የኢትዮጵያን ልማትና ሕልውና የቅንጣት ያህል ጉዳያቸው ባልሆኑ የውጭ አካሎች አደራዳሪነትና ውሳኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት ከስሌት ሳያስገባ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የሚፈረም የባህር በር መብትን የመያስከብር ስምምነት የተጻፈበት ወረቀት ያህል ዋጋ አይኖረውም። ጉዳዩም በአቶ መለስና በአቶ ኢሣያስ ፈርማና አቅፍቅፍ የሚዘጋ ነገር አለመሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጾአል።

የዚህ የዛሬው አነስተኛ መጣጥፍ ዓላማ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ጉደይ በአንድ ወቅት የሚጋጋም በሌላው ጊዜ ደግሞ ደብዛው የሚጠፋ ጉዳይ መሆን እንደሌለበት ክርስቲያኑና ሙስሊም ተስፋ አይቆርጥምና ትንሽ ያለችዋ አንድ የተሰፋ ለወዳፊትም ለመጠቆምም ነው። በተገኘው ዓለም አቀፍ መድረኮች በሚደረጉ ውይይታች ሁሉ የሚነሳ ጉዳይ መሆን አለበት። ጉዳዩ በዓመት በሁለት ዓመት ወይንም በእኛ ዕድሜ ባይፈታ ለልጆቻችን መተላለፍ ይኖርበታል። የአገር ጥቅም ዛላቂ በዓመት በአሥር ዓመት አይሰላም፣ ዘላለማዊ ነው። አንድ ሕዝብ በአንድነት በእውነተኛና ፍትሐዊ በሆነ ዓላማ አምኖ ለዓላማው

208 በዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ተጽፎ ሐምሌ 9 ቀን 1993 ዓ.ም ህብረት ጋዜጣ ውስጥ ከወጣ ጽሁፈ የተወሰደ

በኬታማነት በጽናት ከታገለ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ምንም አይሳነውም። የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ደግሞ ዓለም የተስማማበት ፍትሐዊ ጥያቄ ነው። በአሁኑ ወቅት ዋናው ነገር ጉዳዩ ጊዜ እስኪፈታው እረግቶ እንዳይቀር ማንቀሳቀስ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተግባር ነው። ይዋል ይደር እንጂ ጊዜው ሲደርስ ቦታውን የማይለቅ የለም። ኢሕአዴግም ቦታን ለቅቆ ውሉ አድሮ በታሪክ በሚገመገምበት ጊዜ ካለማቸውና ካጠፋቸው ጉዳዮች ሁሉ ገዝፎ የሚታየው አገሪቱን በጉሣ መከፋፈሉ አይደለም። ይኸ በጊዜው የሚታረም ጉዳይ ነው። የአገሪቱም አንዱን ክፍል ማስገንጠሉም አይደለም። ይኸም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ኤርትራውያን ከፍቶናል ከእናንተ ጋር አንኖርም ካሉም የአንድ ቤተሰብ መነጣጠል እንደሚያሳዝን ሁሉ ቢያሳዝነንም እንቀበለዋለን። ሆኖም ኤርትራውያን መቼም ቢሆን በኢትዮጵያዊነታቸው እስከአመኑ ድረስ ማንም የኢትዮጵያዊነት ዜግነታቸውን ሊነፍጋቸው አይችልም።

ከእነዚህ የኢሕአዴግ ድርጊቶች ሁሉ ገዝፎ የሚታየው በእኔ ግምት ለዝንተ ዐለም የኢትዮጵያ የባህር በር እንዲዘጋ መስማማቱ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድን መሪ አስተዳደር ያደረሰው ጥፋትም ሆነ ያመጣው ልማት ብዙ ቅጾች (Volumes) ሊጻፍበት በሚችል በአንድ ዐረፍተ ነገር አጠቃልሎ የማስቀመጥ ችሎታ አለው። ከልጅ ኢያሱ አንስቶ እስከ ዛሬ ያለው መንግሥት ሕዝቡ ጉልተው የሚታዩትን አንዱን ድርጊት በመጥቀስ ያጠቃልለዋል።

በኢያሱ ዳቦ ነው ትራሱ
በዘውዲቱ ተደፋ ሌማቱ
በተፈሪ ጠፋ ፍርፋሪ
በመንግሥቱ እሬሣ ጉትቱ
በመለስ አገር ተቈረሰ

ይኸ እንግዲህ የኢሕአዲግ የታሪክ ቅሪት (Historical Legacy) ሆኖ ሊኖር ነው። ሆኖም ግን ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ነውና ኢሕአዲግ ከዚህ የታሪክ ወቀሳ አሁንም ሊድን ይችላል። እኛ ግን "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱትም አይሰማም"



ነውና ከእንግዲህ ለኢሕአዲግ መንግሥት የሥራ አስፈጻሚው ክፍል የምንለው የለንም።

ለሕግና አውጪው አካል ግን የምንለው ይኖረናል። በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የበገኑት ኢትዮጵያውያን ሳንቃቸው እስኪለነጠቅ በመጮሃቸው የተረፋቸው ነገር ቢኖር በሻዕቢያ ዓላማ አቀንቃኝነት፣ በጠረኛነትና በተስፋፊነት መፈረጅ ነው። ይኸ ግን የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚችሉትን ሁሉ ከማድረግ የትግል ክንዳቸውን ሊያዝል አይችልም። አጼ ሚኒሊክ ከጣልያኖች ጋር የተፈራረሙአቸው የወሰን መካለል ውሎች ውድቅ እንደሆኑ አሰብና አካባቢው የኢትዮጵያ የባህር በር የአፋሮች መሬት መሆኑን ከቶም ምንም ነገር የማይሳነው ኢሕአዲግ ቀርቶ በስም ሊጠቀሱ የማይችሉ የውጭ አገር የፖለቲካ ጠበብትና አምባሳደሮች ኢሕአዲግ የአገሩ የባህር በር መዘጋት እንዴት እሺ ብሎ እንደተቀበለ ያስገርማቸዋል። የባህር በር በተዘጋበት ጊዜ ለመቃወም አቅም አይፈቅድም ነበር ቢባል እንኳን ጉዳዩን አንጠልጥሎ "እስቲ ተከድኖ ይብሰል" ብሎ ለአመቺ ቀን ማቆየት የአባት ነበር።

አገርን አስገንጥሎ የባህር በርን አዘግቶ ለሉዐላዊነት ቆሜአለሁ ሲባል "ድንቁም ሉዐላዊነት" ያሰኛል። አገራዊ ሉዐላዊነት ያስከበረውስ፣ ኢትዮጵያን ከውርደት መዝዞ ያወጣውስ፣ ክብራችንን በደሙ የዋጀው፣ ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን ነው። ከዚህ ሌላ ጀግና ደግሞ አናውቅም።

የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ ለአንዴና ለሁሌም እንዳይዘጋ የመጨረሻው መንጠልጠያ ኢሕአዴግ ሲያመቸው ባካፋ ሲቸግረው በጭልፋ የሚዝቀው ሕገ መንግሥቱ ሊሆን ይችላል። ሟቹ የግብጽ ፕሬዝደንት ጋማል አብደል ናሥር "ግብጽን የሚጠቅም ከሆነ ከጂኒም ጋር እንኳን እደራደራለሁ" እንዳሉ ሁሉ ለአገራችንና ከጂኒ ጋር ባንዳራዳርም ለሕዝባችን ከጠቀመ በተደጋጋሚ በመንግሥት በተጣሰው ሕገ መንግሥት ከመጠቀም አናመነታም።

የኢትዮጵያ የባህር በር ለአንዴና ለሁሌም እንዳይዘጋ የመጨረሻው ኃላፊነት የወደቀው በተወካዮች ምክር ቤትና በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ላይ ነው። ክሔራዊ ምክር ቤት

ብሔራዊ እንደመሆኑ መጠን የአገርና የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ እንጂ የአንድን ፓርቲ ጥቅምና ፍላጐት ኩሊ መሆን የለበትም። አላፊነቱም በሙስና፣ በአምቻና ጋብቻ፣ በፓርቲ ወያላነት፣ በወንዝ ልጅነት የሚዘረፈው ከውጭ የሚገኘው ብድር ከማጽደቅ የላቀ ነው። የኢትዮጵያ የባህር በር ከማስከበር የበለጠ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚነካ ጉዳይ መቼም ቢሆን በአጀንዳነት ሊቀርብለት አይችልም።

የሕግ መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንኡስ አንቀጽ 12 እና 18 የሕግ አስፈጻሚው ክፍል ማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ ካቢኔው የሚዋዋሉአቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች የማጽደቅ ወይንም ያለማጽደቅ ሥልጣን ለተወካዮች ምክር ቤት ሰጥቶአል። ምክር ቤቱ ከኤርትራ ጋር የሚያደርገው ስምምነት ሰላም የሚመሠርቱና ምንም የማያጠራጥረው ወሰኖችን የሚከልለውን ክፍል ብቻ አጽድቆ አሰብን አካባቢውን የተመለከተውን ክፍል ላለማጽደቅ ምንም የሚከለክለው ነገር የለም። ስምምነቱ በተወካዮች ምክር ቤት ካልጸደቀ ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

ከዚህ ኢትዮጵያን እግር ተወርች ከሚቀፈድደው ስምምነት ማምለጫ ሌላም ሕገ መንግሥታዊ መንገድ አለ። የፌደሬሽኑ ምክር ቤት በከፊል ሕግ አውጪ ሲሆን በከፊል ደግሞ ፍርድ ሰጪም ነው። ሕገ መንግሥቱ በምሁራን ካስነቀፉት ጉዳዮች አንዱ ቢሆንም ለዓላማችን ስኬታማነት ከጠቀመው እሰዬው ነው።

በሕግ መንግሥቱ አንቀጽ 62 (1) መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥቱን የመተርጐም መብት ተሰጥቶታል። በአንዳንድ አገሮች ለምሳሌ ያህል በአሜሪካ እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ነው። የፌዴራል ሕግ መንግሥት ሕግን በመተርጐም ሥልጣኑ ማንኛውም የሕግ አስፈጻሚው ክፍል የገባው ውል ወይንም ስምምነት እንዲሁም የመንግሥት አካላትም ሆኑ የተወካዮች ምክር ቤት ያወጡዋቸው ሕጐች ከሕገ መንግሥቱ ጋር የማይጣጣሙ መስሎ ከታየው ውድቅ አድርጎ ሊሠርዛቸው እንደሚችል ተደንግጓል። ሕገ መንግሥቱ ለሕግ አስፈጻሚው ክፍሉ ማለትም ለጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ ለካቢኔአቸው



የተለያዩ ሥልጣን ሲያድላቸው የኢትዮጵያን ግዛት ቆርሶ ለሌላ የመስጠት ሥልጣን እንዳላቸው ግን አይደነግግም። የኢሕአዲግ መንግሥት ማለት፣ የሕግ አስፈጻሚው አካል ከኤርትራ ጋር በሚፈራረመው ስምምነት የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት የነበረችው አሰብን አሳልፎ ከሰጠ ድርጊቱ ከሥልጣኑ በላይ (Ultra Vires) ስለሆነ ምክር ቤቱ ስምምነቱን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሰርዘው ይችላል።

የደሞክራሲያዊ አስተዳደር በሰፈነባቸው አገሮች ብሔራዊ ሸንጐ የማያምንበት፣ የሕግ አስፈጻሚው ክፍል የተዋዋላቸው ስምምነቶች አለማጽዳቅ ወይንም መሻር በጣም የተለመደ አሠራር ነው። በቅርብ ጊዜ ፕሬዝዳንት ክሊንተን የአየር ብክለትን ለመቀነስ ከሌሎች የዓለም መንግሥታት ጋር በቶኪዮ ጃፓን የተፈራረሙት ስምምነት ብሔራዊው ሸንጐ (Congress) ስለአላጸደቀው በፕሬዝዳንት ክሊንተን እግር የተተኩ ፕሬዝዳንት ቡሽ ሰርዘውታል። እንዲሁም የአሜሪካው ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተለያዩ ወቅቶች ፕሬዝዳንቱ የወሰኑአቸው በርካታ ውሳኔዎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ብሔራዊ ሸንጐ ያወጣቸው አያሌ ሕጐችን ሕገ መንግሥቱን ይዳፈራሉ በማለት ውድቅ አድርጓአቸዋል።

እዚህ ላይ የእኛዎቹስ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባላት እንዲህ ዓይነት ወኔ ኖሮአቸው የአገርና የሕዝብ ጥቅም ለፓርቲአቸው ካላቸው ታማኝነት ያስቀድማሉ ወይ? አይታወቅም። ወላድ በድባብ ትሂድና ኢትዮጵያ ፈተና በገጠማት ጊዜ ሁሉ የቁርጥ ቀን ልጆችዋ ከደዋት አታውቅም። ጣልያኖች ካምፕ እየገባ የኢጣልያንን ጦር ሰልሎ ለአጼ ምኒልክ መረጃ በማቅረብ ለአድዋ ድል የተባ እስዋጽኦ ካደረገው ከአውአሎም አንስቶ በጊዜአችንም የነፍስ ገዳዩ ደርግ ታንክ በድንጋይ የተጋፈጡት ወጣቶች የወለደች አገር ዛሬ መክናለች የምንልበት ምክንያት የለም። የሕዝብ ምክር ቤት አባሎች በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመንም ሆነ በደርግ ለአለው ኃይል ሳያጐበድዱ ሕዝብና አገር ይበልጥብናል ያሉበት ጊዜያትም አሉ።

ኢትዮጵያ በዘጠኝ ወደቦች የመጠቀም ዕድል አላት እየተባለ ጥያቄአችን ፉር ለማስለቀቅ ይለፈፍ የነበረው ዛሬ አይደገምም። ምክንያቱም ከአሰብ መዘጋት በኋላ ጅባ ባያደርጉም ትናንሽ

የጉሮሮ ማነቆዎች ሙከራ እንደተደረገብን፣ እነዚህ ትናንሽ የጉሮሮ ማነቆች በውጭ ኃግዳችን ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ በጉልህ በመታየቱ ነው። እነዚህ ወደቦች በክፉም በደጉም ወቅት እንዳሻን እንጠቀምባቸዋለን የሚሉ ስለአካባቢው ጂኦፖለቲክስ ስለአገራችን ምድራዊ አቀማመጥ፣ ስለ ታሪክ ሂደታችን ግንዛቤ የሌላቸውና ሰፈራችን (የአፍሪቃ ቀንድ) እጅግ አደገኛ አካባቢ መሆኑን ያልተረዱ የዋሃን ናቸው። በአፍሪቃ ምናልባትም ከአብዛኛው የዓለም አገሮች ከእኛ በላይ ጦር የተሰበቀበት አገር የለም። እኛ ግን በረዥሙ ታሪካችን አንድም ቀን ድምበር ተሻግረን የሰውን አገር ወርረን የያዝንበት ጊዜ የለም በየብስ የተከበቡ የበለጸጉ አገሮች ብዙ ናቸው የሚለውን ትተን ብናውቅበት ይበጀል። የአሰብ ወደ ኢትዮጵያ መቃጠፍ የባህር በር ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የሉዐላዊነት የማስከበርም አላፊነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም።





## 3. <u>ግልፅ ደብዳቤ</u>

ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር
<u>አዲስ አበባ</u>

ክቡር ሆይ

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ሲካሄድ የቆየው አሰቃቂ ጦርነት በመቆሙና ወደ ሰላም አቅጣጫ ዝግመት በመጀመሩ፣ ካልነኩት የማይነካው ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ መደሰቱን አልጠራጠርም። የጦርነቱ መቆም ተከትሉ በዲፕሉማሲው መስክ የሚደረገው ትግል እጅግ አስተዋይነትና ጥንካሬ እንደሚጠይቅ ግልፅ ሲሆን ፣ ይህንን ለተገነዘበው አላፊነቱ እጅግ ከባድ ነው። ምክንያቱም የድርድሩ ውጤት ለብዙ ተከታታይ ትውልድ የሚተርፍ ክፉም ሆነ በጎ አሻራ ጥሉ ያልፋልና ። የዚህም ድርድር ውጤት ጦርነቱ ለምን ተዋጋን? የደረሰብን ኪሳራ ምንድን ነው?፣ የብርቅዬ ወንድሞቻችንና ልጆቻችን ክቡር ህይወት ገብረን ያገኘነው ምንድን ነው? የከፈልነውስ መስዋእትነት ካገኘነው ማካካሻ ጋር ይመጣጠናል ወይ ብሎ ስሌት ሲደረግ መልስ የሚገኘው ከዚሁ ድርድር የመጨረሻ ውጤት ነው።

ሚልዮን ጦር ቢያሰልፉ ሀውልት ቢያንፁ እንደ መብረቅ ቢፈሩ ሁሉም ጊዜውን ጠብቆ አላፊ ነው። ከአፈር ገፊው ገበሬ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚህ ዓለም ሳያልፍ በምን እታወሳለሁ ብሎ እራሱን መጠየቁ አይቀርም። እርስዎም እንደ ጠቅላይ ሚኒስትርነትዎ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ አመራሬ መንግስቴ በምን አይነት ይታወሳል፣ በምንስ ይመሰገናል፣ በምንስ ይወቀሳል

ብለው መጠየቅ ያለ ነው። ታሪክ አድልዎ አያውቅምና ሁሉም እንደስራው ሞገስም ሆነ ወቀሳ መለገሱ ደግሞ አይቀርም።

ለዘላለሚቷ አገራቸው ደህንነትና ክብር ለሕዝባቸው ነጻነትና ህልውና አንገታቸውን ለሰይፍ ደረታቸውን ለአረር የሰጡ መሪዎች ፍለጋ እሩቅ አንሄድም። በቤታችን አሉ። ባንጻሩ ደግሞ አውቀው በድፍረትም ሆነ ሳያውቁ በስህተት አገራቸውን በእጅጉ የጐዱ መሪዎችም ኖረውናል። የወቅቱ የኢትዮጵያ ባለስልጣኖችም ከእነዚህ አማራጮች አንዱን ማንሳት ይኖርባቸዋል። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የእርሶም መንግስት ከሚታወቅበትና ከሚገመገምበት ክዋነኛዎቹ ሚዛኖች አንዱ "አሰብን ለሌላ አስረክቦ ኢትዮጵያን ለዝንተ አለም ወደብ አልባ አድርጎ በየብስ የከረቸመ" ወይንም ደግሞ "በህግ በታሪክ የኢትዮጵያ አንጡራ ሃብት የሆነችዋን አሰብን በረቀቀ ዲፕሎማሲያዊ ትግል አስገኝቶ ለኢትዩጵያ ባህር በር ዋርዲያነት የቆመ" መንግስት ተብሎ ነው።ለማንም ቢሆን ሚዛን የሚደፋውም ምርጫ ሁለተኛው ለመሆኑ አያጠራጥርም። መንግስትዎም የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ለማስከበር የወሰደው ቁርጠኛ እርምጃ ማስረጃ ከሆነ ምርጫው የመጀመሪያው ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ። አለዚያም የኢትዮጵያ የባህር በር ቢዘጋ ኢህአዲግ እንዲህ አይነት ከባድ ኃላፊነት እንዴት ሊሸከም እንደሚችል ሲያስቡት እንኳን ይከብዳል። በኢትዩጵያ የተወከሉት ተደራዳሪዎችም የዲፕሎማሲያዊ ጥበብ መለኪያው ይኸው አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ነው።

## ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ትግል ሰልሎ ኢሕአዲግ ወኔ ከድቶት ይህንን ሁሉቀመሳፍርት መስዋእትነት ለከፈለው ፣ ጦር መጣ ባሉት ጊዜ ለደቂቃ ሳያመነታ ጥሪውን አክብሮ ቀፎው እንደተነካ ንብ ተምሞ ለወጣው ለደጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ቢያንስ አንድ ሊያደርጉለት የሚችሉት ነገር አለ። መንግስትዎም አሰብን የኢትዮጵያ አንጡራ ሃብት ሊያደርግ ካልፈለገ ወይንም ካልቻለ ቢያንስ ቢያንስ ድንበር በሚከለልበት ወቅት የአሰብን ጉዳይ ከድርድሩ መዝዞ አውጥቶ "አልስማማም" ከማለት የሚያግደው ነገር ያለ አይመስለኝም። ሕጋዊነት እየተጠበቀ



ከዚያም አልፎ መሄድ ይቻላል። አለም አቀፍ ሕግ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ ይፈቱ ፣ ጦርነት ከፈነዳም ይቁም ይላል እንጂ የግድ ድንበር ተካለል ፣ የወዳጅነት ስምምነት ፈርም ፣ የንግድ ልውውጥ ውል ተዋዋል አይልም። መንግስትዎ የአሰብን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እስኪፈታ ድረስ ድንበር አልካለልም እንኳን ቢል የአለም አቀፍ ህግን ጣሰ ማለት አይቻልም። በስምምነቱ አሰብን በተመለከተ "አልተስማማሁም" የሚል ክፍተት ቢተው የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ክብደት የሚታያቸውና የአገርና የህዝብ ፍቅር ከሁሉ በላይ የሚያስበልጡ መሪዎች ተፈጥረው ኢትዮጵያ የተከበረችና ጠንካራ አገር ከሆነች የባህር በር መብቷን ልታስከብር ትችል ይሆናል። ከአጼ ቴዎድሮስ ጀምሮ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክና አጼ ኃይለ ሥላሴ የደከሙለት በመጨረሻም በአጼ ኃይለ ስላሴ ዘመን እልባት ያገኘው የባህር በር ጉዳይ ዛሬ በችኮላ የአለም ሕብረተሰብ ዋስትናነት በተንተራሰ ውል ኢሕአዲግ የአሰብ ጥያቄ ቢለቅ የመጪው ትውልዶች መብት ከእግራቸው ስር ሰረቀ ማለት ነው።አሰብ ወደ ኤርትራ ሲካለል ነው የኢትዩጵያ የባህር በር እንዳይዘጋ የተዋደቁት የኢትዩጵያ ጀግኖች አፈሩ የሚከብዳቸው።

## ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

አሰብና የኢሕአዲግ አቋም በተመለከተ አንዳንድ ያልገቡን ነገሮች አሉ። አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ስለሆነች ለኢትዮጵያ ትገባለች የሚሉ የተባበሩት መንግስታት ማህበር፣ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ ፣ የራሺያ፣ የራስዋ የቅኝ ገዢ የጣልያን ዶክመንቶችና (በተለያዩ ፅሁፎች ጠቅሻቸዋለሁ) የጽሁፍ ማስረጃችዎች ዛሬ በየመዛግብት ቤቱ እያሉ ኢሕአዲግ በእነዚህ ዶክመንቶች በመንተራስ የአሰብ የባቤትነት ጥያቄ ለምን ማንሳት እንደማይፈልግ እንቆቅልሽ ሆኖብናል። ምናልባት እኛ ተራ ኢትዮጵያውያን የማናውቀውና በውስጡ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ነገር ካለ በከንቱ እንዳንባጅ ቢነገረን መልካም ነበር።

ኢትዮጵያ በጦርነቱ አሸንፋ በአካባቢዋ ባለው የሃይል ሚዛን ስትሰላ የተባ አቅም እንዳላት ለአለም ሁሉ አስረግጣለች። ሃያላን መንግስታትም ይህ ከፍተኛ ስትራተጂካል ጥቅም ያላት የነዳች

መተሳሰሪያና ከፍተኛ የንግድ መስመር ደህንነትና ዋስትና ልታረጋግጥ የምትችለው ቢያንስ በአፍሪካ ዳርቻ በኩል ባለው ከኤርትራ ይልቅ ኢትዮጵያ መሆንዋን አረጋግጠዋል። ይህም ሆኖ ግን "ሃያልነታችሁን አሳምናችሁናልና ቀይ ባህር ወይንም አሰብን እንኩ" የሚለን የለም። አንዳንዱ ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር አቋርጦ በቤታችን ያለው የአባይን ውሃ የእኔ ነው ሲል፣ እኛ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን የአፋሮች አገር ለአፋሮች ብሎም ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ይመለስ ብንል ምን ያስነውራል።

በጦርነት ማሸነፍ በዲፕሎማሲውም ዘርፍ ይሁን በሕግ ብዙ መብቶችን ያጎናጽፋል። ለምሳሌ በያዙት መሬት ላይ መርጋት የተወራረው ደህንነት (ሴኩሪቲ) የሚያረጋግጠው የመሬት መንሸራሸር ማድረግ ፣ ሌሎችም፣ ሌሎችም። ከዚህ ጋር ተያይዞ ታድያ አሁንም ብዙዎቻችን ያልገባን ነገር አለ። በዘልማድ እንደሚነገረውና በሕግም ዋጋ ያለው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰማንያ ከመቶ "ይዞታ" መሆኑ ከታወቀ የኢትዮጵያ ጦር ወደ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ወደ ኤርትራ ዘልቆ የኤርትራ ግዛት መሆንዋ ምንም የማያከራክረው ተሰነይን ሲይዝ ብዙዎቻችን አንጡራ ሃብታችን ነች የምንላትን አሰብን 20 ኪሎ ሜትር ሲቀር ለምን ተዋት? አሁንም ለኢትዮጵያ ጥቅም ነው ከተባለ ዜጎች ብናውቀው መልካም ነበር።

ኢትዮጵያን የባህር በር አሳጥቶ ዙርያውን በየብስ ማጠር በኢትዮጵያ ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት በእኔ አቅም ተዘርዝሮ አያልቅም። ኢትዮጵያን ከዚህ ቁልፍ ከሆነው ከቀይ ባህር አካባቢ ለማግለል የተደረጉ እጅግ ብዙ ደባዎች ኢትዮጵያ ከጦርነት አዙሪት እንዳትወጣ ከሆኑት ምክንያቶች አንዷና ነው። ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር "ጨዋታ" ከወጣች የምትናገረው የማይደመጥላት የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዋ ሽባ ሆኖ ተሰሚነት የሌላት አገር ትሆናለች። ይኽ ደግሞ በኢኮኖሚውና በጸጥታው ሊከተሉ የሚችሉ ከፍተኛ አደጋዎች ሳይጠቀሱ ነው፡

**ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር**

የአሰብን ወደብ በተመለከተ መንግስትዎ የተከተለው አቅጣጫ ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ለመጠቀም ብቻ የሚያስችላትን መብት



ማረጋገጥ ይመስላል። ለዚህ ማንንም አናመሰግንም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በአሰብ በኩል ሸቀጣሸቀጥዋን ለማስተላለፍ ብትፈልግ ኤርትራ የምታስቀምጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎን ከፍያዎችንም እስካጠናቀቀች ድረስ ማንም ሊከለክላት አይችልም። በዛሬ ጊዜ በየብስ የተከበቡ አገሮች አንዳንድ ግዴታዎችን እስካሟሉ ድረስ ማንም የባህር በር ሊዘጋባቸው እንደማይችል ብዙ ዓለም አቀፍ ሕጎች ይደነግጋሉ። በዚህ አይነት የባህር በሩ ቢዘጋ አቅም ካላቸው በጦር ሃይል እንኳን የተዘጋውን የባህር በር አስከፍተው መጠቀም ይችላሉ። ኢትዮጵያውያን ከመነሻው ያለንን ጥያቄ ሸቀጣሸቀጥ የማስተላለፍ መብት ይጠበቅልን ሳይሆን እኛ የምንለው የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአፋሮች መኖርያ የሆነው የሉሲ (የድንቅነሽ) አገር አሰብ ይመለስልን ነው። በወደብ የመጠቀሙ መብት ብቻ ከመቶ አምሣ ዓመታት በፊት ለገናናው ንጉሰ ነገሥት ለአፄ ዮሐንስ አራተኛው አጥጋቢ እንዳልነበረ ዛሬ ለእኛም አጥጋቢ አይደለም። (ምጽዋ በቱርኮች ወኪሎች በግብጾች እጅ በነበረችበት ጊዜ በእንግሊዞች ማግባባት ኢትዮጵያ በወደቡ በነፃ ትጠቀም ነበር)

ኢሕአዴግ ደርግን ከመደምሰሱ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሕይወታቸውን ገብረው ለኤርትራ ነፃነት ከፍተኛ ትግል አካሂደው ኤርትራ ነፃ ወጥታለች። የኢትዮጵያ ህዝብ በሚያውቀው ግን ሕወሓት ከኤርትራ ጋር ድንበር ተካልሎ የኤርትራ በወርዱ ይህን ያህል ኪሎ ሜትር ነው፣ ቁመቱ ደግሞ ይህን ያህል ነው ያለበት ጊዜ የለም ። ምናልባት ሕወሓት በትግሉ ዘመን ለሻቢያ አሰብ ከኤርትራ ጋር እንድትጠቃለል ያደረገው ስምምነት ሊኖር ይችል ይሆናል። ይሆናል ብንል እንኳን ሻቢያ በኢትዮጵያ ላይ ብሎም በሕወሓት ላይ የጥቃት ጦርነት (aggressive war) ከፍቶ የጦር ወንጀል ፈጽሞአል። በሌላው አገር ላይ የጥቃት ጦርነት ከፍቶ ወረራ መፈፀም ደግሞ በኑራምበርግ ፍርድ ቤት ውሳኔዎችና እ.ኤ.አ በ1998 ዓ.ም የአለም ወንጀል ፍርድ ቤት ለማቋቋም በተፈረመው ስምምነት (treaty) መሠረት የጦር ወንጀል መሆኑ በማያዳግም መልኩ ተረጋግጧል። በዚህ ሁኔታ ሕወሓት በገባው ውልም ሆነ በሰጠው ቃል የመፅናት ሕጋዊም ሆነ ሞራላዊ ግዴታ የለበትም። ስለዚህ ሕወሓትም ሆነ ኢሕአዴግ እንዲህ ዓይነቱ ግዴታዎች ገብተውም

ቢሆን እንኳን አንድ የፖለቲካ ድርጅት ቀርቶ የእርሶም መንግስት ሆነ የተወካዮች ምክር ቤት አንዲት ጋት የኢትዮጵያ መሬት ቆርሶ ለማንም የመስጠት መብት እንደሌላቸው እርስዎም አይስቱትም።

ግጭቱ "ሀ" ብሎ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የኤርትራውያን ፍላጎት ድንበር መካለል መሆኑን አልሸሸጉም። ደንበር መካለሉ ለወደፊት ግጭት እንደማይነሳ ባያረጋግጥም ግጭት በድጋሚ እንዳይነሳ በእርግጥ ከተፈለገ የድንበር መካለል ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መከናወን አለበት። አሰብ በባለቤትነት ወደ ኢትዮጵያ እስካልተካለለ ድረስ ለግጭት ምክንያት የሚሆነው ዋነኛው ጉዳይ የእሳት ረመጥ ሆኖ ተዳፍኖ ይቆያል እንጂ ጠፋ ማለት አይደለም።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

ድንበር መካለሉ ለኤርትራውያን እንጂ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን እጅግም አስፈላጊአችን እንዳልሆነ የሚያጡት አይመስለኝም። ለክቡርነትዎ በትሕትና ላሳስብ የምፈልገው ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የጦርነቱም ሆነ የድርድሩ አልፋና ኦሜጋ ድንበር መካለል አይደለም፤ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነትን ማረጋገጥ እንጂ። የኢትዮጵያ ህዝብ የባህር በር ባለቤትነት ሉአላዊነት ከማስከበሩ አሳንሶ አያየውም። እንደ መራሄ መንግስትነትዎ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ማስከበር ካለብዎት ኃላፊነት የአሰብ የባህር በር ወደ ኢትዮጵያ የማጠቃለል ኃላፊነት ትልቁ ነው። ሆኖም ግን መንግስትዎ ወይንም ድርጅትዎ በአብዛኛዎቻችን ግምት የኢትዮጵያ መጻኢ እድል ወሳኝ የሆነው የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ አምኖበት ሲታገል ካልፈለገ "ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጣል" አይነት ስለሆነ ፍርዱን ለታሪክ ከመተው ሌላ ለአሁኑ ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ያዕቆብ ኃይለ ማርያም



## 4. Border demarcation with Eritrea and the Question of Assab

## By Dr. Yacob H. Mariam

## November 18, 2007[207*]

We heard the disturbing news recently that Ethiopian authorities are poised to sign a border delimitation and demarcation agreement based on three treaties Emperor Menelik signed with Italian colonial expansionists, affirming forever Eritrea's dominion over Assab – an Ethiopian sovereign territory and its natural outlet to the sea. The negotiations between the Ethiopian and Ertirian anthorities on border delimitation and demarcation have been conducted in such secrecy and stealth that would put American radar evading fighter plane to shame.

Before we gathered our breath, the EPRDF signed with Eritrea the most infamous treaty Ethiopia has ever been a party to. In quick succession the EPRDF submitted to arbitration at the Hague and the Arbitral

* This article originally appeared in the pro-government Reporter newspaper on January 9, 2002, Addis Ababa. Dr. Yacob Haile-Mariam was Department Head and Associate Professor of Business Law and International Management at Norfolk State University. The Ethiopian native was also a Senior Trial Attorney at the UN International Criminal Tribunal for Rwanda and later Senior Legal Advisor at the UN, Cameroon and Nigeria Mixed Commission. He resigned his post at the UN and ran for Parliament where he was elected by a landslide. Dr. Yacob later became one of the leaders of the popular Coalition for Unity and Democracy (CUD) opposition party, whose overwhelming victory at the rigged 2005 elections led to the arrest of CUD leaders by the Zenawi regime. He and his colleagues were released after 21 months in prison over what US congressman Donald payne described as the "Crime of being elected by the people."

Commission handed down its decision in a matter of months.

With the signature of a border agreement Eritrea becomes a state in earnest, which heretofore was only a concept, an idea or a stretch of some land north of the Ethiopian territory of Tigray. This agreement puts Eritrea on the world map and wrongly awards it Assab as its indisputable territory. Next to the Prime Minister's letter to the OAU and the UN urging them to grant recognition to the former Ethiopian breakaway province, this agreement is the most important step in the long struggle of the TPLF leadership in its role as a midwife in the birth of the Eritrean State.

It was in the eleventh hour that the Ethiopian Minister of Foreign Affaris broached the subject on the border demarcation where in a long winded interview where he said sweet nothing, he claimed that Ethiopia was awarded some territories by the Border Commission. He avoided like a plague apparently in a pere-arranged agreement with the "interviewer" – the most important issue in the boarder demarcation; namely Ethiopia's right of access to the sea through the port of Assab and the right of self-determination of the Red Sea Afars.

Without discussing Assab, the Foreign Ministr's interview was much ado about nothing. Few things in recent memory have gripped the imagination and anxiety of the Ethiopian people as the frightening prospect of losing Assab and being landlocked. No Ethiopian issue in recent memory has galvanized the otherwise fractious Ethiopian intellectuals with such unprecedented unanimity.

Yet the Minister of Foreign Affairs had nothing to say about Assab and Ethiopia's right of access to the sea. Whatever anybody says, however, the question of Assab is not going to be put to rest by mere signatures of their "Excellencies" Ato Meles and Mr. Isayas followed by the obligatory bear hug. It would be belaboring the obvious to dwell on the fact that borders are sacrosanct for Ethiopians. Need we make head-counts of lives lost at the Welwell, Dogali, the Ogaden, Badme and innumerable other theatres of war to show what the sanctity of borders means to Ethiopians?

For most Ethiopians, border demarcation with Eritrea is not whether Eritrea has made an incursion of a kilometer here or a kilometer there-though that is important too. Border demarcation with Eritrea for most Ethiopians is nothing more or nothing less than ensuring Ethiopia's right of access to the sea through its own port of Assab, period.

After WW II, recognizing Ethiopia's right of access to the sea, the 5- nation UN mandated commission that convened to come up with measures for the disposition of Eritrea has underlined its recommendation by clearly stating, that "Taking into account in particular Ethiopia's legitimate need for adequate access to the sea that Ethiopia and Eritrea should federate under the Ethiopian Crown." Furthermore, in its recommendation, the Commission had warned, "The creation of a separate Eritrean State entirely on its own would contain all elements necessary to seriously prejudice the interest of peace and security in East Africa now and in the future." This is a moot question now and obviously the fear is unfounded.

At the Paris Peace Conference on September 24, 1945, among the many world leaders who gave testimonials regarding Ethiopia's right of access to the sea, John Foster Dulles, head of the American

Delegation, said, "to avert the possibility of (Eritrea) being used at any time in the future as a base against Ethiopia, and to give that state access to the sea, the eastern part of Eritea including Massawa should be incorporated into Ethiopia." The British Delegate Mr. Mcnill also said, "The territory ceded to Ethiopia should include the Danakil Coast, the port of Assab." The French and Italians said more or less the same thing. Eventually by the Resolution of the United Nations 390 (IV). Eritrea became federated with Ethiopia under the Ethiopian Crown. This is where Ethiopia became the owner of two Red Sea ports of Assab and Massawa.

It is mind-boggling to learn any leader of a country would ever accept illegal colonial treaties, which were part and parcel of the same colonial scramble for Africa, as a basis for boarder demarcation. Yet in the same breath where EPRDF accepted colonial treaties as legitimate basis of border demarcation, the Ethiopian Minister of Foreign Affairs rightly condemned "maps that have been prepared by Italy, when Eritrea was its colony, [as] reflect [ing] the unilateral interest of the colonial power, and could not serve as an authorized international boundary." (The Ethiopian Hearald, December 20, 2001, p.1)

Whether the acceptance of colonial treaties as a basis for the border demarcation is a case of bad advice or there is something more sinister lurking under it, only time will tell. Ethiopian scholars at home and abroad dissected these so-called colonial treaties in their legal, historical, political and demographic contexts and concluded:

These treaties, driven by colonial ambition of Italy, were designed for the sole purpose of asphyxiating the only free and sovereign African State and the second



black free nation with Hait. A treaty whose purpose is to subjugate a free people is inherently illegal and therefore null and void.

